አትጨቃጨቁ ተከታታይ ዕትም ቁ.1

وَمَآ أَرۡسَلۡنَٰكَ إِلَّا رَحۡمَةٗ لِّلۡعَٰلَمِينَ

መውሊድ

የታላቁ ነብይ ﷺ የልደት መታሰቢያ

በሀሰን ታጁ

በማህበረሰባችን ዉስጥ ያለአግባብ ተበትነዉ ያለአግባብ እያመሱን ከሚገኙ 20 ያህል አጀንዳዎች መካከል በዚህች አነስተኛ ጥናት አንዱን ብቻ በመጠኑ ቃኝቸዋለሁ፡፡ የጥናቱ ዓላማ ላለፉት 20 ዓመታት ደጋግመን ከሰማነዉ እይታ አንጻር የሚገኘዉን የብዙሀን ዑለሞች ድምጽ በማሰማት በአጀንዳዉ ዙሪያ ሚዛናዊ ግንዛቤ መፍጠርና ከተዛቡ ግንዛቤዎች በመነሳት ለዑለሞቻችንና ለታሪካችን የተሰጡ የተሳሳቱ ግምቶችን ማስተካከል፤ብሎም ሙስሊሙ ህብረተሰብ በዚህ አጀንዳ ሰበብ በየዓመቱ ረቢዕ በተቃረበ ቁጥር መጨቃጨቁን ትቶ ሁሉም ያመነበትን መስመር እየተከተለ ኪጋራ ጉዳዮቹ ላይ እንዲያተኩር ማድረግ መሆኑን በአንክሮ እየገለጽኩ፣ከዉገና ነጻ በሆነ አዕምሮ ይህችን መጽሀፍ የሚያነብቡ ወንድሞችና እህቶች ለግንዛቤያቸዉ መስፋት በተደረገዉ አስተዋጽኦ እንደሚደሰቱ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

በሰከነ መንፈስ የመወያየትን ስልጡን ባህል እናዳብር፤
መልካም ንባብ፤

ሀሰን ታጁ

WWW.HASSENTAJU.COM

ማዉጫ

መግቢያ **5**
ምዕራፍ አንድ **11**
አጠቃላይ ግንዛቤ **11**
የቃሉ ትርጉም 11
አፈጻጸሙና ይዘቱ 11
የሚፈጸምበት ጊዜ 13
ዓላማና ፋይዳ 14
ምዕራፍ ሁለት **32**
ታሪካዊ አመጣጥ **32**
መዉሊድን የጀመሩስብዕና 32
ህዝባዊና ኦፊሴላዊ አከባበር 35
ለምን እስከዚህ ጊዜ ዘገየ? 42
ምዕራፍ ሦስት **58**
ሸሪዐዊ መነሻዎች **58**
የእስልምና አበይትና ደጋፊ ምንጮች 58
ቁርአናዊ መረጃዎች 60
የሀዲስ መረጃዎች 75
የይዘት መረጃዎች 90
የኢጅማዕ መነሻ 93
የቂያስ መነሻ 107

መሳሊሀል መ·ርሰላ 108
መወሊድን በመደገፍ ኪታብ የጻፉና ፈትዋ ያስተላለፉ ዕወቅዐሊሞች ዝርዝር በከፊል 111
የሀገራችን ዑለሞች እይታ 119
ተጨማሪ ተቃወሞዎችና ምላሾቻቸዉ 122
ማዘን ሲገባ መደሰት 122
የታሪክ ነቀፌታ 123
የቢድዐ ጽንሰ ሀሳብ 126
አዲስ ዒባዳ 151
በክርስቲያኖች ላይ የደረሰ ወቀሳ 152
ከሌሎች ጋር መመሳሰል 158
የይዘት ተቃዉሞ 162
የተቃዉሞዉ የጀርባ ምክንያቶች 194
ምዕራፍ አራት 208
ልዩ ልዩ 208
መወሊድ በሀገራችን የተጫወተዉ ሚና 208
የአሁን ዘመን ሚና 215
ማጠቃለያ 221
የመረጃ ምንጮች 226
ሀገራዊ ፈትዋዎችና ዋቢ ስብዕናዎች 234

መግቢያ

بِسْمِ اللَّهِ الرَّحْمَنِ الرَّحِيمِ

‹ረቢውል አወል›ብተሰኘዉ ነቢያዊዉ ወርበዓለማችን ታሪክ ጉልህ ስፍራ ያላቸዉ፣የሰዉን ልጅ አዲስ ልደት ያበሰሩ ወይም የታሪክን ሂደት የቀየሩ ቢያንስ ሦስት ዋና ዋና ክስተቶች እዉን ሆነዋል፡-

1. የዓለማት እዝነት ﷺ የተወለዱት በዚህ ወር ዉስጥ ነዉ፤
2. ለርሳቸዉ ወህይ መዉረድ የጀመረዉ በዚህ ወር ዉስጥ ነዉ፤ ማለትም የመጅመሪያዉ የቁርአን መልዕክት በረመዳን ከመዉረዱ በፊት ለ 6 ወራት ያህል በህልም መልክ ወህይ ይወርድላቸዉ ነበር፡ ፡ ስሌቱ እነብያዊዉ ወር ያደርሰናል፤
3. ነብዩ ﷺ ይህችን ዓለም የተሰናበቱትም በዚሁ ወር ዉስጥ ነዉ፡፡

‹ዓለም ከተፈጠረችበት ዕለት አንስቶ እነዚህን ክስተቶች የሚመጥን ሌላ አጋጣሚ ፈጽሞ አላየችም› ብል ሚሊዮኖች ይስማማሉ፡፡

‹ረቢዕ› ስሙ በራሱ የምድርን ነፍስ መዝራት፣በልምላሜ መዋብ ይጠቁማል፡፡ በጸደይ አዝርዝት ለፍሬ ይበቃሉ፡፡ አትክልቶች ይጎምራሉ፡፡ ረሀብ በጥጋብ፣ድርቅ በልምላሜ ይተካሉ፡፡ የዓለማት እዝነት ﷺ በዚህ ወር መወለዳቸዉ ያጋጣሚ ጉዳይ አይመስለኝም፡፡ በአላህ ተግባር ዉስጥ አጋጣሚ ቦታ የለዉምና፡፡ ምድር በመልዕክታቸዉ፣ የሰዉ ልጅ በትጋታቸዉ ህያዉ እንደሚሆኑ፣የክህደት ድርቅ በእምነት ልምላሜ፣ የሽርክ ረሀብ በተዉሂድ ጥጋብ እንደሚተኩ፣የምንዱባን እንባ የሚታበስበት፣የነዳያን ፊት በሀሴት የሚደምቅበት፣የበደል ጨለማ ተገፎ ብርሀን ወደ እያንዳንዱን ጎጆ የሚገባበት፣ልክ እንደጸደይ ጊዚያት የማይሞቅ፣የማይበርድ፣ ለሠዉ ልጅ ተፈጥሮ ስምሙ የሆነ የህይወት

ጎዳና የሚገለጥበት ዘመን መቃረቡን ለማብሰር ሆነ ተብሎ የተከናወነ አምላካዊ ተግባር እንደሆነ ይሰማኛል።

ይህ ወር ሲቃረብበሙስሊሙ ህብረተሰብ ዉስጥ ሁለት ዓይነት ስሜቶችንና ቅኝቶችን እናነባለን። በአንድ በኩል በብዙ የዓለማችን ክፍሎች ልዩ መንፈሳዊ ድባብ ይሰፍናል። የዓለማትን እዝነት ﷺ የሚያወድሱና የሚያሞግሱ ዝግጅቶች ይደመጣሉ። ገድላቸዉ በስፋት ይነገራል። ስብእናቸዉ አብዝቶ ይዘከራል። በሀገራችን፣ በተለይም ከሁለት አስርት ዓመታት በፊት ወሩ የተለየ ክብደትና ግምት ይሰጠዉ ነበር። ቀዮዎች ዳር እስከዳር ያረገርጋሉ። የሰዎች እንቅስቃሴና ጉዞ በጉልህ ይታያል። የታሰሩ እጆች በሶደቃ ይፈታሉ። አንደበቶች ለመንዙማና ዜማ ይሰላሉ። እስላማዊ የኪነ ጥበብ ዉልዶች በስፋት ይደመጣሉ። (ይህ ልምድ አሁንም በከፊል አለ።) በዚያ ዘመን ለረቢዕ ወር የነበረዉን በጎ ስሜት የሀርጡሜዉ እዉቅ ዓሊምና ማዲህ[1] ሸህ አህመድ ሸህ ሲራጅ[2] ‹መኸረመ› በተባለዉ መንዙማቸዉ[3] እንዲህ ዘክረዉታል፡-

يا شهرا موسما بربع الأول

فاق كل شهر شرفك الأجل

أفرحت قلوبا لأبناء الأزل

جأتنا بالهنا وبلوغ الأمل

[1]ነብዩን በግጥሞቹ አሞጋሽ

[2]ታላቅ ዓሊም ናቸዉ። ደበልጡኑ በመሳጭ የዐረብኛ ግጥሞቻቸዉ ይታወቃሉ። ነብዩን በማፍቀር እንደተምሳሌት ይታያሉ። ሸኽ ሙሀመድ ወሌ ‹‹ኢቃዙ ሂመሚል አግቢያእ›› ከተሰኘ መጽፋቸዉ ዉስጥ ከገጽ 134-136 ታሪካቸዉን አስፍረዋል።

[3] ሸኽ ሙሀመድ ወሌ በላይኛዉ የግርጌ ማስታወሻ ላይ በተጠቀሰዉ ኪታባቸዉ ‹‹መሳጭ›› ሲሉ የዚህችን መንዙማ ይዘት አድንቀዋል-ገጽ135፤

إذ ولد فيك نبينالأكمل

فلك علينا عهد وزمام

የዚህን የዐረብኛ ግጥም መልዕክት ከነዉበቱ ማስተላለፍ ፈተና ነዉ። በግርድፉ ከመሞከር ሌላ አማራጭ የለንም፡-

ረቢዕ ተብለህ ምትጠራ፤

የወራት ጓል፣ ንጉስ፣ አዉራ፤

ነቢ ባለሙሉ ስብዕና፤

እዉስጥህ ዘለቁና፤

ሀሴት አዘለህ አስደሰትከን፤

ተስፋ ወልደህ አደመቅከን፤

ቃል አደራህ ለኛ ከብዷል፤

ዉስታህ ከፋይን ገዷል፤[4]

በገሚሶቹ የማህበረሰባችን አባላት ዘንድ ደግሞ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ስለዚህ ወር ጸለምተኛ ስዕል እናገኛለን። በተቻለ መጠን በዚህ ወር ዉስጥ ይሠራል ብለዉ የሚያምኑትን ‹ቢድዐ› ለማስቀረት ሁሉንም ዓይነት ጥረቶች ያደርጋሉ። ነብያዊ ወር መሆኑ እንዳይታወስ የብዕር ሰይፎች ከየአፎቱ ይመዘዛሉ። አንደበቶች በሰፊዉ ይከፈታሉ። የመስጊድ ዳዕዋዎች፣የጁመዐ ኹጥባዎች በዚሁ መንፈስ የተቃኙ ይሆናሉ።

በነዚህ ሁለት አቅጣጫዎች መካከል የሚደረገዉ ፍትጊያ ማህበረሰብን ክፉኛ አዉኳል። ህብረትን አናግቷል። የወንድማማችነት መንፈስን ገድሏል። እስላማዊዉ ዳዕዋ የንትርክ ገጽታ እንዲይዝ አድርጓል።

[4] ‹ሙከረሙ› ከተሰኘዉ የመንዙማ ግጥም የተወሰደ

ወደማህበረሰባችን ያለአግባብ በተረጨ የኺላፍ አጀንዳዎች ሰበብ የተፈጠረዉ መደናገርና ግራ መጋባት ህዝባችንን መሄጃና መተንፈሻ አሳጥቶታል። ይህን ተጨባጭ እዉነታ መንዙማ አቀንቃኙ ለማህበረሰባችን አንደበት ሆኖ እንዲህ ገልጾታል፡-

አሁን ምን ይሠራል አስን ድንግርግር፣

ያዉም በዚህ ዘመን በበዛበት ነዉር፣

ሰማይ አይወጣ አይገባ ምድር

በመሆኑም የነብዩን ﷺ ልደት መታሰቢያ በተመለከተ ከዚህ ትርምስ ለመዉጣት የሚያስችለንን የሰከነ ምሁራዊ ዉይይት ለማድረግና በተለይም ከኛ አገር ጠጨባጭ ሁኔታ አኳያ የሚበጀንን እንመርጥ ዘንድ እገዛ የሚያደርግልንን የተወሰነ ሀሳብ ለመሰንዘር ይህችን መጽሀፍ ለኢትዮጵያ ሙስሊም ማህበረሰብ አበርክቻለሁ።

በእርግጥ በእንዲህ ዓይነት ቅርንጫፍ አጀንዳዎች ዙሪያ የመጻፍ ፍላጎት የለኝም። ከዚህ ይበልጥ አሳሳቢና ጊዜ የሚፈልጉ ጉዳዮች ሞልተዉ ተትረፍርፈዋል። ሆኖም በጥቃቅን አጀንዳዎች ዙሪያ አዉራ እየተነሳ የህዝበ-ሙስሊሙን ጊዜና ጉልበት ሲባክን፣ህብረቱ ሲናጋ አይቼ እንዳላየሁ መሆን አልተቻለኝምና ለአጀንዳዉ ትኩረት መስጠቴ ግድ ሆኗል።

በቅርንጫፍ ጉዳዮች ህዝበ ሙስሊሙን በአንዲት ቀጭን መስመር ለማስኬድ የሚደረገዉ የየትኛዉም ወገን አንጉል ጥረት እስካልተገታ ድረስ በሀገር ዉስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተብትቦ ይዞ አላንቀሳቅሰን ያለዉ ዉስጣዊ ችግር እስከ ወዲያኛዉ ይቀጥላል።

የመጻፌ ዓላማና መግፍኤ እንዲህ ዓይነቱ መደናገርና ግራ መጋባት ከተቻለ ማጥፋት፣ካልሆነም መቀነስ ነዉ።

መወሊድን የተመለከቱ አጀንዳዎችን፣ከታሪኩ እስከ አፈጻጸሙ፣እስከ ዓላማዉና ሚናዉ፣እስከ ሽሪዐዊ መነሻዎቹ... ከሞላ ጎደል በዚህች መጽሀፍ ዉስጥ ለማካተት ሞክሪያለሁ። የሀሳቤ መደገፊያዎች በዋነኛነት ቁርአን፣ሀዲስ፣ኢጅማዕና ቂያስ የተሰኙ የሸሪዐችን ዋነኛና ደጋፊ ምንጮች ሲሆኑ፣ ለምጠቅሳቸዉ የቁርአንና የሀዲስ መልዕክቶች፣ እንዲሁም የፊቅህና የኡሱል ሀሳቦች በእዉቀታቸዉ የበለጸጉ የየመስኩ ዐሊሞችን ትንታኔና ግንዛቤ ብቻ አስፍሪያለሁ። የታሪክ መረጃዎቼን በተቻለ መጠን ከእዉቅ የእስልምና ታሪክ ምንጮች ለመቅዳት ጥረት አድርጊያለሁ። የዐሊሞችንና የምሁራንን ሀሳብ ለማፍታታት ወይም ፖለቲካዊ አንደምታዎችን ለማሳየት ካልሆነ በስተቀር የግል ሀሳቤን አላሰፈርኩም። በሁሉም ጉዳዮች ላይ የብዙሀን ዐሊሞችን ሀሳብ እንደመረጃ የተጠቀምኩ ቢሆንም የአናሳዎቹን ግንዛቤም ለንጽጽር ያህል ጠቅሻለሁ። ሀሳቦቼ የተቀዱባቸዉን መረጃዎች ከግርጌ ማስታዎሻዎች ላይ፣እንዲሁም ከዋቢ መጽሀፍት ዝርዝር ዉስጥ አኖሪያለሁ።

‹‹አትጨቃጨቁ›› በተከታታይ የማነሳቸዉን መሰል ሀሳቦች አቃፊ ርእስ ሲሆን፣ስሙ የተገኘዉ ከሚከተለዉ የቁርአን መልዕክት ነዉ፦

وَأَطِيعُوا اللَّهَ وَرَسُولَهُ وَلَا تَنَازَعُوا فَتَفْشَلُوا وَتَذْهَبَ رِيحُكُمْ , وَاصْبِرُوا , إِنَّ اللَّهَ مَعَ الصَّابِرِينَ [٨:٤٦]

‹‹አላህንና መልክተኛዉንም ታዘዙ። አትጨቃጨቁም። ትፈራላችሁና ኃይላችሁም ትኼዳለችና። ታገሱም፤ አላህ ከትዕግስተኞች ጋር ነውና።››[5]

በኢልሙ ዓለም ክንደ-ብርቱ የሆኑ ብዙሀን ታላላቅ ዑለሞች (ጁምሁር) ጽድቅ የቸሯቸዉን በመረጃ የከበሩ ሀሳቦች በማጉላት የእርስ በርስ መተዋወቅንና መግባባትን ፈጥሮ በተለያዩ እይታዎች አራማጆች መካከል አሁን የሚታየዉን መኮራረፍ እና መራራቅ የሚያስቀር ተከታታይ ሥራ

[5] አል አንፋል 46

ይሆናል ብየ ተስፋ አድርጊያለሁ፡፡ በዚህ ማዕቀፍ ይካተቱ ዘንድ ከመረጥኳቸዉ 20 ያህል ርእሶች መካከል መዉሊድ አንዱ ብቻ ነዉ፡፡ ሌሎችን በሂደት በአላህ ፈቃድ ይፋ አደርጋቸዋለሁ፡፡

ሀሳቤን በሀሳባቸዉ ለማበልጸግ ወይም ለማረቅ የሚተጉ ወንድሞችን ከወዲሁ ከልብ እያመሰገንኩ ያልተገባ መንገድን የሚከተሉትን ደግሞ አላህ ሂዳያ እንዲሰጣቸዉና የስልጣኔን እስላማዊ የዉይይት አደብ እንዲያገራላቸዉ ከልቤ ዱዐ አደርጋለሁ፡፡

በሰከነ መንፈስ የመወያየትን ስልጡን ባህል እናዳብር፤መልካም ንባብ፤

ሀሰን ታጁ

ታህሳስ/ 2008

ምዕራፍ አንድ

አጠቃላይ ግንዛቤ

ስለመውሊድ ሀይማኖታዊና ታሪካዊ ትንታኔ ከመስጠታችን በፊት አጠቃላይ ግንዛቤ ሊያሰጨብጡ የሚችሉ አጀንዳዎችን ማየት ጠቃሚ ሆኖ ስላገኘሁት ዋና ዋናዎችን በያዝነዉ ምዕራፍ ዉስጥ ባጭሩ እመለከታቸዋለሁ።

የቃሉ ትርጉም

‹መዉሊድ› ሥርወ ቃሉ ‹ወለደ› የሚለዉ የዐረብኛ ግስ ሲሆን ቋንቋዊ ትርጉሙ ‹*የመወለጃ ቦታ ወይም ዕለት*› ማለት ነዉ።[6] በዑለሞች ዘንድ ለታላቁ ነብይ ﷺ የልደት ቀን ልዩ ክብር መስጠትንና ማሰብን እንደሚወክል ሆኖ ያገለግላል።[7] በሀገራችን አጠቃቀም ደግሞ በየትኛዉም ጊዜ ወይም ቦታ በዱዐ አላህን ለመለመን የሚደረግን መሰባሰብ ወይም ድሆችን ሶደቃ ማብላትን የሚያካትት ሰፋ ያለ ትርጉም ይይዛል።[8] በዚህ ጽሁፍ አቅራቢ አጠቃቀም መዉሊድ የነብዩ ሙሀመድ ﷺ ልደት መታሰቢያ ዝግጅቶችንና በዕለቱ የሚደረጉ መንፈሳዊና ትምህርታዊ ድርጊቶችን አቃፊ ጽንሰ ሀሳብ ሆኖ ያገለግላል። የሀገራችን ዑለሞች ቴክኒካዊ አጠቃቀም ከሞላ ጎደል ይህዉ ስለሆነ ይህን ትርጉም በልቦናችን ይዘን ዉይይታችንን እንቀጥላለን።

አፈጻጸሙና ይዘቱ

ሰዎች የነብዩን ﷺ ልደት መታሰቢያ ምክንያት በማድረግ ተሰባስበዉ ለዲን ወይም ለዱንያ የሚጠቅሙ በጎ ሥራዎችን መስራታቸዉና

---

[6] አል-ሙዕጅሙል ወሲጥ-ማዳህ ‹ወለደ›

[7] አል-ሀዊ ሊልፈታዊ-ጀላሉዲን አልሱዩጢ

[8] ምንጭ፡-ሸኽ ሲራጀ ማህሙድና ሸኽ በብደላ ኢድሪስ

መማማራቸዉ መዉሊድ የሚለዉን ጽንሰ-ሀሳብ እንደሚይዝ ዑለሞች ቢናገሩም[9] የመዲናዉ የሀዲስ ሊቅ ዶክተር ሙሀመድ አብነል ዐለዊ በዓለም አቀፍ ደረጃ-በተለይም በመካና በመዲና ፣እንዲሁም በርሳቸዉ ቤት- የሚከናወኑ የመዉሊድ መታሰቢያዎች ከጥንት እስከዛሬ የሚከተሉት ዋና ዋና ይዘቶች እንዳሏቸዉ ጽፈዋል፡-

- የታላቁ ነብይ ﷺ ገድል (ሲራ) ይዘረዘራል፤
- የርሳቸዉን ታላቅነት የሚያወሱና ዲንን የሚያስታዉሱ ምክሮች በዐሊሞች ይነገራሉ፤
- ከዕለቱ ጋር የሚሄዱ የቁርአን መልዕክቶች ይነበባሉ፤[10]

በሀገራችንም ከላይ ከተጠቀሱት በጎ ተግባራት በተጨማሪ በመዉሊድ ማዕዶች ላይ ፡-

- በሸኽ አህመድ ዳኒ (እስከ 1321 ሂጅሪያ)[11] የተደራጁት ‹ራምሳ›ና ‹ተራ መንዙማ› የተሰኙ የዚክርና የዱዐ መድብሎች ይደመጣሉ፤
- የሶሀቦች፣ ታቢያችና ሌሎች ታላላቅ ሰዎች፣በተለይም የሀገራዊ ጓል ስብዕናዎች ገድል (ቂሷ) ይነገራል፤
- ነብዩን ﷺ የሚያወድሱ ግጥሞችና መንዙማዎች ይደመጣሉ፣
- በዐሊሞች መካከል የሚልም ዉይይትና መጠያየቅ ይደረጋል፤
- መዉሊድ የዱዐና የመገናኛ መድረክ በመሆን ያገለግላል፤
- ድግስ ተደግሶ ድሆች ሶደቃ ይቋደሳሉ፤

[9]ዶ/ር ሙሀመድ አብን አልዐለዊ አልማሊኪ አልሁሰይኒ፣ሀዉስል ኢህቲፋል ቢዚክራ መዉሊዲ ነቢዊይ ሸሪፍ፣መክተበተልዒስማ፣ቢይሩት፣2010፣ገጽ 39

[10]ያስፈዉ ምንጭ

[11] በቅርብ ዘመኑ የኢትዮጵያ የሚልም ታሪክ ዉስጥ ታላቅ ሚና በመጫወት አቻ የማይገኝለት የዳና የሚልምና የተርቢያ ማዕከል መሥራችና የመጀመሪያ መሪ ናቸዉ፡፡ ሸኽ ሙሀመድ ወሌ፣ኢቃዙ ሂመሚል አግቢያአ ከተባለዉ ኪታባቸዉ ዉስጥ ታሪካቸዉን ጽፈዉታል፡፡ (ኢቃዙ ሂመሚል አግቢያአ፣ነጃሽ ማተሚያ ቤት፣1425 ሂጅሪያ፣ ቅጽ 1፣ገጽ 78-85)

- አላህን የሚያወድሱ ልዩ ልዩ ዚክሮች ይባላሉ፤
- በነብዩ ሙሀመድ ﷺ ላይ ሶለዋት ይወረዳል፤

በዑለሞች ጽድቅ የተቸረዉ መዉሊድ አፈጻጸሙ ከላይ የተገለጸዉን ይመስላል።

የሚፈጸምበት ጊዜ

ነብዩ ﷺ ዘወትር ሠኞ የልደት ቀናቸዉን በጾም አስበዉት ይዉሉ እንደነበር በሶሂህ ሀዲስ ተዘግቧል። ለታላላቅ ክስተቶች ዓመታዊ መታሰቢያ ማድረግን ያስተማሩበትን ሀዲስ ወደፊት የመዉሊድን ታሪካዊ አመጣጥ ስንተነትን እናነሳዋለን። የመዉሊድ የኋለኛ ዘመን ህዝባዊ አፈጻጸሙ ዓመታዊ ዑደትን የተከተለ ነዉ። በመካና በመዲና ለዘመናት የቆየዉንና እስከአሁንም በቤተሰባቸዉ የቀጠለዉን የመዉሊድ አፈጻጸም የመዲናዉ የሀዲስ አዋቂ ዶ/ር ሙሀመድ እብን አልዐለዊ ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፦

‹‹ደስታና ብርታት በሚሰማን በየትኛዉም ቀንና አጋጣሚ የነብዩን ﷺ መዉሊድ እናስባለን። በርሳቸዉ የመወለድ ጸጋ እንደሰታለን። ይህ መደሰታችን ሰኞ ቀንና በተወለዱበት በወርሀ ረቢዐል አወል መጠኑ ይጨምራል። ጤነኛ አዕምሮ ያለዉ ሰዉ ‹በኪስራእና በሚዕራጅ ባለቤት ለምን ትደሰታላችሁ?›› ብሎ ሊጠይቀን አይችልም። ይህ ጥያቄ በአላህ ብቸኛ አምላክነትና በነብዩ ሙሀመድ ﷺ መልዕክተኛነት ከመሰከረ ሙስሊም እንደበት ሊወጣ ይችላልን? እርባና ቢስ ጥያቄ ስለሆነ መልስ አያሻዉም። ቢሆንም፦ *‹ሙእሚን ስለሆንክ ነብዩን ﷺ እወዳለሁ፤ስለወደድካቸዉ በርሳቸዉ እደሰታለሁ፤ ደስታዩንም ዘወትር እገልጻለሁ›* ካልክ በቂ ነዉ።››[12]

[12] ሀዉለል ኢህቲፋል... ገጽ 13

የሀገራችንን የመውሊድ ሂደት ስናጠና ከላይ ሸኽ አልዐለዊ ከሰጡት ገለጻ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የነብዩﷺ ልደት በሳምንታዊ፣በወርሀዊ ወይም በቀናት ዑደት ዓመቱን ሙሉ ይታሰባል፡፡ ሆኖም በረቢዐል አወል ይህ ደስታ ይጨምራል፡፡ ከወሩ ዉስጥ ከ9-12 ባሉት ቀናት ደግሞ እርሳቸዉን የማሰቡና ገድላቸዉን በጋራ እያወሱ የመመሰጡ መጠን ይበልጥ ያይላል፡፡[13]

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በየትኛዉም የዓመቱ ቀን ድሆችን ደግሶ የማብላቱ ክንዉን መዉሊድ ይባላል፡፡ በእንዲህ ዓይነት ሶደቃዎች ላይ ምንጊዜም የነብያችንﷺ ገድል ይነበባል፡፡ በርሳቸዉ ላይ በብዛት ሶለዋት ይወረዳል፡፡ እርሳቸዉን የሚያወድሱና የሚያሞግሱ መንዙማዎች ምንጊዜም ይደመጣሉ፡፡ በዋነኛነት በእዉቁ ዓሊም በአህመደ ዳኒ (ዳንዩል አወል) የተደራጀዉ ‹‹ራምሳ› እና ‹ተራ መንዙማ› የተሰኘ ሙሉ ዝግጅት ይቀርባል፡፡ ይህ የመዉሊድ ሂደት በሌሎችም የሀገራችን ክፍሎች የተለመደ ነዉ፡፡[14]

ስለዚህ መዉሊድን በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ የሚከናወን ሂደት አድርጎ ማሰብ ስህተት ነዉ፡፡

ዓላማና ፋይዳ

በመዉሊድ ዙሪያ የተጻፉ ሰነዶችን ስናጠና የነብዩﷺ ልደት መታሰቢያዎችን ዓላማና ፋይዳ በሚከተሉት ነጥቦች ማጠቃለል እንደሚቻል እንረዳለን፡፡

1. **<u>ደስታን መግለጽ</u>፡-** አላህበቁርአኑ በአላህ እዝነትና ችሮታ እንደሰት ባዘዘን መሠረት፣[15] ከነብዩﷺ መወለድ የበለጠ ለሰዉ ልጅ የተሰጠ

[13]ምንጭ፡-ሸኽ ሲራጀ ማህሙድና ሸኽ ዐብደላ ኢድሪስ
[14]ምንጭ፡-ሸኽ ሲራጀ ማህሙድና ሸኽ ዐብደላ ኢድሪስ
[15] ዩኑስ 58

ችሮታና የአላህ እዝነት ስለሌለ መውሊድ ይህን ደስታ ለመግለጽ ሁነኛ መድረክ ሆኖ ያገለግላል ይላሉ ለመውሊድ ድጋፍ የቸሩ ዑለሞች፡፡ በተጠቀሰዉ የቁርአን አንቀጽ ዙሪያ በቂ ትንታኔና ማብራሪያ ወደፊት አቀርባለሁ፡፡

2. **<u>ለአላህ ምስጋና ማቅረብ</u>**፡- ጥቃቅን ጸጋዎቹን ሳይቀር አስታዉሰን እናመሰግነዉ ዘንድ አላህ በቁርአኑ አዞናል፡፡አላህ በዚህች ምድር ላይ ከዘረጋቸዉ ጸጋዎች ሁሉ ትልቁ የነብዩ ﷺ ወደዚህች ዓለም መምጣት ነዉና ለዚህ ጸጋዉ የከበደ ምስጋና ያሻዋል፡፡ መዉሊድ በባለቤቶቹ ዘንድ ይህ ምስጋና በስፋት የሚተገበርበት መድረክ ሆኖ ያገለግላል፡፡

3. **<u>ነብዩን ﷺ ማስታዎስና ማወደስ</u>**፡-የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ዘወትር ሊታወሱና ሊወደሱ እንደሚገባ እሙን ነዉ፡፡ ዉለታቸዉ ከሰማይ ከምድር የከበደ፣ችሮታቸዉ የሰፋ፡፡ የስብዕናቸዉን እያንዳንዷን ገጽታ፣የአካላቸዉን እያንዳንዷን ክፍል፣ዒባዳቸዉን፣የህይወት እንቅስቃሴዎቻቸዉን፣ገድሎቻቸዉን እያስታወሱ መመሰጥ፣ ልዕልናቸዉን ማወደስና ማሞገስ ከምንም በላይ ተገቢ ነዉ፡፡ ይህን ያስተማረን በዋነኛነት ቁርአን ነዉ፡፡ ስለርሳቸዉ ያላወሳዉ ነገር የለም፡፡ ለምሳሌ፡-

   - ሥነምግባራቸዉን አዉስቷል፤[16]
   - ቀልባቸዉን አዉስቷል፤[17]
   - ፊታቸዉን አዉስቷል፤[18]
   - ዓይናቸዉን አዉስቷል፤[19]

[16] አልቀለም፣4
[17] አልበቀራህ 97፣አልፉርቃን 23፣ አልነጅም 11
[18] አልበቀራህ 144

- ደረታቸውን አውስቷል፤[20]
- እድሚያቸውን አውስቷል፤[21]
- ስማቸውን አውስቷል፤[22]
- ሀገራቸውን አውስቷል፤[23]
- ድምጻቸውን አውስቷል፤[24]
- ሚስቶቻቸውን አውስቷል፤[25]
- ወዘተ ወዘተ

ምን ያልተወሳላቸው ነገር አለ? ከአላህ መልዕክተኛﷺ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ነገሮች ሁሉ በአላህ በክብር ተነግረዋል። ሰዉ ሲያፈቅር በተፈቃሪዉ ወገን ሁለመና እንደሚመሰጠዉ አላህም በርሳቸዉ ሁለመና የተመሰጠ ይመስላል። ፈጥሮ ወደዳቸዉ። አስገኝቶ አደነቃቸዉ። ‹‹ሰማይ ምድርን ከዘረጋሁ ጀምሮ እንዳንተ ያስ ዉብ አላየሁም፤ወደፊትም አላይም›› ይላቸዋል በአንደምታ-‹‹ወኢነከ ለዐላ ኹሉቂን ዐዚም።››[26] ይህን ምስክርነት የሰጠዉ ሁሉንም ነገር አዋቂ የሆነዉ አምላክ መሆኑ ፍጹም አቻ የለሽ እማኝነት ያደርገዋል። በዚህ ብቻ አላበቃም። ‹‹ሀቢቢ›› አላቸዉ። ከኢብራሂም በስተቀር ለማንም ያልሰጠዉን ‹‹ኸሊል›› የተባለ ማዕረግ ደገማቸዉ። ስማቸዉ ከስሙ ጋር አቆራኘ። ‹‹ደስታዉ ደስታዮ፣ ሀዘኑ ሀዘኔ ነዉ›› ሲል አወጀ።‹‹ እኔን ማስደሰት

[19] አልነጅም 17፣ጧሀ 131
[20] አልአዕራፍ 2
[21] አልሂጅር 72
[22] ሙሀመድ 2፣አልአህዛብ 40፣አልፈትህ 29
[23]አልበለድ 1 እና 2
[24] አልሁጁራት 2
[25] አል አህዛብ 6፣32
[26]አልቀለም 4

ከፈለጋችሁ እርሱን አስደስቱ፤እኔን ለማግኘት ፈለጉን ተከተሉ›› አለን፡፡ ካፈቀሩ አይቀር እንዲህ ነዉ፡፡ ከተፈቀሩም እንዲህ፡፡ በአላህ ይሁንባችሁ፣ የሚከተሉትን የቁርአን መልዕክቶች አስተዉሉ፡-

وَاللَّهُ وَرَسُولُهُ أَحَقُّ أَن يُرْضُوهُ

‹‹አላህንናመልክተኛውንሲያስወድዱተገቢያቸውሲኾን››[27]

مَّن يُطِعِ الرَّسُولَ فَقَدْ أَطَاعَ اللَّهَ

‹‹መልክተኛውንየሚታዘዝሰውበእርግጥአላህንታዘዘ፡፡››[28]

إِنَّ الَّذِينَ يُبَايِعُونَكَ إِنَّمَا يُبَايِعُونَ اللَّهَ

‹‹እነዚያቃልኪዳንየሚጋቡህቃልኪዳንየሚጋቡትአላህንብቻነው፡፡››[29]

ስማቸዉ ከስሙ ጋር አንድ የሆኑ ያህል ተቆራኝቷል፡፡ አላህን ለማስደሰት እርሳቸዉን ማስደሰት፤አላህን ለመታዘዝ እርሳቸዉን መታዘዝ፤ከአላህ ጋር ቃል ለመጋባት ከርሳቸዉ ጋር ቃል መጋባት፤ አላህ እንዲህ ሲል እዉነቱን ተናግሯል፡-

وَرَفَعْنَا لَكَ ذِكْرَكَ [٩٤:٤]

‹‹መወሳትህንም ሳንተ ከፍ አድርገንልሃል፡፡››[30]

ሶሀቦች የአላህን መልዕክተኛ ﷺ ሁለ-ነገር በማዉሳትና በማሞገስ ይህን የአላህ ፍላጎትና ዓላማ አብዝተዉ ተግብረዋል፡፡ የጥቂቶቹን ቃል ላስፍር፡ -

[27] አልተዉባ 62
[28] አል ኒሳእ 62
[29] አልፈትህ 10
[30] አልሸርህ 4

- ‹‹እጅግ የተዋበ ፊት ነበራቸዉ››-በራእ እብን ዐዚብ፤[31]
- ‹‹ጨረቃ በፊታቸዉ ላይ የምትንዝዝ ይመስል ነበር››-አቡሁረይራ[32] እና አቡ ጡፊይል፤[33]
- ‹‹ፊታቸዉ ክብና ዉብ ነበር››-ኢማም ዐሊ እብን አቢ ጧሊብ[34] እና ጃቢር፤[35]
- ‹‹ሲደሰቱ ፊታቸዉ እንደ ጨረቃ ቁራጭ ያበራል››-እናታችን እመት ዐኢሻ፤[36]
- ‹‹አካላቸዉ ልከኛ ነዉ፤ወፍራምም ቀጭንም አይደሉም››-ኢማም ዐሊ[37] እና ሀሰን እብን ዐሊ፤[38]
- ‹‹ስታያቸዉ ጸሀይን ራሷን ያየሀት ያህል ትደመማለህ››-ረቢዕ ቢንት መዑዝ፤[39]
- ‹‹ጨረቃንና መልዕክተኛዉን እያፈራረቅኩ አየሁ፤በአላህ እምላለሁ፤ እርሳቸዉ ከጨረቃዋ የበለጠ የተዋቡ ናቸዉ››- ጃቢር እብን ሰሙረህ፤[40]
- ‹‹እንደርሳቸዉ ያለ አይቼ አላዉቅም፤ወደፊትም አላይም››-ከሀመዳን ጎሳ የሆነች እንስት፤[41]

---

[31] ቡካሪና ሙስሊም
[32] ቲርሚዚ
[33]ሙስሊም
[34] ቲርሚዚ
[35] ሙስሊም
[36]አስሀበሸማኢል
[37] ቲርሚዚ
[38] ቲርሚዚ
[39] ቲርሚዚና በይሀቂ
[40] ቲርሚዜ
[41] ቲርሚዚ

- ‹‹በጨለማም በብርሀንም፣ከፊትም ከኋላም ያያሉ››[42]
- በርሳቸዉ ስብዕና ዙሪያ የተጻፉ (ሸማኢለል *ሙሀመድያ*) ኪታቦችን ስናይ ስለረሱሉ ﷺ ሶሀቦች ሳያወሱትና ሳያወድሱት ያለፉት ነገር እንደሌለ እንረዳለን፡፡

ነብዩን ﷺ አዘዉትሮ ማስታወስ ፍቅራቸዉን ያሰርጻል፡፡[43] ዑለሞች፡- ‹‹ፍቅር ማለት ተፈቃሪን ዘወትር ማስታወስ ነዉ›› ይላሉ፡፡[44] እብንል ቀይም እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፡-

إنها سبب لدوام محبته للرسول و زيادتها و تضاعفها ، و ذلك عقد من عقود الإيمان الذي لايتم إلا به ، لان العبد كلما أكثر من ذكر المحبوب و استحضار محاسنه و معانيه الجالبة لحبه تضاعف حبه له و تزايد شوقه إليه و استولى على جميع قلبه ، وإذا أعرض عن ذكره و إحضاره ، و إحضار محاسنه بقلبه نقص حبه من قلبه، ولا شئ أقر لعين العبد المحب من رؤية محبوبه ، ولا أقر لقلبه من ذكره و إحضار محاسنه، فإذا قوى هذا في قلبه جرى لسانه بمدحه و الثناء عليه و ذكر محاسنه، و تكون زيادة ذلك ونقصانه بحسب زيادة الحب ونقصانه في قلبه

‹የአላህን መልዕክተኛ አዘዉትሮ ማዉሳት ፍቅራቸዉን ዘዉታሪ ስማድረግ፣ስመጨመርና ስማነባበር ሰበብ ነዉ፡፡ የኢማን መቋጠሪያ ዉል ነዉ፡፡ እምነት ያስርሱ አይሞላም፡፡ አንድ ሰዉ የሚያፈቅረዉን አካል አብዝቶ ባወሳናስፍቅሩ ሰበብ የሆነዉን በጎ ባህሪ አዘዉትሮ ባስታወሰ ቁጥር ፍቅሩ ይጨምራል፡፡ ናፍቆቱ በርትቶ ልቦናዉን ይቆጣጠራል፡፡ በአንጻሩ እርሱን ከማዉሳትና በጎ ባህሪዉን ከማሰብ ሲዘናጋ ፍቅሩ ይቀንሳል፡፡ ስአፍቃሪ ተፈቃሪዉን ከማየት የበለጠ የሚያስደስተዉ፣በጎ ስብዕናዉን ከማዉሳት የበለጠ ልቦናዉን የሚያረጋጋለት ነገር

[42] ቡኻሪ
[43] አልሺፋእ 2/24
[44] አልሺፋእ 2/25

የስም።በቀልቡ ዉስጥ ይህ ማስታወስ ሲበረታ አንደበቱ ስለርሱ አብዝቶ ይናገራል። በገ ባህሪዉን መዘርዘር አይታክተዉም። ይህ ዉዳሴዉና ትዉስታዉ ፍቅሩ ሲጨምር ይጨምራል፤ ሲቀንስ ይቀንሳል።››[45]

የመዉሊድ መታሰቢያዎች ዋነኛ ዓላማ ነብዩን እንዲህ ማስታወስና ማወደስ ነዉ ይላሉ ባለቤቶቹ።

መልዕክተኛዉ ﷺ ራሳቸዉን አብዝተዉ አወድሰዋል፦

‹‹ከቀኝ ጓዶች ሁሉ በላጩ እኔ ነኝ››[46]

‹‹እኔ የጥንቶቹም የወደፊቶቹም ሁሉ የበላይ ነኝ።››[47]

መላኢካዉ ጅብሪልም እንዲህ ሲል አሞግሷቸዋል፦

‹‹ምድርን ከምስራቅ እስከምዕራብ አስሻስሁ፤ከሙሀመድ የበለጠ ሰዉ አላየሁም።››[48]

‹‹መወሳትህን ከፍ አደረግንልህ›› ሲል አላህ እዉነትን ተናገረ።[49]የሀበሻ ዐሊሞች ይህን የአላህ ዓላማ በመተግበር አቻ የለሽ ይመስሉኛል። በዘመን ተሸጋሪ ግጥሞቻቸዉ ነብዩንﷺ እስከ ጥግ አሞግሰዋል። በገለጻ ስልታቸዉ ልባማዎችን አስደምመዋል። አይናማዎችን አስለቅሰዋል። ለምሳሌ እዉቁ ዐሊም ሸኽ አህመድ ሲራጅ እንዲህ ተቀኝተዋል፦

ذاك نبينا الحبيب المصطفا

محط الرحال شمس بلا خفا

منتهى الأمال كما قد عرفا

---

[45] ጀላኡል አፍሀም፣248

[46] ጦበራኒና በይሀቂ

[47]ቲርሚዚና ዳሪሚ

[48]በይሀቂና አቡኑዐይም

[49] አልሸርህ 4

أعرف العرفا أشرف الشرفا

إمام الحنفا ونعم الإمام

እነሆ ነብያችን ምርጡ፣

የኛ ተፈቃሪ አማላይ፤

የጉዞዎች ሁሉ ማብቂያ፣

አንጸባራቂ፣ ደፋ እንደጣይ፤

የምኞቶች ዳርቻ፤

ፕበብ ዕዉቀቱ ያሳቻ፤

ኢማም- የቅኖች መሪ፤

እጹብ ድንቅ አስተማሪ፤[50]

بحر أنواره عميق دافق

فمن أمواجه تبد الحقائق

مدد الحضرت كأسها الرائق

كبرت أحمر وبدر شارق

إمام فائق جاهه عظيم

የብርሀኑ ባህር ፕልቀቱ፤

ደግሞም (ስፋት) ዉበቱ፤

[50]‹ሙከረሙ› ከተሰኘዉ የመንዙማ ግጥም የተወሰደ

ማዕበሉ ሲማታ፤

ያፈልቃል (ጥበብ) እዉነታ፤

የማዱ መደድ ችሮታ፤

ባስዉብ ጽዋ ገበታ፤

አንጸባራቂ ኮከብ፣ዉድ ገጸ በረከት

የተዋጣለት መሪ፣ለክብሩ አቻ የታጣለት፤[51]

ታላቁ ዐሊም ሸኽ ሸሀቡዲን አህመደ እብን አህመድ አል-ዳኒ (ዳንዩል አወል)(እስከ1321 ሂጅሪ) ነብዩን ﷺ እንዲህ ተቀኝተዉ ገልጸዋቸዋል፡-

أول المخطوب للحب

فى ذاك الجناب الأغرب

በዚያ በሳይኛዉ ሀገር፣

ቀድመዉ የታጩ ለፍቅር፣[52]

منبع العلم والحكم

حامل رايات الكرم

مهبط السر الربانى

نخبة أولاد أدم

የእዉቀት የጥበብ መፍለቂያ፣

የችርነት አርማ መዝለቂያ፣

[51] ያለፈዉ ምንጭ

[52]‹በሳዘይኒል ዉዱድ› ከተሰኘ የግጥም መድብል የተወሰደ

የአምላክ ሚስጥርገበታ፣

ያደም ልጆች ዓይነታ፤[53]

በእርግጥ ነብዩን ﷺ ለመግለጽና ለማሞገስ ሁሉም ትዉልዶች ያቅማቸዉን ያህል ጥረዋል። ዳር የደረሰ ግን የለም። ሁሉም እንደተሳናቸዉ ገልጸዋል። ግብጻዊዉ ማዲህ ሸኽ ቡሰይሪ (608- 694 ሂጅሪያ)[54] እንዲህ ሲሉ መሸነፋቸዉን ተናዘዋል፦

إن من معجزاتك

العجز عن وصفك

አምላክ ከሰጠህ ታምር፣
ምጠናህ ገደ መችገር፤[55]

ኢትዮጵያዊዉ ዐሊም ሸኽ ሰይድ ኢብራሂም (የጫሌ ሸኽ)[56] እንዲህ ይሉናል፦

ሙሀመድ አሚኑ የጀሊል ቢትወደድ

ማዕናዉ[57] የተሳነዉ በሀድም በዐደድ[58]

---

[53]‹ሶለላህ ዐለይህ ወሰለም> ከተሰኘዉ የግጥም መድብል የተወሰደ

[54]ሸኽ ቡሰይሪ ታዋቂ ግብጻዊ ገጣሚና የአረብኛ ቋንቋና ስነጽሁፍ ሊቅ ናቸዉ። በግጥሞቻቸዉ ደበልጡኑ ይታወቃሉ። በተለይም ሀምዝያ እና ቡሩዳህ የተባሉ ነብዩን የሚያወድሱ ግጥሞቻቸዉ ሳስፋት 700 ዓመታት የብዙዎችን ቀልብገዝተዋል። በሀገራችን ዑለሞች ዘንድም በስፋት ይታወቃሉ። ማድ ተደርገዉም ይቀራሉ። በዚህ መጽሀፍ ዉስጥ ደጋግመን እናወሳቸዋለን።

[55]‹ሀምዝያ› ከተሰኘዉ የግጥም መድብል የተወሰደ

[56]እዉቅ ዐሊም ናቸዉ። በሀገራችን ዐሊሞች ላይ ተጽዕኖ በማሳደር አቻ የሚገኝላቸዉ አይመስልም። ሸኽ ሙሀምደ ሳኒ ሀቢብ ስለርሳቸዉ ባዘጋጁት ግጥም ‹የነብዩ ሙዕጂዛ› ብለዋቸዋል። ሀጅ ሙሀመድ ወሌ ‹ሲቃዙ ሂመሚል አግቢያአ› ከተባለ ኪታባቸዉ ዉስጥ (ቅጽ2፣ ያልታተመ) ‹ሀሳን አንደበቱን፣ቡሰይሪ ብዕሩን ያዋሳቸዉ ሰዉ ናቸዉ› በማለት ችሎታቸዉን መስክረዉላቸዋል።

[57] ትክክለኛ ማንነቱ

[58]ሀድ-ምጠና፣ዐደድ-አሀዝ

ከሀድራዉ[59] ደፈልቃል ኑቡዋ[60]ና ሱዩድ[61]

ሌላዉ ኢትዮጵዊ ማዲህ ሸኽ አህመድ ሲራጅ ይህንኑ ያጸናሉ፡-

حرت العقول فى حسن نعته

عن وصف ذاته كلت الأقلام

የስብዕናዉ ማማር አዕምሮን ፈተነ፤

ዛት ሲፈቱን[62] መግለጽ ስብዕር ተሳነ፤[63]

قدر كماله جل عن الحد

فاق شرفه كل أهل المجد

وما لأحد فوقه مقام

የልዕልናዉ ምልዓትከምጠና ሳቀ፤

አንቱዎችን ሁሉ ከበጃዉ ዘለቀ፤

ከርሱ በላይ ልዑል ከቶም አልታወቀ፤[64]

مديحه الصاف حرفت الكرما

فاق الدر نظما والشهد مطعما

قد أعجز الوصف فما وقلما

[59] ከማዕዱ
[60] የነብይነት ጥበብ
[61] ትክክለኛና ቅን መመሪያዎች
[62] አካል ባህሪዉን
[63] ‹ሙከረሙ› ከተሰኘ ግጥማቸዉ
[64] ያስፈዉ ምንጭ

ማወደስ የርሱን ክበጃ[65]፣

ያንቱዎች ሞያ ደረጃ፣

ክብሩ ገዝፎ ገነነ፣

ስብዕር ሳንደበት ተሳነ፤[66]

ነብዩን ﷺ ማወደስ አምላካዊ ዓላማ ነዉ። የርሳቸዉም ጥብቅ ፍላጎት ነዉ። ሶሀቦች ተክነዉበታል።ዑለሞች የክህሎታቸዉ መመዘኛ አድርገዉታል። **ከዕብ እብን ዙሀይር የተባሉት ሶሀባ የተቀኝዋት *‹ባነት ሱዐዱ›* ቅኔ ለዚህ አባባላችን ቋሚ ምስክራችን ናት። ነብዩን ﷺ የፍቅር ንግስት በሆነች ሴት አስመስለዉ አሞካሽተዋቸዋል።**

የመዉሊድ ማዕዶች ይህን አምላካዊ ፍላጎት በሚገባ ያሳካሉ፤ የመደራጀታቸዉ አብይ ዓላማም ይህ ነዉ ይላሉ ደጋፊ ዑለሞች።

ሀሳባችንን ስንጠቀልለዉ የመዉሊድ አንደኛዉ ዓላማ ነብዩን ﷺ ማስታወስና ክብራቸዉን ከፍ ከፍ ማድረግ ተደርጎ ይነገራል።

4. <u>ከነብዩ ﷺ ጋር በፍቅርና በስሜት (emotion) ማስተሳሰር</u>፡- ነብዩን ﷺ ማፍቀር የኢማን አስኳል መሆኑን መግለጽ አስፈላጊ አይመስለኝም። ‹‹ጸሀይ በምስራቅ ትወጣለች›› ብሎ የመናገር ያህል ነዉና። ሶሀቦች ልዩ የሆኑት ከምንም በላይ በፍቅር ነዉ። የአላህን መልዕክተኛ ﷺ ከራሳቸዉ በላይ ወደዱ። ይህ ፍቅር የኢማንን ለዛ ሰጣቸዉ። ጥልቅ እምነት ተአምራትን አሠራቸዉ። የአላህ

[65] ልዕልና
[66] ያስፈዉ ምንጭ

መልዕክተኛﷺ ይህን እውነታ ሲናገሩ ፦ ‹‹ ሦስት ባህሪያት ያሉት ሰዉ የኢማንን ስዛ አጣጥሚል›› ካሉ በሁዋላ አንደኛዉ ‹‹አላህንና መልዕክተኛዉን ከማንም በላይ የሚወድ››መሆኑን ገልጸዋል።[67] ‹‹ከናንተ አንዳችሁ ከልጁ፣ ከወላጁና ከሰዉ ልጆች ባጠቃላይ አስበልጦ እስካልወደደኝ ድረስ አላመነም፤››[68]

ሶሀቦች ለነብዩﷺ ከነበራቸዉ ፍቅር የተነሳ ከርሳቸዉ መለየት ይጨንቃቸዉ ነበር። በመጭዉ ዓለም የሚሆነዉ ሳይቀር እንቅልፍ ይነሳቸዋል። ለካ ይህ ሀሳብ ሁሉንም ያለልዩነት ያብሰለሰል ኖሯል፡ ፡ አንድ ቀን አንድ ሰዉ ለነብዩ፦ ‹‹ያረሱለላህ›› ብሎ በመጀመር ያቀረበዉ ጥያቄ የሁሉንም የልብ ትርታ የነካ ነበር። አላህ ጀዛዉን ይክፈለዉ። ለኛም ታላቅ ብሥራት አስተላለፈልን። ‹‹ ቂያማ መቼ ነዉ?›› በማለት ጠየቃቸዉ። ‹ለርሷ ምን አዘጋጅተሀል?› ሲሉት ‹‹የአላህንና የመልዕክተኛዉን ﷺፍቅር›› በማለት መለሰ። መልዕክተኛዉﷺ እንዲህ ሲሉ አበሰሩት። ምን እርሱን ብቻ፤ ሁላችንንም አበሰሩን እንጅ። ቃላቸዉን እነሆ፦

فإنك مع من أحببت

‹‹በመጭዉ ዓለም ከወደድካቸዉ ጋር ትሆናለህ።››[69]

‹ወዳችሁኛልና አይሏችሁ፤አንለያይም፤አብረን እንዘልቃለን› ማለታቸዉ ነዉ። ይህ ብሥራት ለሶሀቦች በምንም ነገር የሚተመን አልነበረም። የተሰማቸዉን ጥልቅ ደስታ በአነስ አንደበት ሲገልጹ፦ ‹‹ከእስልምና ቀጥሎ እንደዚያን ቀን ተደስተን አናዉቅማ፤እኔ አላህን፣

[67] ቡኻሪና ሙስሊም
[68] ቡኻሪ፣ሙስሊም አህመድ፣ቲርሚዚ፣ነሳኢ
[69] ሙስሊም

መልዕክተኛዉን፣አቡበክርንና ዑመርን ስለምወድ የነርሱን ሥራ ባልሠራም በመጭዉ ዓለም አብሪያቸዉ እንደምሆን ተስፋ አደርጋስሁ።››[70]

በነብዩﷺ ፍቅር ክፉኛ የተጠመዱት ሶሀቦች ያልፈጸሙት የፍቅር ጀብዱ አልነበረም፡-

1. አንድ ቀን ነብዩﷺ ታግመዉ ሲጨርሱ፡- ‹‹ይህን ደም ዉሰድና ሰዉ እንዳያገኘዉ አድርገህ ቅበረዉ›› ተብሎ ዐብደላህ እብን ዙበይር ታዘዘ። ደም ያለበትን ገበታ አነሳና ከቤት ወጣ። ዙሪያዉን ገልመጥ አድርጎ ሰዉ አለመኖሩን ሲያረጋግጥ ግጥም አድርጎ ጠጣዉና አፉን አባብሶ ወደቤት ተመልሶ ገባ። ‹የት ቀበርከዉ?› በማለት ጠየቁት። ‹ማንም ከማይደርስበት ቦታ ቀብሬዋለሁ›› አላቸዉ። ነብዩﷺ ነገሩ ገባቸዉና፡- ‹‹ጠጥተህዉ እንዳይሆን›› አሉት። ‹‹አዎ፣የአላህ መልዕክተኛ፣ጠጥቸዋለሁ›› አላቸዉ። ፈገግ አሉና፡- ‹‹ለምን?›› በማለት ሲጠይቁት፡- ‹‹የርስዎ ደም ከሰካሴ እንዲቀላቀል›› አላቸዉ። ‹‹እንግዲያዉስ አካልህን አሳት አይነካዉም›› አሉት።[71]

2. ከዚህ የባሰም ጀብዱ አለ። የዚህ ጀብዱ ባለቤት የረሱሉﷺ አሳዳጊ ኡም አይመን (በረካ) ናት። እንዲህ ሆነ። ነብዩﷺ ሽንት የሚሸኑበት ገበቴ ነበር። ከአልጋቸዉ ሥርም ይቀመጣል። አንድ ቀን አነሳችና ግጥም አድርጋ ጠጣችዉ። ባዶ ሆኖ ሲያዩትና የት እንደተደረገ ሲጠይቋት ‹‹ጠጣሁት›› አለቻቸዉ። ከዚያን ዕለት ጀምሮ የሆድ ህመም ነክቷት አያዉቅም። ‹‹ከአሳት በጥሩ መጠበቂያ ተጠበቅሽ›› ብለዋታል።[72]

[70] ሙስሊም

[71] ሀኪም፣ጦበራኒ፣በዛር

[72] ዐብዱረዛቅ፣አቡዳዉድ፣ነሳኢ፣እብን ዐብደልበር፣

ዑለሞች እነዚህንና መሰል ክስተቶችን መረጃ በማድረግ ከነብዩ ﷺ አካል የሚወጣ ማንኛውም ነገር ጦሀራ እንደሆነ መግለጻቸውን ኢማም አልነወዊ[73]፣በድረዲን አልዐይኒ[74]፣እና ሌሎችም ጽፈዋል። በዚህ ረገድ ሊጠቀሱ የሚችሉ መረጃዎች በርካታ መሆናቸውንና ሚዛን የሚደፋዉም ይህ መሆኑን አልሀፊዝ አልቀስጦላኒና አልሀፊዝ እብንሀጀረል ዐስቀላኒ መጻፋቸዉ ታዉቋል።[75]

ይህ ፍቅር በትዕዛዝ የሚመጣ አይደለም። ‹‹ከዛሬ ጀምሮ ነብዩን ﷺ እወዳለሁ›› በማለት ስለወሰንን ወይም ስለፎከርንብቻ አይከሰትም። ጥረቶችን ይፈልጋል። ዋነኛዉ ግን ስብዕናቸውን ጠልቆ ማወቅ ነዉ። በወጉ የማናዉቀዉን አካል ‹‹ዉደዱት›› ተብለን ስለታዘዝን ብቻ ልንወደዉ አንችልም።

የመዉሊድ ማዕዶች አስኳል ሚና ይህን መተዋወቅ መፍጠር ነዉ። በዉስጣቸዉ የዓለማት ዕዝነት ﷺ ገድል ይዘከራል። እያንዳንዱ የህይወት እርከናቸዉ በመሳጭ ገለጻዎች ይዘረዘራል። የዚያ መድረክ ገለጻዎች ነብዩ ﷺ ካጠገባችን ያሉ ያህል እንዲሰማን ያደርጉናል። የሀምዝያዉ ከያኒ በአስደማሚ ስንኞቹ የቅድመ ልደት ታሪኮችን እየጠቀሰ፣ ***‹‹ለምተዘል ፊዶማኢሪል ከዉኒ ቱኽታሩ ለከል ኡመሀቱ ወልአባኡ››***/ያንተን ክብርና ልዕልና የሚመጥኑ ተስማሚ ወላጆች፣ተስማሚ ማህጸን እየተፈለገልህ ከዩኒቨርሱ ሙዳይ ዉስጥ በክብር ተኑረህ ስሚሲዮኖች ዓመታት ስትጠባበቅ ኖረሀል/በሚሉና መሰል መሳጭ መልዕክቶቹ የታዳሚዉን ስሜት ሲያግል ከቆየ በኋላ ***‹‹ዉሊደል***

[73] ሸርህ አልሙሀዘብ 1/233

[74]ዑምደቱል ቃሪ 2/35

[75]አብን አልዐለዊ፣መፋሂም የጂቡ አንቱሶሀህ፣ ጀዋሚዐል ከሲም አሳታሚ፣(ዘመኑ ያልተጠቀሰ)፣ካይሮ፣ገጽ 169-170

ሙሰጦፉ ወሀቀል ሀናኡ››ክሚለዉ ቦታ ላይ ሲደርስ መልዕክቱ የገባዉ ታዳሚ ነብዩﷺ አሁን የተወለዱ ያህል ይሰማዉና ደስታዉ ወሰን ያጣል። በዘመናቸዉ የመዲና የሻፊዒ መዝሀብ ሙፍቲ የነበሩት የሀዲስ ሊቁ ***ጀዕፈር እብን ሀሰን እብን ዐብዱልከሪም ሐልበርዘንጂይ*** (እስከ1177 ሂጅሪያ) ያዘጋጁት ***በርዘንጅ*** የተባለ የመዉሊድ ኪታብ በሚቀራ ጊዜ መልዕክቱ የሰረጸዉ ታዳሚ በምናብ ምዕተ ዓመታት ተሻግሮ መንዙ የሚጠበቅ ነዉ። ነቢዩﷺ መወለዳቸዉ ሲበሰር፣ ብስራቱ ዛሬ የተሰማ ይመስል ስሜት ፈንቅሎት ‹‹እንኳን ደህና መጡልን›› በማለት የዓለማትን እዝነት ሊቀበል ከተቀመጠበት ይነሳል-‹‹***መርሀበን ቢል ሙሰጦፉ***።።›› ይህ ሂደት ልምድ ሆኖ በዱዐ ማዕዶች ላይ እስካሁን ይተገበራል።[76]

በመዉሊድ ማዕዶች ላይ የሚደመጡ ነብዩንﷺ የሚያወድሱ ግጥሞችና ዜማዎች ልዩ የፍቅር ስሜት ይፈጥራሉ። ልብን ከርሳቸዉ ጋር ያስተሳስራሉ። የኪነጥበብ ጉልበት ኃያል መሆኑን ለመረዳት ከሆሊዉድ ዘመን በላይ እማኝ አያሻም። ‹ነቢዘይኔ›ና ‹‹ጌታየ እንዴት ነሁ››[77]ከወሎ እስከራያ፣እስከ ጎንደርና ጎጃም፣ እስከ ሰሜን ጫፍ ፣እስከመሀል ሀገር፣ ከዐሊም እስከ ተራዉ ህዝብ ሺዎችን ለዘመናት አስለቅሰዋል። በ‹‹*ሙክረመ*››[78] ያላነባ፣ በ‹*ራምሳ*›[79] ያልቆዘመ የዚያ የሀገራችን ጥግ ሙስሊም የለም ቢባል አልተጋነነም። የማዉቀዉን አካባቢ ጠቀስኩ እንጅ በሁሉም የሀገራችንና የዐለማችን ክፍሎች ሂደቱ ተመሳሳይ ነዉ። እነሆ አሁንም ድረስ በየዱዐ ማእዱ እየተነበበ ያስለቅሳል። የቅርቡ

[76] የነብዩ መወለድ ሲበሰር መቆም ግዴታ የሚመስላቸዉ ካሱ ስህተት ነዉ። ነብዩን ለማላቅ የሚደረግ ልምድ እንጅ ሸሪዐዊ ግዴታ አይደለም፤

[77] ዕዉቅ መንዙማዎች ናቸዉ።

[78] የሸኽ አህመድ ሸኽ ሲራጅ መሳጭ ግጥም

[79] በሀበሻ ዐሊሞች፣በዋነኝነት በሸኽ አህመዲዲ የተዋቀረ የዱዐና የዚክር ስብስብ

‹‹ፊዳኽ››[80] እንኳ ወጣቶቻችንን ማማለል ችሎ የብዙ ሺህ ሞባይል ስልኮች የጥሪ ድምጽ ለመሆን ታድሏል። ***የሸኽ ቡሰይሪ ‹ቡሩዳ›ና ‹ሀምዚያ›*** በዓለም ሙስሊሞች ላይ ላለፉት 700 ዓመታት ያሳደሩት የፍቅር ተጽዕኖ ምን ማካካሻ ይገኝለታል?

የመዉሊድ ማዕዶች እንዲህ ዓይነት መሳጭ አጋጣሚዎችን በመፍጠር ህዝበሙስሊሙን ከነብዩ ﷺ ጋር በስሜትናበፍቅር ያስተሳስሩ ዘንድ የታለሙ ናቸዉ።

5.<u>የዳዕዋና የዚክር መድረክ መፍጠር</u>:- አጋጣሚዎችን እየተጠቀሙና መድረክ እየፈጠሩ ሰዎችን ዲን ማስተማር ከዐሊሞች ይጠበቃል። ታሪካዊ ክስተቶች ደግሞ ጥሩ አጋጣሚዎች ናቸዉ። በረመዳን ከጾም በተጓዳኝ ስለበድር፣ፈትህና ሌሎች በወሩ የተከሰቱ ዘመቻዎች፣እንዲሁም ሌሎች የሀይማኖት ዕዉቀቶችን፣ በሀጅ ወቅት ከሀጅ በተጨማሪ ሌሎች ሀይማኖታዊ መልዕክቶችን እንደምናስተላልፈዉ ሁሉ የመዉሊድ ማዕዶችም በተመሳሳይ ሁኔታ ጥሩ የዳዕዋ መድረኮች ናቸዉ። በተለይም ነብያዊዉ ወር ሲገባ ስለዓለማት እዝነት ﷺ ብዙ ለመናገር ጥሩ ታሪካዊ አጋጣሚ ይፈጥራል። ከርሱ በተጨማሪ ሌሎች መንፈሳዊ መልዕክቶች ይተላለፋሉ።

የመዲናዉ የሀዲስ አዋቂ ሸኽ ሙሀመድ እብን አልዐለዊ በመካና በመዲና ለዘመናት ሲደረጉ የነበሩ የመዉሊድ መታሰቢያ ዝግጅቶች ከፍተኛ የዳዕዋ መድረክ ሆነዉ ሲያገለግሉ እንደኖሩ ጽፈዋል።[81]

---

[80] በነፊያ አባሚጫ የተዜመ፣

[81] ሰይድ ሙሀመድ አብን አልዐለዊ አልማሊኪ አልሐሰይኒ፣ አል ኢዕላም ቢፈታዋ አሺመቲል ኢስላም ሀዉስል መዉሊዲ ወስይሂ ሶላቱ ወሰላም፣ዳረል ኩቱቡል ዒልምያህ፣ ቤይሩት፣2005፣ገጽ 10

በሀገራችን ያለዉ የመዉሊድ ታሪክና ልምድም ተመሳሳይ አንደሆነ አዛዉንቶች ይተርካሉ።ከዚህም አልፎ መዉሊድ ብቸኛዉ የዳዕዋ መድረክ ነበር ማለት ይቻላል።[82]

መዉሊድ አላህን የማስታወሻ (ዚክር) መድረክ፣በነብዩﷺ ላይ በብዛት ሶለዋት የማዉረጃ ማዕድ ሆኖም ያገለግላል።

[82] Informants shekh siraj and shekh abdela

ምዕራፍ ሁለት

ታሪካዊ አመጣጥ

የመዉሊድን ሸሪዐዊ መነሻዎች ለመተንተንና በርሱ ዙሪያ የተከሰቱ የሀሳብ ልዩነቶችን በወጉ ለመረዳት ታሪካዊ አመጣጡን ማወቅ ትልቅ እገዛ ያደርጋል፡፡ በያዝነዉ ምዕራፍ ዉስጥ የሚከተሉትን አጀንዳዎች እንመለከታለን፡-

1. መዉሊድ በግለሰባዊና በነፍስ ወከፍ ደረጃ መከበር የጀመረበት ጊዜ፣
2. በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በሀገራችን ህዝባዊና ኦፊሴላዊ ባዕል በመሆን መከበር የጀመረበት ጊዜና
3. ህዝባዊና ኦፊሴላዊ አከባበሩ እስከኋለኛዉ ዘመን ሊዘገይ የቻለባቸዉ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ድባቦች፤

መዉሊድን የጀመሩስብዕና

ለነብዩ ﷺ ልደትና ለሌሎች ታሪካዊ አጋጣሚዎች ልዩ ትኩረትና ክብር መስጠት የተጀመረዉ በነብዩ ﷺ ዘመን፣ በራሳቸዉ በነብዩ ﷺ እንደሆነ ከሚያመለክቱ የሀዲስ ዋቢዎች መካከል የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸዉ፡-

1.ሙስሊም በዘገቡት ሀዲስ የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ሰኞ ቀን ለምን እንደሚጾሙ ተጠይቀዉ ሲመልሱ፡- ‹‹የተወለድኩበትናየተላኩበት ወይም ወደኔ መልዕክት የተወረደበት ቀን ስለሆነ ነዉ›› አሉ፡፡[83]

ይህ ሀዲስ ሁለት ነገሮችን ያስተምራል፡

ሀ. ነብዩ ﷺ ለልደታቸዉ ቀን ትኩረት መቸራቸዉና ማላቃቸዉ፣

ለ. ዕለቱን በዒባዳ ማሳለፋቸዉ፤

[83]ሶሂህ ሙስሊም

የነብዩﷺ ልደት መታሰቢያ (መውሊድ) እነዚህ ሁለት እሴቶች የሚንጸባረቁበት መድረክ እንጅ ሌላ አይደለም።

2. ቡኻሪና ሙስሊም እንደዘገቡት የአላህ መልዕክተኛﷺ ወደመዲና ሲገቡ አይሁዶች የዐሹራን ቀን ሲጾሙ አገኟቸዉና ለምን እንደሚጾሙ ሲጠይቋቸዉ፦ ‹‹አላህ ፈርዐዉንን አስጥሞ ሙሳን ያዳነበት ቀን ስለሆነ እርሱን ለማመስገን ስንል ዕለቱን በጾም እናሳልፈዋለን›› አሏቸዉ። ነብዩም፦ ‹‹ ለሙሳ እኛ ከናንተ ይበልጥ የተገባን ነን›› አሉና የዐሹራ ቀን እንዲጾም አዘዙ።[84]

ኢማም እብንሀጀር አልዐስቀላኒ (እስከ 826 ሂጅሪያ) ይህን ሀዲስ *‹‹አስለ-ን ሳቢት›› /ለመወሊድ መታሰቢያ ሸሪዐዊነት ጽኑ መነሻ/* ካሉት በኋላ ሁለት መሠረታዊ ትምህርቶች እንደሚቀሰሙበት ገልጸዋል። *አነርሱም፦*

ሀ.አላህ በአንድ የታሪክ ወቅት ጸጋዉን በመለገስ ለዋለዉ ዉለታ በየዓመቱ በልዩ ሁኔታ ማመስገን፣

ለ. ምስጋናዉ በጾምና በሌሎች ዒባዳዎች መገለጽ እንደሚችል፤ ኢማሙ ይህን ካሉ በኋላ፦ *‹‹ ነብዩﷺ ከመወለዳቸዉ የበለጠ ለሰዉልጅ የተሰጠዉ ጸጋ የለም››* ሲሉ የሚከተለዉን የቁርአን መልዕክት በዋቢነት ጠቅሰዋል፦[85]

لَقَدْ مَنَّ اللَّهُ عَلَى الْمُؤْمِنِينَ إِذْ بَعَثَ فِيهِمْ رَسُولًا مِّنْ أَنفُسِهِمْ يَتْلُو عَلَيْهِمْ آيَاتِهِ وَيُزَكِّيهِمْ وَيُعَلِّمُهُمُ الْكِتَابَ وَالْحِكْمَةَ وَإِن كَانُوا مِن قَبْلُ لَفِي ضَلَالٍ مُّبِينٍ [٣:١٦٤]

> ‹‹አላህ በምእምናን ላይ ከገሳቸው የኾነን፤ በእነርሱ ላይ አንቀጾቹን የሚያነብ፣ የሚጠራቸውም፣ መጽሐፍንና ጥበብን የሚያስተምራቸውም የኾነን መልእክተኛ በውስጣቸው በላከ ጊዜ፤ በእርግጥ ለገሰላቸው። እነርሱም ከዚያ በፊት በግልጽ ስህተት ውስጥ ነበሩ።››[86]

---

[84]ቡኻሪና ሙስሊም

[85]ጀላሉ ዲን አልሱዩጢ፣ሁስነል መቅሰድ ፊዐመሊል መዉሊድ

[86]አስ-ሳምራን፣ 164

ስለዚህ በታሪክ ውስጥ ታላቅ የአላህ ጸጋ የተከሰተባቸዉን ቀናት በየዓመቱ በዒባዳና በበጎሥራ አስቦ መዋል ከራሳቸዉ ከነብዩﷺ የተሰጠ ትምህርት ነዉ።

ከላይ የተጠቀሱ ሁለት ሀዲሶች እና የዑለሞች ገለጻዎች በአንድ ላይ ሲገጣጠሚ፡-

1. አላህ ዉለታ የዋለበትን ቀን በየዓመቱ ማሰብ ሱና ነዉ፣

2. የማሰቡና የምስጋናዉ አፈጻጸም በበጎ ሥራ ሊሆን ይገባል፣

3. ነቢዩﷺ ልደታቸዉን በዚህ መልኩ ዘወትር ሰኞ በጾም በማሳለፍ መዉሊድን ማክበርን በተግባር አሳይተዋል።

4. ጾም የዒባዳዎች ናሙና ሆኖ ቀርቧል። ልክ እንደርሱ ሁሉ ሌሎች ዒባዳዎችም ‹ቂያስ› በተሰኘዉ የሸሪዐ ምንጭ መሠረት አላህን ለማመስገን አገልግሎት ይዉላሉ።

ከላይ የቀረቡትና መሰል ሀዲሳዊ መረጃዎች፣እንዲሁም ሊቃዉንት ለነርሱ የሰጡት ትንታኔና አገነዛዘባቸዉ ለሸኽ እብን አልዐለዊና ለመዉሊድ አወንታዊ እይታ ላላቸዉ ሌሎች ዐሊሞች መዉሊድ በነብዩﷺ በራሳቸዉ እንደተጀመረ አስረጅዎች ናቸዉ። እንዲህ ይሉናል፡-

‹‹መዉሊድ በግለሰብ ደረጃ መከበር የተጀመረዉ በነብዩﷺ ዘመንና በራሳቸዉ በመልዕክተኛዉﷺ ነዉ፤ይህም በመሆኑ በፋጢምዮች ዘመን እንደተጀመረ የሚናገሩ ሰዎች አንድም መሠይማን፣አስደም እዉነቱን የሚያድበሰብሱ ናቸዉ።››[87]

[87]አል ኢዕላም...ገጽ 12

ህዝባዊና ኦፊሴላዊ አከባበር

መዉሊድ በግለሰብ ደረጃ፣በሳምንታዊ ዑደት በነብዩ ﷺ በራሳቸዉ የተጀመረና በሶሀቦችም በነፍስ ወከፍ ደረጃ የተተገበረ ቢሆንም እንደማህበረሰብና በመንግስት የሙስሊሙ ህብረተሰብ የጋራ ክስተት ሆኖና በዓመታዊ ዑደት መታሰብ የጀመረዉ ነብዩ ﷺ ካለፉ ከ5 ምዕተ ዓመታት በኋላ እንደሆነ የታሪክ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ እዉቁ የታሪክ ሊቅ ኢማም እብን ከሲር አልቢዳየቱ ወኒሀያ በተባለ ድርሳናቸዉ እንደገለጹት የመዉሊድ ሥራ በየዓመቱና በኦፊሴል እንዲከበር ፊር የቀደደዉ የአዩባዊዉ ሱልጣኔት አካልና የታላቁ ሙጃሂድ የሶለሀዲን አልአየቢ የእህት ባል የሆነዉ የኤርቢሉ አስተዳዳሪ መሊክ ሙዞፈር (549-630 ሂጅሪያ)[88] ነዉ፡፡ ኤርቢል በዒራቅ ሰሜናዊ ክፍል የምትገኝ ከተማ ናት፡፡[89] ኢማሙን በቀጥታ ልጥቀስ፡-

‹‹ንጉስ ሙዞፈር፣አቡሰዒድ አልከዋኪቢ ቸርና የተከበረ ከሆኑ ታላላቅ ንጉሳን መካከል አንዱ ሲሆን፣ ብዙ መልካም አሻራዎች አሉት፡፡ በወርሀ ረቢዐል አወል የተሳቀዉን የመዉሊድ ሥራ ይሠራ ነበር፡፡ ታላቅ በዐልም ያዘጋጅ ነበር፡፡ ከዚህ ምግባሩ ጋር አይበገሬ ጀግና፣ጠንካራ፣አስተዋይ፣ዐሊምና ፍትሀዊ ነበር፡፡ አላህ ይዘንለት፡፡ ማረፊያዉንም ያሳምርለት፡፡...ስመዉሊድ 300 ሺህ ዲናር ወጭ ያደርግ ነበር፡፡››[90]

የኢማም አልነወዊ ሸኽ የሆኑት አልሀፊዝ አቡሻመህም እንደዚሁ መዉሊድን በህዝባዊ መታሰቢያነት የጀመረዉ ንጉስ ሙዞፈር መሆኑን ጠቅሰዉ ጽፈዋል፡፡[91] ኢማም አልሱዩጢም እንደዚሁ ይህንኑ

[88]ወፈያቱልአዕያን 4/120
[89]ሙዕጀሙል ቡልዳን
[90]አብን ከሲር፣አልቢዳየቱ ወልኒሀያ፣ገጽ 13/136
[91]አል ባዒስ ዐላኢንካሪል ቢደዒ ወልሀዋዲስ፣ገጽ 21

አረጋግጠዋል።[92] በሀገራችን ዑለሞች ዘንድ የሚታወቀዉና የሚታመነዉም ይህዉ ነዉ።[93]

ኢማም እብን ከሲር ስለዚህ ንጉስ የሰጡት አንጸባራቂ ምስክርነት ለሰዉየዉና ለድርጊቶቹ ያላቸዉን ድጋፍ በጉልህ ያሳያል። የቁርአን ተፍሲራቸዉ በመዉሊድ ተቃዋሚዎች ዘንድ ሰፊ ተቀባይነት ያገኘ፣የሀዲስና የታሪክ ሊቅ፣ እንዲሁም በአንዳንድ ወገኖች ዘንድ በጣሙን የሚከበሩት የሸኽ እብን ተይሚያህ ተማሪ መሆናቸዉ ምስክርነታቸዉን እጅግ ጠቃሚ ያደርገዋል። በነገራችን ላይ ሌላኛዉ የእብን ተይሚያህ ተማሪ የሆኑት ኢማም አልዘሀቢም የኤርቢሉን ንጉስ እንዲህ አሞግሰዉታል፡-

‹‹ትሁት፣በንተግባር የሚያበዛ፣ሱንደ፣እንዲሁም የሀዲስና የፊቅህ ሲቃዉንትን የሚወድ መልካም ሰዉ ነበር።››[94]

ከመዉሊድ ቀንደኛ ነቃፊዎች መካከልም ብዙ ጸሀፍት መዉሊድን በኦፊሴል የጀመረዉ ንጉስ ሙዘፈር መሆኑን ይቀበላሉ። የሳዉዲዉ ዕዉቅ ዐሊም ሸኽ ሳሊህ አል-ፈዉዛን ከነርሱ መሀል አንዱ ሲሆኑ የሚከተለዉን ጽፈዋል፡-

فأول من أحدثه الملك المظفر أبو سعيد كوكبوري ملك إربل في آخر القرن السادس

أو أول القرن السابع الهجري، كما ذكره المؤرخون كابن كثير وابن خلكان وغيرهما.

‹‹እንደ እብን ከሲርና እብን ኸልካን ያሉ የታሪክ አዋቂዎች እንደጻፉት መዉሊድን ስመጀመሪያ ጊዜ የፈበረከዉ የኤርቢሉ ንጉስ መሊክ ሙዘፈር

[92]አልሱዩጢ፣አልሀዊ ሊልፈታዊ 1/189
[93]ሙፍቲ ሀጅ ዑመር እድሪስ፣ሸኽ ዐብደላ እድሪስና ሸኽ ሲራጅ ማህሙድ፣
[94]ሲየር አዕላመ ኑበላእ፣22/336

አልከዋኪቢ ሲሆን፣ጊዜዉም አንደ ሂጅሪያ አቆጣጠር በስድስተኛዉ ክ/ዘመን መጠናቀቂያ ወይም በሰባተኛዉ ክ/ዘመን መጀመሪያ ላይ ነዉ።››[95]

አንዳንድ ወገኖች መዉሊድን የፈበረኩት የሸዐ እምነት አራማጅ የነበሩትና ግብጽን ከ357-567 የገዙት **ፋጢምዮች** መሆናቸዉን እብን ከሲር አልቢዳየቱ ወኪሀያ 11/72 ላይ እንደጻፉ አድርገዉ ይናገራሉ። በእርግጥ ይህ ስህተት ነዉ። የተጠቀሰዉን መጽሀፍ ከጫፍ እስከጫፍ ብታገላብጡ ይህን ሀሳብ አታገኙም። ይህ ማለት ‹በፋጢምዮች መዉሊድ ተጀመረ› የሚሉ አጥኝዎች የሉም ማለት አይደለም፣ አሉ። ኢብን ከሲር ግን ከነዚህ አይመደቡም። በተለይም ለመዉሊድ አሉታዊ እይታ ያላቸዉ ልሂቃን ይህኛዉን ትርክት ከመጀመሪያዉ ያስበልጣሉ። ለምሳሌ ሸኽ ዐብደላህ አልቱወይጅሪ የተባሉ የሳዉዲ ዐሊም ይህን ሀሳብ ደግፈዉ ጽፈዋል።[96]

ዓመታዊዉን የነብዩን ﷺ ልደት የርሳቸዉን ታሪክ በማንበብና በሌሎች ዒባዳዎች አስቦ መዋል ከመዘፈርም በፊት በታላላቅ ዐሊሞች የተለመደ ተግባር እንደነበር የሚያመለክቱ የሰነድ ማስረጃዎች ይገኛሉ። እብን ጀቢር (ከ540 ሂጅሪ) እንደጻፉት ‹‹በረቢዐል አወል ወር ዘወትር ሰኞ የነብዩ ቤት ደከፈትና ታላላቅ ሰዎች እዉስጡ በመግባት ከበረካዉ ይቋደሳሉ።››[97]

እብን ጀቢር ወደመካ የተጓዙት በ579፣መዲና የገቡት በ580 ሂጅሪ እንደሆነና መዲና ዉስጥ ለ5 ቀናት መቆየታቸዉን በጉዞ ማስታወሻ መጽሀፋቸዉ ተርከዋል። ስለሆነም ከዚያ ዘመን በፊት በተቀደሰችዉ የመካና የመዲና ከተሞች ዑለሞች የመዉሊድን ዕለት የማክበር ልምድ እንደነበራቸዉ ይህ ጠቃሚ ሰነድ ያመለክታል።

---

[95] ሸኽ ፈዉዛን፣ሁክሙል ኢህቲፋል ቢዚክራ መዉሲዲ ነቢዊ፣መክተበተ ሻሚላ፣ቂስመል ዐቂዳ፣ገጽ 1

[96]አልቱወይጅሪ፣ቢድዐቱል ኢህቲፋል ቢል መዉሲድ፣መክተበተ ሻሚላ፣ገጽ6-8

[97]እብን ጀቢር፣ኪታቡ ሪህል፣ገጽ114-115

አቡሻመህ እንደጠቀሱትም ሸኽ ሳሊህ አልሙላ (እስከ 570 ሂጅሪ) የተባሉት የዕዉቁ መሪ የኑረዲን አልዙንኪ ወዳጅ ዐሊም በየዓመቱ የነብዩን ﷺ ልደት የሚያከብሩበት ድግስ ነበራቸዉ፡፡ በዚያ ድግስ ላይ ዑለሞችና ኑረዲንን ጨምሮ ታላላቅ ሰዎች ይሳተፉ ነበር፡፡[98]ስለኒህ ታላቅና ዛሂድ ሰዉ ልቅና ኢማም አልዘሀቢ[99]፣እንዲሁም እብን ከሲር የዚያን ዓመት ክስተት ሲጠቅሱ[100] ጽፈዋል፡፡ ኑረዲን የሹለፋኡ ራሽዲን ዓይነት መንግስትና ሥርዓት የዘረጋ እጅግ መልካም መሪ ነበር፡፡ ኢማም ዘሀቢ[101] እና ኢማም እብን ከሲር[102] ልቅናዉንና ለሱና ያለዉን ጽናት እየዘረዘሩ ጽፈዋል፡፡ እብን አሲር፡- ‹‹የንጉሳንንና የመሪዎችን ታሪክ ጠንቅቄ ያነበብኩ ሲሆን ከኹለፋኡ ራሽዲንና ከዑመር እብን ዐብድልዐዚዝ ቀጥሎ ኑረዲን አልዙንኪን የሚስተካከል ስብዕና ያለዉ የለም›› ሲሉ መስክረዋል፡፡[103]

በዚህ ንጉስ እዉቅና ስር፣በወቅቱ በነበሩ ታላላቅሰዎችና ዐሊሞች አማካይነት የነብዩ ﷺ ልደት በየዓመቱ ይታሰብ ነበር፡፡

የኤርቢሉ ንጉስ ሙዞፈር በሶለሀዲን የተሾመዉ በ586 ሂጅሪያ እንደመሆኑና መሓላ ዑመር የሞቱት በ570 እንደመሆኑ፣እንዲሁም የእብን ጀቢር የታሪክ ማስረጃ መዉሊድ በመካ፣በመዲናና በሌሎች የሙስሊሙ ዓለም ክልሎች በግለሰባዊ ደረጃ ይከበር እንደነበር ያመለክታሉ፡፡ የተጠቀሱት ግዛቶች በሙሉ ፋጢምዮች ይገዟት ከነበረችዉ ግብጽ በጣም የራቁና ከነርሱ የተጽእኖ ክልል ዉጭ መሆናቸዉ እነዚህን ክስተቶች መነሻ አድርገዉ መዉሊድን

98 አቡሻመህ፣አልባኢስ ፊሲንካሪል ሀዋዲስ
99ታሪኽል ኢስላም፣41/130
100 አልቢዳየቱ ወኒሀያ
101ሲየር አዕላመኑበላእ 20/532-532
102 አልቢዳያቱ ወኒሀያ፣12/278
103ታሪኽ እብን አሲር 9/125

የጀመሩት ፋጢምዮች እንደሆኑ ለማሳመን የሚጥሩ ወገኖች የገነቡትን ሀሳብ ያፋልሳል።

መዉሊድን በመጀመር መሊክ መዘፈር በዋነኛነት የሚጠቀሰዉ ምን አልባትም ከግለሰባዊ መታሰቢያ ወደህዝባዊና ኦፊሴላዊ መድረክ ስላሸጋገረዉ ይሆናል።

መዘፈር ነብዩን ﷺ ከፍ ከፍ የሚያደርግ የመዉሊድ ክብረ-በዐል ሲያዘጋጅ የወቅቱ ዑለሞች እጅግ ተደሰቱ። የዚያ ዘመን የሚልም አዉራ የነበሩት አልኢማም አቡል ኸጣብ እብን ደህየህ (540-633 ሂጅሪ)፡- ‹‹አልተንዊር ፊመዉሊዲ በሺሪነዚር›› የተባለ ኪታብ ጻፉለት።[104]የታሪክ ድርሳናትን ስናይ ስለእብን ደህየህ ከዑለሞች የተሰጡ አስደናቂ ምስክርነቶችን እናገኛለን። አልዘሀቢ፤-‹‹ታሳቅ የሀዲስ ሲቅና በሴሎች መስኮችም የበቁ ዐሊም››[105]ሲሏቸዉ፣እብን ኸልካን፡- ‹‹በነብዩ ﷺ ሀዲስና ከርሱ ጋር በተያያዙ መስኮች ሁሉ ጥልቅ ዕዉቀት የነበራቸዉ››[106] በማለት መስክረዉላቸዋል። **ይህ ምስክርነት መዉሊድ ጽድቅ የተቸረዉ በሸሪዐ እዉቀት በተካኑ ዐሊሞች እና ኢማሞች እንጅ በጃሂሎች ወይም በኹራፍዮች እንዳልሆነ ያረጋግጣል።**

በሀገራችን

በሀገራችን እስልምናን ከዘመን ዘመን በማሸጋገር የአንበሳ ድርሻ ያላቸዉ የሱፊ መሻኢኾች እንደመሆናቸዉና እነርሱ ደግሞ ከነብዩና ከልደታቸዉ ጋር የተለየ ትስስር ስላላቸዉ መዉሊድ ምናልባትም የነሸኽ አባድርንና የሌሎችን ሊቃዉንት የህልዉና ዘመን ይጋራ ይሆናል። በተለይም ጀላሉዲን አልሱዩጢና እብን ነጀር አልሀይተሚ የተባሉት ዑለሞች በኛ

[104] ሲየር አዕላመኑበላእ፣22/336፣ሁስነልመቅሰድ ፊዐመሲል መዉሊድ፣ወፈያቱል አዕያን እና ሌሎችም የታሪክ ድርሳናት ዘክረዉታል።
[105]ሲየር አዕላመኑበላእ-የእብን ደህያህ ታሪክ ዝርዝር ይመልከቱ፤
[106]ታ□ኽ እብን ኸልካን

ሀገር ሊቃውንት ዘንድ ካላቸዉ ደረጃና ተቀባይነት አኳያም የሁለቱ ሊቃውንት ፈትዋ ከሀገራችን ዐሊሞች እጅ መድረሱ ይጠበቃል። ሆኖም በሀገራችን፣በተለይም በሰሜኑ ክልል በተናጠል ይከበር የነበረዉን የመዉሊድ መታሰቢያ ወደተደራጀ ሥርዓት የለወጡት እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር እስከ 1798 ዓ.ል የቆዩትና ጀማንጉስ ወይም ሙጃሂዱ በመባል የሚታወቁት ታላቁ ዐሊም ሸኽ ሙሀመድ አልሻፊ መሆናቸዉ ይነገራል።[107] ሰበብ የሆናቸዉም ወደመካ ተጉዘዉ የዚያን ጊዜዉን የሀረም ሙፍቲ ለጅሀድ ፈቃድና የሎጂስቲክ እርዳታ መጠየቃቸዉ ነበር። ሙፍቲዉ እንደ ኢትዮጵያ ባለች ሀገር ከጅሀድ ይልቅ ህዝቡን ሰብስቦ ማስተማር የበለጠ ዉጤታማ እንደሚያደርግ ጠቆሚቸዉ። ሙጃሂዶ ለሦስት ዓመታት ያህል እዚያዉ ሀረም ዉስጥ ከነበሩ ሊቃዉንት ዒልም ሲገበዩ ከቆዩ በኋላ ወደ ሀበሻ በመመለስ ህዝቡን የሚሰበስቡበት መንገድ አዉጠነጠኑ። የነብዩን ﷺ የልደት ቀን ለመጠቀምም ወሰኑ። እናም መዉሊድ ዐሊሞችን ከተራዉ ህዝብ የሚያገናኝና የዲን ፍቅርን በሺዎች ልቦና ዉስጥ የሚያቀጣጥል መድረክ ሆኖ በሀበሻ ታወጀ። ከዚያ በኋላ ላደረጓቸዉ የጅሀድ ፍልሚያዎች መዉሊድን እንደ ግብአት ሳይጠቀሙበት አልቀረም። ይህ የሆነዉ በ18ኛዉ ክ/ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ ዉስጥ ነዉ።[108]

ከዚያ በኋላ የተማሪያቸዉ ተማሪ ጀማሉዲን አልዐኒ ቀጠሉበት። የዳና ከዋክብት ዐሊሞች ይበልጥ አደራጁት። ከዚያ ጊዜ ወዲህ በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች በተደራጀና ሰፊ ህዝብ በሚያሳትፍ ሁኔታ መከበር ጀመረ። ብሄራዊ በዓል ይሆን ዘንድ ተግተዉ የታገሉት ሀጅ ሙሀመድ ሳኒ ሀቢብ (እስከ 1981 ዓ.ል) ጥረታቸዉ በደርግ ዘመነ መንግስት ፍሬ ያዘላቸዉ።[109]

---

[107] ሀጅ ሙሀመድ ወሴ፣ኢቃዙ ሂመሚል አግቢያእ፣ቅጽ 2፣ያልታተመ

[108] ያስፈዉ ምንጭ

[109] Informants,shekh abdela,shekh siraj

ሀሳባችንን ስናጠቃልለዉ መዉሊድ በኦፊሴላዊና ህዝባዊ ደረጃ በ6ኛዉ ክ/ዘመን መጠናቀቂያ ላይ ተጀምሯል። ለምን እስከዚህ ዘመን ድረስ ዘገየ? ቁርአናዊና ሀዲሳዊ መነሻዎቹስ ምን ምን ናቸዉ? የሚሉ ጥያቄዎች በቀጣዩቹ ርእሶች ይዳሰሳሉ።

ለምን እስከዚህ ጊዜ ዘገየ?

መውሊድ በነብዩ ﷺ ሀዲሶችና ድርጊቶች ይሁንታ እንዳገኘ የሚያመለክቱ ሁኔታዎች ከመኖራቸዉ ጋርና በግለሰብ ደረጃ በዑለሞች ይከበር እንደነበር የሚያመለክቱ መረጃዎች ከመኖራቸዉ ጋር በመንግስት ደረጃ በአዋጅ፣ በህዝባዊነትና በኡፊሴል ለመታሰብ ለምን ይህን ያህል ዘመን ዘገየ? ለዚህ ጥያቄ መልስ ለማግኘት ሳብሰለስል ፕሮፌሰር ዐሊ ጁንዲ የተባሉ ምሁር በጉዳዩ ዙሪያ የጻፉትን አንድ መጣጥፍ[110]የመዲናዉ የሀዲስ ሊቅ ዶ/ር እብነል ዐለዊ ‹አልኢዕላም› ከተሰኘዉ መጽሀፋቸዉ ዉስጥ በረዥሙ ጠቅሰዉት አገኘሁ።[111] ቀጥሎ ላሰፈርኩት ሀሳብ ይህ መጣጥፍ ጥሩ ግብአት ሆኖኛል።

በነብዩ ﷺ ዘመን

ነብዩ ﷺ የልደት ቀናቸዉን በየሳምንቱ በጾም በነፍስ ወከፍ ከማሰብና ታላላቅ ክስተቶች ለተፈጸሙባቸዉ ቀናት በየሳምንቱና በየዓመቱ አላህን በዒባዳ ማመስገንን ከማስተማር ባለፈ የራሳቸዉን የልደትና የስኬት ቀናት በኡፊሴል ያስብ ዘንድ ህዝበ ሙስሊሙን ያላዘዙት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ሳቢያ ሊሆን ይችላል፡-

1. የተለየ ፈቃድ የማያስፈልገዉ፣ከአጠቃላይ የእስልምና መርህ ዉስጥ የሚካተት፣ኡለሞች፡ ***‹መንጢቀል ዐፍዉ›*** ወይም ***‹መንጢቀል ፈራግ›***[112]ከሚሉት የሸሪዐና የህይወት መስክ ዉስጥ የሚገባ ነገር ከሆነ በተለየ ሁኔታ ላያዙት ወይም ላይተገብሩት ይችላሉ። ይህን በተመለከተ ነብዩ ﷺ ሲናገሩ፡-

[110]መጣጥፉ ‹ኑፍሀቱል አዝሀር ፊመዉሱዲል ሙኽታር› ይሰኛል፤
[111]አል-ኢዕላም...ገጽ 244-257
[112]አል-ቀረዳዊ፣ ዐዋሚሱ ሰዐህ ወልሙሩናህ ፊሸሪዐቲል ኢስላምየህ፣ ገጽ 15

‹‹አላህ ወሰኖችን አበጅቷልና አትለፏቸዉ፤ ግዴታ ያደረጋቸዉ ነገሮች አሉና አታጥፏቸዉ (ተግብሯቸዉ)፤የከለከላቸዉ ነገሮችም አሉና አትዳፈሯቸዉ፤ረስቶ ሳይሆን ለናንተ በማዘን በዝምታ ያለፋቸዉ ነገሮችም አሉና ስለነርሱ አትፈላፈሉ፡፡ ››[113]

‹አትፈላፈሉ› የሚለዉ ትዕዛዝ ሶሀቦችን ብቻ የሚመለከት ነዉ፡፡[114] ምክንያቱም ያንጊዜ ወህይ ይወርድ ስለነበር ጸጉር ስንጠቃዉ ጠበቅ ያሉ ህግጋት እንዳያስከትል ያሰጋልና፡፡ ለዚህም ነዉ ነብዩ ﷺ ‹የተዉኳችሁን ነገር ተዉኝ›› ያሉት፡፡[115] ቁርአንም እንዲህ ሲል አሏቸዋል፡-

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا لَا تَسْأَلُوا عَنْ أَشْيَاءَ إِن تُبْدَ لَكُمْ تَسُؤْكُمْ وَإِن تَسْأَلُوا عَنْهَا حِينَ يُنَزَّلُ الْقُرْآنُ تُبْدَ لَكُمْ عَفَا اللَّهُ عَنْهَا وَاللَّهُ غَفُورٌ حَلِيمٌ

‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ለእናንተ ቢገለጹ ከሚያስከፏችሁ ነገሮች አትጠይቁ፡፡ ቁርኣንም በሚወርድበት ጊዜ ከእርሷ ብትጠይቁ ለናንተ ትገለጻለች፤ ከእርሷ አላህ ይቅርታ አደረገ፡፡ አላህም መሓሪ ታጋሽ ነው፡፡››[116]

በሌላ ሀዲሳቸዉም እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹አላህ በመጽሀፉ ዉስጥ ሀላል ያለዉ ሁሉ ሀላል፣ሀራም ያለዉ ሁሉ ደግሞ ሀራም ሲሆን፣በዝምታ ያለፈዉ ነገር የተፈቀደ (ዐፍዉ) ነዉ፡፡ ከአላህ ፈቃዱን ተቀበሉ፡፡ ምክንያቱም ምንንም ነገር አይረሳምና፡፡›› ይህን ካሉ በኋላ ‹‹ጌታህ የሚረሳ አይደለም››[117] የሚለዉን የቁርአን መልዕክት አነበቡ፡፡[118]

---

[113]ዳረል ቁጥኒ ዘግበዉታል፤አልነዉዊናሰምዐኒ ሀሰን ብለዉታል፤
[114]በዋሚሉ ሰዐህ ወልሙሩናህ ፌሸሪዐቲል ኢስላምየህ፣ ገጽ 15
[115]ቡኻሪ፣ሙስሊምና አህመድ
[116]አልማኢዳህ፣101
[117]መርየም 64
[118]በዛርና ሀኪም ዘግበዉታል፤ ሰነዱ ሶሂህ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡ አልዘሀቢም በዚህ ብይን ተስማምተዋል፡፡

ነብዩ ﷺ ያልሰሩት ወይም ያልተናገሩት ነገር ሁሉ ሀራም የሚመስላቸዉን ወገኖች ስህተት እነዚህና መሰል ሀዲሶች በጉልህ ያሳያሉ።

በዝምታ የታለፉ ነገሮች ከሸሪዐዉ አምስት ብይኖች (አህካሙል ኸምሳ) ዉስጥ ያላቸዉን ቦታ ለመለየት ዑለሞች ***ቂያስ፣ኢስቲህሳን፣ኢስቲስላህ*** እና መሰል የምርምር ስልቶችን እሥራ ላይ ያዉላሉ። እንዳስፈላጊነቱ ወደፊት አያቸዉ ይሆናል።[119] አህካመል ኸምሳ የሚባሉት ዋጅብ፣ መስተሀብ፣መባህ፣ከራሀና ሀራም ናቸዉ።

ወደርእሳችን ጉዳዩን ስንመልሰዉ ነብዩ ﷺ መዉሊድን በህዝባዊ መድረክ ያላከበሩት ምን አልባትም ከላይ ከተሰጠዉ ማብራሪያ አኳያ ሊሆን ይችላል።

2. ነብዩ ﷺ የተፈቀዱ የህይወት አጀንዳዎችንም ስላልፈለጉ ይተዋሉ። መተዋቸዉ ግን ሀራምነትን አያመለክትም። ለምሳሌ አንድ ጊዜ ምግብ ቀረበላቸዉ። ሊበሉ እጃቸዉን ከሰደዱ በኋላ የድብ ስጋ መሆኑ ሲነገራቸዉ ሰበሰቡት። ‹‹ሀራም ነዉን?›› ተብለዉ ሲጠየቁ ‹‹ ሀራም አይደለም። ግና ከኖርኩበት ሀገር ስለሌለ ነዉ።›› በማለት መለሱ።[120]

መዉሊድ ዓላማዉ ነብዩን ﷺ ማስታወስ በመሆኑና ያንየ እርሳቸዉ በህይት በመኖራቸዉ ሌላ ማስታወሻ ስለማያስፈልግ ትተዉት ሊሆን ይችላል።

3. የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ደግና ተወዳጅ ነገሮችን በኡመታቸዉ ላይ ግዴታ እንዳይሆኑ በመስጋት ይተዋቸዋል። ቢላል ዉዱኡ ባደረገ ቁጥር ሁለት ረከዐ እንደሚሰግድ በነገራቸዉ ጊዜ፡- ‹‹ እኔምኮ በተጸዳዳሁ ቁጥር

[119]ስተጨማሪ ግንዛቤ ‹ዐዋሚሱሰዐህ ወልሙሩናህ..› የተሰኘዉን የአልቀረዳዊ መጽሀፍ ያንብቡ።
[120]ቡኻሪና ሙስሊም

ዉዱእ ባደርግና ብሰግድ እወድ ነበር›› ሲሉ ምኞታቸዉን ገልጸዋል።[121] ይህም ሆኖ ግን በኡመታቸዉ ላይ ግዴታ እንዳይደነገግ በመስጋት ፍላጎታቸዉን ከመተግበር ታቅበዋል። ለምሳሌ አንድ ጊዜ ሽንት ሸኑ። ዑመር በእቃ ዉሀ ይዘዉ ጠበቋቸዉ። ‹ይህ ዉሀ ለምንድን ነዉ?›› ሲሉ ጠየቁ። ‹‹ዉዱእ ያደርጉበት ዘንድ ነዉ›› አሉአቸዉ። ‹‹በተጸዳዳሁ ቁጥር ዉዱእ አደርግ ዘንድ አልታዘዝኩም። ባደርግ ኖሮ ሱንና ሆኖ ይደነገግ ነበር›› አሉ።[122]

ዐኢሻ ይህን የነብዩ ﷺ ባህሪ ሲገልጹ፦

‹‹ነብዩ ﷺ በኡመታቸዉ ላይ ግዴታ እንዳይደነገግ በመስጋት ሲያደርጓቸዉ የሚመኟቸዉንና የሚወዷቸዉን ነገሮች ይተዉ ነበር። የዱሀ ሶላት ሰግደዉ አያዉቁም። እኔ ግን እሰግዳታለሁ።››ብለዋል።[123]

ስለዚህ መዉሊድን በህዝባዊ ደረጃ ያላከበሩት ምንአልባትም ልክ እንደዒድና እንደዐረፋ ሱንና ሆኖ እናዳይደነገግና በህዝባቸዉ ላይ ጫና እንዳይፈጠር ሰግተዉ ሊሆን ይችላል።

4. የህዝባቸዉን ተጨባጭ ሁኔታ በማጤን መልካም ነገሮችን ከመተግበር የሚቆጠቡባቸዉ አጋጣሚዎች አሉ። ለዐኢሻ እንዲህ ብለዋቸዋል፦

‹‹ ወገኖችሽ ለክህደት ዘመን ቅርብ ባይሆኑ ኖሮ ካዕባን አፍርሸ በኢብራሂም መሠረት ላይ አንጸዉ ነበር። ቁረይሾች ያለቦታዉ ገንብተዉታል።››[124]

ነብዩ ﷺ ይህን ምኞታቸዉን ሳያሳኩ ሞቱ። ካዕባ ፈርሶ በኢብራሂም መሠረት ላይ የተገነባዉ እርሳቸዉ ካለፉ ከሁለት አስርት ዓመታት በኋላ

[121]ቡኻሪ
[122]አቡዳዉድ ቲርሚዚና አብን ማጀህ
[123]ሙስሊም
[124]ቡኻሪና ሙስሊም

ነው፡፡ መውሊድን በህዝባዊ ደረጃ ከማክበር ያቀባቸዉ ምን አልባትም እንዲህ ዓይነት ስጋት ሊሆን ይችላል፡፡

5. ነብዩ ﷺ የትህትናና የመተናነስ ተምሳሌት ከመሆናቸዉ አኳያ እንደ ምድራዊ ንጉሳን የልደት ቀናቸዉን ህዝባዊ በዓል በማድረግ ሊኮፈሱ አይችሉም፡፡ በተጨማሪም ከርሳቸዉ በኋላ የሚመጡ ሙስሊም መሪዎች ‹ልደቴን አክብሩ› በማለት ህዝብ እንዳያስቸግሩ መንገዱን ለመዝጋት (ሰደዘሪዐህ) አልመዉ ትተዉት ሊሆንም ይችላል፡፡

6. ትዝ ሳይላቸዉ ቀርቶ የሚተዉት ነገርም አለ፡፡ ለምሳሌ ዝጥባ የሚያደርጉት የተምር ግንድ ተደግፈዉ ነበር፡፡ ሚንበር የመስራት ጉዳይ አልታወሳቸዉም፡፡ ሶሀቦች ናቸዉ ያስታወሱአቸዉና የሠሩላቸዉ፡፡

7. ረስተዉት የሚተዉት ነገርም ነበር፡፡ ህዝባዊና ማህበራዊ አጀንዳን ቀርቶ ዒባዳ ዉስጥ እንኳ ሊረሱ ይችላሉ፡፡ አንድ ጊዜ የሶላት ረከዐ ረሱ፡ ፡ ‹‹ሶላት አጭር ተደረገችን›› ተብለዉ ተጠየቁ፡፡ አልተደረገችም አሉ፡፡ ረከዐ እንደረሱ ተነገራቸዉና ሞሉ፡፡ የመርሳት ሱጁድም አደረጉ፡፡[125]

8. አላህ የሰዉን ልጅ እንዲህ ሲል አሟል፡-

وَافْعَلُوا الْخَيْرَ لَعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ

‹‹በጎንምነገርሥሩ፣ልትድኑይህችጀልሳችኋልና፡፡››[126]

በጎ ሥራ ተዘርዝሮም ሆነ ተተግብሮ የሚያልቅ አይደለም፡፡ ለዱንያ ወይም ለአኼራ የሚጠቅሙ፣ለሰዉ ልጆች ቁሳዊ ወይም መንፈሳዊ ብልጽግና የሚፈይዱ፣ እስከ ዕለተ ቂያማ ድረስ ሊኖሩ የሚችሉ የትየለሌ ነገሮችን ያካትታል፡፡ አንድ ነገር ‹በጎ ሥራ› ከሚባለዉ ሰፊ መስክ ዉስጥ የሚካተት ከሆነ ነብዩ ﷺ ለይተዉ ላይጠቅሱት ይችላሉ፡፡

[125]ቡኻሪና ሙስሊም
[126] አልሀጅ 77

እነዚህን ለናሙና አነሳን እንጅ ነብዩﷺ ነገሮችን ሳይሰሩ የሚተዉባቸዉን ብዙ ምክንያቶች መዘርዘር ይቻላል። ስለሆነም አንድን ነገር ‹ነብዩ አልሠሩትም ወይም አልተናገሩትም›› ብሎ ‹‹ሀራም›› ወይም ‹‹ቢድዐ›› በማለት መንቀፍ ችኩልነትና አላዋቂነት ነዉ። የነብዩﷺ እንደዚህ ከሆነ ‹ሠለፎች አልተናገሩትም ወይም አልሠሩትም›› የሚለዉ ምክንያትማ በዒልም ሚዛን እዚህ ግባ የሚባል አይደለም።

መወሊድ በነብዩﷺ ዘመን በኦፊሴል ላለመተግበሩ ከላይ ከተዘረዘሩ ምክንያቶች አንዱ ሰበብ ሊሆን ይችላል ነዉ የወይይታችን መቋጠሪያ ዉል።

በኸሊፋዎች ዘመን

በአራቱ ኸሊፋዎችና በሶሀቦች ዘመንስ ለምን ኦፊሴላዊ አልሆነም? የሚከተሉትን ሰበቦች መጥቀስ ይቻላል፡

1. የመወሊድ ኦፊሴላዊ መታሰቢያ ዓላማ ነብዩንﷺ ማስታወስ ነዉ። የአራቱም ኸሊፋዎችና የሶሀቦች ዘመን በርሳቸዉ ትዉስታዎች የተሞላ ስለነበር ሌላ ማስታዎሻ አያስፈልገዉም። የኋለኛዉ ዘመን ሙስሊሞች ግን ከዚህ ትዉስታ ስለሚርቁ የነብዩንﷺ ገድልና ባህሪ የሚያስተዋዉቁ አጋጣሚዎችን በብዛት ይፈልጉ ነበር። ሰፅድ እብን አቢወቃስ ስለዚያ ዘመን የነብዩﷺ ትዉስታ ህያዉነት ሲናገሩ፡-‹‹ስልጆቻችን ቁርአንን የምናስተምረዉን ያህል ስለነብዩ ዘመቻዎች እናስተምር ነበር።›› ብለዋል። እያንዳንዱ ህጻን ስለበድር፣ ዑሑድ፣አህዛብ ፈትህ ወዘተ ዘመቻዎች፣ በነዚህ ዘመቻዎች ምን እንደተከናወነ፣ነብዩና ሶሀቦች ምን እንዳደረጉ፣ ምንስ እንደተባባሉ...በዝርዝር ይማር ነበር። ይህና ሌሎች ትምህርቶች ነብዩ ከመሀከላቸዉ እንዳሉ ያህል እንዲሰማቸዉ ያደርጋል። የመወሊድ

ዓላማ ተሳካ ማለት ነዉ። ለዕዉቁ ዐሊም ለዶ/ር ዩሱፍ አልቀረዳዊ መወሊድ በሶሀቦች ዘመን ላለመጀመሩ ይህ ዋነኛዉ ምክንያት ነዉ።[127]

ይህ ምክንያት ብቻዉን በቂ ቢሆንም አጀንዳዉን ይበልጥ ለማጽናት ሌሎች ሰበቦችን ላክል።

2. ከላይ ለነብዩ ﷺ የተጠቀሱ ሰበቦች በከፊል እዚህም ላይ ይሠራሉ። ኸሊፋዎች ጭራሹኑ በሀሳባቸዉ ሳይመጣ ቀርቶ ወይም ረስተዉ ኦፊሴላዊ መወሊድ ላያደርጉ ይችላሉ። ለምሳሌ ቁርአንን በአንድ መጠረዝን አቡበክር አስበዉት አያዉቁም ነበር። ዑመር አስታወሷቸዉ። ዑመርም እንዲያስታዉሱት የገፋፋቸዉ የማማ በተባለዉ ጦርነት በርካታ የቁርአን አዋቂዎች መገደላቸዉ ነበር። የየማማ ጦርነት ባይደረግ ወይም የቁርአን አዋቂዎች በብዛት የመገደላቸዉ አጋጣሚ ባይፈጠር ኖሮ ዑመርም ላያስታዉሱት ይችሉ ነበር። አቡበክር ከብዙ ማንገራገር በኋላ የዑመርን ሀሳብ ተቀብለዉ ተገበሩ።

የተራዊህ ሶላት እንዲህ እንደአሁኑ ቁጥሩ ተወስኖ በአንድ ኢማም መሰገድ የተጀመረዉ በዑመር ዘመን ነዉ። ህዝቡ ተበታትኖ በኢማምም ያለኢማምም የተለያዩ ረከዐዎችን አዘበራርቆ ሲሰግድ ዑመር ባስተዋሉ ጊዜ በአንድ ኢማም ሥር 20 ረከዐ ቢሰገድ መልካም እንደሆነ ታያቸዉና ተገበሩት። የአሁኑን የተራዊህ ሶላት ሥርዓት ነብዩም፣ አቡበክርም አያዉቁትም። ዑመር በወቅቱ ያ ሀሳብ ብልጭ ባይልባቸዉ ኖሮ ተራዊህ በአሁኑ ይዘቱና ሥርዓቱ ህልዉና አይኖረዉም ነበር።

በአሁኑ ሰዐት ለጁሙዐ ሶላት ሁለት አዛን ይደረጋል። በነብዩ ﷺ፣ በአቡበክርና በዑመር ዘመን አልነበረም። ዑስማን ናቸዉ የጀመሩት።[128] ሀሳቡ የመጣላቸዉ ህዝበ ሙስሊሙ ቁጥሩ እየበዛ በመሄዱ ለጁሙዐ ሶላት ተጨማሪ የጥሪ ማስታወሻ እንደሚያስፈልግ ስለደረሱበት ነበር።

[127] በድረገጻቸዉ በ19-3-2008 ከሰጡት ፈትዋ የተወሰደ
[128] ቡኻሪ

ይህ ሀሳብ ብልጭ ባይልባቸዉ ኖሮ የጁሙዐ አዛን አንድ ብቻ ሆኖ ይቀር ነበር።

ተመሳሳይ የቁርአን ቅጅዎችን አዘጋጅቶ በመበተን አንድ እና ወጥ የቁርአን ቅጅ በዓለም ላይ እንዲኖር የማድረጉን ሥራ ያከናወኑት ነብዩ ﷺ፣አቡበክር ወይም ዑመር ሳይሆኑ ዑስማን ናቸዉ።[129] ኹዘይፋ እብንል የማን ከአዘርባጃን ጦርነት ሲመለስ እቦታዉ ያየዉ የአቀራር ግድፈት አስደንግጦት አንድ ነገር ይደረግ ዘንድ ዑስማንን ተማጸነ። ዑስማን በጉዳዩ አመኑበትና ኦፊሴላዊ የቁርአን ቅጅ አዘጋጅተዉ በመበተን ቀሪዎቹን ቅጅዎች አስወገዱ።[130] ኹዘይፋ ወደአዘርቤጃን ባይዘምት ወይም የሚያስደነግጥ የአቀራር ልዩነት የሚሰማበት አጋጣሚ ባይፈጠር፣ወይም ሰምቶ ባይደነግጥ ወዘተ ተመሳሳይ የቁርአን ቅጅ የማደራጀቱ ሀሳብ ለዑስማን ላይከሰት ይችል ነበር።

በነብዩም ﷺ ሆነ በኸሊፋዎች ዘመን የነበረዉ የቁርአን ቅጅ ነጥብ አልባ ነበር። ማለትም ‹ባ› እና ‹ታ›፣‹ፋ› እና ‹ቃፍ›፣‹ዳል› እና ‹ዛል› ወዘተ አንዱን ከሌላኛዉ የሚለየዉ ነጥብ ስለሌለ ቅርጻቸዉ ተመሳሳይ ነዉ። የሚለዩት በድምጽ ብቻ ነበር። ይህ ሁኔታ የአነባበብና የትርጉም ልዩነት በኋለኛዉ ዘመን እየፈጠረ ሲመጣ ዚያድ እብን ሰሚያህ በተባለ የበስራ ገዥ አመላካችነት አቡል አስወድ ደኡሊ የተባሉ ዐሊም ፊደላትን በሀረካ የመለየት ሥራ አከናወኑ። በሀጃጀጅ እብን ዩሱፍ ጊዜ ደግሞ በነጥብ የመለየቱ ሥራ ተከናወነ።[131]ይህ ባይሆን ኖሮ ‹ኸረጀ› የሚለዉን ቃል ‹ኸ› ፊደል ነጥብ ስለሌላትና ሀረካ ስላልነበር ‹ሀረጀ› ብለን ልናነበዉ እንችል ነበር። የመጀመሪያዉ ‹ወጣ› ማለት ሲሆን ሁለተኛዉ ‹ችግር›

[129] በደሀቂ
[130]ቡኻሪ
[131] ሙሀመድ ጣሂር አልኩርዲ፣ታሪኽል ቁርአኒል ከሪም፣መጥበዐተል ፈትህ፣ጅዳ፣ የመጀመሪያ ፅትም 1946፣ገጽ 181

ማለት ነዉ። ይህ በቁርአን መልዕክት ላይ ከፍተኛ መመሰቃቀል ይፈጥር ነበር። አራቱም ኸሊፋዎች ይህ ትዝ አላላቸዉም።

ስለዚህ ለመዉሊድ በኸሊፋዎች በኦፊሴል አለመከበር ምን አልባትም አለማስታወስ ወይም እንዲያስታዉሱት የሚያደርግ አጋጣሚ አለመፈጠር አንዱ ምክንያት ሊሆን ይችላል።

3. የኸሊፋዎች ዘመን የዉጭ ጠላትንና የዉስጥ አዋኪዎችን በመፋለም የተሞላ ነዉ። አቡበክር ስልጣን እንደያዙ አመጽ (ሪዳ) ገጠማቸዉ። እርሱን ሲፋለሙና ማህበረሰባቸዉን ለማደራጀት ደፋ ቀና ሲሉ ይህችን ዓለም በሞት ተሰናበቱ። የዑመር ዘመን ከዉስጥ ጠላቶች በተንዳኘ የዉጭ ሀይሎችን አደብ የማስያዝ ትንቅንቅ ያየለበት ነበር። የዚያ ዘመን አጣዳፊ ተግባር እስልምና ግዛቱ ሰፍቶና ጠላቶቹ ሁሉ አደብ ይዘዉ ህልዉናዉ እንዲረጋገጥ ማስቻል ነዉ። ዑመር ለዚህ ተግባር እንደተጉ ፋታ ሳያገኙ ተገደሉ። የዑስማንና የዐሊ ዘመን በዉስጥ አለመረጋጋቶችና የእርስ በርስ ግጥቶች የተሞሉ ናቸዉ። ግጭቶቹ በመጨረሻ የሁለቱን ኸሊፋዎች የህይወት ዋጋ አስከፍለዋል።

በእንዲህ ዓይነቱ ድባብ ዉስጥ ኦፊሴላዊ የመዉሊድ በዓል የማዘጋጀቱ ሀሳብ ባይታወስ አይገርምም።

4. በነብዩ ﷺ ዘመን የነበሩ ሁኔታዎች ባሉበት እንዲቀጥሉ ማድረግ የአራቱም ኸሊፋዎች ፍላጎት ነበር። በመሆኑም ደግ ነገሮችን እንኳ ካልተገደዱ በስተቀር አይፈጽሞአቸዉም። አቡበክር ቁርአንን በአንድ ለመጠረዝ በተጠየቁ ጊዜ የሰጡት ምላሽ ይህንኑ ያሳያል።እንዲህ ነበር ያሉት፡-

أفعل ما لم يفعل رسول الله صلى الله عليه وسلم

‹‹ነብዩ ያልሠሩትን ልሠራ ነዉን?››[132]

ይህ ማንገራገርና ተቃዉሞ ነገሩ መጥፎ ስለሆነ ሳይሆን ሁኔታዎች ነብዩ ﷺ ሲያልፉ በነበሩበት መልኩ እንዲቆዩ ከመፈለግ ብርቱ ፍላጎት የተነሳ ነዉ፡፡ ከዚህ ዉጭ ሌላ ትርጉም ሊሠጠዉ አይችልም፡፡ይህ ማለት ግን ለዉጡ ክፉ ነዉ ማለት አይደለም፡፡ አስፈላጊና ግዴታም ነበር፡፡ ዘይድ እብን ሳቢት የተበታተኑ የቁርአን ጽሁፎችን የሚያሰባስብና በአንድ የሚጠርዝ ኮሚቴ ያቋቁም ዘንድ በአቡበክር በታዘዘ ጊዜ፡- ‹‹ይህን ተግባር እንዳከናዉን ከሚያዙኝ ተራራ እንድገፋ ቢያዙኝ ይሻለኝ ነበር››[133] ያሉት ከዚህ ስሜት በመነሳት ነበር፡፡ ጥያቄዉን ላቀረቡላቸዉ ዑመር እንዲህ ሲሉ ተቃወሙ፡-

كيف تفعل شيئا لم يفعله رسول الله صلى الله عليه وسلم

‹‹የአላህ መልዕክተኛ ያላደረጉትን እንዴት አንተ ታደርጋለህ?››[134]

ዑመር በብዙ ጥረት አቡበክርንና ዘይድን አሳመኑ፡፡**ሽሊፋዎች የመዉሊድን ህዝባዊ መታሰቢያ የተዉት በዚህ ስሜታቸዉ ሰበብ ሊሆንም ይችላል፡፡**

በኡመያዉያን ዘመን

ዑስማን በአማጺዎች ተገደሉ፡፡ ዐሊ ስልጣን ላይ ወጡ፡፡ ሙዐወያና ረዳቶቻቸዉ በዐሊ ላይ አመጹ፡፡ ችግሩ ሳይፈታ ዐሊ ተገደሉ፡፡ ሙዐወያም ስልጣን ያዙ፡፡ የኡመያዉያን በዘር የሚተላለፍ ሥርዎ-መንግስት ተመሠረተ፡፡ እስከ 132 ሂጅሪያ ድረስም ቆየ፡፡ የዚህ ቤተሰብ ዋነኛ የፖለቲካ ተቀናቃኝ የአሊ የልጅ ልጆች የሆኑት የነብዩ ﷺ ቤተሰቦች

[132] ቡኻሪ፣ኪታቡ ተፍሲር
[133]ቡኻሪ፣ኪታቡ ተፍሲር
[134]ያስፈዉ ምንጭ

ነበሩ። እነርሱን የማሳደዱንና የማጣጣሉን ተግባር ኡመያዉያን የህልዉናቸዉ መገለጫ አደረጉት።

የዚህ ዘባባል ማሳያዎች ብዙ ናቸዉ። ዐሊ በጁመዐ ኹጥባ ለብዙ አስርት ዓመታት እንዲረገሙ ሲደረግ ኖሯል። ሀሰን በግፊት ኸሊፋነት ስልጣናቸዉን ለመዐወያ አስረክበዋል። ሁሴን ከርበላእ ላይ ተገድለዋል...። ከአልጦበሪ፣ከእብንከሲር፣ከሱዩጢ፣ ከእብን አሲርና ከሌሎች የታሪክ ድርሳናት የነብዩ ቤተሰቦችንና የዐሊ ዝርያዎችን ታሪክ ያነበበ የመሳደድ ህይወት ማሳለፋቸዉን በጉልህ ይገነዘባል። የነብዩﷺ ቤተሰብ ከህዝበ ሙስሊሙ ትዉስታ እንዲጠፋ ኡመያዉያን በቂ ጥረት አድርገዋል። የፖለቲካ ድባቡ ‹ናሲቢ› የሚባል እንቅስቃሴ ፈጥሮ የአህሉል በይትን ልዕልና በዲን ስም ለማንኳሰስ የተደረገዉ ጥረት ግን ጠባሳዉ እስከዛሬም ሊለቀን አልቻለም። ይህ ማለት ከሥርዓቱ አራማጆች መካከል ለአህሉል በይት ቀና አመለካከት የነበራቸዉ ግለሰቦች የሉም ማለት አይደለም። እንደ ዑመር እብን ዐብድል ዐዚዝ ያሉ የፍትህ ከዋክብት ብቅ ብለዉ ነበር። ግና እድሜ አልነበራቸዉም። ወዲያዉኑ በመርዝ ተገደሉ። ከዚህ የተነሳ ይመስላል እንደ አቡሀኒፋ ያሉ ታላላቅ ዐሊሞች ለኡመያዉያን በይዐ ሳይገቡና ለሥርዓቱ እዉቅና ሳይሰጡ እንደተቃወሙት የኖሩት።[135]

በእንዲህ ዓይነቱ የፖለቲካ ድባብ ዉስጥ ነብዩንﷺ የሚያስታዉስ ክብረባዕል ማዘጋጀት የሥርዓቱ ቀንደኛ ተቀናቃኝ ለሆነዉ ለዚህ ቤተሰብ ክብር እዉቅና መስጠት በመሆኑ የሚሞከር አልነበረም። ቅንነት ያላቸዉ መሪዎች ቢኖሩ እንኳ ከተበጀዉ የፖለቲካ መስመር የመዉጣት አቅም ላይኖራቸዉ፣ መዉሊድ ላይታወሳቸዉ ወይም አጣዳፊ አጀንዳቸዉ ላይሆን ይችላለ። እያንዳንዱ ሥርዓት የራሱ ትኩስ አጀንዳዎች (priorities) ስለሚኖሩት።

[135]አቡዛህራ፣አቡሀኒፋ፣ገጽ 39

በዐባሳዉያን ዘመን

በ133 ሂጅሪያ ኡመያዉያንን ተክቶ ሥርወ መንግስቱን የመሠረተዉ እና እስከ 656 የቆየዉ[136] የዐባሳዉያን ዳይናስቲም እንደአለመታደል ሆኖ በአህሉል በይት ላይ የተከተለዉ ፖሊሲ ከበፊተኞቹ ንጉሳን የባሰ ሆኖ ቀጠለ፡፡ በሁለቱ ዳይናስቲዎች ዘመን የነብዩﷺ የልጅ ልጅ ሁሴን ኢብን ዐሊ የደረሱባቸዉ ግፎች የዳይናስቲዎችን ባህሪና በነብዩﷺ ቤተሰቦች ላይ የተከተሉትን አሉታዊ ፖሊሴ ያሳያሉ፡፡ ሁሴን በሙዐወያ ልጅ በየዚድ የንግስና ዘመን በአሰቃቂ ሁኔታ ተገደሉ፡፡ በአባሳዊዉ ንጉስ በአልሙተወኪል ዐለላህ እብንል ሙዕተሲም እብን ረሺድ ደግሞ በ236 ሂጅሪ መቃብራቸዉ ተቆፈረ፣በዙሪያዉ የነበሩ ቤቶችም እንዲፈርሱ ተደረገ፡፡[137]

በኡመያዉያንና በዐባሳዉያን ዘመን ለአህሉል በይት አወንታዊ እይታ ያሳዩ ዐሊሞች ሁሉ በስርዓቱ አራማጆች ወይም እነርሱን በሚደግፉ ወገኖች ‹ሽዐ› ተሰኝተዉ ሲወገዙ ኖረዋል፡፡ በዚህ ረገድ ታላላቆቹ የፊቅህ ሊቆች ኢማም አቡሀኒፋና ኢማም አልሻፊዒ ለአብነት ይጠቀሳሉ፡፡ አቡሀኒፋ ለአህለል በይት ልዩ ፍቅር ነበራቸዉ፡፡ በዚያ ዘመን የአህሉልበይት አዉራ የነበሩት ዘይድ እብን ዐሊ በኡመያዉያን ገዥዎች ላይ ባመጹ ጊዜ አቡሀኒፋ በገንዘብም በሀሳብም ደግፈዋቸዋል፡፡[138] የዘይድን ዘመቻም ከነብዩﷺ የበድር ዘመቻ ጋር አመሳስለዉታል፡፡[139] ኢማም ዘይድ በ122 ሂጅሪያ፣ልጃቸዉ የህያ በ125 ሂጅሪያ፣የልጅ ልጃቸዉ ዐብደላህ በ130 ሂጅሪያ በኡመያዉያን በግፍ ሲገደሉ የአቡሀኒፋ ሀዘን ጥልቅ ነበር፡፡ ከዚህ የተነሳ ኡመያዉያን ገዥዎችን

---

[136]አነቃሲም ዐብደላህ ኢብራሂም፣አልመዉሱዐቱል ሙየሰረህ ፊታሪኺል ኢስላሚ፣ሙአሰሰተ ኢቅራ፣2013፣ቅጽ1 ገጽ 331

[137] ያስፈዉ ምንጭ ገጽ 287

[138]ያስፈዉ ምንጭ ፣ገጽ 37

[139]ያስፈዉ ምንጭ

ይጸየፉ ነበር፡፡ የዚያ ዘመን የኩፋ ገዥ ኢብን ሁበይራህ ዒልማቸውንና በህዝብ ዘንድ ያላቸውን ተቀባይነት በማየት ዋና ቃዲ ሊያደርጋቸዉ በጠየቀ ጊዜ አቡሀኒፋ አሻፈረኝ በማለታቸዉ ታስረዉ ከሞት አፋፍ ላይ እስኪደርሱ በተደጋጋሚ ተደብድበዋል፡፡ ከእስር እንደተለቀቁም ወደመካ ሸሽተዋል፡፡[140] ህይወታቸዉን ሙሉ ለኡመያዉያን ገዥዎች እዉቅና ሰጥተዉ ወይም ቃልኪዳን (በይዐ) ገብተዉ አያዉቁም፡፡[141]

ዑመያዉያን ወድቀዉ በዐባሳዉያን ሲተኩ አቡሀኒፋ መጀመሪያ ድጋፍ ችረዋቸዋል፡፡በይዐም ገብተዉላቸዋል፡፡[142] ምክንያቱም ዐባሳዉያን የኡለሞችንና የህዝቡን ድጋፍ ለማግኘት ሲሉ የነብዩ ﷺ ቤተሰቦች ወዳጅ እንደሆኑ አድርገዉ ነበር ህዝቡን የቀሰቀሱትና ያሳመኑት፡፡ እናም በአህሉል በይት ላይ የሚፈጸመዉ ግፍ ያበቃበት ዘመን እንደመጣ አቡሀኒፋ ተስፋ አድርገዉ ኖሯል፡፡[143] እያደር ዐባሳዉያን በአህሉል በይት ላይ የሚከተሉት ፖሊሲ ዉሉን እየሳተና እየከፋ ሲሄድ አቡ ሀኒፋም ስለነርሱ ያላቸዉ እይታ ከድጋፍ ወደ ጠንካራ ተቃዉሞ ተቀየረ፡፡ በዚህ የተነሳ በዐባሳዊዉ ገዥ በአባ ጃዕፈር ታሰሩ፡፡ ግፍም ተፈጸመባቸዉ፡፡[144]

ኢማም አልሻፊዒም እንደዚሁ በሺዐነት ተጠርጥረዉ በዐባሳዊዉ ገዥ በአልረሺድ (እስከ194 ሂጅሪ)[145] እንግልት ደርሶባቸዋል፡፡ በዚሁ ጦስ ተከሰዉ ከቀረቡ 10 ሰዎች መካከል 9ኙ ተገድለዋል፡፡ በህይወት የተረፉት እርሳቸዉ ብቻ ናቸዉ፡፡ ታዝናላቸዉ ሳይሆን በዘዴ፡፡ ከየመን እስከባግዳድ በሰንሰለት ታስረዉ ተወስደዋል፡፡[146]

---

[140] ያስፈዉ ምንጭ ገጽ 39
[141] ያስፈዉ ምንጭ
[142] ያስፈዉ ምንጭ ገጽ 41
[143] ያስፈዉ ምንጭ ገጽ 43
[144] ያስፈዉ ምንጭ ገጽ 47
[145] ያስፈዉ ምንጭ
[146] አቡዘህራ፣ኢማመሻፊዒ፣ገጽ 53

በጥቅሉ ዐባሳዉያን ለአህሉል በይት የነበራቸዉ ጥላቻና እነርሱን ዋነኛ የፖለቲካ ተቀናቃኞቻቸዉ አድርገዉ መዉሰዳቸዉ የአህሉል በይትን ፍቅር በህዝቡ ልቦና ዉስጥ የሚያቀጣጥለዉን የመዉሊድ ኦፊሴላዊ መታሰቢያ ፈጽሞ እንዳያስቡት በቂ መግፍኤ ነበር፡፡

ማጠቃለያ

ከላይ ባጭሩ የተመለከትነዉ ታሪካችን እስከ ኋለኛዉ ዘመን ድረስ መዉሊድ በህዝባዊ ባዕልነቱ ይከበር ዘንድ እንዳይታሰብ እንቅፋት ሆነዉ የቆዩ ሰበቦችን በመጠኑ ያሳያል ተብሎ ይታሰባል፡፡

በግብጽ የነገሱትና የፋጢመቱ ዛህራ ዝርያዎች ነን የሚሉት ፋጢምዮች መዉሊድን እንደጀመሩት የሚገልጸዉን ትርክት በፖለቲካ ስሌት ስናሰላዉ የሚጠበቅ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ድርጊታቸዉን በደጉ እንተርጉምላቸዉ ካልን ለዘመናት ተረስቶ የኖረዉን የአህሉል በይት ክብር ለመመለስ አንድ እርምጃ ወደፊት እንደተራመዱ ይቆጠራል፡፡ ወይም ደግሞ ህዝቡ ለአህሉል በይት ከነበረዉ ፍቅር አኳያ ቀልቡን ለማግኘት አድርገዉት ሊሆን ይችላል፡፡ ‹የለም፣ክፉዎች ስለሆኑ የህዝበ ሙስሊሙን ዐቂዳ ለመበከል የሸረቡት ሴራ ነዉ››[147] የሚል ክፉ ጥርጣሬ መኖሩን ሳንዘነጋ፡፡

አብዛኛዎቹ ዑለሞች እንደሚሉት መዉሊድን በኦፊሴል ማክበር የጀመረዉ ፍትሀዊዉና ደጉ ንጉስ ሙዘፈር መሆኑን ካጸደቅንም ቁድስን ከመስቀላዉያን ወራሪዎች ነጻ ያወጣዉ የሶለሀዲን አልአዩቢ ቤተሰብ የሙስሊሙን ዓለም የፖለቲካ አየር ለዘመናት አፍኖት ከቆየዉ አህሉል በይትን የማሳደድ ጭጋግ ነጻ የማዉጣቱ ብስራትና መገለጫ ተደርጎ ይመዘገብለታል፡፡ መዉሊድ በኦፊሴል በሙዞፈር ሲጀመር በዚያ ዘመን የነበሩ ታላላቅ ዐሊሞች የተሰማቸዉ ደስታና እፎይታ ፖለቲካዊ ትርጉሙ ይህ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ዉሀዉ ወደቦዩ እየተመለሰ እንደሆነ

[147]ሀቂቀቱል ኢህቲፋል ቢል መዉሊድ፣በብዱረህማን በብዱል ኻሲቅ፣መክተበተ ሻሚላ

ሳይሰማቸዉ አልቀረም፡፡ ከመደሰት አልፈዉ የመዉሊድ ኪታብ አዘጋጅተዉለታል፡፡ ለምሳሌ የዚያ ዘመን ዓሊሞች አዉራ ሸኽ ኢብኑልሽጣብ ኢብን ደህያህ ‹‹አልተንዊር ፊመዉሊዲል በሽር አልነዚር›› የተባለ የመዉሊድ ኪታብ አዘጋጅተዋል፡፡ ኢማም እብን ከሲር የዚህን መጽሀፍ ይዘት በ625 ሂጅሪያ ከንጉሱ አጠገብ ሆነዉ መስማታቸዉን ጽፈዋል፡፡[148]በእርግጥም አህሉል በይትን የማሳቀቅ የግፍ ልምድና ሥርዓት ሲያከትም እፎይታ የማይሰማዉ ማን አለ?

በ699 ሂጅሪያ ከሙስሊሙ ዓለም የፖለቲካ ሰማይ ላይ መንገስ ጀምረዉ በ923 ሂጅሪያ የሸሊፋነቱን ስልጣን የጨበጡትና እስከ 1337 ሂጅሪያ የቆዩት[149] የቱርክ ዑስማንያ ኺላፋ መሪዎች በአንድ አያት ልጆች መካከል ለዘመናት ነግሶ ከቆየዉ ቤተሰባዊ ፉክክርና የአህሉል በይት ጥላቻ አባዜ ነጻ ስለነበሩ የመዉሊድን መታሰቢያ በቅንነት ተቀብለዉ ሲያራምዱት ኖረዋል፡፡ በተለያዩ ዘመናትና የሙስሊሙ ዓለም የመዉሊድ ታሪክና ሂደት እብን አልዐለዊ የታሪክ ድርሳናትን መሠረት አድርገዉ የጻፉ ጸሀፍትን በስፋት ጠቅሰዋል፡፡[150]

ከታሪኩ ሂደት እንደምንረዳዉ በመዉሊድ ላይ የተያዙ አቋሞች ከሀይማኖታዊ ገጽታነት ይልቅ ፖለቲካዊ ቃና ያላቸዉ ይመስላል፡፡ <u>በአስተሳሰብ ደረጃ ከኡመያዉያን የወገኑት ከሞላ ጎደል የመዉሊድን መታሰቢያ በክፉ ዓይን ማየታቸዉ የሚጠበቅ ሲሆን ከዚህ ጫና ነጻነት ያገኙት የአህሉል በይት ቅን ደጋፊዎች ደግሞ ጉዳዩን በአወንታዊነቱና በቅንነት ሲያስተናግዱት ኖረዋል፡፡</u>

[148]የዚህ ኪታብ የእጅ ቅጅ በደማስቆ አልአሳድ ላይብረሪ ዉስጥ ይገኛል፣ (አል ኢዕላመ)
[149]አል መዉሱዐቱል ሙየሰራህ ፊታሪኺል ኢስላሚ፣ቅጽ 2፣ገጽ 121
[150]አልኢዕላም ገጽ 250-255

ታሪካዊ ቅኝታችንን እዚህ ላይ ገታ እናድርግና ወደሀይማኖታዊ መረጃዎች ፍተሻ እናምራ። የመዉሊድ ቁርአናዊ፣ሀዲሳዊና ፊቅሀዊ መነሻዎች ምን ምን ናቸዉ? ቀጣዩ ምዕራፍ በዚህ ላይ ያተኩራል።

ምዕራፍ ሦስት

ሸሪዐዊ መነሻዎች

እንደምንም አዝግመን እዉይይታችን አስኳል ላይ ደርሰናል። በዚህ ምዕራፍ ዉስጥ ለመዉሊድ መነሻ የሆኑ ቁርአናዊና ሀዲሳዊ መልዕክቶችን፣ እንዲሁም የፊቅህ ጽንሰሀሳቦችን በቅርበት እንመረምራለን።

የእስልምና አበይትና ደጋፊ ምንጮች

ሸሪዐዊ መረጃዎችን በወጉ ለማገናዘብ ይረዳን ዘንድ በመጀመሪያ ስለ መረጃ ምንጮቻችን ጥቂት ግንዛቤ ላስጨብጥ። እስልምና ቁርአንና ሀዲስ የተባሉ ዋነኛ ምንጮች ያሉት ሲሆን፣ከደጋፊ ምንጮቹ መካከል አበይቶቹ ኢጅማዕና ቂያስ ይባላሉ።

1.<u>ቁርአን</u>፡-ዋነኛዉ የሸሪዐ ምንጭ ሲሆን፣የአተረጓጎም (ተፍሲር) ስልቱን ተመለከተ ብዙ መጽሀፍት ተዘጋጅተዋል። ሸኽ እብን ተይሚያህ ያዘጋጇትና ኢማም እብን ከሲር ለተፍሲር መጽሀፋቸዉ መግቢያ ያደረጓት አነስተኛ መጽሀፍ ለዉይይታችን በቂ ስለሆነች የእርሷኑ ሀሳብ አሳጥሬ ላቅርብ።

ሀ.የቁርአን ዋነኛ ተርጓሚ ቁርአን ራሱ ነዉ። ቃላት እና ጽንሰሀሳቦቹን ራሱ በራሱ ያብራራል። በአንድ ቦታ ላይ በጥቅሉ ያቀረበዉን ሀሳብ በሌላ ቦታ ያፍታታዋል። ቁርአንን በቁርአን መተርጎምን ሸኽ እብን ተይሚያህ፣ብሎም እብን ከሲር፡-‹‹**አሶህ ጡሩቅ›› ብለዉታል-/ይበልጥ ትክክለኛዉና አስተማመማኙ የቁርአን አፈሳሰር መንገድ/**።[151]

[151]የተፍሲር እብን ከሲር መግቢያ

ለ. አንድን ቃል ወይም ጽንሰ ሀሳብ ከቁርአን ዉስጥ ፍች ስናጣለት ብቻ ወደ ሀዲስ እናመራለን፡፡ ምክንያቱም ቁርአንን ከማንም በላይ የተረዱትና በቃልም በተግባርም ያብራሩት ነብዩ ﷺ ናቸዉና፡፡ አላህም፡- ‹መልዕክቱን ለሰዎች ታብራራ ዘንድ አወረድንልህ›[152] ብሏቸዋል፡፡

ሐ.የአንድን ቃል ወይም ጽንሰ ሀሳብ ትርጉም ከቁርአን ወይም ከሀዲስ ካጣን ወደ ሶሀቦች አተረጓጎም እናመራለን፡፡ ሶሀቦች ቁርአን ሲወርድ በቦታዉ ስለነበሩና የወረደበትን ድባብ ስለሚያዉቁ፣እንዲሁም የነብዩ ﷺ ተማሪዎች ስለሆኑና በህይወትም ስለኖሩት ቁርአንን ከማንም በላይ ይረዱታልና የነርሱ ትርጉምና ግንዛቤ ጠቃሚ ነዉ፡፡

መ.ከሶሀቦች ቃል ትርጉሙን ላጣንለት የቁርአን መልዕክት የሶሀቦች ተማሪዎች የሆኑትን የታቢያች ቃል ለግንዛቤያችን እንጠቀማለን፡፡

ሸኽ እብንተይሚያህም ሆኑ ኢማም እብን ከሲር ለዚህ ግንዛቤ መነሻ ያደረጉት ነብዩ ﷺ ሙዐዝን ወደየመን ሲልኩ ‹‹በምን ትፈርዳለህ?›› በማለት በጠየቁት ጊዜ የሰጣቸዉ ተከታዩ ምላሽ ነዉ፡-

‹‹በቁርአን እፈርዳለዉ፣ከርሱ ካጣሁ በሀዲስ እፈርዳለዉ፡፡ከርሱ ካጣሁ ግንዛቤየን እጠቀማለሁ›› አላቸዉ፡፡ እርሳቸዉም በግንዛቤዉ ተደስተዉ አላህን አመሰገኑ፡፡[153]

በዚህ ጽሁፍ ለማቀርባቸዉ መረጃዎች ይህንን ስልት እጠቀማለሁ፡፡

<u>2.ሀዲስ</u>፡-ሁለተኛዉ የመረጃ ምንጭ ሀዲስ ሲሆን፣ ሦስት ዓይነት ነዉ፡-

- ‹ሱና አል-ቀዉልያህ›-ነብዩ የተናገሩት፣ወይም
- ‹ሱና አል-ፊዕልያ›-የተገበሩት፣ወይም

---

[152] አልነህል 44

[153] አህመድ፣አቡዳዉድና ቲርሚዚ

- ‹ሱና አል-ተቅሪርያህ›-ሌሎች ሲሰሩት አይተዉ በዝምታ ያጸደቁት፤[154]

3.ኢጅማዕ፡- ለምርምርና ፍተሸ ብቁ የሆኑ ዑለሞች በአንድ ዲናዊ አጀንዳ ላይ የሚደርሱበት የጋራ አቋም ‹‹ኢጅማዕ›› ይባላል፡፡[155]

4.ቂያስ፡- በሸሪዐዉ እርም የሆነ ወይም የተበረታታ ነገር ምክንያቱ ይታወቅና በዚያ ምክንያት የሚመሳሰሉት ነገሮች ሁሉ ልክ እንደርሱዉ የተፈቀዱ ወይም የተከለከሉ ይሆናሉ፡፡ ይህን የማዛመድ ስልት ዑለሞች ቂያስ (inference) ይሉታል፡፡ ለምሳሌ በቁርአን ወይን ጠጅ (ኸምር) ተከለከለ፡፡ የመከልከሉ ሰበብ አስካሪ መሆኑ ነዉ፡፡ ስለዚህም ማንኛዉም አስካሪ ነገር በቂያስ መረጃ አማካይነት ክልክል ይሆናል፡፡

እነዚህን ምንጮች በቅደም ተከተል ተጠቅመን የመዉሊድን ሸሪዓዊ መደገፊያ እንመለከታለን፡፡

ቁርአናዊ መረጃዎች

1.<u>በአላህ እዝነትናትሩፋት ተደሰቱ</u>፡- ለመዉሊድ ይሁንታ የሚጠቀሰዉ ጠንካራዉና የመጀመሪያዉ የቁርአን መልዕክት እንዲህ ይላል፡-

قُلْ بِفَضْلِ اللَّهِ وَبِرَحْمَتِهِ فَبِذَٰلِكَ فَلْيَفْرَحُوا هُوَ خَيْرٌ مِّمَّا يَجْمَعُونَ

‹‹በአላህችሮታናበእዝነቱደስቱ፡፡እርሱከሚሰበስቡትሀብትበላጭነው፣በላቸው፡፡››[156]

ይህ የቁርአን አንቀጽ በአላህ እዝነት (ረህመት) እና ችሮታ (ፈድል) እንደሰት ዘንድ ያዘናል፡፡ አላህ በምድር ላይ ብዙ ችሮታዎችን ለግሶናል፡

[154]ዙሀይሊ፣ኡሱልፈቅህ፣ቅጽ1፣ገጽ 451
[155] ዙሀይሊ፣ኡሱልፈቅህ፣ቅጽ1፣ገጽ 490
[156] ዩኑስ 58

፡ መፈጠር ችሮታ ነዉ፡፡ ጤንነት ችሮታ ነዉ፡፡ ኢማን ችሮታ ነዉ ወዘተ፡፡ በዚህ ሁሉ መደሰትና ለአላህ ምስጋና ማድረስ ተገቢ ሲሆን የነብዩ ሙሀመድንﷺ መወለድ የሚያክል እዝነትና ችሮታ ግን ፈጽሞ የለም፡፡ ወደፊትም አይኖርም፡፡ ስለዚህ በዚህ አንቀጽ ዉስጥ ‹እዝነት ና ችሮታ› የሚሉት ቃላት ከማንምና ከምንም በፊትና በላይ ነብዩ ሙሀመድንﷺ ይመለከታሉ፡፡ እርሳቸዉን በተዘዋዋሪ ሳይሆን በቀጥታ ይጠቅሳሉ፡፡ ዕዉቁን የተፍሲር ሊቅ ሸኽ አልአሉሲ አንቀጡን ሲያብራሩ እንዲህ ብለዋል፡-

والمشهور وصف النبي صلى الله عليه وسلم بالرحمة كما يرشد إليه قوله تعالى : { وَمَا أرسلناك إِلاَّ رَحْمَةً للعالمين } [الأنبياء : 107]

‹‹ነብዩ እዝነት መባላቸዉና መሆናቸዉ የታወቀ ነዉ፡፡ አላህ እንዲህ በማለት ገልጹዋቸዋልና፡-

‹‹(ሙሐመድሆይ!) ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጅ አልላክንህም፡፡›› (አል አንቢያእ 107)[157]

የሸኽ አሉሲ ድምዳሜ ከቁርአን ተፍሲር ስልቶች ዉስጥ ከፍተኛ ተአማኒነት ያለዉን ስልት መሠረት ያደረገ ነዉ፡፡ ቁርአንን ከቁርአን የተሻለ ሊያብራራዉ የሚችል ነገር የለምና፡፡

ነብዩ ሙሀመድﷺ የዕዝነት ተምሳሌት መሆናቸዉን ሌላ የቁርአን መልዕክት እንዲህ አጽንቶታል፡-

لَقَدْ جَاءَكُمْ رَسُولٌ مِّنْ أَنفُسِكُمْ عَزِيزٌ عَلَيْهِ مَا عَنِتُّمْ حَرِيصٌ عَلَيْكُم بِالْمُؤْمِنِينَ رَءُوفٌ رَّحِيمٌ

[157]ረሀል መዐኒ-አልአሉሲ፣መክተበተ‌ሸሚላ፣ገጽ40

‹‹ከገሳችሁ የሆነ ችግራችሁ በእርሱ ላይ ጽኑ የሆነ፣በእናንተ (አምነት) ላይ የሚጓጓ፣በምእምናን (ላይ) ርኅሩኅ አዛኝ የኾነ መልክተኛ በእርግጥ መጣሳችሁ፡፡ ››[158]

አላህ ነብዩ ሙሀመድን በመላክ ትልቅ ጸጋና ችሮታ ለአማኞች መለገሱን ሲገልጽ፡-

لَقَدْ مَنَّ اللَّهُ عَلَى الْمُؤْمِنِينَ إِذْ بَعَثَ فِيهِمْ رَسُولًا مِّنْ أَنفُسِهِمْ يَتْلُو عَلَيْهِمْ آيَاتِهِ وَيُزَكِّيهِمْ وَيُعَلِّمُهُمُ الْكِتَابَ وَالْحِكْمَةَ وَإِن كَانُوا مِن قَبْلُ لَفِي ضَلَالٍ مُّبِينٍ [٣:١٦٤]

‹‹አላህ በምእምናን ላይ ከገሳቸው የኾነን፤ በእነርሱ ላይ አንቀጾቹን የሚያነብ፣ የሚጠራቸውም፣ መጽሐፍንና ጥበብን የሚያስተምራቸውም የኾነን መልእክተኛ በውስጣቸው በላከ ጊዜ፤ በእርግጥ ለገሰላቸው፡፡ እነርሱም ከዚያ በፊት በግልጽ ስህተት ውስጥ ነበሩ፡፡››[159]

ኢብን ዐባስ ‹ረህማ› የሚለዉን የአንቀጹን ቃል ‹‹የአላህ መልዕክተኛ››፣ ‹‹ፈድል›› የሚለዉን ቃል ደግሞ ‹‹እዉቀት›› በማለት መተርጎማቸዉ[160] ከላይ የሰጠነዉን ማብራሪያ ትክክለኛነት ያጸናል፡፡ አነስኢብን ማሊክ[161]፣ በራእና አቡ ሰዒድ አል'ኹዱሪም በተመሳሳይ መልኩ ተርጉመዉታል፡፡[162]

የእብ ዐባስን ቃል ‹‹አልዱር አልመንሱር›› ከተሰኘዉ ኪታብ በዐረብኛ እንዲህ ተቀምጧል፡-

وأخرج أبو الشيخ عن ابن عباس رضي الله عنهما في الآية قال : فضل الله العلم ورحمته محمد صلى الله عليه وسلم قال الله تعالى (وما أرسلناك إلا رحمة للعالمين) (الأنبياء الآية 107)

[158]አልተዉባህ 128
[159] አስ ሷምራን 164
[160]አልዱር አልመንሱር፣ሲዩዩጢ-ስለንቀጹ ካሰፈሩት ማብራሪያ
[161]ሩሀል መዐኒ-ስልአሉሲ፣መክተበተአሽሚላ፣ገጽ40
[162]ያስፈዉ ምኝጭ፣ገጽ41

‹‹አቡሸኽ እንዳስተላለፉት እብን ዐባስ አንቀጹን በሚመለከት፡- **<u>የአላህ ችሮታ ዕዉቀት፣ ረህመቱ ደግሞ ሙሀመድ ﷺ ናቸዉ።</u>**አላህ፡- ‹የዓለማት ዕዝነት አድርገን እንጅ አልላክንህም› ብሏልና››

‹ረህማ› የሚለዉን ቃል ‹ቁርአን›፣‹ፈድል› የሚለዉን ደግሞ ‹የቁርአን ቤተሰብ መሆን› በማለት የተረጎሙ የሶሀባና የታቢዕ ዘመን ምሁራንም አሉ።።[163] በእርግጥ ቁርአን ችሮታ ነዉ፣እስልምና ችሮታ ነዉ፤የነዚህ ሁሉ ችሮታዎች አስኳልና ሰበብ ግን ያለ ጥርጥር ነብዩ ሙሀመድ ﷺ ናቸዉ። ኢማም ሸዉካኒ በአንቀጹ ዙሪያ በሶሀባና በታቢዕ ትዉልድ የተፍሲር ሊቃዉንት የእዝነትና የችሮታ ናሙናዎችንና ተፍሲሮችን ከጠቃቀሱ በኋላ እንዲህ የሚል ማጠቃለያ አስፍረዋል፡-

والأولى حمل الفضل والرحمة على العموم

‹‹ይበልጥ ተገቢዉ አተረጓጎም እዝነትና ችሮታ የሚሉ ጽንሰሀሳቦችን አጠቃላይበሆነ (ሁሉንም ሊያካትት በሚችል) መልኩ መረዳት ነዉ።።››[164]

‹እዝነትና ችሮታ የሚሉት ንሰ ሀሳቦች በሶሀባና በታቢዒ የተፍሲር ሊቃዉንት በተናጠል የተጠቀሱ ነገሮችን ሁሉ ያጠቃልላሉ› ይሉናል አልሸዉካኒ። እርሳቸዉን ለይቼ የጠቀስኩት በገሚስ ወንድሞች ዘንድ ከእብን ተይሚያህና እብንልቀይም ቀጥሎ ቃላቸዉ ተሰሚነት ያለዉ ስብዕና ስለሆኑ ነዉ።

ነብዩ ﷺ ታላቁ የአላህ እዝነትና ችሮታ የመሆናቸዉን እንደረፋድ ጸሀይ ግልጽ የሆነ እዉነታ ለማስረዳት ይህን ያህል መድከም አያስፈልግም ነበር።

ሀሳቡ ሲጠቀለል አላህ በእዝነቱና በችሮታዉ መደሰትን አዘዘ። የነብዩ ﷺ ልደት መታሰቢያ ይህን ደስታ በአደባባይ መግለጽ ነዉ።

---

[163]ተፍሲር እብን ከሲርን ደመልከቱ

[164]ፈትሁል ቀዲር፣ስእንቀጹ ከተሰጠ ማብራሪያ የተወሰደ

‹‹ሁልጊዜ አትደሰቱም? ጊዜና አጋጣሚ መጠበቅ ለምን አስፈለገ?›› ለሚለዉ ጥያቄ ‹‹በእርግጥ በነብዩﷺ ሁልየም መደሰት ተገቢ ነዉ። ሆኖም የሰዉ ልጅ አጋጣሚዎች ይገዙታል፤ያስታዉሱታል። በረመዳን ጸጋ ሁልየም መደሰት አለብን። ግና ሰዉ ነንና አንዘነጋለን። የወሩ መቃረብ ደወል ሆኖን እንነቃለን። ሀጅና ሌሎች አጋጣሚዎችም እንደዚሁ ዘወትር መታወስ ቢኖርባቸዉም ወቅታቸዉ ሲደርስ መታወሳቸዉ የበለጠ ይበረታል። የነብዩﷺ ልደት ጸጋም እንደዚሁ ነዉ። በእያንዳንዷ ቅጽበት ልንደሰትበት ይገባል። ሆኖም ረቢዐል አወል የበለጠ አስታዋሽ ይሆነናል።›› የሚል መልስ ለመዉሊድ ይሁንታ የቸሩ ዑለሞች ይሰጣሉ።[165]

በተጨማሪም መዉሊድ ዘወትር በሳምንታዊ ወይም በወርሀዊ ዑደቶች ዓመቱን ሙሉ በመደጋገም ነብዩንﷺ ትዉስታና ፍቅር ሀያዉ አድርጎ የሚያቆይ ጠንካራ የህዝበ ሙስሊሙ ልምድ መሆኑ መዘንጋት የለበትም። ስለዚህ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ እንደሚደረግ ማሰብ ስህተት ነዉ። ሆኖም ረቢዕ ወር ይህን ትዉስታ ጫፍ ያደርሰዋል። ለተጨማሪ ግንዛቤ ከምዕራፍ አንድ ላይ **‹‹የሚከናወንበት ጊዜ››** በሚል ርዕስ ያሰፈርነዉን ጽሁፍ ይመልከቱ።

ተቃዉሞና ምላሽ

‹‹የለም፤ይህ የቁርአንመልዕክት ለመዉሊድ መረጃ አይሆንም›› በማለት የሚከራከሩ ወገኖች የክርክር ጭብጥ ያስደነግጣል። ከአንቀጹ ላይ ‹‹ረህማ›› የሚለዉ ቃል ቁርአንን፣ሀዲስንና እስልምናን እንጅ ነብዩንﷺ አያጠቃልልም ነዉ ይሉናል። ከራሴ ያልኩት እንዳይመስል ከባለቤቶቹ ልጥቀስ። የሳዉዲዉ እዉቅ ዐሊም ዐብላህ አልቱወይጂሪ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፦

[165] አብንል ዐስዊ፣ሀዉስል ኢህቲፋል...ገጽ

أن كبار المفسرين قد فسَّرُوا هذه الآية الكريمة ، ولم يكن في تفسيرهم أن المقصود بالرحمة في هذه الآية رسول الله صلى الله عليه وسلم

‹‹ይህን የቁርአን አንቀጽ የፈሰረ ታሳሳቅ ሲቃዉንት በዚህ አንቀጽ ዉስጥ የተጠቀሰዉ ‹ረህማ›የአላህን መልዕክተኛ እንደሚያካትት አልጠቀሱም።።።›››[166]

በእርግጥ ይህ የቱወይጅሪ ብቻ ሳይሆን የሌሎች ሰለፊ/ዉሀቢ ዑለሞች እይታ ነዉ። በሸኽ እብን ባዝ የሚመራዉና ማዕከሉን ጅዳ ያደረገዉ ‹‹መርከዘ ዳዕዋ ወልኢርሻድ›› ማዕከል በሰጠዉ ፈትዋ ላይ፡- ‹‹በዚህ አንቀጽ ዉስጥ ረህማ የሚለዉ ቃል ነብዩን አይመለከትም፤ቁርአንንና ሱናን ብቻ እንደሚመለከት እብንል ቀይም ተናግረዋል›› ሲል ፈትዋ ሰጥቷል። የፈትዋዉን ሙሉ ቃል እብንል ዐለዊ ‹‹አልኢዕላም›› ዉስጥ አስፍረዉታል።[167]

ይህ የሸኹ እና የመሰሎቻቸዉ ሀሳብ ስህተት ከመሆኑ በተጨማሪ ከነብዩ ﷺ ጋር ሊኖር የሚገባዉን አደብም የጣሰ መሆኑን የመዲናዉ የሀዲስ ሊቅ ሸኽ እብንል ዐለዊ ጠቅሰዉ፡-‹‹ሰዎቹ ሸሀዳ የመሰከሩ ሆኑና ተቸገርን እንጅ ከእስልምና ዉጭ ናቸዉ ለማለት ይዳዳን ነበር››በማለት በዚህ ግንዛቤ የተሰማቸዉን ድንጋጤና ጥልቅ ሀዘን ገልጸዋል።[168]

ይህ ሀሳብ ካቆራቸዉ እንከኖች መሀል የሚከተሉት ጥቂቶቹ ናቸዉ፡-

አንደኛ፡-ወደ ዝርዝር ምላሽ ከመግባ በፊት ለቱወይጅሪና ለመሰሎቻቸዉ ጥያቄዉን ገልብጠን እናቅርብላቸዉ። ***‹‹ነብዩ ﷺ ሙሀመድ በዚህ አንቀጽ ከተጠቀሰዉ ረህማ ዉስጥ አይካተቱም ያለ የሰለፍ ዐሊም አለን?››*** በእርግጥ የለም። ይህን ለማለት ማን ይደፍራል? ታዲያ የእናንተ ግንዛቤ ከየት በቀለ? በምን ሚዛን የሰለፍ ተሰኘ?

---

[166]ቢድዐቱል ኢህቲፋል ቢልመዉሲዩነቢዊ፣መክተበተ ሻሚላ፣ገጽ 32
[167] አል ኢዕላም 105-116
[168]ሀዉስል ኢህቲፋል...፣ገጽ 66

ሁለተኛ፡-ከሸኽ ቱወይጂሪና ከመሰሎቻቸዉ ዘንድ ቃላቸዉ በእጅጉ ተቀባይነት ያለዉ ሸኽ እብን ተይሚያህ፣ ከቁርአን ተፍሲር ስልቶች መካከል ከፍተኛዉና ይበልጥ አስተማማኙ ቁርአንን በቁርአን መፈሰር እንደሆነ በአንክሮ መግለጻቸዉን ከአሁን ቀደም ጠቅሰናል።[169]

በዚሁ ስልት ተጠቅመን አንቀጹን ከተረጎምነዉ በዋነኛነት ሊካተቱ የሚችሉት ነብያችንና ነብያችን ናቸዉ። አላህ ‹‹የዓለማት ረህመት አድርጌ ልኪያቸዋለሁ›› ከማለቱ የተሻለ ምን ምስክርነት ያሻል?

ሦስተኛ፡-‹ታላላቅ መፈሲሮች እዚህ አንቀጽ ዉስጥ ነብዩን ﷺ አላካተቱም› የሚለዉ የሸኽ ቱወይጅሪ ገለጻ ቢያንስ ስህተት፣ሲበዛ ደግሞ ቅጥፈት ነዉ። ቱወይጂሪን በቅጥፈት መጠርጠር ይከብዳል። መሳሳታቸዉን ግን እርግጠኞች ነን። የሸኽ አል አሉሲን፣የጀላሉዲን አልሱዩጢን ወይም የሸዉካኒን የተፍሲር ኪታቦች አላዩአቸዉም ለማለት እቸገራለሁ።ሳያዩና ሳያገናዝቡ ጽፈዉ ከሆነ፣ ያለዕዉቀት መናገር በመሆኑ መከራ ነዉ። እያወቁ ደብቀዉ ከሆነ ደግሞ የባሰ መከራ። በሀዲስ ሊቃዉንት ቋንቋ ‹*ተድሊስ› /መረጃን ሆነ ብሎ ማዛባት/* ይባላል። ሸኽ እብን ባዝና የፈትዋ ኮሚቴያቸዉ ከቁርአንና እንደ እብን ዐባስ ካሉ ሶሀቦች ተፍሲርና ምስክርነት፣እንዲሁም እንደ አልአሉሲ ካሉ የቁርአን ተፍሲር ሊቃዉንት የእብንል ቀይምን ቃል ያስበለጡበት ሰበብ ምክንያታዊ አይደለም። ከላይ እንደጠቀስኩት ከሸኽ አሉሲ ተፍሲር ላይ እንዲህ የሚል መልዕክት በጉልህ ሰፍሯል፡-

والمشهور وصف النبي صلى الله عليه وسلم بالرحمة كما يرشد إليه قوله تعالى : { وَمَا أرسلناك إِلاَّ رَحْمَةً للعالمين } [الأنبياء : 107]

[169] የእብን ከሲርን ተፍሲር መግቢያ ያንብቡ።

‹‹ነብዩ እዝነት መባላቸዉና መሆናቸዉ የታወቀ ነው። አላህ እንዲህ በማለት ገልጹዋቸዋልና፡-

‹‹(ሙሐመድሆይ!) ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጅ አልላክንህም።›› (አል አንቢያእ 107)[170]

ኢብን ዐባስ ‹ረህማ› የሚለዉን የአንቀጹን ቃል ‹‹የአላህ መልዕክተኛ››፣ ‹‹ፈድል›› የሚለዉን ቃል ደግሞ ‹‹እዉቀት›› በማለት መተርጎማቸዉ አልዱሩል መንሱር ከተባለዉ የተፍሲር ኪታብ ዉስጥ ይገኛል።[171] አነስኢብን ማሊክ[172]፣ በራእና አቡ ሰዒድ አልኹዱሪም በተመሳሳይ መልኩ መተርጎማቸዉም ተመዝግቧል።[173]

ወይስ ኢብንዐባስ፣አነስ እብን ማሊክ፣በራእ፣አቡሰዒድ አልኹዱሪና ሸኽ አልአሉሲ በቱወይጂሪና በጓዶቻቸዉ ዘንድ ዕዉቅ የተፍሲር ሊቃዉንት አይደሉም? ታዲያ ማን ነዉ ሊቁ?

‹‹ቁርአንና ሀዲስ እንጅ ነብዩ ከዚህ የአላህ ረህመት ዉስጥ አይካተቱም›› ብሎ መናገር ለሰሚዉ ይነዝራል። ግራም ያጋባል። ቁርአኑ፣ሀዲሱ፣ እስልምናዉ በማን አማካይነት ተላለፈልን? የዓለማትን እዝነት ﺺ በዚህ መንገድ መግለጽ አደብ አይደለም። ለክህደት ቀረብ ያለ እንደሆነም ይሰማኛል።ነብዩﷺእዝነት ናቸዉ፣ታላቅ እዝነት። ችሮታ ናቸዉ፣ወደር የለሽ ችሮታ። ህይወት ናቸዉ፣ ፍጹም ህይወት። ሶለዋቱላሂ ወሰላሙሁ ዐለይህ፤

‹‹ሰለፎች በዚህ መልኩ አልተረዱትም›› የሚል ተቃዉሞ ከቱወይጅሪና ከመሰሎቻቸዉ መሰማቱም የሚደንቅ ነዉ። ከእብን ዐባስ፣ከአነስ እብን

[170]ሩህል መዐኒ-አልአሉሲ፣መክተበተሽሚላ፣ገጽ40
[171]አልዱር አልመንሱር፣ሲዩዩጢ-ስእንቀጡ ካሰፈሩት ማብራሪያ
[172]ሩህል መዐኒ-አልአሉሲ፣መክተበተሽሚላ፣ገጽ40
[173]ያስፈዉ ምኝጭ፣ገጽ41

ማሊክ፣ከበራእና ከአቡሰዒድ አልኹድሪ በላይ ሰለፍ ከየት ይመጣል? ወይስ ሰለፍ የሚለዉ ቃል ሶሀቦችን አያካትትም?

የመዉሊድንም ሆነ ሌሎች አጀንዳዎችን ሳጠና እንደተገነዘብኩት ገሚስ ወንድሞቻችን ሱፊ ከሚሉት ወገን ጋር የተገኛኙ አጀንዳዎችን ሲያጠኑ ሚዛን ይስታሉ። የሚያምኑባቸዉን መሠረታዊ መርሆዎች (ቀዋዒድ) ሳይቀር ይጨፈልቃሉ። የቁርአንና የሶሂህ ሀዲስ መልዕክቶችን እነርሱ ከማይደግፉት ግንዛቤ ለማራቅ ይተጋሉ። ነብዩ ﷺ በአንቀጹ ከተጠቀሰዉ የአላህ እዝነትና ችሮታ ዉስጥ አይካተቱም ብሎ መከራከር ከዚህ ዉጭ ሌላ ምን ትርጉም ሊሰጠዉ ይችላል?

ለመዉሊድ ሸሪዐዊነት ከላይ የቀረበዉ የቁርአን አንቀጽ ዋነኛ መደገፊያና በቂ ቢሆንም ሌሎችንም ብናክልበት አይከፋም።

2.<u>‹የአላህን ቀናት አስታዉሳቸዉ›</u>፦ ለመዉሊድ መረጃ ሆኖ የሚቀርበዉ ሁለተኛዉ የቁርአን መልዕክት የሚከተለዉ ነዉ፦

وَذَكِّرْهُم بِأَيَّامِ اللَّهِ

‹‹የአላህንም ቀኖች አስገንዝባቸዉ...።››[174]

ይህ ትዕዛዝ የተላለፈዉ ለሙሳ ነዉ። የአላህን ቀናት ለህዝባቸዉ እንዲያስታዉሱና እንዲያስገነዝቡ አላህ አዘዛቸዉ።

የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ‹‹የአላህ ቀናት›› የሚለዉን መልዕክት ‹‹የአላህ ጸጋዎች›› በማለት መተርጎማቸዉን ኢማም እብን ከሲር እብን ዐባስንና ኡበይ እብን ከዕብን ዋቢ አድርገዉ ጽፈዋል።[175] ራሳቸዉ እብን ዐባስና

[174] ኢብራሂም 5

[175]ተፍሲር እብን ከሲር

ኡበይ፣እንዲሁም ሙጃሂድና ቀታዳ በተመሳሳይ መልኩ ተርጉመዉታል፡ ፡[176]

በዚህ አንቀጽ ዙሪያ የተነገሩ ትርጉሞችን በአንድ ስንደምራቸዉ አላህ ጸጋ የዋለባቸዉን ቀናት እና ጸጋዎቹን ሙሳ ለበኒ እስራኤል እንዲያስታዉሱ ማዘዙን እንረዳለን፡፡ በሌላ የቁርአን አንቀጽ አላህ የጥንት ነብያትን ታሪክ ከዘረዘረልን በኋላ እንዲህ ሲል አዞናል፡-

أُولَٰئِكَ الَّذِينَ هَدَى اللَّهُ فَبِهُدَاهُمُ اقْتَدِهْ

‹‹እነዚህ (ነቢያት)፣እነዚያአላህየመራቸውናቸው፡፡በመንገዳቸውምተከተል፡፡››[177]

የአላህን ቀናት ያስታዉሱ ዘንድ ሙሳ ታዘዋል፡፡ እኛ ደግሞ የርሳቸዉን አርአያነት እንከተል ዘንድ ታዘናል፡፡ ስለዚህ የአላህን ቀናት ማስታዎስ ይገባናል፡፡ **ለዚህ ኡማ ትልቁ የአላህ ቀን፣ ነብዩ ወደዚህች ዓለም የመጡበት ቀን ነዉ፡፡ በሌላ አባባል ይህ የቁርአን አንቀጽ ነብዩ ﷺ የተወለዱበትን ቀን አናስታዉስ ዘንድ መመሪያ ያስተላልፍልናል፡፡ ማስታዎስ ምንጊዜም ለአማኞች ጠቃሚ ነዉና፡፡** በነገራችን ላይ ቁርአን ዉስጥ ከብዙ ጸጋዎች ጋርተያይዞ እንዲህ የሚለዉ መልዕክት በአስሮች ለሚቆጠር ጊዜ ተደጋግሞ ተወስቶአል፡-

وَاذْكُرُوا نِعْمَتَ اللَّهِ عَلَيْكُمْ

‹‹በናንተ ላይ የአላህንምጸጋ ...አስታዉሱ፡፡››[178]

አንደኛዉ ግን በቀጥታ ከነብዩ መሀመድ ﷺ ጋር የተያያዘ ነዉ፡፡ እንዲህ ይላል፡-

[176]ተፍሲር አልጦበሪ
[177] አል አንዐም 90
[178] አልበቀራህ፣231

وَاعْتَصِمُوا بِحَبْلِ اللَّهِ جَمِيعًا وَلَا تَفَرَّقُوا وَاذْكُرُوا نِعْمَتَ اللَّهِ عَلَيْكُمْ إِذْ كُنتُمْ أَعْدَاءً فَأَلَّفَ بَيْنَ قُلُوبِكُمْ فَأَصْبَحْتُم بِنِعْمَتِهِ إِخْوَانًا وَكُنتُمْ عَلَىٰ شَفَا حُفْرَةٍ مِّنَ النَّارِ فَأَنقَذَكُم مِّنْهَا كَذَٰلِكَ يُبَيِّنُ اللَّهُ لَكُمْ آيَاتِهِ لَعَلَّكُمْ تَهْتَدُونَ [٣:١٠٣]

‹‹የአላህንም (የማመን) ገመድ ሁላችሁም ያዙ። አትለያዩም።ጠበኞችም በነበራችሁ ጊዜ በእናንተ ላይ (የዋለውን) የአላህን ጸጋ አስታውሱ። በልቦቻችሁም መካከል አስማማ። በጸጋውም ወንድማማቾች ኾናችሁ።በእሳት ጉድጓድ አፋፍም ላይ ነበራችሁ። ከእርስዋም አዳናችሁ።እንደዚሁ ትመሩ ዘንድ አላህ ለእናንተ አንቀጾቹን ያብራራል።››[179]

አንቀጹ የወረደዉ አዉስና ኸዝረጅ የተባሉ የመዲና ሁለት ጎሳዎች የቅድመ ኢስላም ጥላቸዉን አስታዉሰዉ ለጠብ በተገባበዙበት ጊዜ ነበር። እዚህ ላይ ‹የአላህ ጸጋ› ለሚለዉ ቃል በሊቃዉንት ከተሰጡ ትርጉሞች መካከል አንደኛዉ ‹ነብዩ መ·ሀመድ ናቸዉ› የሚል ነዉ።[180]አ፥ፍጹም ጠላት የነበሩት እነዚህ ሁለት ጎሳዎች በነብዩ መ·ሀመድ አማካይነት ጥልቅ ፍቅር ተጎናጽፈዋል። በርሳቸዉ ትጋት በወንድማማችነት ተሳስረዋል። ከእሳት አፋፍ የነበረች ነፍሳቸዉ የዘላለም ድነትን አግኝታለች።

‹ነብዩንና እርሳቸዉ በመወለዳቸዉ የተገኘዉን አላህ ቀንና ጸጋ ለምን ዓመቱን በሙሉ አታስታዉሱም?› የሚል የተለመደ ጥያቄ ከተነሳ ‹ነብዩንና የመወለዳቸዉን ጸጋ ሁልየም ማስታወስ ተገቢ ቢሆንም ታሪካዊ አጋጣሚዎች ለማስታወስ ጠንካራ ምክንያቶች ናቸዉ።›› የሚል የተለመደ ምላሽ ይሰጣል።

<u>3.ልቦናህን ልናጸና</u>፡- የጥንት ነብያትን ታሪክ አላህ የሚተርክበትን ሰበብ ለነብዩ መ·ሀመድ ﷺ ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡-

---

[179]አስሚምራን 103

[180]አብን ኢስሀቅን በመጥቀስ አብን ጀሪር አልጦበሪ ከተፍሲራቸዉ ዉስጥ አስፍረዉታል፤

وَكُلًّا نَّقُصُّ عَلَيْكَ مِنْ أَنبَاءِ الرُّسُلِ مَا نُثَبِّتُ بِهِ فُؤَادَكَ وَجَاءَكَ فِي هَٰذِهِ الْحَقُّ وَمَوْعِظَةٌ وَذِكْرَىٰ لِلْمُؤْمِنِينَ [١١:١٢٠]

‹‹እነዚያ በምድር ውስጥ (ከአላህ) የሚያመልጡ አልነበሩም፡፡ ከአላህም ሌላ ለእነርሱ ረዳቶች አልነበሯቸውም፡፡ለእነሱቅጣቱይደራረብላቸዋል፡፡ (እውነትን) መስማትን የሚችሉ አልነበሩም የሚያዩም አልነበሩም፡፡››[181]

አላህ የነብዩንﷺ፣ብሎም የኛን ልብ ሊያጸና የሌሎች ነብያትን ታሪክ በብዛት ተርኳል፡፡ የተለያዩ ነብያትን ስም እየጠራም ‹የእገሌን ገድል አስታውስ› በማለት ደጋግሞ አሳስቦአቸዋል፡፡ ለምሳሌ መርየምን[182]፣ ኢብራሂምን[183]፣ሙሳን[184]፣እስማዒልን[185]፣ኢድሪስን[186]፣ዳዉድን[187]፣ አዩብን[188]፣ኢስሀቅንና የዕቁብን[189]፣የሰዖንና ዙል ኪፍልን[190]፣ዑድን[191] ወዘተበስም ዕየጠራ ገድላቸዉን ያስታውሱ ዘንድ ነብዩንﷺአበክሮ አሏል፡ ፡ ‹ወዝክር ዐብደና...› ደጋግሞ ብሎአቸዋል፡፡ ይህ ሁሉ እንዲሁ የሆነ አይደለም፡፡ ከፍተኛ መንፈሳዊ ፋይዳ ስላለዉ እንጅ፡፡ የሌሎች ነብያት ታሪክ ይህን ያህል ልቦናን የማጽናት ጉልበት ካለዉ፣ የነብያት ቁንጮ የሆኑት የነብዩ መሀመድﷺ ታሪክማ ተጽእናዉ የከበደ ነዉ፡፡

[181]ሁድ 20
[182]መርየም 16
[183]መርየም 41ና ሷድ 45
[184]መርየም 51
[185]መርየም 54
[186]መርየም 56
[187]ሷድ 17
[188]ሷድ 41
[189]ሷድ 45
[190]ሷድ 48
[191]አል አህቃፍ 21

መዉሊድን እንደደገፉ ዑለሞች እምነት የነብዩﷺ ልደት ሳምንታዊም ሆነ ዓመታዊ መታሰቢያዎች አብዩ ይዘታቸዉ ገድላቸዉን መዘርዘር በመሆኑ የዚህን የቁርአን መልዕክት ዓላማ ከየትኛዉም አጋጣሚ በላይ ያሳካሉ።

4. **<u>‹‹የጌታህን ጸጋ...››</u>**፦አላህ አማኞችን ጸጋዉን አዘዉትረዉ እንዲገልጹና ስለርሱ እንዲያወጉ ሲያዝ እንዲህ ይላል፦

وَأَمَّا بِنِعْمَةِ رَبِّكَ فَحَدِّثْ [٩٣:١١]

‹‹በጌታህም ጸጋ አውራ፤ (ግለጻት)።››[192]

ይህ የቁርአን መልዕክት ስለአላህ ጸጋዎች አዘዉትረን እንድናወጋ ያዘናል። ስለሁሉም ዓይነት ጸጋዎች። **ከጸጋዎች ሁሉ ትልቁ የነብዩ ሙሀመድﷺ መወለድ በመሆኑ ስለርሱ ይበልጥ ማዉጋት ተገቢ ነዉ። የመዉሊድ ማዕዶች አብይ ዓላማ ደግሞ ይህ ነዉ።**

‹ስለነብዩﷺ ታላቅ ጸጋዉ ለምን ዘወትር አታወጉምና አላህን ዘወትር ለምን አታመሰግኑም?›ለሚለዉ የተለመደ ጥያቄም፦ ‹ዘወትር ማዉጋትና ማመስገን ተገቢ ቢሆንም ታሪካዊ አጋጣሚዎች ግን ይህን ምስጋና የበለጠ ያስታዉሱናል› የሚል የተለመደ መልስ ይሰጣል። ነብዩﷺ የነቢ ሙሳን ድል ዘወትር ማስታወስ ቢኖርባቸዉምና የሚያስታዉሱት ቢሆንም በዓመት አንድ ጊዜ በዐሹራ በጾም የሚያስቡት መሆኑ መዘገቡ[193] የሰዉ ልጅ ከታሪካዊ አጋጣሚዎች ጋር ያለዉን ትስስር በነብያዊ ስልት ያስተምራል።

5. **<u>ዝናህን ከፍ አደረግንልህ</u>**፦አላህ እንዲህ ይላል፦

[192] አልዱሀ፣11

[193] ቡኻሪና ሙስሊም

وَرَفَعْنَا لَكَ ذِكْرَكَ [٩٤:٤]

‹‹መወሳትህንም ሳንተ ከፍ አድርገንልሃል፡፡››[194]

የተፍሲር ምሁራን በዚህ አንቀጽ ዙሪ ያሰፈሯቸዉን መልዕክቶች ስንደምራቸዉ አላህ የነብያችንንﷺ ክብርና ዝና ከፍ ለማድረግ በቀደምት መጽሀፍት ዉስጥ፣በአዛን፣በኢቃማ፣በዒዶችና በሌሎች አጋጣሚዎች እንዲወሱ ማድረጉንና ስማቸዉን ከስሙ ጋር ማቆራኘቱን በዚህ አንቀጽ እያስታወሰን እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡[195]

የነብዩንﷺ መወሳት፣ክብርና ዝና ከፍ ከፍ ማድረግ የአላህ ዓላማና ፍላጎት መሆኑን አንቀጹ ያመለክታል፡፡ የመዉሊድ መታሰቢያ ይህን የአላህ ዓላማ ከሚያሳኩ ክንዉኖች መካከል አንደኛዉ ነዉ፡፡

‹‹መወሳትህን ከፍ አደረግንልህ›› አለ እንጅ ‹‹የተለያዩ ዘዬዎችን ተጠቅማችሁ ክብርና ዝናዉን ከፍ አድርጉ›› አላለም፣የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ በእርግጥ የቁርአንን የገለጻ ስልት ካለመገንዘብ የሚመነጭ ጥያቄ ነዉ፡፡ ‹ነገር በምሳሌ..›ነዉና ሌላ የቁርአን አንቀጽ ጠቅሼ ሀሳቡን ላፍታታ፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፡-

إِنَّا نَحْنُ نَزَّلْنَا الذِّكْرَ وَإِنَّا لَهُ لَحَافِظُونَ [١٥:٩]

‹‹እኛ ቁርአንን እኛዉ አወረድነዉ፡፡እኛም ለእርሱ ጠባቂዎች ነን፡፡››[196]

ይህ አንቀጽ ቁርአንን አላህ እንደሚጠብቀዉ ይገልጻል፡፡ ዑለሞች ይህን አንቀጽ መሠረት አድርገዉ፡- ‹‹ቁርአን በአላህ ስለሚጠበቅ እኛ በሂደቱ ሚና የለንም›› በማለት እጃቸዉን አጣጥፈዉ አልተቀመጡም፡፡ እያንዳንዱ ትዉልድ ቁርአንን ለመጠበቅ የበኩሉን ድርሻ አበረከተ፡፡ አቡበክር የቁርአን ጽሆፎች እንዳይጠፉ በአንድ ጠረዙ፡፡ ዑስማን በቁርአን

[194]አል-ሸርህ፣4

[195] ተፍሲር እብን ከሲር፣አቡሲ፣ቁርጡቢና አልሙንተኽብ ስለብነት ይመልከቱ፡፡

[196]አል ሂጅር 9

ቅጅዎች ብዛት ህዝብ እንዳይደናገር አንድና ወጥ የቁርአን ቅጅ አሰራጩ፡ ፡ የያንየዎቹ የዐረብኛ ፊደላት ነጥብና ሀረካ ስላልነበራቸዉ የቁርአን መልዕክት እንዳይዛባ ፊደላትን አንዱን ካንዱ የሚለዩ ነጠብጣቦችንና ሀረካዎችን የታቢዕ ትዉልድ ፈጠረ፡፡ ቁርአን መልዕክቱ በትክክል ይታወቅ ዘንድ ሀዲሶች ወሳኝ ሚና ስላላቸዉ ከታቢዕ ቀጥሎ ያለዉ ትዉልድ ሀዲስ የመሰብሰብና የማጣራት ተግባር አከናወነ፡፡ የተለያዩ አንጃዎች ተፈጥረዉ ሁሉም አንጃ ሀሳቡን በቁርአን ለማስደገፍ ሲሮጥ ሲያዩት ቁርአንን የምንረዳበት የተፍሲር ስልትና መርህ፣እንዲሁም ሀሳብ ከቁርአን ለማመንጨት የሚረዳ መርህ (ኡሱሉል ፊቅህ) ዘረጉ፡፡ እርስ በርስ የሚጋጩ የሚመስሉ የቁርአን መልዕክቶችን የሚያስታርቁ ኪታቦችን አዘጋጁ፡፡በጥቅሉ ቁርአንን መጠበቅ የአላህ ዓላማ መሆኑን ‹‹እኛዉ እንጠብቀዋለን›› ከሚለዉ መልዕክት ተረድተዉ ይህን ዓላማ ለማሳካት ተጉ፡፡

ልክ እንደዚሁ ‹መወሳትህን ከፍ አደረግንልህ› ከሚለዉ መልዕክት የነብዩ ሙሀመድ ﷺ ዝና ከፍ ማለቱ የአላህ ዓላማ መሆኑን ተገንዝቦ እርሱን ለማሳካት መትጋት እንጅ እጅን አጣጥፎ መቀመጥ ትክክለኛ ግንዛቤ አይደለም፡፡ በዚህ ረገድ ከሚደረጉ ጥረቶች መካከል አንዱ የመዉሊድ መታሰቢያ ነዉ፡፡ በመዉሊድ ነብዩ ﷺ በጣም ይወደሳሉ፣ይሞገሳሉ፡፡ገድላቸዉ አብዝቶ ይተረካል፡፡ ዝናቸዉ ከፍ ይላል፡፡

‹‹ነብዩን ﷺ ለማወደስ የመዉሊድ ማዕድ ለምን አስፈለገ? ሁልየም ለምን አታወድሷቸዉም?›› ለሚለዉ የተለመደ ጥያቄ ‹‹እርሳቸዉን ሁልየም ማስታወስና ማወደስ ተገቢ ቢሆንም የሰዉ ልጅ መዘንጋት ባህሪዉ ስለሆነ አጋጣሚዎች ከዝንጋታ ያነቁታል፡፡ ዐሹራን በየዓመቱ የመጾምና የአላህን ቀናት የማሰብ አስፈላጊነት ይህ ነዉ›› የሚል የተለመደ ምላሽ ከደጋፊዎቹ ይሰጣል፡፡

የሀዲስ መረጃዎች

መረጃ አንድ፡-የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ለተወለዱባት ዕለት ልዩ አክብሮት ነበራቸዉ፡፡ በዒባዳም ያሳልፉት ነበር፡፡ አቡ ቀታዳን ዋቢ አድርገዉ ሙስሊም የዘገቡት ሀዲስ ይህንኑ ያመለክታል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ሰኞ ቀን ለምን እንደሚጾሙ ተጠይቀዉ ሲመልሱ፡- ‹‹ የተወለድኩበት ቀን ስለሆነ ነዉ›› ብለዋል፡፡[197]

ይህ ሀዲስ ሁለት ነገሮችን ያስተምራል፡

ሀ. ነብዩ ﷺ ለልደታቸዉ ቀን ትኩረት መቸራቸዉና ማላቃቸዉ፣

ለ. ዕለቱን በዒባዳ ማሳለፋቸዉ፤

የነብዩ ﷺ ልደት መታሰቢያ (መዉሊድ) እነዚህ ሁለት እሴቶች የሚንጸባረቁበት መድረክ እንጅ ሌላ አይደለም፡፡

መረጃ ሁለት፡-ቡኻሪና ሙስሊም እንደዘገቡት የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ወደመዲና ሲገቡ አይሁዶች የዐሹራን ቀን ሲጾሙ አገኟቸዉና ለምን እንደሚጾሙ ሲጠይቋቸዉ፡- ‹‹አላህ ፊርዐዉንን አስጥሞ ሙሳን ያዳነበት ቀን ስለሆነ እርሱን ለማመስገን ስንል ዕለቱን በጾም እናሳልፈዋለን›› አሏቸዉ፡፡ ነብዩም ﷺ፡- ‹‹ ለሙሳ እኛ ከናንተ ይበልጥ የተገባን ነን›› አሉና የዐሹራ ቀን እንዲጾም አዘዙ፡፡[198]

ሸይኹል ኢስላም እብንሀጀር አልዐስቀላኒ ይህን ሀዲስ *‹‹አሰሉን ሳቢት›› /ለመዉሊድ መታሰቢያ ሸሪዐዊነት ጽኑ መነሻ/* ካሉት በኋላ ሁለት መሠረታዊ ትምህርቶች እንደሚቀሰሙበት ገልጸዋል፡፡ *አነርሱም፡-*

ሀ.አላህ በአንድ የታሪክ ወቅት ጸጋዉን በመለገስ ለዋለዉ ዉለታ በየዓመቱ በልዩ ሁኔታ ማመስገን፣

ለ. ምስጋናዉ በጾምና በሌሎች ዒባዳዎች መገለጽ እንደሚችል፤ ኢማሙ ይህን ካሉ በሁዋላ፡- *‹‹ነብዩ ከመወለዳቸዉ የበለጠ ለሰዉልጅ የተሰጠዉ*

[197] ሙስሊም

[198] ቡኻሪና ሙስሊም

ጸጋ የለም›ብማለት የሚከተለዉን የቁርአን መልዕክት በዋቢነት ጠቅሰዋል፡-[199]

لَقَدْ مَنَّ اللَّهُ عَلَى الْمُؤْمِنِينَ إِذْ بَعَثَ فِيهِمْ رَسُولًا مِّنْ أَنفُسِهِمْ يَتْلُو عَلَيْهِمْ آيَاتِهِ وَيُزَكِّيهِمْ وَيُعَلِّمُهُمُ الْكِتَابَ وَالْحِكْمَةَ وَإِن كَانُوا مِن قَبْلُ لَفِي ضَلَالٍ مُّبِينٍ [٣:١٦٤]

‹‹አላህ በምእምናን ላይ ከገሳቸው የኾነን ፤በእነርሱ ላይ አንቀጾቹን የሚያነብ፣ የሚጠራቸውም መጽሐፍንና ጥበብን የሚያስተምራቸውም የኾነን መልእክተኛ በውስጣቸው በሳከ ጊዜ፤ በእርግጥ ስገሰሳቸው፡፡ እነርሱም ከዚያ በፊት በግልጽ ስህተት ውስጥ ነበረ፡፡››[200]

የሸይኹል ኢስላም እብንሀጀርን ቃል እንደወረደ ልጥቀስ፡-

فيستفاد منه فعل الشكر لله على ما منَّ به في يوم معين من إسداء نعمة أو دفع نقمة، ويعاد ذلك في نظير ذلك اليوم من كل سنة والشكر لله يحصل بأنواع العبادة كالسجود والصيام والصدقة والتلاوة ، وأي نعمة أعظم من النعمة ببروز هذا النبي نبي الرحمة- عليه السلام - في ذلك اليوم

‹‹አላህ ጸጋ በመስገስ ወይም ጉዳትን በማስወገድ ስዋስዉ ዉስታ እንደ ሱጁድ፣ጾም፣ሶደቃና ቁርአን መቅራት ባሉ ዒባዳዎች ምስጋና ማድረስና ይህ ዉስታዉ የተፈጸመበትን ቀን እየጠበቁ በየዓመቱ ምስጋናዉን መደጋገም ተገቢ መሆኑን ከዚህ ሀዲስ እንማራለን፡፡ ይህ የእዝነት ነብይ ከመወለዳቸዉ የበለጠ ምን ጸጋ አለ?››[201]

ስለዚህ በታሪክ ዉስጥ ታላቅ የአላህ ጸጋ የተከሰተባቸዉን ቀናት በየዓመቱ በዒባዳና በበጎሥራ አስቦ መዋል ከራሳቸዉ ከነብዩ የተሰጠ ትምህርት ነዉ፡፡

[199]አልሀዊ ሲልፈታዊ
[200]አስ-ዒምራን፣ 164
[201] አልሀዊ ዉስጥ የተጠቀሰ

ተቃዉሞና ምላሽ

ሸኽ ቱወይጅሪና ጓዶቻቸዉ በዚህ ሀዲስ ላይ ያነሱትን ተቃዉሞና ምላሹን እነሆ፡-

1. እብን ሀጀር ከፈትዋቸዉ መግቢያ ላይ መዉሊድን ‹‹አዲስ የመጣ ነገር /ቢድዐ/›› ማለታቸዉ መዉሊድ መሠረት አልባ መሆኑን ያመለክታል ይሉናል ቱወይጅሪ፡፡[202]

በእርግጥ ኢማም ሻፊዒ፣ኢማም እብን ሀጀር፣ኢማም ነወዊና ሌሎች ፅዉቅ ዐሊሞች ቢድዐን ‹‹ጥሩና መጥፎ›› በማለት ከሁለት እንደሚከፍሉት ቱወይጅሪና ሌሎች የሰለፊ/ዉሀቢ ዐሊሞች ያጡታል ብየ አላምንም፡፡ እብን ሀጀር መዉሊድን ከሚበረታቱ አዲስ ነገሮች ዉስጥ እንደሚፈርጁትና እንደሚደግፉት ገለጻቸዉ ያረጋግጣል፡፡ እብን ሀጀር ስለቢድዐ የሰጡትን የሚከተለዉን ትርጉም ቱወይጅሪና መሰሎቻቸዉ አላነበቡትም ለማለት እቸገራለሁ፡-

والمراد بالبدعة ما أحدث مما لا أصل له في الشريعة يدل عليه، وأما ما كان له أصل من الشرع يدل عليه فليس ببدعة شرعاً، وإن كان بدعة لغة.

‹‹ ቢድዐ ማለት ከሸሪአዉ የሚደገፍበት ምንም ዓይነት መሠረት የሌለዉ አዲስ ነገር ሁሉ ነዉ፡፡ ከሸሪዐዉ የሚደገፍበት መሠረት ያለዉ ነገርማ ከቋንቋ አኳያ ቢድዐ ቢሆንም በሸሪዐዉ ቢድዐ አይባልም፡፡››[203]

ስለዚህ እዚህ ላይ እብን ሀጀር መዉሊድን ‹ቢድዐ› ካሉት በኋላ ‹‹ከሸሪዐዉ ጽኑ መሠረት አለዉ›› በማለት መደገፋቸዉ፡ -‹‹ከቋንቋ አኳያ ቢድዐ ቢሆንም በሸሪዐዉ ቢድዐ አይባልም›› ካሉት ጽንሰ ሀሳብ ዉስጥ

[202] ቢድዐቱል ኢህቲፋል...ገጽ 19
[203] ጃሚዑል ዑሱሚ ወልሂከም

ያካተቱት መሆኑን ያመለክታል። የቱወይጅሪ ተቃዉሞ ከዚህ አኳያ ሲታይ ‹ዉሀ የሚያነሳ› አይደለም።

2. የሀዲሱ መልዕክት ይህ ቢሆን ኖሮ ሰለፎች ይተገብሩት ነበር-ሌላኛዉ ተቃዉሞ ነዉ። መዉሊድን ታሪክ ስንተነትን በኡፊሴል ደረጃ እስከኧለኛዉ ዘመን ሊዘገይ የቻለባቸዉን ሰበቦች ጠቅሰናል። ለቱወይጅሪ ጥሩ ምላሽ ይሆናሉ ብለን እናምናለን። ደግሞስ ‹ሰለፎች ያልሰሩት ነገር ቢድዐ ነዉ›› የምትለዋ ትምህርት ከየትኛዉ የቁርአን ወይም የሀዲስ ዘገባ የመነጨች ናት? ሠለፎች ይቅርና ነብዩ ﷺ ራሳቸዉ ያልሰሩት ነገር እንኳ ‹‹*ክልክል ስለሆነ አታድርጉት*›› ካላሉ በስተቀር ሀራም አይሆንም። ይህችን እዉነታ *የኡሱለል ፊቅህ* ‹ሀሁ› የሚያዉቅ ማንም ሰዉ ይረዳታል። ከሸሪዐ ምንጮች ዉስጥ ቁርአን፣ሀዲስ፣ኢጅማዕ፣ ቂያስ...እንጅ ‹የሰለፎች ሥራ› የሚል አይገኝበትም።ይህች ቃል ሀሳብን በመረጃ መደገፍ ያቃታቸዉ ሁሉ ማምለጫና ማመካኛ ሆና በስፋት ስታገለግል ትስተዋላለች።

ይህ ተቃዉሞ፡- ‹‹የጥንት ሙስሊሞች /ሰለፎች/ በጎሥራዎችን ሁሉ ሠርተዉ ጨርሰዋቸዋል።›› ከሚል የተሳሳተና ያለአግባብ የተሰራጨ አስተሳሰብም የመነጨ ነዉ። ከታሪክ እዉነታዎች ጋርም ይጣረሳል። ነብዩ ﷺ ሳይሰሯቸዉ አልፈዉ ኹለፋኡራሺዲን የሠሯቸዉ፣እነርሱ ሳይሰሯቸዉ ቀርተዉ የታቢዕ ትዉልድ ያከናወናቸዉ ወዘተ በርካታ ተግባራት እንዳሉ ከታሪክ እንማራለን። የቁርአን ታሪክ ለዚህ አባባል ጥሩ ማሳያ ነዉ። የነብዩ ﷺ ኡማ በጎ ነገሮችን በየዘመናቱ ለሰዉ ልጅ ማበርከት የሚገደዉ አይደለም። የእስልምና እዉቀቶች አደረጃጀትም ይህንኑ ያሳያሉ። የተደራጀና የተቀናጀ ፊቅህ ከኢማሞች በፊት የት ይታወቅ ነበር? የእስልምናን የህግ ፍልስፍና (ኡሱለል ፊቅህ) ያደራጁት ዑመር ወይም አቡበክር ሳይሆኑ ኢማመሻፊዒ መሆናቸዉ የሚያሳየን ብዙ ነገር አለ።

ሰለፎች ነብዩን ﷺ ይወዳሉ፤ የርሳቸዉ ወደዚህች ዓለም መምጣት ጸጋ መሆኑን ያምናሉ። እያንዳንዱ ጸጋ ለአላህ ምስጋና እንደሚያሻዉም ይገነዘባሉ። ስለዚህ በነፍስ ወከፍ ለዚህ የአላህ ጸጋ ምስጋና ላለማድረሳቸዉ መረጃ የለም። ተራዊህ ሶላት በየግል ይሰግዱ እንደነበረዉ ይህንንም በየግል አድርገዉት ሊሆን ይችላል። የመዉሊድን ታሪክ ስንጠቅስ ለናሙና ያወሳናቸዉ የሀዲስ ሊቃዉንት የነፍስ ወከፍ የመዉሊድ በዐል አከባበር ይህንኑ ይጠቁማል። ሁኔታዉ በግል ቀጥሎ ዑመር ለተራዊህ መሰብሰብን እንዳስታወሳቸዉ ንጉስ ሙዘፈር ለመዉሊድ መሰብሰብን አስታዉሷቸዉ ሊሆን ይችላል።

3. የሸኽ ቱወይጅሪ ሌላዉ ተቃዉሞ፡- ‹‹ዒባዳ ‹ተዉቂፊ›[204] ስለሆነ አንዱን በሌላዉ ላይ ቂያስ ማድረግ አይቻልም፤ ስለዚህ እብን ሀጀር ከዐሹራ ላይ መዉሊድን፣ከነብዩ የዐሹራ ጾም ሌሎች ዒባዳዎችን ቂያስ ማድረጋቸዉ ግድፈት ነዉ›› የሚል ነዉ።

በመሠረታዊ የዒባዳ አፈጻጸሞች (ዑሱለል ዒባዳት) ላይ ‹ቂያስ› እንደማይቻል ዑለሞች ይስማማሉ። በቅርንጫፍ የዒባዳ ጉዳዮች (ፉሩዐል ዒባዳት) ላይ ግን ቂያስ አይቻልም የሚሉ ወገኖች ቢኖሩም ብዙሀን ዐሊሞች እንደሚቻል ተናግረዋል።[205]የአራቱንም መዝሀቦች የፊቅህ መድብሎች ስናጠና ሁሉም ያለልዩነት በዒባዳ ላይ ቂያስን መጠቀማቸዉን እንገነዘባለን። ለምሳሌ ለሙታን ቁርአን መቅራትና ምንዳዉ እንዲደርሳቸዉ መነየት በሀዲስ በግልጽ የተነገረ ባይሆንም የሀነፍይ[206]፣ የሀንበሊ[207] እና የማሊኪ[208]መዝሀብ ምሁራን እንዲሁም

[204]አላህ ወደም መልዕክተኛዉ ባስተማረን መልኩ ብቻ መፈጸም ያስብን።

[205] ዶ/ር ዐብዱልከሪም እብን ዐሊ እብን ሙሀመድ አልነምላ፣አልጀሚዕ ሊመሳሲሊ ኡሱሊል ፊቅሂ ወተጥቢቁሀ ዐላ መዝሀቢ ራጂህ፣መክተበተ ሩሽድ፣ሪያድ፣አራተኛ እትም፣ 2002፣ገጽ 335

[206] ዘይለዒ፣ ተብይኑል ሀቃኢቅ ሸርሁ ኪንዚደቃኢቅ 2/86

[207] እብን ቁዳመህ፣ አልሙግኒ 2/425

[208] ኢማም አልቀራፊ፣አልፉሩቅ 3/192

የሻፊዒ መዝሀብ ምሁራን በከፊል[209]በሀጅ፣ በሶላትና በዚካ ላይ ቂያስ በማድረግ ፈቅደዉታል።[210]እብንልቀይም ‹‹አልሩህ›› ከተሰኘ መጽሀፋቸዉ ዉስጥ በአስሮች የሚቆጠሩ መረጃዎችን እየጠቀሱ እንደሚፈቀድ ተከራክረዋል። ሸኽ እብን ተይ ሚያህም ከ22 ያላነሱ መረጃዎችን ዘርዝረዋል። ሁለቱም ዐሊሞች የተጠቀሙት ቂያስ የተሰኘዉን መንገድ ነዉ። ስለዚህ በዚህችም ነጥብ እዉነቱ የሚያደፋዉ ወደ ኢማማችን ወደ እብን ሀጀር አቋም ነዉ።

4. ‹‹ነብዩ በጾም ነዉና ያሳለፉት እናንተስ ለምን በጾም አታሳልፉትም?››የሚል መከራከሪያም ሸኽ ቱወይጅሪ አንስተዋል። መዉሊድን አስቦ በመዋሉ ላይ ከተስሙ ከአፍቃሪ መዉሊዶች ጋር ብዙ ርቀት አብረዉ ተጉዘዋል። የቀረቻቸዉ የአፈጻጸሙ ጉዳይ ነዉ። እርሱም ቢሆን በብዙሀን ዑለሞች በተደገፈዉና ከላይ በገለጽነዉ የኢማም እብንሀጀር የቂያስ ስልት መፍትሄ ያገኛል። ከዐሹራ ላይ መዉሊድን ቂያስ በማድረጉ ጉዳይ ከተስማሙና ከተቻለ፣ከጾም ላይ ዚክርን፣ሶደቃን፣ ሶላዋትን ወዘተ ቂያስ ማድረግ የማይቻልበት ምንም ምክንያት የለም። ሁሉም ዒባዳዎች አላህን ለማመስገን ተግባር ይዉላሉና።

<u>መረጃ ሦስት</u>፡- የነብዩ ﷺ አጎት ዐባስ አቡለሀብን በህልማቸዉ አዩት። ስለሁኔታዉ ሲጠይቁት ዘወትር ሰኞ ቅጣት እንደሚቃለልለትና ይህ የሆነበት ሰበቡም ነብዩ ﷺ መወለዳቸዉን ያበሰረችዉን ሱወይባ የተባለች አገልጋዩን ነጻ ስለለቀቃት መሆኑን ገለጸ። ዐባስ ህልማቸዉን ለነብዩ ﷺ አወጉ። እርሳቸዉም በዝምታ አጸደቁት። ቡኻሪ ‹‹መዐለቅ›› በሆነ ሰነድ[211] የዘገቡት ሀዲስ ነዉ።

[209]አልነወዊ፣አል መጅሙዕ ሸርሁል ሙሀዘብ 5/286
[210] አልመዉሱዐቱል ፈቅህያ ማዳ ‹ቂራአህ›
[211]ኪታቡኒካህ ዉስጥ

አልሀፊዝ ሸምሰዲን ሙሀመድ አብንናስር አልደመሽቂ ይህን ሀዲስ ተንተርሰዉ በሰጡት አስተያየት፡- ‹‹ይህ ካፊር ነብዩﷺ በመወለዳቸዉ ተደስቶ በሰራት በጎ በሥራ ዘወትር ሰኞ ቅጣት የሚቃለልለት ከሆነ ሙእሚን ሆኖ በልደታቸዉ የተደሰተና አምነቱን እንደያዘ የሞተማ የሳቀ ደረጃ ያገኛል፡፡›› ብለዋል፡፡[212]

አልሀፊዝ ሸምሰዲን አልጀዘሪ በበኩላቸዉ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹የእሳት መሆኑ በቁርአን የተረጋገጠበት አቡለሀብ በነብዩ ልደት በመደሰቱ ይህን እድል ካገኘ በርሳቸዉ ልደት ስሚደሰትና ያቅሙን ያህል ሶደቃ ሚሰጥ ሙእሚንማ ችሩ አምላክ በችሮታዉ ጀነትን እንደሚመነዳዉ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ››[213]

በነብዩﷺ መወለድ ተደስቶ በጎ ሥራ መስራት ሙእሚንን ቀርቶ ካፊርን እንኳ ይጠቅማል፣ነዉ የዚህ ሀዲስ ጭብጥ፡፡ ሀዲሱን በመረጃነት ለሚቀበሉ ሰዎች መዉሊድ የሚፈቀድ ብቻ ሳይሆን የሚበረታታና ለጀነት የሚያበቃ ምንዳ የሚያስገኝ በጎ ተግባር ነዉ፡፡

ተቃዉሞ

ሸኽ ቱወይጅሪና ሌሎች የመዉሊድ ነቃፊዎች በዚህች ሀዲስ ዙሪያ ያነሷቸዉ ቅሬታዎችና ተቃዉሞዎች በሚከተሉት ነጥቦች ተጠቃለዋል፡-

1.ሀዲሱ ‹ሙርሰል› ነዉ፤ስለዚህ ጠንካራ መረጃ አይደለም፤

2. ‹መዉሱል› ቢሆን እንኳ በህልም የታየ ስለሆነ ሸሪዐዊ ብይን አይታነጽበትም፤

[212] አልሱዩጢ፣ሁስነል መቅሰድ ፊዐመሊል መዉሊድ፣(አልዐስዊ፣ ሀዉስል ኢህቲፋል..ገጽ 23 እንደጠቀሱት)
[213]ያስፈዉ ምንጮች

3. ዐባስ ህልሙን ያዩት ሳይሰልሙ በፊት ስለሆነ ተአማኒነቱ ያጠያይቃል፤

4. አቡ ለሀብ ሱወይባህን ነጻ የለቀቃት ነብዩ ﷺ ከተወለዱ ከዘመናት በኋላ መሆኑን አንዳንድ የታሪክ ምንጮች መግለጻቸዉ ተአማኒነት ያሳጣዋል፤

5. አቡለሀብ የነብዩ ﷺ መወለድ ብስራት በሱወይባ በኩል እንደደረሰዉና እንደተደሰተ የሚያመለክት ተአማኒ መረጃ የለም፤

6. አቡለሀብ ካፊር ነዉ፤የካፊር ሥራ ደግሞ ከአላህ ዘንድ እንደማይፈይደዉ በቁርአን[214] ተገልጿል።[215]

ምጥን ምላሽ

እነዚህን የሸኽ ቱወይጅሪና የሌሎች የሰለፊ/ዉሀቢ ልሂቃን ተቃዉሞዎች በቅደም ተከተልና በተናጠል ቀጥሎ እናያቸዋለን፦

1. ታቢዒ ሶሀባን ሳያወሳ ወይም ከነብዩ በቀጥታ ያልሰማ ሶሀባ የሚያስተላልፈዉ ዘገባ ‹መርሰል› ይባላል።[216] መርሰል ሀዲስ ቱወይጅሪ ባሉት መልኩ በደፈናዉ ወድቅ የሚደረግ (ዶዒፍ) አይደለም። ሶሂህ ሊሆን የሚችልባቸዉን አራት ሁኔታዎች ሸኽ እብን ዑሰይሚን ጠቅሰዋል።[217]ዑለሞች በዚህ አጀንዳ ዙሪያ የሰነዘሯቸዉን ሀሳቦች በአንድ ስንደምር ከሚከተሉት ማጠቃለያዎች ላይ እንደርሳለን፦

[214] አል-ፉርቃን 23
[215] ቢድዐቱል ኢህቲፋል...፤መክተበተሽሚላ ገጽ 25-26
[216] ሸኽ መሀመድ እብን ሳሊህ አል-ዑሰይሚን፤ሸርህ መንዙመተል በይቁንያህ፤ዳረ ሰርያ አሳታሚ፤2002፤ገጽ 79
[217] ያስፈዉ ምንጭ

ሀ. በቀጥታ ከነብዩ ﷺ ያልሰማ ሶሀባ የሚያስተላልፈዉ ሙርሰል ሀዲስ ተቀባይነት ያለዉ (ሶሂህ) ነዉ።[218] ይህን ዑለሞች በአንድ ድምጽ አፅድቀዋል።[219]

ለ. የታቢዕን ‹ሙርሰል› በተመለከተ ኢማም አቡሀኒፋን፣ኢማም ማሊክንና ኢማም አህመድን ጨምሮ ብዙሀን ዐሊሞች ተቀባይነት እንዳለዉ (ሶሂህ መሆኑን) አጽድቀዋል።[220]

ስለዚህ ዑርወት እብን ዙበይር ያስተላለፉትና ቡኻሪ የዘገቡት ይህ ዘገባ በብዙሀን ዑለሞች እይታ መሠረት ተቀባይነት አለዉ። ሸይኹል ኢስላም እብን ሀጀር አልዐስቀላኒ[221]፣ኢማም ሶንዐኒ[222]፣አል-ሀፊዝ አል-በይሀቂ[223]፣ ኢማም እብን ከሲር[224]፣ኢማም እብን ደይበዕ አል-ሸይባኒ[225]፣አል-ሀፊዝ አልበገዊ[226]፣ኢማም እብን ሂሻም አልሱሀይሊ[227] እና ኢማም አልዐሚሪ[228] ያሉ የሀዲስ አዋቂዎች ሀዲሱን ተቀብለዉ ሳይቃወሙ ማስተላለፋቸዉ ድጋፋቸዉን ያመለክታል። ጠንካራና ሰፊ ተቀባይነት ያለዉ ዘገባ መሆኑንም ያረጋግጣል። ሸኽ ቱወይጂሪ ይህን ጉልህ እዉነታ አድበስብሰዉ ለማለፍ መሞከራቸዉ ምሁራዊ ታማኝነታቸዉን ጥያቄ ዉስጥ ይከተዋል።

---

[218] ያስፈዉ ምንጭ
[219] ዙሀይሊ፣ኡሱል ፈቅህ፣ቅጽ 1 ገጽ 474፣
[220] ያስፈዉ ምንጭ
[221] ፈትሁል ባሪ
[222] ሙሶነፍ 7/478
[223] ደላኢሉ ኑቡዋህ
[224] አልቢዳየቱ ወኒሀያ 1/224
[225] ሀዳኢቁል አንዋር 1/134
[226] ሸርሁ ሱናህ፣9/76
[227] አልረዉዳ 5/192
[228] በህጀተል መሀፊል 1/41

በዚህ ረገድ በቱወይጅሪና በጓዶቻቸዉ የተሰጡ አስተያየቶች ‹‹የአልሀፊዞችን›› ብይን ተቃርነዉ የመጡ ስለሆኑ ከግምት ዉስጥ የሚገቡ አይደሉም፡፡ በሀዲስ ምሁራን ቋንቋ ቢያንስ ‹ሻዝ››፣ ካለበለዚያም ‹ሙንከር› ነዉ፡፡[229]

2. ህልም ስለሆነ ሸሪዐዊ ብይን አይታነጽበትም የሚለዉ ተቃዉሞም አግባብ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ይህ ተራ ህልም ሳይሆን ነብዩ ﷺ ሰምተዉ ያጸደቁት ነዉ፡፡ አሁን የምንጠቀምበት አዛን በህልም አይደል የጸደቀዉ?

3. ዐባስ ህልሙን ያዩት ሳይሰልሙ በፊት ቢሆንም ያወጉት ከሰለሙ በኋላ ስለሆነ የሙስሊም፣ለዚያዉም የሶሀባ ምስክርነት ነዉና -ሶሀቦች ሁሉ ታማኝ ናቸዉ በሚለዉ የሀዲስ ሊቃዉንት መርህ መሠረት- ተቀባይነቱ ጥያቄ ዉስጥ የሚገባ አይደለም፡፡

4. አቡ ለሀብ ሱወይባህን ነጻ የለቀቃት ነብዩ ﷺ ከተወለዱ ከዘመናት በኋላ መሆኑን አንዳንድ የታሪክ ምንጮች መግለጻቸዉም ዘገባዉን ተአማኒነት አያሳጣዉም፡፡ ምክንያቱም ይህ የቡኻሪ ዘገባ ነዉ፡፡ ሀዲስ በማጣራት አንቱ የተሰኙ ዑለሞችም ተቀብለዉታል፡፡ በሌሎች የታሪክ ምንጮች የተላለፉ ዘገባዎች የዚህን ያህል ጥንካሬ የላቸዉም፡፡ ሁለት ዘገባዎች በሚቃረኑ ጊዜ የሚጸናዉ የበለጠ ጠንካራ የሆነዉ ነዉ፡፡ ይህን እዉነታ የሀዲስ ሀሁ የሚያዉቅ ማንም ሰዉ አይስተዉም፡፡

5. አቡለሀብ የነብዩ ﷺ መወለድ ብስራት በሱወይባ በኩል እንደደረሰዉና እንደተደሰተ የሚያመለክት ተአማኒ መረጃ የለም፤የሚለዉ ተቃዉሞ የዚህን ሀዲስ ተቀባይነት ስላሳየን እዚያ ላይ ምላሽ አግኝቷል፡፡ ‹አንድ ተአማኒ ሀዲስ በሌላ ተአማኒ ሀዲስ ካልተረጋገጠ አልቀበልም› ማለት

---

[229] በታማኝነት ከርሱ የሚልቁ የሀዲስ ሊቃዉንትን ተቃርኖ የተሳሰፈ ዘገባ ‹ሻዝ›ሲሆን፣ ተአማኒዎችን ተቃርኖ የተሳሰፈ ደካማ ዘገባ ደግሞ ሙንከር ይባላል፤ አብን ዑሰይሚን፣ ሸርህ መንዙመተል በይቁንያህ ገጽ 92)

በረኸመ የእስልምና ታሪክ ማንም ብሎት የማያዉቅ የሸኽ ቱወይጅሪ ‹ቢድዐ› ሳይሆን አይቀርም።

6. ‹አቡለሀብ ካፊር ነዉ፤የካፊር ሥራ ደግሞ ከአላህ ዘንድ አይፈይደዉም› የሚለዉ ተቃዉሞም ‹ይህ ለነብዩ ክብር የተደረገ ልዩ ሁኔታ ነዉ› በሚለዉና በሌሎችም የብን ሀጀር[230]፤ የቁርጡቢና የእብን ከሲር[231]፤እንዲሁም የሌሎች ዑለሞች[232]ማብራሪያዎች ምላሽ አግኝቷል። የነብዩ ﷺ አጎት የሆኑት አቡጣሊብ ተመሳሳይ እድል እንዳገኙ የተረጋገጠ ነዉ።[233] የአቡለሀብም ጉዳይ ከዚህ የተለየ አይደለም።ቱወይጅሪ ከእብን ሀጀር ማብራሪያ ዉስጥ፡- *‹አቡለሀብ ካፊር ነዉ፤የካፊር ሥራ ደግሞ ከአላህ ዘንድ አይፈይደዉም›* የምትለዋን ክፍል ብቻ ቆርጠዉ በመጥቀስና እብን ሀጀር ለዚህ ተቃዉሞ የሰጡትን ምላሽ በማስቀረት እብን ሀጀር የተቃዉሞዉ ደጋፊ እንደሆኑ ማስመሰላቸዉ ታማኝነት የጎደለዉ ድርጊት ነዉ።[234] በዑለሞች ቋንቋ ***‹ተድሊስ›*** ይባላል። አጀንዳዉን በምሁራዊ አግባብ ከመፈተሽ ይልቅ መረጃን ወደማዛባታ ማሸቆልቆል የመረጃን ምክነት ያመለክታል። በነገራችን ላይ በሌሎች አጀንዳዎችም ላይ ተመሳሳይ ‹ተድሊስ› ሲፈጸም አስተዉያለሁ። ወደፊት በየአጋጣሚዉ እጠቅሳለሁ።

ማጠቃለያ፡- ሀሳባችንን ስንጠቀልለዉ ይህ ሀዲስ በነብዩ ﷺ ልደት መደሰት የሚያስገኘዉን መንፈሳዊ ፋይዳ ያረጋግጣል። መዉሊድ ትርጉሙ፣ዓላማዉና ይዘቱ ከዚህ ሀዲስ መልዕክት ጋር ይጣጣማል። በሀዲሱ ዙሪያ የተነሱ ተቃዉሞዎች ደካማ መሆናቸዉ ሀዲሱን ለመረጃነት ብቁ ያደርገዋል።

---

[230] ፈትሁል ባሪ ስሀዲሱ በሰጡት ማብራሪያ

[231] አልቢዳየቱ ወኒሀያ ላይ 1/224

[232] ሀዳኢቁል አንዋር ፊሲረህ 1/134፣ሸርሁሱና 9/76

[233] ቡኻሪ

[234] ቢድዐቱል ኢህቲፋል ቢልመዉሲድ፣መክተበተ ሻሚላ ገጽ 25 ይመልከቱ

<u>መረጃ አራት</u>፡-የአላህ መልዕክተኛ ﷺ የጁሙዐን ቀን ልቅና ሰበብ ሲገልጹ ፡- ‹‹አደም የተፈጠሩበት ቀን ስለሆነ ነዉ›› ብለዋል፡፡ ይህ ሀዲስ በአንደምታ፡- ‹‹ነብያት ወደዚህች ዓለም የመጡባቸዉ ቀናት የተከበሩ ናቸዉ›› የሚል መልዕክት ያስተላልፋል፡፡

ነብያት የተወለዱባቸዉ ቀናት ብቻ ሳይሆኑ ቦታዎችም ልቅና አላቸዉ፡፡ ይህን ከሚያመለክቱ ዘገባዎች መካከል አንዱን ልጥቀስ፡፡የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ቤተልሄም ዉስጥ እንዲሰግዱ ጅብሪል አዘዛቸዉ፡፡ ሁለት ረከዐ ሰገዱ፡፡ ‹‹የት እንደሰገድክ ታዉቃለህን?›› ሲልም ጠየቃቸዉ፡፡ ‹‹አላዉቅም›› አሉት፡፡ ‹‹የሰገድከዉ ዒሳ ከተወለደበት ሥፍራ ሳይ ነዉ፤ ቤተልሄም ይባላል፡፡›› አላቸዉ፡፡[235]

የዚህን ሀዲስ አስተላላፊዎች አልሀይተሚ ‹‹ሶሂህ›› ብለዋቸዋል፡፡[236] ኢማም እብን ሀጀረል ዐስቀላኒም ፈትህ ዉስጥ ጠቅሰዉታል፤ስለደረጃዉ ያሉት ነገር የለም፡፡[237]

ሁለቱ ዘገባዎች ነብዩ ﷺ ለታሪካዊ ዘመናትና ቦታዎች ይሰጡ የነበረዉን ክብር ያመለክታሉ፡፡ **ከነብዩ ﷺ መወለድ የበለጠ ታሪካዊ ዘመን፣ እርሳቸዉ ከተወለዱበት ሥፍራ የበለጠ ታሪካዊ ቦታ የለም፡፡** ይህ ግንዛቤ ለመዉሊድ አንዱ መነሻ ነዉ፡፡ መዉሊድ ነብዩ ﷺ የተወለዱበትን ቀን በበጎ ሥራ ማሰብ ነዉና፡፡

እግረመንገዴን አንድ የዘገነነኝን ነገር ላንሳ፡፡ ነብዩ ﷺ የተወለዱበት ቤት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የከብቶች መገበያያ ተደርጎ እንደነበር

235 በዛር፣አቡየዕላ፣ጦበራኒ
236 መጅሙዐ ዘዋኢድ፣1/47
237 ፈትሁልባሪ 7/199

መስማት ይሰቀጥጣል። ድርጊቱ ያመማቸዉ አስተዋዮች ባደረጉት ጥረት የመከተል ሙከረማህ ጽ/ቤት ሆነ።[238]

የእመት ኸዲጃ ቤት እና የወህዩ መዉረጃ በአሁኑ ሰአት ሸንት ቤት መደረጉን መስማት ደግሞ የበለጠ ያማል።[239]**ከነብያችን ጋር የተያያዙ የዘመንና የቦታ ቅርሶቻችንን የአሁኑ የሳዉዲ መስተዳድር እንዲህ ማጣጣሉ የሚያሳዝን ነገር ነዉ።**

እጅግ የሚያሳዝኑ እስላማዊ ቅርሶችን የማዉደም ተግባራት በሳዉዲ እየተከናወነ መሆኑ ‹ነሳኢህ...› ከተሰኘዉ መጽሀፍ ዉስጥ ከብዙ በጥቂቱ ተዘርዝሯል። ለመጽሀፉ መግቢያ የጻፉት ዶ/ር ረመዳን ቡጢ፦ ‹‹በዚህ ዘመን የሳዉዲ መስተዳድርና ዑለሞች እየፈጸሙት ከሚገኘዉ እስላማዊ ቅርሶችን የማዉደም ድርጊት ይበልጥ የሙስሊሙን ዓለም ዑለሞችበጋራ ያስከፋና ያሳዘነ ክስተት እዉን ሆኖ አያዉቅም›› በማለት ጥልቅ ሀዘናቸዉንና ቁጭታቸዉን ገልጸዋል።[240]

የመካና የመዲና አብዛኛዎቹ ቅርሶች ወድመዉ በምትካቸዉ እድሜዉ ከአሥሮች ዓመታት የማይዘለዉን የሱዑድ ቤተሰብ ልዕልና ከፍ በሚያደርጉ ምትኮች ተሞልተዋል። በ2005 ዓ.ል ለሀጅ በተጓዝኩ ጊዜ ይህን በሚገባ ለመታዘብ ችያለሁ። በወቅቱ ያየሁትንና የተሰማኝን በጉዞ ማስታወሻየ ላይ እንደሚከተለዉ ጽፌዉ ነበር፦

‹‹በተባረኩ እጆች ከታነጸዉ ካዕባ ልንደርስ ጥቂት እርምጃዎች ቀርተዉናል። ደረጃዉን ጨርሰን ብቅ ስንል ***«ባበል መሊክ»(የንጉሱ በር)*** ከፊት ለፊታችን ብቅ አለ። ንጉስ ስላችሁ የሰማዩን ማለቴ አይደለም። እርሱ ቢሆንማ ደስታዬ። የሳዉዲን ማለቴ ነዉ።

---

[238]ዩሱፍ አብን ሰይድ ሀሽም አልሪፋዒ፣ነሲሀህ ሲሲኽዋኒነ ዑለማእ ነጅድ፣ኢቅራእ አሳታሚ፣ደማስቆ፣1999፣ ገጽ 60

[239] ያስፈዉ ምንጭ

[240]ያስፈዉ ምንጭ፣ገጽ 8

የሀረም መስጊድ ትልልቅና የሚያማምሩ በሮች የተሰየሙት በንጉሳኑ ስም መሆኑ ይገርማል። ሀገሪቱ *ሂጃዝ* በሚለዉ እስላማዊ ስሟ መቆየት ሲገባት እርሱን ሰርዘዉ *ሱዑዲ* በማለት በግለሰብ ስም ጠሯት። ካዕባ ከነቢዩ አብራሂም ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ከመሆኑ አኳያ ሁሉም ነገር በርሳቸዉና በቤተሰቦቻቸዉ መሰየም ነበረበት። ትልቁ በር ኢብራሂም፣ቀጥሎ ያለዉ ሀጀር፣የወዲያኛዉ እስማዔል፣አራተኛዉ ሳራ ወዘተ መባል ነበረበት። እነርሱ ግን «ንጉስ አብደላ፣ንጉስ ፈህድ ወዘተ» እያሉ ሰየሟቸዉ። የዓለም ሙስሊሞች ወደዚያች ሀገር የሚሄዱት የነቢዩ ኢብራሂምንና የቤተሰቦቻቸዉን ገድል በማስታወስ አላህን የመታዘዝን ጥበብ ለመማር እንጅ የሳዉዲን ገዥዎች ለመተዋወቅ አይደለም። ከኋላ በኩል ያለችን ሰዎች በቅጡ የማያዩዋት በር **«ባበነቢ»** ብለዋታል ሲሉኝ በሸቀኝ...።

‹‹መካ በኢብራሂምና በቤተሰባቸው እንደተቆረቆረች ሁሉ መዲና በነቢዩ ﷺ እና በሶሐቦች ክብርና ሞገስ የተጎናጸፈች ከተማ ናት። **ከዚህ አኳያ የነቢዩ ﷺ መስጊድ በሮች፣ የከተማዋ ጎዳናዎችና መንደሮች በነቢዩ፣ በቤተሰቦቻቸውና በሶሐቦቹ ስም መሰየም ነበረባቸው። የሚያሳዝነው ግን ይህ አልሆነም። የሳኡዲ ንጉሳዊ ቤተሰብ መካ ላይ ነቢ ኢብራሂምን እና ቤተሰቦቻቸዉን እንደተቀናቀኑ ሁሉ መዲና ውስጥም ነቢዩንና ሶሐቦቻቸውን ተቀናቅነዋል። የከተማዋን ቦታዎች በስማቸው ሰይመዋል። በዚህ ብቻ ቢወሰኑ መልካም ነበር። የመስጊዱ ዋና ዋና በሮች ሙሐመድ፣ አቡበክር፣ ዑመር ተብለው መሰየም ሲገባቸው ንጉስ ፈህድ፣ ንጉስ አብደላህ፣ ምንትስ እየተባሉ ተሰይመዋል።**

ይህን ሳይ ውስጤ ተነካ። ልቤ በሐዘን ተሰበረ። ክፉኛ ከነከነኝ። የዚህ ድርጊታቸው ትርጉም ሊገባኝ አልቻለም። *ፖለቲከኞቹስ* ያሻቸውን ቢያደርጉ ላይገርም ይችላል። ዓሊሞቻቸዉ ለምን ይህን ጉዳይ በዝምታ

ተመለከቱት? **ቁርአን "ድምጻችሁን ከነቢዩ ድምጽ በላይ ከፍ አታድርጉ"[241] ሲል ሙእሚኖችን አዟል። የንጉሳኑን ስም ከነቢዩ እና ከቤተሰቦቻቸው ስም በላይ ከፍ ማድረግስ ይቻላልን?** ውስጤ እነዚህን እና መሰል ጥያቄዎችን እያብሰለሰለ ሦስት ቀናት ቆየሁ...።

‹‹በመዲና ቆይታችን የሰራነው ሌላ ነገር የንጉስ ፈህድን የቁርአን ማተሚያ ማእከል መጎብኘት ነበር። ካረፍንበት ሆቴል የተወሰነ ርቀት ላይ ይገኛል። በአለውቶብስ ተጭነን ወደዚያው ተወሰድን። በተንጣለለ ግቢ ውስጥ የሚገኝ ዘመናዊ ማተሚያ ቤት ነው። ሙሉ ማብራሪያ የሚሰጡ አስጎብኝዎች አሉ። በየዓመቱ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ቁርአኖችን እያተሙ ለዓለም እንደሚያሰራጩ ተነገረን። የሕትመት ግድፈት እንዳይኖር የሚከታተሉና የሚያርሙ 85 ያህል የቁርአን ሊቃውንት መኖራቸውንም ሰማን። በርካታ ሰራተኞች በውስጡ ይዟል። አጠቃላይ ይዘቱ አስደስቶኛል።። በስሙ ግን ቅር ተሰኝቻለሁ።**ለቁርአን ከንጉስ ፈህድ ይልቅ ዘይድ ቢን ሳቢት ይቀርባሉ፤ የነቢዩ የወህይ ጸሐፊ ስለነበሩ። አቡበክር ይቀርባሉ፤ በነቢዩ የተጻፈውን ቁርአን በአንድ ያሰባሰቡ ሰው ስለነበሩ። ዑስማን ይቀርባሉ፤በነቢዩ ተጽፎና በአቡበክር ተጠብቆ የቆየውን ቁርአን በጥንቃቄ በማባዛት ለኛ እንዲደርሰን ስላደረጉ። ኢብን መስዑድ ይቀርባሉ፤ቁርአንን በወረደበት መልኩ መቅራት እንደሚችሉ በነቢዩ ስለተመሰከረላቸው። ኢብን አባስ ይቀርባሉ፤ የቁርአንን መልእክት ከማንም በላይ የተገነዘቡ (ቱርጁማኑል ቁርአን) ስለነበሩ። ኢብን ጀሪር ጦበሪ፣ ቁርጡቢ፣ ቢን ከሲር፣ ሰይድ ቁጥብ እና ሌሎች የቁርአን ተፍሲር ዓሊሞችም ከፈህደ የተሻለ ለቁርአን ቅርበት አላቸው። ከሁሉም በላይ ነቢዩ ይቀርባሉ፤ቁርአን በቀጥታ የወረደላቸው ስብእና በመሆናቸው።** እናም ማተሚያ ቤቱን ፈህድ

[241]አልሑጁራት 2

ከማለት ይልቅ ከነዚህ ስብእናዎች በአንዱ ቢሰይሙት መልካም ነበር። ግና ንጉሳዊው ቤተሰብ በዚህ በኩል ቀልድ አያውቅም። ነብዩ፣ ሶሐቦቻቸውና ዓሊሞች በዚህች እንኳ እንዲቀናቀኑት አልፈለገም። አንዲትም ሕንጻ ብትሆን በነርሱ ስም ለመሰየም አልፈቀደም። **ንጉስ ፈህድ ማተሚያ ቤት** በማለት ስሙን ለራሱ አስቀረ።››[242]

<u>መረጃ አምስት</u>:- ኢማም ጀላሉዲን አልሱዩጢ ለመወሊድ ሸሪዐዊነት ዋቢ አድርገው ያቀረቡት ሌላው ሀዲስ የሚከተለው ነው፡-

ነብዩ ﷺ ከነብይነታቸው በኋላ ለራሳቸው ዐቂቃ[243] ማድረጋቸውን አነስን ዋቢ በማድረግ በይሀቂ ዘግበዋል።[244] ህጻን እያሉ አቡሟሊብ ዐቂቃ እንዳደረጉላቸው ስለሚታወቅ ይህኛው ልደታቸውን በማስመልከት አላህን ለማመስገንና ለተከታዮቻቸውም ይህንኑ ለማስተማር ያደረጉት እንደሆነ ይታሰባል። ስለዚህም እኛም ወንድሞችን ሰብሰበን በመጋበዝ እና መሰል ወደ አላህ የሚያቃርቡ ሥራዎችን በመሥራት ለአላህ ምስጋና ማድረሳችን የሚወደድ ነው።[245]

ይህ ሀዲስ እንደ እብን ሀጀር ባሉ ሊቃውንት ተሀይሷል።[246] ጀላሉዲን አልሱዩጢና ኢማም አልበይሀቂ በበኩላቸው እንደመረጃ በማቅረባቸው ይዘቱን እንደተቀበሉት ያመለክታል።

የይዘት መረጃዎች

‹መወሊድ በህጋዊና ሸሪዊ ተግባራት የተሞላ ስለሆነ ሸሪዐዊነቱ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም› የሚል የይዘት መረጃም ይቀርባል።

---

[242] ካልታተመ የግል ማስታወሻ የተወሰደ

[243] ልጅ ስለተወለደ እንስሳ አርዶና ደግሶ ሰዎችን መጋበዝ ዐቂቃ ይባላል። በእስልምና ሱና ተደርጓል፤

[244] ሱነን አልበይሀቂ፣ ኪታቡ ዳሀያ

[245] አልሱዩጢ፣ ሁስነል መቅሰድ ፊዐመሊል መዉሊድ

[246] ፈትሁልባሪ 9/595

የመዉሊድ አበይት ክንዉኖችንና ሸሪዐዊ መደገፊያቸዉን ቀጥሎ እናያለን፡-

1. በመዉሊድ አላህ በብዛት ይወሳል። እርሱን የሚያወድሱ ዚክሮች ይደጋገማሉ። ዚክር ማብዛት ደግሞ በሸሪዐዉ የሚበረታታ ተግባር ነዉ። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

الَّذِينَ آمَنُوا وَتَطْمَئِنُّ قُلُوبُهُم بِذِكْرِ اللَّهِ ۗ أَلَا بِذِكْرِ اللَّهِ تَطْمَئِنُّ الْقُلُوبُ [١٣:٢٨]

‹‹(እነሱም) እነዚያ ያመኑ ልቦቻቸዉም አላህን በማዉሳት የሚረኩ ናቸዉ።ንቁ! አላህን በማዉሳት ልቦች ይረካሉ።››[247]

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا اذْكُرُوا اللَّهَ ذِكْرًا كَثِيرًا [٣٣:٤١]

‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ብዙ ማዉሳት ንአዉሱት።››[248]

وَاذْكُر رَّبَّكَ كَثِيرًا وَسَبِّحْ بِالْعَشِيِّ وَالْإِبْكَارِ [٣:٤١]

‹‹ጌታህንም በብዙ አዉሳ።በማታና በጧትም አወድሰዉ» አለዉ።››[249]

وَاذْكُرِ اسْمَ رَبِّكَ وَتَبَتَّلْ إِلَيْهِ تَبْتِيلًا [٧٣:٨]

‹‹የጌታህንም ስም አዉሳ፤ወደእርሱም (መግገዛት) መቁረጥን ተቁረጥ።››[250]

وَاذْكُرِ اسْمَ رَبِّكَ بُكْرَةً وَأَصِيلًا [٧٦:٢٥]

‹‹የጌታህንም ስም በጧትና ከቀትር በላይ አዉሳ።››[251]

---

247 አልረዕድ 28
248 አልአህዛብ 41፣አልጁሙዐ 10
249 አስሚምራን 41
250 አልሙዘሚል 8
251 አልኢንሳን 25

2. የመዉሊድ ሌላኛዉ ዋነኛ ተግባር በነብዩﷺ ላይ በብዛት ሶለዋት ማዉረድ ነዉ። እርሱን በተመለከተ አላህ እንዲህ ሲል አሏል፡-

إِنَّ اللَّهَ وَمَلَائِكَتَهُ يُصَلُّونَ عَلَى النَّبِيِّ يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا صَلُّوا عَلَيْهِ وَسَلِّمُوا تَسْلِيمًا [٣٣:٥٦]

‹‹አላህና መላእክቱ በነቢዩ ላይ የአክብሮት እዝነትን ያወርዳሉ። እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በእርሱ ላይ የአክብሮት እዝነትን አውርዱ።የማክበርንም ሰላምታ ሰላም በሉ።››[252]

3. በመዉሊድ መታሰቢያ እንስሳ ታርዶ ድሆች እንዲመገቡት ይደረጋል፡ ፡ ድሆችን መመገብ እጅግ የተወደደ ተግባር ነዉ። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

وَيُطْعِمُونَ الطَّعَامَ عَلَىٰ حُبِّهِ مِسْكِينًا وَيَتِيمًا وَأَسِيرًا إِنَّمَا نُطْعِمُكُمْ لِوَجْهِ اللَّهِ لَا نُرِيدُ مِنكُمْ جَزَاءً وَلَا شُكُورًا

‹‹ምግብንም ከመዉደዳቸዉ ጋር ለድኻ፣ ለየቲምም፣ለምርኮኛም ለእስረኛም ያበላሉ።ምናበላችሁ ለአላህ ውዴታ ብቻ ነው።ከእናንተ ዋጋንም ማመስገንንም አንፈልግም (ይላሉም)።››[253]

4.ነብዩንﷺ አብዝቶ ማዉሳት፣ማወደስ፣እርሳቸዉን ለመከተል የገቡትን ቃል ማደስ፣የርሳቸዉን፣የሶሀቦችንና የሌሎችና ደጋግ ሰዎች ታሪክ እያወሱ መመሰጥ የመዉሊድ ክንዉኖች አካል ሲሆኑ ሁሉም ሸሪዐዊ ተግባራት ናቸዉ። የከፊሎቹን መረጃ ከአሁን በፊት አይተናል።

መዉሊድ ከይዘት አንጻር እንከን የሌለበት መሆኑ ለሸሪዐዊነቱ ተጨማሪ መረጃ ነዉ።

[252] አልአህዛብ 56
[253] አልኢንሳን 8-9

የኢጅማዕ መነሻ

ለእጅቲሀድ ብቁ የሆኑ የአንድ ዘመን ዑለሞች በአንድ አጀንዳ ላይ የጋራ አቋም መያዛቸዉ ኢጅማዕ እንደሚሰኝ ከአሁን ቀደም መግለጼ ይታወሳል። ኢጅማዕ ሁለት ዓይነት ነዉ፦

1.**‹ኢጅማዑን ሶሪህ›**-በግልጽ የተነገረ ኢጅማዕ፣ለምርምር ብቁ የሆኑ ዐሊሞች በአንድ ጉዳይ ላይ በግልጽ አቋማቸዉን ሲያሳዉቁና ሲስማሙ፣

2. **‹ኢጅማዕ ሱኩቲ›**-አንዱ ወይም ከፊሎቹ አቋማቸዉን ገልጸዉ ሌሎቹ ሳይቃወሙ ሲቀሩ ወይም በዝምታ ሲስማሙ፤[254]

በመረጃነት ጥንክርና የመጀመሪያዉ ይበልጣል። መረጃ (ሁጃ) እንደሆነ ብዙሀን ዑለሞች ተናግረዋል። ሁለተኛዉ ጥንካሬዉ ሰሳ ያለ ሲሆን መረጃ በመሆኑ ላይ ዑለሞች በሀሳብ ተለያይተዋል።[255]

በመዉሊድ ጉዳይ ንጉስ ሙዘፈር መዉሊድን በኦፊሴል በጀመረበት ጊዜ የነበሩ ዕዉቅ ዐሊሞች ስለደገፉትና ስላበረታቱት፣ከዝግጅቱ ላይም ስለታደሙና የመዉሊድ ኪታብ ስለጻፉለት[256]፣መዉሊድ በሙስሊሙ ዓለም በስፋት ስለተተገበረ፣ እንዲሁም እስከ እብን ተይሚያህ ዘመን ድረስ የመዉሊድ ተቃዋሚ ስላልነበር የዑለሞች አጠቃላይ ይሁንታ የተቸረዉ ይመስላል።

ሸኽ እብን ተይሚያህም ቢሆን ያነሱት ሀሳብ ወደ ተቃዉሞ ደረጃ ከፍ የሚል አይደለም። ***‹‹እቅቲዳዉ ሲራጦል ሙስተቂም››*** ከተሰኘዉ ኪታባቸዉ ዉስጥ ‹‹መዉሊድ የሚያወጡ ሰዎች አንድም ከክርስቲያኖች ጋር ስመመሳሰል፣አስበስዚያም ለነብዩ ፍቅር ነይተዉ የነብዩን ልደት ሲያስቡ ይችላሉ›› ካሉ በኋላ ‹‹ለነብዩ ስላላቸዉ ፍቅር በድርጊታቸዉ አጅር (ምንዳ)

[254] ኢማም አልገዛሊ፣አልሙስተስፋ፣ 1/121፣ ዙሀይሊ፣ኡሱሉል ፈቅህ፣ ቅጽ 1፣ገጽ 552
[255]ዙሀይሊ፣ኡሱሉል ፈቅህ፣ ቅጽ 1፣ገጽ 552-558ይመልከቱ
[256]እብን ከሲር፣ አልቢዳየቱ ወኒሀያ 13/131 ፣አልሱዩጢ፣አልሀዊ 1/189-190

ያገኛሉ›› ሲሉ ይደመድማሉ።[257] ይህ ሀሳብ ጠንካራ ተቃዉሞን አያሳይም። እንዲያዉም ወደ ድጋፍ ይጠጋል። አንዳች የቸገራቸዉ ነገር እንዳለ ይጠቁማል። ይህ የእብን ተይሚያህ ለዛባ አቋም ደጋፊዎቻቸዉን ክፉኛ አስቆጥቷል። ሸኽ ሳልሀ እብን አል-ዑሰይሚንና ሸኽ ሙሀመደል ፈቂ ለተጠቀሰዉ መጽሀፍ በጋራ ባዘጋጁት የግርጌ ማስታወሻ ሸኽ እብን ተይሚያህን ስለዚህ ሀሳባቸዉ ክፉኛ ነቅፈዋቸዋል።[258]

በእርግጥ መዉሊድን ነብዩን ﷺ ለማሰብ እንጅ ክክርስቲያኖች ጋር ለመመሳሰል ነይቶ የሚያወጣ ይኖራል ተብሎ ስለማይታሰብ ቀሪዉ የእብን ተይሚያህ ገለጻ ከተቃዉሞ የሚፈረጅ አይደለም። ከርሳቸዉ በፊት የነበሩ ዑለሞችን ሀሳቦች በማብጠልጠል የሚታወቁት እብን ተይሚያህ በመዉሊድ ላይ እንዲህ የተሰላሰለ አቋም እንዲይዙ ያስገደዳቸዉ በሸሪዐዊነቱ ዙሪያ የቀረቡ መረጃዎች ጥንካሬና ከእስልምና መንፈስ ጋር መጋጨቱን የሚያሳላ ሁነኛ ምልክት ስለማግኘታቸዉ እርግጠኛ አለመሆናቸዉ ይመስለኛል። ይህን ከተረዳን ሸኽ ፈዉዛን፡-‹‹ ***እብን ተይሚያህ መዉሊድን አዉግዘዉ ጽፈዋል***›› በማለት በጥቅሉ መናገራቸዉ[259] ስህተት መሆኑ ይገባናል። ሸኽ ፈዉዛን እንዲህ በማለት ***ኢማም እብንል ሀጅን (እስክ 737 ሂጅሪ)*** ከተቃዋሚዎች ጎራ መፈረጃቸዉ ደግሞ ያስገርማል፡-

فممن أنكر الاحتفال بهذه المناسبة شيخ الإسلام ابن تيمية في "اقتضاء الصراط المستقيم"، والإمام الشاطبي في "الاعتصام"، وابن الحاج في "المدخل"

[257]እብን ተይሚያህ፣ እቅቲዳእ ሲራጠል ሙስተቂም ሙኻለፈተ አስሀቢል ጀሂም፣አልቅሳ አሳታሚ፣ ኢትዮጵያ፣የህትመት ዘመኑ ያልተጠቀሰ፣ገጽ 401

[258]ያስፈዉ ምንጭ፣ገጽ 401 የግርጌ ማስታወሻ ቁ.1 እና ገጽ 403፣የግርጌ ማስታወሻ ቁ.1

[259] ፈዉዛን፣ሁክመል ኢህቲፋል ቢዚክራ መዉሲዲ ነቢዊ፣መክተበተ ሻሚላ፣ቂስመል ዐቂዳ፣ገጽ 4

‹‹ሸይኽል ኢስላም እብን ተይሚያህ ‹ኢቅቲዳኡ ሲራጠል ሙስተቂም› በተባለ መጽሀፋቸዉ፣ ኢማም ሻጢቢ ‹አልኢዕቲሳም› በተባለ መጽሀፋቸዉ፣እብንል ሀጅ ‹አልመዶኽል› በተባለ መጽሀፋቸዉ...መዉሊድን ነቅፈዉ ከዳፉ ዑለሞች መካከል ናቸዉ።።››[260]

እብንል ሀጅ መዉሊድን ፈጽሞ አልነቀፉም። የነቀፉት በመዉሊድ ወር የወሩን ክብር ጥሶ መጥፎ ተግባር መሥራትን ብቻ ነዉ። በመሆኑምሸኽ ፈዉዛን ለአባባላቸዉ አንዲት ፊደል መረጃ ማቅረብ አይችሉም።የእብንል ሀጅን አባባል፣ለኛም ለሸኽ ፈዉዛንም ጠብቀዉ ካቆዩልን ዐሊም ከጀላሉዲን አልሱዩጢ ኪታብ በቀጥታ ልጥቀስ። ኢማም እብንል ሀጅ በወሩ ዉሥጥ ሰዎች በዒባዳ ስም የሚሰሩትን በጎ ያልሆነ ሥራ ከጠቃቀሱ በኋላ ይበልጥ ተገቢ የሆነዉን አቅጣጫ እንዲህ በማለት አሳወቁ፡-

وكان يجب أن يزاد فيه من العبادة والخير شكرا للمولى على ما أولانا به من هذه النعم العظيمة، وإن كان النبي صلى الله عليه وسلم لم يزد فيه على غيره من الشهور شيئا من العبادات، وما ذاك إلا لرحمته صلى الله عليه وسلم لأمته ورفقه بهم، لأنه عليه الصلاة والسلام كان يترك العمل خشية أن يفرض على أمته رحمة منه بهم، لكن أشار عليه السلام إلى فضيلة هذا الشهر العظيم...

‹‹አላህ ለሰገሰዉ ታላቅ ጸጋ እርሱን ለማመስገን ሲባል በዚህ ወር ዒባዳ መጨመር ይገባ ነበር። ነብዩ ከሌላዉ ወር በተለየ ሁኔታ በዚህ ወር ዒባዳ ያልጨመሩት ስተከታዮቻቸዉ በማዘን ነዉ። ግዴታ እንዳይሆኑ በመስጋት በጎ ተግባራትን የመተዉ ልምድ ነበራቸዉ። ሆኖም የዚህን ወር ልቅና ጠቁመዋል።።››[261]

---

[260] ያለፈዉ ምንጭ

[261] ሁስነል መቅሰድ ፊዐመሊል መዉሊድ

እብንል ሀጅ ይህን ከጻፉ በኋላ የወሩን ክብር የሚያሳሉ መረጃዎችን ደረደሩ። ከዚያም የሚከተለዉን ማጠቃለያ ሰጡ፡-

فعلى هذا تعظيم هذا الشهر الشريف إنما يكون بزيادة الأعمالالزاكيات فيه والصدقات إلى غير ذلك من القربات، فمن عجز عن ذلك فأقل أحواله أن يجتنب ما يحرم عليه ويسكن له تعظيما لهذا الشهر الشريف

‹‹ይህም በመሆኑ ይህን ታሳቅ ወር የማክበሩ ሂደት መከናወን ያለበት በሶደቃና ሌሎች በጎ ተግባራትን በመፈጸም ሲሆን ይገባል። ይህን ማድረግ የተሳነዉ ቢያንስ ከሀራም በመራቅ ለወሩ ተገቢዉን አክብሮት ይስጥ።››[262]

<u>ስለዚህ ኢማም እብንል ሀጅ የመዉሊድ ደጋፊ ብቻ ሳይሆን በመልካም ሥራ እንዲታሰብ የሚያበረታቱ ዐሊም ናቸዉ።</u> **<u>ሸኽ ፈዉዛን ይህን እያወቁና እየተረዱ እብንል ሀጅን ከተቃዋሚዎች ጎራ መፈረጃቸዉ ባጋጣሚ የተከሰተ ስህተት ብቻ አይመስለኝም። በሀዲስ ሊቃዉንት ቋንቋ ድርጊታቸዉ ‹ተድሊስ› /መረጃን ሆነ ብሎ ማዛባት/ ይባላል። አንድ ሰዉ ይህን ድርጊት በህይወቱ አንድ ጊዜ ሲፈጽም ከታየ ከታማኝነት ጎራ ወዲያዉኑ ይወጣል። ሸኽ ፈዉዛን በዚህች መረጃ መሠረት ‹‹ሙደሊስ›› ሆነዋል</u>።**

እብን ተይሚያህን ከመዉሊድ ተቃዋሚዎች ወይም ደጋፊዎች ጎራ መመደብ እንደሚያስቸግርና ለሁለቱም መነሻ የሚሆን ፈትዋ ማስተላለፋቸዉን አብራርቼ ነበር። መዉሊድን የመደገፍ አዝማሚያ ያለዉን ቃላቸዉን በመግለጽ የሸኽ ፈዉዛን ድምዳሜ ምን ያህል ስህተት እንደሆነ ላሳይ፡-

[262] ያስፈዉ ምንጭ

فتعظيم المولد واتخاذه موسماً قد يفعله بعض الناس ويكون له فيه أجر عظيم؛ لحسن قصده وتعظيمه لرسول الله – صلى الله عليه وسلم

‹‹መዉሊድን ማክበርና መታሰቢያ አድርጎ መያዝ በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ የሚተገበር ሲሆን ስለመልካም ንያቸዉና ነብዩን በማላቃቸዉ ታላቅ ምንዳ ሲያገኙበት ይችላሉ...::››[263]

ኒያን በተመለከተ ሸሪዐዉ የሚከተሉት አቋሞች አሉት፡-

1.ኒያ ለዒባዳ አስፈላጊ ነዉ፤ያለንያ የሚደረግ ዒባዳ ከንቱ ነዉ::

2. የተፈቀደ (መ-ባህ) ነገር በመልካም ኒያ ምንዳ የሚያስገኝ ድርጊት ይሆናል፣

3. <u>**በመሠረቱ ሀጢአት የሆነ ነገር በበጎ ንያ ወደመልካምነት እንደማይቀየርና ምንዳም እንደማያስገኝ ዑለሞች ተስማምተዋል**</u>::[264] ለምሳሌ መስጊድ ለመሥራት ነይቶ የሰረቀ ድርጊቱ ሀጢአት ነዉ:: ኒያዉ መልካም ስለሆነ ተብሎ ሐጢአትነቱ አይቀርለትም:: ነብዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹አላህ መልካም ነዉ:: መልካምን እንጅ አይቀበልም::››[265]

‹‹አላህ ወንጀልን በመልካም ሥራ እንጅ በወንጀል አያብስም፤ቆሻሻ ቆሻሻን አያጸዳምና::››[266]

ይህን የሸሪዐዉን መርህ ከሸኸ እብን ተይሚየህ አቋም ጋር ስንደምረዉ ሰዉየዉ የመዉሊድ ደጋፊ ይሆናሉ:: ምክንያቱም ሀጢአት የሆነ ነገር በመልካም ንያ ምንዳ እንደማያስገኝ ያዉቃሉና መዉሊድ ምንዳ ያስገኛል

[263]አብን ተይሚያህ፣ አቅቲዳአ ሲራጠል ሙስተቂም ሙኻስፈተ አስሀቢል ጀሂም፣አልቅሳ አሳታሚ፣ ሲትዮጵያ፣የህትመት ዘመኑ ያልተጠቀሰ፣ገጽ 401

[264] አል ቀረዳዊ፣ኒያና ኢኽላስ፣ገጽ 31

[265]ሙስሊም

[266] አህመድ

ካሉ፣በመሠረቱ ሀጢአት አይደለም ወይም የተፈቀደ ነዉ ማለታቸዉ ነዉ። **በመሆኑም ሸኽ ፈዉዛን ይህችን የእብን ተይሚያህ አቋም አድበስብሰዉ ሙሉ በሙሉ ተቃዋሚ በማስመሰል ማቅረባቸዉ ያለ ጥርጥር ‹ተድሊስ› ይሆናል።**

ወደ ታሪክ ቅኝታችን ስንመለስ ከእብን ተይሚያህ ህልፈት በኋላ ብዙም ሳይቆይ በዒልመ- ሰማይ ላይ የደመቁት እብን ሀጀረል ዐስቀላኒበእብን ተይሚያህ ገርበብ ብሎ የተከፈተዉን የመዉሊድ የቅሬታ በር በምሁራዊ አግባብና በጥበብ መልሰዉ ዘጉት።

ቀጥሎ ኢማም ሻጢቢ አል ***ኢዕቲሳም*** በተሰኘ ኪታባቸዉ ስለቢድዐ ትንተና ሲሰጡ እግረ መንገዳቸዉን መዉሊድን አንስተዉ የተቃዎሞ አዝማሚያ አሳዩ።[267] ዋነኛ መደገፊያቸዉ ***‹ቢድዐ ኢዳፍያ›*** በማለት የሰየሙት ጽንሰ ሀሳብ ሲሆን፣ ይህን ጽንሰ ሀሳብ በመፍጠርና በማሰራጨት የመጀመሪያዉ ሰዉ ይመስሉኛል። ይህ ጽንሰ ሀሳባቸዉ በተለይና መጽሀፋቸዉ ባጠቃላይ ከብዙሀን ዑለሞች የቢድዐ ግንዛቤ ያፈነገጠ በመሆኑ ከነቀፌታ የጸዳ አይደለም። በመጽሀፉ ዙሪያ ጥልቅ ጥናት ያደረጉ ዐሊሞች የሰዉየዉን ባለ ረዥም ትንፋሽነትና የገለጻ ክህሎት አድንቀዉ አፈንጋጭ ይዘቱን ሀይሰዋል።የሁለቱን ላስፍር። ሸኽ ሰከንደሪ አልበራድ እንዲህ በማለት ተችተዉታል፡-

‹‹የሻጢቢ ኢዕቲሳም ኪታብ ከአንዳንድ ሥፍራ ላይ አስቅጥ ደንዛዛል፤በሌላሥፍራ ደግሞ ሀሳብ ያስሸግባብ ያሳጥራል። ጸሀፊዉ የምናብ ጉዞ (ኺያል) ያበዛል። አጀንዳዎችን የማበጠር (ተህቂቅ) ክህሎቱ ደካማ ነዉ። የቋንቋ ዉበት የሚያማልስዉና በምርምር መስክ ልምድ የሌለዉ ሰዉ ግን በቀላሉ ይታለልበታል።››[268]

---

[267]ሻጢቢ፣አል አስዕቲሳም፣መክተበተ ሻሚላ፣ቂስመል ሉሱል ወልቀዋሚድ፣ ገጽ 247ና 330

[268]ዶ/ር ሚዘት ዐሊ ዐጥያህ፣አልቢድዐቱ ተህዲዱሀ ወመዉቂፊል ኢስላሚ ሚንሀ፣ ቤይሩተረ፣ዳሩል ኪታብ አልዐረቢ፣1980፣ገጽ 9

ዶ/ር ዒዘት ዐሊ ዐጥያህ በበኩላቸዉ እንዲህ ተችተዉታል፡-

‹‹መጽሀፉ ረዥምና የጸሀፊዉን ትዕግስት የሚመሰክር ቢሆንም ድግግሞሽ፣ መንዛዛት፣መጣረስና መምታታት ጎልቶ ይስተዋልበታል፡፡ የጸሀፊዉ የትንተና ችሎታና መሳጭ አቀራረብ ይህን ነዉሩን ሲሸፍንበት አልቻለም፡፡›[269]

በጥቅሉ ኢማም ሻጢቢ ስለመዉሊድ ራሱን የቻለ መጽሀፍ ስላልጻፉ የአቋማቸዉን ሌሎች መደገፊያዎች ለማወቅ አዳጋች ሲሆን፣አል-ኢዕቲሳም ከተባለዉ ኪታባቸዉ ዉስጥ የጠቀሱት የ‹ቢድዐ ኢዳፍያ› ጽንሰ ሀሳብ አከራካሪና ክፉኛ የተሀየሰ ነዉ፡፡ ወደፊት እንከኑን በጥቂቱ በምሳሌ ለማሳየት እሞክራለሁ፡፡ ስለቢድዐ በጻፍኩት ራሱን የቻለ መጽሀፍ ደግሞ በስፋት እመለስበታለሁ፡፡

የተወሰኑ አሥርት ዓመታት ቆይቶ ሸኽ ታጀዲን ዑመር እብን ዐሊ አለከሚ ሰከንደሪ ወይም ***አልፋኪሀኒ*** በመባል የሚታወቁት የኋለኛዉ ዘመን የማሊኪ መዝሀብ አዋቂ ***‹‹አልመዉሩድ ፊል ከላሚ ዐለል መዉሊድ››*** የተሰኘ መዉሊድን የሚተች መጽሀፍ ሲጽፉ ***አልሀፊዝ ጀላሉዲን አልሱዩጢ***(849-911 ሂጅሪያ) ***‹‹ሁስኑል መቅሰድ ፊዐመሊል መዉሊድ››*** የሚል ኪታብ በመጻፍ ለአልፋኪሀኒ ትችቶች በቂ ምላሽ ሰጡና ዉሀዉን ወደ ቦዩ መለሱት፡፡ አልሱዩጢ ልክ እንደ እብንል ሀጅ ሁሉ የአልፋኪሀኒን ሂስም ከራሳቸዉ መጽሀፍ ጋር አብረዉ በማሳተም አንባብያን ሁለቱንም እይታዎች ጎን ለጎን በማየት የራሱን የህሊና ፍርድ እንዲሰጥ ትተዉት ነበር፡፡ የአልፋኪሀኒና የእብንል ሀጅ ሂስም ሳይጠፉ ተጠብቀዉ እንዲቆዩ አድርገዋል፡፡ የሻጢቢ የተቃዉሞ አዝማሚያም ጠንካራ ባይሆንም በዚህ የሱዩጢ ማብራሪያ ከበቂ በላይ ምላሽ አግኝቶ ታርሟል፡፡

አሁን አሁን አንዳንዶች የሱዩጢን ምላሽ በመተዉ የአልፋኪሀኒንና የእብንል ሀጅን ሥራዎች ብቻ ከሱዩጢ መጽሀፍ ነጥለዉ እያወጡ

[269] ያስፈዉ ምንጭ

በማሳተም፣ተቃዉሞና ምላሽ ያላስተናገደ ሥራ በማስመሰል ሸፍጥ ሲፈጽሙ ማየት ያሳዝናል። ለምሳሌ በሳዉዲ አረብያ ሪያድ ዉስጥ የሚገኘዉ ***ዳረል ዐሲማ*** አሳታሚ ድርጅት እንደፈረንጆች አቆጣጠር በ1997 ***‹‹ረሳኢሉን ፊሁክሚ አልኢህቲፋል ቢል መዉሊደ ነበዊ››*** በሚል ርዕስ ከሌሎች የሳዉዲ መሻኢኾች ስራዎች ጋር አዳብሎና የጀላሉዲን አልሱዩጢን ምላሽ ነጥሎ አስቀርቶ የአልፋኪሀኒን ሥራ -የተገኘበትን ምንጭና መተሀየሱን ሳይጠቅስ- አሳትሞታል።

በእርግጥ እንዲህ ዓይነት *የእዉቀት ሸፍጦች* ፍትሀዊና ምሁራዊ ዉይይትን እንደጦር በሚፈሩ ወገኖች ዘንድ በስፋት የተለመደነዉ። ከመጽሀፍ ዉስጥ ሀሳብ ቆርጦ ማስቀረት፣ርዕስ መቀየር፣የተሳሳተ ፅትም ማተም ወዘተ ይጠቀሳሉ። ለምሳሌ ከሸኽ እብን ተይሚያህ ***መጅሙዐል ፈታዋ*** ዉስጥ ስለሱፍያ የሚተነትነዉ አሥረኛዉ ጁኡዝ ተነጥሎ ወጥቶ ቀሪ ክፍሎቹ እየታተሙ ይገኛሉ።[270] ሸኽ እብን ተይሚያህ ስለሱፍያ ያሰፈሩትን ድጋፍ አዘል መልዕክት ከዕይታ ለማራቅ ሆነ ተብሎ የሚደረግ ጥረት ነዉ። ከኢማም አልነወዊን ***‹‹ልአዝካር››*** ኪታብ ዉስጥ ***‹‹ፈስሉን ፊዚያረቲ ቀብሪ ረሱል››*** የሚለዉንርዕሱ ***‹ፈስሉን ፊዚያረቲ መሰጅደ ረሱል..››*** በሚል ተክተዉ አትመዋል።[271]የዚህ ሌብነት ዓላማ ኢማም አልነወዊ ልክ እንደሌሎቹ ዑለሞች የነብዩን ቀብር መዘየር ሱና ነዉ ስለሚሉና ሌብነቱን የሚፈጽሙ ወገኖች ይህ ሀሳብ ስለሚጎረብጣቸዉ ነዉ። በነወዊ ሀሳብ አለመስማማት መብታቸዉ ሲሆን እርሳቸዉ ያላሉትን እንዳሉ አስመስሎ ማቅረብ ግን ዉንብድና ነዉ። ለጀላለይን የቁርአን ተፍሲር ከተጻፈዉ ***‹‹አልጀዋ››*** የተባለ ኪታብ ዉስጥ

[270]ዩሱፍ እብን ሰይድ ሀሽም ሪፋዒ፣ነሲሀህ ሲኺዋኒና ዑለማኢ ነጅድ፣ዳር ኢቅራእ፣ ደማስቆ፣1999፣ገጽ 56

[271] አል ነወዊ፣አልአዝካር ቢተህቂቅ ወብዱልቃድር አርናዉጠ ሻሚ፣ዳረል ሁዳ አሳታሚ፣ ሪያድ፣1409 ሂጅሪ፣ ገጽ 295

ለነርሱ የማይስማሟቸውን ቃላትና ጽንሰሀሳቦች በብዛት አዉጥተዋል።[272] ከሀነፍያ ዕዉቅ የፊቅህ ኪታቦች መካከል ***‹‹ሀሸየት እብን ዐቢዲን አልሻፊዒ››*** ከተሰኘዉ ኪታብ ዉስጥ ስለአላህ ወዳጆች (አዉሊያእ) እና ደጋግ ሰዎች (ሷሊሂን) የሚተነትነዉን ክፍል በሙሉ ቆርጠዉ አዉጥተዉታል።[273]

ከላይ ያቀርብኩት የመዉሊድ ተቃዉሞ ታሪክ አጭር ዳሰሳ መዉሊድን በመቃወሙ አቅጣጫ የገፉ ዐሊሞች ጥቂት መሆናቸዉንና በየዘመናቱ በዕዉቅ ዓሊሞች ምላሽ እንዳገኙ ያመለክታል። ይህን በልቦናችን ይዘን ተከታዩ የሸኽ ፈዉዛንን ድምዳሜ ስናነብ መገረማችን አይቀርም፡-

فممن أنكر الاحتفال بهذه المناسبة شيخ الإسلام ابن تيمية في "اقتضاء الصراط المستقيم"، والإمام الشاطبي في "الاعتصام"، وابن الحاج في "المدخل"،والشيخ تاج الدين علي بن عمر اللخمي ألَّف في إنكاره كتاباً مستقلاً، والشيخ محمد بشير السهسواني الهندي في كتابه "صيانة الإنسان"، والسيد محمد رشيد رضا ألَّف فيه رسالة مستقلة، والشيخ محمد بن إبراهيم آل الشيخ ألف فيه رسالة مستقلة، وسماحة الشيخ عبد العزيز بن باز، وغير هؤلاء ممن لا يزالون يكتبون في إنكار هذه البدعة كل سنة في صفحات الجرائد والمجلات، في الوقت الذي تقام فيه هذه البدعة.

‹‹ሸይኽል ኢስላም እብን ተይሚያህ ‹ኢቅቲዳኡ ሲራጠል ሙስተቂም› በተባለ መጽሀፋቸዉ፣ ኢማም ሻጢቢ ‹አልኢዕቲሳም› በተባለ መጽሀፋቸዉ፣እብንል ሀጅ ‹አልመድኽል› በተባለ መጽሀፋቸዉ...መዉሊድን ነቅፈዉ ከዳፉ ዑለሞች መካከል ናቸዉ።ሸኽታጁዲን ዐሊ እብን ዑመር ለኽሚ (ራሱን የቻለ መጽሀፍ ጽፈዋል)፣ ሸኽ ሙሀመድ ሸህ ሳዉንዲ አልሂንዲ፣ ሲያነተል ኢንሳን በተባለ ኪታባቸዉ፣

[272] የሱፍ እብን ሰይድ ሀሽም ሪፋዒ፣ነሲሀህ ሲኺዋኒና ዑለማኢ ነጅድ፣ዳር ኢቅራእ፣ ደማስቆ፣1999፣ገጽ 55

[273] ያስፈዉ ምንጭ

ሰይድ ረሽድ ሪዳ ራሱን የቻለ ኪታብ አዘጋጅተዉ፣ሸኽ ኢብራሂም አስሸኽ፣ሸኽ አብን ባዝና ሌሎችም ጽፈዋል፤አሁንም በመረጻፍ ላይ ናቸዉ።።››[274]

የሸኽ አብን ተይሚያህን፣ የአብንል ሀጅንና የኢማም ሻጢቢን ጉዳይና በሸኽ ፈዉዛን የተፈጸመዉን ‹ተድሊስ› /የመረጃ ማዛባት/ ከላይ ስላየሁት አልመለስበትም። የኢማም ረሽድ ሪዳን ግን ሸኽ ፈዉዛን እዚህችም ላይ ስልታዊ ተድሊስ /የመረጃ ማዛባት/ስለፈጸሙበት ጥቂት ብርሀን ልርጭበት።

ሸኽ ረሽድ ሪዳ ግብጻዊ ዐሊም ሲሆኑ፣ ምንም እንኳ የሸኽ ሙሀመድ ዐብዱል ወሀብ አድናቂና በንጉስ ፈይሰል ቀጥተኛ የገንዘብ ድጋፍ የሰለፊ/ዉሀቢ አስተሳሰብ በግብጾች ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረዉ ‹አልመናር› በተሰኘዉ መጽሄታቸዉ አማካይነት የታገሉና የሠሩ ከመሆናቸዉ አኳያ[275] በመዉሊድ ጉዳይ የወዳጆቻቸዉን አቋም ቢይዙ የሚገርም ባይሆንም ፈትዋቸዉ እንደተጠበቀዉ የመዉሊድ ‹ተቃዋሚ› የሚሰኙ አይደለም። ለምሳሌ በ1335 ሂጅሪያ በወርሀ ረመዳን በጻፉት ***‹‹ዚክራ አልመዉሊዲ ነበዊ››*** የተሰኘ መጣጥፋቸዉ የነአልፋኪሀኒን ተቃዉሞና የብዙሀን ዐሊሞችን መረጃ ካቀረቡ በኋላ፣ መዉሊድ በመሠረቱ በተለምዶ ‹ዒባዳ› ከሚባለዉ ክልል ዉስጥ የሚገባ ስላልሆነ የሸሪዐዉ የቢድዐ ዉግዘት እንደማይመለከተዉ ገለጹና በካይሮ አንዳንድ መዉሊዶች ላይ ስለሚፈጸሙ ግድፈቶች ካነሱ በኋላ ‹‹አሁን አሁን ግን እየቀሩ መጥተዋል›› በማለት አላህን አመሰገኑ። አንድ ወዳጃቸዉ ከጋበዟቸዉ የመዉሊድ ማዕድ ተገኝተዉ የታዘቡትን የይዘት እንክን ለባለ መዉሊዶቹ ጠቆሙ። ቀጥሎም አፈጻጸሙ ይበልጥ የተሸለ የሚሆንባቸዉን ነጥቦች ጠቃቀሱ። ከዚያም እርሳቸዉ በሚያዉቁት አካባቢ የመዉሊድ ኪታብ እና ንባቡ እንደሚረዝም በመጠቆም ማላጠር

[274]ፈዉዛን፣ሁክመል ኢህቲፋል ቢዚክራ መዉሲዲ ነበዊ፣መክተበተ ሻሚላ፣ቂስመል ወቂዳ፣ ገጽ 4

[275] ማባዕደ ሰለፊያህ...ገጽ 221

የሚቻልበትን መንገድ አመላክተዉ አጭር የመዉሊድ ኪታብ አዘጋጁ። ይህ እንዴት ሆኖ ተቃዉሞ ሊሰኝ እንደቻለ አይገባኝም። ይህን የሸኽ ረሽድ ሪዳ መጣጥፍ እብንል ዐለዊ ‹አል ኢዕላም…› ከተባለዉ ኪታባቸዉ ዉስጥ እንዳለ አስፍረዉታል።[276] እርሱን መመልከት ይቻላል። ሸኽ ፈዉዛንና ወገኖቻቸዉ‹‹ሙብተዲዕ›› እያሉ ዘወትር የሚያብጠለጥሏቸዉን ግብጻዊ ዐሊም እዚህ ላይ አምጥተዉ መሰንቀራቸዉ የተቃዋሚዎችን ቁጥር ለማበራከት ካላቸዉ ጉጉት የተነሳ ይመስላል።

የሳዉዲዉን የቀድሞ ሙፍቲዎች የሸኽ ኢብራሂምንና የሸኽ እብን ባዝን፣ የሸኽ ሙሀመድ በሽርን ጉዳይ ከሌሎች የሰለፊ/ዉሀቢ ዑለሞች ጋር በአንድነት የሚታይ ነዉ።

የሸኽ ሙሀመድ ዐብዱል ወሀብ ንቅናቄ እስከተነሳበት እስከ አስራ ስምንተኛዉ ክ/ዘመን አጋማሽ ድረስ ሁኔታዎች በዚሁ ቀጠሉ። የሸኹ እንቅስቃሴ በወቅቱ ከነበሩ የነጅድ፣የሀረሞችና የአካባቢዉ ዑለሞች ጋር የተካረረ ዉዝግብ ዉስጥ ገብቶ እንደነበር ይታወቃል። ደም እስከማፍሰስ ደርሶም ነበር። ይህ እንቅስቃሴ መዉሊድን በተመለከተ በታሪክ ያልታየ አክራሪ አቋም ያዘ። በእንቅስቃሴዉ አስተሳሰብ ላይም የአሁኑዋ ሳዉዲ አረብያና መንግስታ ተመሠረቱ። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስትና ብቸኛዉ የመንግስት ሀይማኖት እንደነበረዉ ሁሉ የሸኹ የእስልምና ግንዛቤም የመንግስት ኦፊሴላዊ ሀይማኖት ሆነ። ሌሎች የእስልምና መዝሀቦችና ዘርፎች በሂደት ተወገዱ። ሳዉዲ በተለምዶ ዉሀብያ/ሰለፍያ እየተባለ ከሚጠራዉ የሸኹ ንቅናቄ አስተሳሰቦች በስተቀር ላለማስተናገድ ወሰነች። በሳዉዲ ከፍተኛዉን የሀይማኖት ጉባኤ የሚይዙት በዚሁ አስተሳሰብ የተጠመቁት ብቻ ሆኑ። የጉባኤዉ ሊቀመንበርና የመምለካ ሙፍቲ የሸኽ ሙሀመድ ዐብዱል ወሀብ ልጆችና የልጅ ልጆች /አለ ሸኽ/

[276] አል ኢዕላም…ገጽ 181-190

ብቻ እንዲሆኑ ተደረገ፡፡ ሌላዉ ቀርቶ የሁለቱ ሀረሞች ኢማም እንኳ ከነጅድ ብቻ የሚቀጠር ሆነ፡፡[277]

ከዚህ ጊዜ አንስቶ የመዉሊድ እጣ ፈንታና በዚያች ሀገር ስለመዉሊድ የሚጻፉ ጽሁፎች አንድ ዓይነት ገጽታ ብቻ እንዲይዙ ተደረገ፡፡ በዚያች ሀገር ላይ በሀይማኖቱ መስክ ተቀባይነት ማግኘት የፈለገ፣ለምርምሩ ዳጎስ ያለ ድጋፍ የሚሻ፣ቀጣይ ስኮላርሺፕ የማግኘት ምኞት ያለዉ፣ በሰላም ለመመረቅ ያለመ...ተማሪ ወይም ምሁር በመዉሊድ፣አስማ ወሲፋትና መሰል አጀንዳዎች ላይ ከኦፊሴላዊዉ የዉሀብይ/ሰለፍይ አስተሳሰብ ቅንጣት ታክል ዝንፍ እንዲል አይፈቀድለትም፡፡ ከሸኹና ከቤተሰቦቻቸዉ ሀሳቦች ወይም የፊቅህ ምርጫዎች መካከል አንዷን እንኳ መንቀፍ ከፍተኛ ቅጣት ያስከትላል፡፡ ታዋቂዉ የሀዲስ ሊቅ ሸኽ ናስረዲን አልባኒ ***‹‹ሀቂቀቱ ዳዕዋ ሰለፍያ››*** በሚል ርዕስ ባደረጉት ንግግር የሸኽ ሙሀድ ዐብዱል ወሀብን የሀዲስ ችሎታ በማጣጣላቸዉ፣ማለትም ሸኹ የሀዲስ ዕዉቀት እንደሌላቸዉ በመግለጻቸዉ[278]ከፍተኛ ዉግዘትና መከራ አስተናግደዋል፡፡ በዚህና በሌሎች አቋሞቻቸዉ ሰበብ በ1960ዎቹ ከሳዉዲ ተባረዋል፤ በ1980ዎቹ ደግሞ እንዳይገቡ ተከልክለዋል፡፡[279]

ኢትዮጵያዊዉ የሸሪዐ ሊቅ የራያዉ ሙፍቲ ሲራጅ (እስከ 1969 ዓ.ል) ሳዉዲ ለሀጅ በሄዱበት ስለሸኹ ተጠይቀዉ የሰጡት መልስ የሸኽ አልባኒ ግምገማ ዕዉነት መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ የሆነዉ እንዲህ ነበር፡፡ ሙፍቲ ሲራጅ ሀጅን እንዳጠናቀቁ ወደሀገር ቤት ሊመለሱ ሲሉ ከዚያ የሚኖሩ የሀገር ልጆች ከመምለካ ዕዉቅ ዐሊሞች ጋር እንዲገናኙ ይጠይቋቸዋል፡፡ እርሳቸዉ ግን ሳዉዲ ዉስጥ ያለዉን የአስተሳሰብ ጫናና ሀይማኖታዊ ድባብ ስለሚያዉቁ ያመነታሉ፡፡ ያገራቸዉ ልጆች ሲማጸኗቸዉ እነርሱን

---

[277]ዩሱፍ አብን ሰይድ ሀሽም ሪፋዒ፣ነሲሀህ ሲኢኽዋኒና ዑለማኢ ነጅድ፣ዳር ኢቅራእ፣ ደማስቆ፣1999፣ገጽ 43

[278] http/audio.islamweb.net/Fulltxt.oho?audioid=4842፣ (ማበዕደሰለፍያ ገጽ 322)

[279] ማባዕደ ሰለፍያህ...ገጽ 217

ለማስደሰት ሲሉ ሀሳቡን ተቀበሉ፡፡ ከሸኽ እብንባዝ ዘንድ ወሰዷቸዉ፡፡ ያንየ የመምለካዉ ሙፍቲ ባይሆኑም ዕዉቅ ሰዉ ናቸዉ፡፡ ሁለቱ ዐሊሞች ጥቂት እንደተጨዋወቱ የራያዉ ሙፍቲ ስጋት እዉን ሆነ፡፡ ‹‹ስለ ሦስቱ ሸኾች ምን ትላለህ?›› በማለት እብንባዝ ጠየቋቸዉ፡፡ ስለእብን ተይሚያህ፣እብንልቀይምና ሙሀመድ ዐብዱልወሀብ ማለታቸዉ ነዉ፡፡ ኢትዮጵያዊዉ ሊቅ የጥያቄዉን መንፈስና አቅጣጫ ባይወዱትም መልሳቸዉ እቅጩን ነበር፡፡ የዒልም ብቃታቸዉንና አስደናቂ የግምገማ ክህሎታቸዉን የሚያሳይ ምላሽ እንዲህ በማለት ሰጡ፡-

‹‹ሸኽ እብን ተይሚያህ ከአማዉ ኢጅማዕ ያፈነገጡባቸዉ ጥቂት አጀንዳዎች ቢኖሩም እዉቀታቸዉ ጥልቅና ሰፊ ነዉ፡፡ ሸኽ እብንልቀይም በዕዉቀት ከሸኻቸዉ ከእብን ተይሚያህ ባይተናነሱም ከደረስነት ወጥተዉ ሬሳቸዉን ስመቻል አልፈቀዱም፡፡ <u>የናንተዉ ሸኽ ሙሀመድ ዐብዱል ወሀብ ግን ስዓስም ቀርቶ ስአንዲት ቀዬ እንኳ ሸኽ የመሆን ብቃት የሳቸዉም</u>፡፡››

የራያዉ ሊቅ መልስ ለሸኽ እብንባዝ የመርግ ያህል የከበደ ነበር፡፡ ‹‹አስተግፊሩላህ›› በማለት ደጋግመዉ አማተቡ፡፡ የሁለቱ ሸኾች ዉይይት ከዚህ በላይ አልቀጠለም፡፡ ተሰነባብተዉ ተለያዩ፡፡ ሙፍቲ ሲራጅን ከሸኹ ጋር ያገናኙ የሀገር ልጆች በተፈጠረዉ ሁኔታ ተደናገጡ፡፡ የሳዉዲ መስተዳድር በሙፍቲዉ ላይ ጥቃት እንዳይፈጽምባቸዉ በመስጋትም ወዲያዉኑ ወደ አስመራ ሸኟቸዉ፡፡[280]

ፕሮፌሰር ሁሴን አህመድ የሸኽ ሙሀመድ ሳኒ ሀቢብን ታሪክ በጻፉበት መጣጥፋቸዉ እንደገለጹት የኮምቦልቻዉ ዐሊም ሸኽ ሙሀመድ ታጁዲን ሀረም ዉስጥ ያስተምር የነበረን አንድ የሠለፊ/ዉሀቢ ሸኽ በጥያቄ በማስጨነቃቸዉ በፖሊስ ተይዘዉ ዘብጥያ ወርደዉ ነበር፡፡ የተፈቱት

[280] የሸሪዐ ፍ/ቤት የቀድሞዉ ፕሬዝዳንት ሸኽ ሙሀመድ ታጁዲን እንደተረኩልኝ፡፡

በሸኽ ሙሀመድ ሳኒ ሀቢብ ጥበብና ጥረት ነበር፡፡ ‹‹የአፅምሮ በሽታ አለበት›› በማለት ፈርመዉ እንዳስለቀቋቸዉ ሀጅ ወሌ ተርከዋል፡፡[281]

እንዲህ ዓይነት የአስተሳሰብና የመዝሀብ ጭቆና በሰፈነበት ሀገር ዉስጥ የተለየ ሀሳብ መጠበቅ የዋህነት ነዉ፡፡ በዚያ የዓለማችን ጥግ ስለመዉለድ የሚጻፍ ማንኛዉም ኪታብ ወይም ጥናት አንድ ዓይነት ገጽታ እንዳለዉ ከተረዳን ዘንዳ የሳዉዲዎችን አቋም በአንድ ደምረን ***‹‹የአንድ ግለሰብ ወይም ቤተሰብ እይታ››***ብንለዉና የአንድ ሰዉ አቋም አድርገን ብንወስደዉ አልተሳሳትንም፡፡

ሸኽ ሙሀመድ ዐብዱል ወሀብ ለኢጅቲሀድ ብቁ የሚያደርግ የዒልም ቁመና እንዳልነበራቸዉ የሸኽ አልባኒ፣የሙፍቲ ሲራጅና የሌሎችም ዑለሞች ምስክርነት ያመለክታል፡፡ ከሀዲስ በስተቀር ለኢጅቲሀድ አብይ መስፈርት የሆኑት የፊቅህ፣የኡሱል፣የቋንቋና ሌሎች የእዉቀት ዘርፎች በዚያች ሀገር ለረዥም ጊዜ ትኩረት ስላልተቸራቸዉ ዑለሞቻቸዉ በአብዛኛዉ ምሁራዊ አቋም ለመያዝ ከሚያስችል የዒልም እርከን ላይ የደረሱ ካለመሆናቸዉ አኳያም አቋሞቻቸዉ ከጥልቅ ምርምር የመነጩ ናቸዉ ለማለት ያዳግታል፡፡[282]

እናም ከሸኽ እብን ተይሚያህ መንታ ገጽታ ያለዉ ገለጻ ዉስጥ ከነበሩበት ማህበራዊ፣ፖለቲካዊና ሀይማኖታዊ ድባብ አኳያ ተስማሚ ሆኖ ያገኙትን የተቃዉሞ አዝማሚያ እንደወረደ የተከተሉ (ተቅሊድ) ይመስላል፡፡ ስለዚህ ከነጀላሉዲን አልሱዩጢ በኋላ መዉለድን በመቀናቀን

[281] Husen Ahmde (professor), From local to national prominence:The life and achivment of shaykh Mohamed Thanu b.Habib b.Beshir (1914-1989):Ethiopian Muslim scholar, teacher and spiritual leader,A papere orepared in advance for presentation to the 16the international conference of Ethuopian studies to be held in Trondhem-norway 2-6 Julay 2007.P.12.

[282]ማባዕደ ሰለፍያ....ገጽ 289-400 ድረስ የሰለፊ/ዉሀቢ ዑለሞች በተጠቀሱት የዕዉቀት ዘርፎች ከፍተኛ ድክመት ስላስባቸዉ ባጠቃላይ አስተሳሰቡ ላይ የተፈጠረዉን አሳሳቢ እንከን ጸሀፊዎቹ በመረጃ እያስደገፉ ጽፈዋል፡

ድምጽ ያሰማዉ ብቸኛዉ ሰዉ/ቤተሰብ/ናቸዉ ማለት እንችላለን፡፡ ለዚህ ቤተሰብ እንደ ኢማም ዛሂድ አልከዉሰሪ (እስከ 1371)[283]ያሉ እዉቅ የሀዲስ፣የፊቅህና የታሪክ ሊቃዉንት በቂ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ሆኖም የነዳጅ በሳዉዲ ምድር መገኘት ሸኽ መሀመድ ዐብዱል ወሀብን ከአንዲት ቀዬ ዳዒነት አዉጥቶ ***‹‹ሸይኹል ኢስላም››*** አደረጋቸዉ፡፡ የርሳቸዉና የልጆቻቸዉ አስተሳሰብና የፊቅህ ምርጫም በፍጥነት ወደተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች በገንዘብ ሀይል እንዲሰራጭ እድሉን ተመቻችለት፡፡ ለዚህ የተቃዉሞ አስተሳሰብ ያለፉት 30 ዓመታት ወርቃማዎች ናቸዉ ማለት ይቻላል፡፡[284] የሸኽ መሀመድ ዐብዱል ወሀብ ቤተሰብና የሱዑዲ መስተዳድር በመዉለድ ላይ እንዲህ እንዲያመርሩ ያደረጋቸዉን ፖለቲካዊ መግፍኤ ወደፊት ***‹‹የተቃዉሞዉ የጀርባ ምክንያቶች››*** በሚል ርዕስ ካሰፈርኩት ጽሁፍ ዉስጥ በመጠኑ ተመልክቸዋለሁ፡፡

ከሳዉዲ በስተቀር በአብዛኞቹ ሙስሊም ሀገሮችና ህዝቦች ዘንድ ስለመዉለድ ያለዉ እይታ አወንታዊ ነዉ፡፡ ምን አልባትም ይህ ሁሉ ተደማምሮ ከዉሀብይ/ሰለፍይ ንቅናቄ በስተቀር ሌሎች ኡለሞች በመዉለድ ላይ የያዙት አቋም **‹ኢጅማዕ ሱኩቲ›** ሊሆን፣ ከፍ ሲልም **‹‹ኢጅማዕ ሶሪህ››** ከተሰኘዉ መስክ ዉስጥ ሊጠቃለል ይችል ይሆናል፡፡

የቂያስ መነሻ

ከደጋፊ የሸሪዐ ምንጮች መካከል ዋነኛዉ ቂያስ መሆኑን ከአሁን ቀደም ተነጋግረናል፡፡ ከላይ ከጠቀስናቸዉ የቁርአንና የሀዲስ መረጃዎች መካከል ገሚሶቹ ለመዉለድ ዋቢ የሆኑት በዚህ የሸሪዐ ምንጭ ስልት አማካይነት መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

---

[283]ሙሀመድ ዛሂድ አልከዉሰሪ፣መቃላቱል ከዉሰርይ፣አልመክተበተ ተዉፊቅያህ፣ካይሮ፣ገጽ 356-370 ስለብነት ይመልከቱ፤

[284] ማባዕደ ሰለፍያ፣ገጽ 217

መሷሊሀል ሙርሰላ

ሸሪዐዉ ሊጠብቃቸዉና ሊያስጠብቃቸዉ የሚያልማቸዉ ጥቅሞች (መስለሀ) በዋነኛነት አምስት ሲሆኑ፣በቅደም ተከተል ዲን፣ነፍስ፣ዐቅል (አዕምሮ)፣ማል (ሀብትና ንብረት) እና ነስል (የዘር ጥራትና ቀጣይነት) ይባላሉ።[285]

ሸሪዐዉ በግልጽ ያልደነገገዉ ወይም ያልተቃወመዉ፣ግና ከነዚህ የሸሪዐዉ ዓላማዎች አንዱን ለማስጠበቅ፣ወይም በነዚህ መስኮች የሚመጣን ጉዳት ለመከላከል የሚያስችል ነገር ‹‹መሳሊሀል ሙርሰላ›› ይባላል።[286]ብዙሀን የፊቅህ ጠበብት እንደ አንድ የህገ ሸሪዐ (አህካም) ምንጭና መሠረት አድርገዉ ተቀብለዉታል።[287]

በዚህ ረገድ ከሚሰጡ ምሳሌዎች መካከል የቁርአን በአንድ መጠረዝና በተመሳሳይ ቅጅዎች ተባዝቶ መሠራጨት ይገኝበታል። ይህ ድርጊት ሸሪዐዉ በግልጽ ባያዘዉም ወይም ባይከለክለዉም ዲንን የመጠበቅ መገለጫ በመሆኑ ‹‹በመሳሊሀል ሙርሰላ›› መንገድ ይሁንታ አግኝቷል። እንደ ኢማመሻፊዒና እንደ ኢማም ዒዝ እብን ዐብዱ ሰላም ያሉ ሊቃዉንት ይህን መስክ ‹ቢድዐ ዋጅባ› /ግዴታ የሆነ ቢድዐ/ ከሚሉት ዘርፍ ዉስጥ መድበዉት እናገኛለን።[288]

ቢድዐ ከመሳሊሀል ሙርሰላ ጋር ስለሚምታታ ነብዩ ﷺ ሳይሰሯቸዉ ካለፉ ነገሮች መካከል የትኛዉ ቢድዐ የትኛዉ ደግሞ መሳሊሀል ሙርሰላ እንደሆነ ለመለየት የሚያስችል መስፈርት ሸኽ እብን ተይሚያህ (661-728 ሂጅሪ) እንደሚከተለዉ አስቀምጠዋል፦

---

[285] አልገዛሊ፣አልሙስተስፋ፣ 1/139-140

[286] አልሻጢቢ፣አልሙዋፈቃት፣1/39

[287]ዙሀይሊ፣2/762ሰ

[288]የቢድዐ ጽንሰ ሀሳብ ስንወያይ እናነሳዋለን

الأول: ما تركه مع وجود المقتضي لفعله في عهده صلى الله عليه وسلم، وهذا الترك يدل على أنه ليس بمصلحة ولا يجوز فعله.

‹‹ነብዩﷺ መስራት የሚያስችላቸዉ ሁኔታ ከነበረና ሆነ ብለዉ ሳይሰሩት ከቀሩ ያነገር መስለሀ እንዳልሆነና መሥራቱም እንደማይፈቀድ ያመለክታል፡፡››[289]

እብን ተይሚያ ለዚህ መርህ የዒድ ሶላት አዛንን እንደምሳሌ አቅርበዋል፡፡ ነብዩﷺ ለኢድ አዛን ማድረግ በሚችሉበት ሁኔታ ዉስጥ ነበሩ፡፡ ከልካይም አልነበረባቸዉም፡፡ ሆኖም ትተዉታል፡፡ ስለዚህ ለዒድ አዛን ማድረግ መስለሀ ሳይሆን ቢድዐ ነዉ፡፡

በሌላ በኩል እንዲሠሩት የሚያስገድዳቸዉ ወይም መስራት የማያስችላቸዉ ሁኔታ ከነበረ፣እርሳቸዉ ከሞቱ በኋላ ያ ከልካይ ሁኔታ ከተወገደ ወይም ድርጊቱን ለመፈጸም የሚያስችል አስገዳጅ ተጨባጭ ከተፈጠረ ያ ነገር መስለሀ ይሆናል፡፡ ነገለጻቸዉን እንይ፡-

والثاني: ما تركه النبي صلى الله عليه وسلم لعدم وجود ما يقتضيه، لحدوث المقتضي له بعد موته صلى الله عليه وسلم، ومثل هذا قد يكون مصلحة وقد يكون جائزاً.

‹‹ሁለተኛዉ በወቅቱ አስፈልጎቱ ባለመኖሩ የተዉትና እርሳቸዉ ከሞቱ በኋላ የተከሰተ ከሆነ መስለሀ ይሆናል፡፡››[290]

ለዚህ አባባል እንደምሳሌ ያቀረቡት የቁርአን በአንድ መጠረዝ ጉዳይ ነዉ፡፡ በነብዩﷺ ዘመን ወህይ ገና ይወርድ ስለነበርና ቁርአኑ ስላልተሟላ በአንድ መጠረዙ አላስፈለገም፡፡ እርሳቸዉ ካለፉ በኋላ ግን ይህ ከልካይ ነገር ስለተወገደ ድርጊቱ መሳሊህ ሆነ፡፡

---

[289]አልቢድዐቱል ሀሰና.. ፣ገጽ 105 /አቅቲዳኡ ሲራጦል ሙስተቂም፣ገጽ 133-135 በማሳጠር ካቀረቡት የተወሰደ)

[290]ደስፈዉ ምንጭ ገጽ 106

በእርግጥ በዚህ የእብን ተይሚያህ መርህ ዙሪያ ጠንካራ ነቀፌታዎች መሰንዘራቸዉ[291] እንዳለ ሆኖ ለመዉሊድ እንደወረደ ልንጠቀምበት እንችላለን፡፡ ይኸዉም የመዉሊድ ዋነኛ ዓላማ ነብዩንﷺ ማስታወስ ነዉና እርሳቸዉ በህይወት እያሉ አስፈላጊ አልነበረም፡፡ ካለፉ በኋላ ግን አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ በሸኽ እብን ተይይሚያህ ሁለተኛ መርህ መሠረት ቢድዐ ሳይሆን ‹መሳሊህ› ይሆናል፡፡ አልቀረዳዊን[292] ጨምሮ የዘመናችን ብዙ ዑለሞች ለመዉሊድ ይሁንታ ለመስጠት ይህን ነጥብ አብዝተዉ ተጠቅመዋል፡፡

የመሳሊሀል ሙርሰላን ጽንሰ ሀሳብ ወደያዝነዉ ርዕስ ስናመጣዉ ለመዉሊድ ከላይ የዘረዘርናቸዉ መረጃዎች እንዳሉ ሆነዉ እነርሱ ባይኖሩ እንኳ ነብዩንﷺ ከፍ በማድረግ ዲንን የመጠበቅ ሚና ስላለዉ ‹በመሳሊሀል ሙርሰላ› አግባብ በሸሪዐዉ ይሁንታ ያገኛል፡፡ ይህ እንግዲህ፡- ‹‹መረጃ ባይኖርም እንኳ›› በማለት ያቀረብነዉ ነዉ፡፡

ማጠቃለያ፡- ከላይ የቀረበዉ ማብራሪያ የመዉሊድን ሸሪዐዊነት ደግፈዉ የሚከራከሩ ዐሊሞች ዋና ዋናዎችን የሸሪዐ ምንጮች ተንተርሰዉና ተጠቅመዉ አቋማቸዉን ማደራጀታቸዉን ያመለክታል፡፡

መዉሊድ በዑለሞች ዘንድ ከጥንት እስከዛሬ ያለዉ ተቀባይነት ምን ያህል ነዉ? ቀጣዩ ርዕስ ይህን የሚዳስስ ይሆናል፡፡

---

[291] ያስፈዉ ምንጭ ገጽ 107

[292] በ23-2-2010 እና በሴሎች ጊዚያት በድረ ገጻቸዉ የሰጡት ፈትዋ

መዉሊድን በመደገፍ ኪታብ የጻፉና ፈትዋ ያስተላለፉ ዕዉቅዐሊሞች ዝርዝር በከፊል

ከጥንት እስከዛሬ በርካታ ዐሊሞች ለመዉሊድ ጽድቅ ችረዉ፣ኦፊሴላዊ መታሰቢያ ያዘጋጀዉን ንጉስ ሙዛፈርን አወድሰዉ ጽፈዋል። ከመሀከላቸዉ ***በአሥሮች የሚቆጠሩእና አል-ሀፊዝ*** ከተሰኘ የሀዲስ ዕዉቀት ደረጃ የደረሱ ናቸዉ። እዚህ ደረጃ ለመድረስ ***100 ሺህ ሀዲሶችን ከነሰነዳቸዉ በቃል ጠንቅቆ ማወቅ*** ያስፈልጋል። በአሁኑ ሰዓት በምድራችን ላይ እዚህ ደረጃ የደረሰ አንድም የሀዲስ አዋቂ ስለመኖሩ እርግጠኛ አይደለሁም። እንደ ኢማም ዛሂድ አልከዉሰሪ፣ሸኽ አልባኒና ሸኽ እብን ሲዲቅ አልጊማሪ ያሉ የሀዲስ አዋቂዎች እንኳ እዚህ ደረጃ ደርሰናል ብለዉ የሚያምኑ አይመስለኝም። ስለመድረሳቸዉም እርግጠኞች አይደለንም። የመዉሊድን የተቀባይነት ስፋት ስለሚያሳየን ከጥንቶቹም ከአሁኖቹም ቀላቅየ አዉራዎችን ቀጥሎ እጠቅሳለሁ።

1) **አል ሀፊዝ አቡሻመህ** (599-665)፡-ዕዉቅ የሀዲስና የሌሎች የሸሪዐ መስኮች ሊቅ ናቸዉ። የዕዉቁ ዐሊም ጠኢማም አልነወዊ ሸኽም ናቸዉ። መዉሊድን በመደገፍ ፈትዋ ሰጥተዋል።[293]

2) **አል-ሀፊዝ እብን ሀጀር አልዐስቀላኒ** (773-852 ሂጅሪ)፡-ሸሀቡዲን አህመድ እብን ሙሀመድ ይባላሉ። ተወልደዉ ያደጉትም ሆነ የሞቱት ግብጽ ዉስጥ ነዉ። ዕዉቅ የሀዲስ ሊቅ ናቸዉ። 150 ያህል ምትክ የማይገኝላቸዉን ኪታቦች ከትበዋል። ለቡኻሪ የሀዲስ ስብስብ እስካሁን ለይዘቱ ወደር ያልተገኘለት ‹‹***ፈትሁል ባሪ***›› የተባለ አስደናቂ ማብራሪያ (ሸርህ) አዘጋጅተዋል።[294] መዉሊድን በተመለከተ ከነብዩ ህልፈት በኋላ የተከሰተ ነገር መሆኑን ገልጸዉ፣ሆኖም

[293] አልባሚስ ዐላኢንካሪል ቢደዒ ወልሀዋዲስ፣ገጽ 23

[294] ሙዕጀሙል ሙዐሲፌን 2/20

ለሸሪዐዊነቱ ጽኑ መሠረት (አስሉን ሳቢት) የሆነ መረጃ እንዳገኙለት አብራርተዉ ጽፈዋል። መዉሊድ የሚበረታታ በጎ ሥራ መሆኑን ከገለጹ ሊቃዉንት መካከል አዉራዉ ናቸዉ። ስለመዉሊድ የሰጡት ፈትዋ ዝርዝር ‹ሁስነል መቅሰድ ፊዐመሊል መዉሊድ› ከተባለዉ የጀላሉዲን አልሱዩጢ ኪታብ ዉስጥ ይገኛል።

3) **አል-ሀፊዝ ጀላሉዲን አልሱዩጢ (849-911)** ፦ የሀዲስ፣የቁርአን፣ የታሪክና የህገ ሸሪዐ ሊቅ። በሀገራችን በስፋት የሚታወቀዉ ‹‹ጀላለይን›› የተባለ የቁርአን ተፍሲር አዘጋጆች መካከል አንዱ። አስዩጥ በትባል ከተማ ተወለዱ።ያደጉት ግን ካይሮ ዉስጥ ነዉ። የቲም ሆነዉ አደጉ። እዚያዉም ትምህርት ቀሰሙ በዘመናቸዉ በሀዲስ፣ በቁርአን ትንታኔና በዐረብኛ ቋንቋ ወደር አልነበራቸዉም። [295]መዉሊድን በተመለከተ ‹ሁስነል መቅሰድ ፊዐመሊል መዉሊድ› የተባለ ኪታብ ጽፈዋል። ለኪታቡ መጻፍ ምክንያት የሆነዉ በቅጽል ስማቸዉ **አልፋኪሀኒ** በመባል የሚታወቁ የኂለሞቹ የማሊክይ መዝሀብ ዐሊም መዉሊድን ተችተዉ መጻፋቸዉ፣ሲሆን አልሱዩጢ የኒህን ሰዉ ስህተት ለማረም የተጠቀሰዉን ኪታብ ከተቡ። የጀላሉዲን አልሱዩጢ ይህ ኪታብ በኂላ ላይ ‹አልሀዊ ሊልፈታዊ› ከተባለዉ የፈትዋ ስብስባቸዉ ዉስጥ ተካቷል።

4) **አልሀፊዝ ሸምሰዲን እብንል ጀዘሪ (751-833)፦** ዕዉቅ የሀዲስና የህገ ሸሪዐ ሊቅ ናቸዉ። በፊቅህ፣በታሪክና በተፍሲር መስኮችም ይታወቃሉ። ደማስቆ ተወልደዉ አድገዋል። ወደ ግብጽ ተመላልሰዋል። በመጨረሻ ወደ ሺራዝ ተጉዘዉ እዚያዉ ሞተዋል። [296]ጀላሉዲን አልሱዩጢ ‹ሁስነል መቅሰድ...› ዉስጥ በዋቢነት ጠቅሰዋቸዋል። ለመዉሊድ ጠንካራ ድጋፍ አላቸዉ። ‹ዑርፈተዕሪፍ ቢልመዉሊዲ ሸሪፍ› የተባለ ኪታብም መዉሊድን ደግፈዉ

[295] ሸዘራቱዘሀብ 8/51
[296] ሙዕጀሙል ሙአሊፊን 11/291

ጽፈዋል፡፡በዚህ ኪታባቸዉ ዉስጥ አቡለሀበ ሱወይባ የተባለች አገልጋዩን የነብዩንﷺ መወለድ ስለነገረችዉ ነጻ በመልቀቁ ከአላህ ዘንድ ያገኘዉን ዕድል ጠቅሰዉ፡- ‹‹በነብዩﷺ መወለድ ደስታ የተሰማዉና ያቅሙን ያህል ሶደቃ በማዉጣት ደስታዉን የገለጸ ሙስሊምማ አላህ ጀነት በማስገባት ይመነዳዋል ብዩ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡›› የሚል ማጠቃለያ ሰጥተዋል፡፡[297]

5) **አል-ሀፊዝ አቡል ፈረጅ እብንል ጀዉዚ (እስከ 597 ሂጅሪያ)**፡- የሀንበሊ መዝሀብ ሊቅ ናቸዉ፡፡ በሀዲስ ጥናት ‹አልሀፊዝ› ደረጃ ደርሰዋል፡፡ በታሪክና በህገ-ሸሪዐ አንቱታን አግኝተዋል፡፡ ***‹‹አልዐሩስ››*** የተባለ የመዉሊድ ኪታብ ጽፈዋል፡፡ ይህ ኪታባቸዉ በግብጽ ለበርካታ ጊዜ ታትሟል፡፡[298]ስለመዉሊድ ቀን ሲናገሩ፡- ‹‹የልብ ሰላም የሚገኝበትና ስዓላማ መሳካት ፈጣን ብስራት የሆነ ዕስት›› ብለዉታል፡፡[299]

6) አል-ሀፊዝ እብን ደህያ አልከለቢ (እስከ 633 ሂጅሪያ)፡- ሙሉ ስማቸዉ አቡል ኸጧብ ኡመር እብን ዐሊ እብን ሙሀመድ ይባላል፡፡ የሚታወቁት ግን እብን ደህያህ በሚለዉ ቅጽል ነዉ፡፡ ዕዉቅ የሸሪዐ ሊቅ ናቸዉ፡፡ በሀዲስ ጥናትም አልሀፊዝ፡፡ መሊክ ሙዞፈር የመዉሊድን መታሰቢያ ህዝባዊ ሲያደርገዉ ከስፍራዉ በመገኘት ደግፈዉታል፡፡ ***‹‹አልተንዊር ፊመዉሊዲል በሺሪነዚር››*** የሚል የመዉሊድ ኪታብ ጽፈዋል፡፡ በአስታንቡል ‹ባይዘድ› ቤተ መጽሀፍት ዉስጥ ቅጅዉ ይገኛል፡፡[300]

7) **አል-ሀፊዝ እብን ከሲር(759-803 ሂጅሪያ)**፡-ሙሉ ስማቸዉ ሙሀመድ እብን ኢስማኤል እብን ዑመር እብን ከሲር ሲሆን፣

---

[297] አልሱዩጢ፣ ሁስነል መቅሰድ ፊዐመሊል መዉሊድ

[298]እብንል-ዐለዊ፣አልኢዕላም...ገጽ 51

[299] አልመዋሂቡስዱንያህ፣1/27

[300] እብንል-ዐለዊ፣አልኢዕላም...ገጽ 51

መጀመሪያ በስራ ከዚያም ደማስቆ ኖረዋል። የኢማም እብን ሀጀርና የኢማም እብን ተይሚያህ ተማሪ ናቸዉ። በታሪክ፣ በሀዲስና በቁርአን ጥልቅ እዉቀታቸዉ ይታወቃሉ።[301] ከታሪክ መጽሀፋቸዉ ላይ የመዉሊድን ህዝባዊ መታሰቢያ ጀማሪ የሆነዉን ንጉስ ሙዞፈርን አድንቀዉና አሞካሽተዉ ጽፈዋል። አንድ የመዉሊድ ኪታብም አዘጋጅተዋል። መጽሀፉ በቅርቡ ዶ/ር ሰለሀዲን አልሙነጅድ በተባሉ ዐሊም ታርሞ ካይሮ ዉስጥ ለህትመት በቅቷል።[302]

8) **አልሀፊዝ አልዒራቂ (725-808)፡-** በሀዲስ ከፍተኛ ሊቅ ናቸዉ። የኢማም አቡሀሚድ አልገዛሊ ዕዉቅ ሥራ ለሆነዉ ኢህያእ ዑሉሙዲን ሀዲስ የማጣራት (ተኽሪጅ) ተግባር አከናዉነዋል። ***‹‹አልመዉሩዱል ሀና ፊልመዉሊዲ ሰና››*** የተባለ የመዉሊድ ኪታብ ጽፈዋል። የእጅ ጽሁፉ በበርሊን ይገኛል።[303]

9) **አል-ሀፊዝ እብን ናስር አልደመሽቂ (777-842 ሂጅሪያ)፡-** በሀዲስ ከፍተኛዉን እርከን ተቆናጠዋል። በዘመናቸዉ በደማስቆ የዳረል ሀዲስ ዋና ሸኽ (ቁንጮ) ነበሩ። ሦስት የመዉሊድ ኪታቦችን ጽፈዋል፡-

1.ጃሚዑል አሳር ፊመዉሊዲ ነብይል ሙኽታር፣

2. አለፍዙ ራኢቅ ፊመዉሊዲ ኸይሪል ኸላኢቅ፣

3.መዉሩዱሳዲ ፊመዉሊዲል ሀዲ፤

አቡለሀብ በነብዩ ﷺ መወለድ ተደስቶ ባሪያዉን ነጻ በመልቀቁ ዘወትር ሰኞ ቅጣቱ የሚቃለልለት የመሆኑን ታሪክ መሠረት አድርገዉ

---

301 ሙዕጀሙል ሙአሊፊን 9/59

302 እብንል-ዐለዊ፣ አልኢዕላም...ገጽ 52

303 እብንል-ዐለዊ፣ አልኢዕላም...ገጽ 52

ስለመወሊድ ልቅና በግጥም በሰጡት ድምዳሜ ‹‹በቁርአን በግልጽ የተነቀፈዉና ጀሀነም ዉስጥ ዘለዓለም እንደሚኖር የተረጋገጠበት አቡለሀብ በአንድ ጊዜ የደስታ ድርጊቱ ይህን ፅድል ካገኘ በነብዩ መወለድ ፅድሜ ልኩን ሲደሰት የኖረና በተዉሂድ የሞተ ሙስሊምማ ደረጃዉ የላቀ ነዉ።።›› ብለዋል።[304]

10) **አልሀፊዝ አልሰኽዊ (831-902 ሂጅሪያ)**፦የሀዲስና የሌሎች የሸሪዐ እዉቀቶች ሊቅ ናቸዉ።[305] ስለመወሊድ፦***‹‹አልፈኽሩልዐለዊ ፊልመወሊደ ነበዊ››*** የተባለ ኪታብ ጽፈዋል። በ1407 ሂጅሪያ ዮርዳኖስ ዉስጥ ታትሟል። [306]

11) **ኢማም እብን ሀጀር አልሀይተሚ (909- 973 ሂጅሪያ)**፦ በመካ የሻፊዕይ መዝሀብ ሙፍቲ የነበሩ፣በኛ አገር የሻፍዕይ የትምህርት መስክ ዕዉቅና አላቸዉ። ስለመወሊድ ***‹‹ኢትማሙ ኒዕመቱል ኩብራ ዐለል ዐለም ቢመወሊዲ ሰይዲ ወለዲ አደም››*** የተባለ ኪታብ ጽፈዋል። ዕዉቁ ዐሊም ሸኽ ኢብራሂም አልባጁሪ ማብራሪያ ጽፈዉላታል።

12) **ኢማም ሙላ ዐሊልቃሪ (እስከ1014 ሂ)**፦ ሸኽ ኑረዲን እብን ዐሊ ሱልጣን አልዐለዊ ይባላሉ።በፊቅህ፣በሀዲስ፣በተፍሲርና በሌሎች መስኮች ዕዉቅና አላቸዉ። ስለመወሊድ ***‹‹አልመወሩዱነዊ ፊልመወሊዲነበዊ››*** የተባለ ኪታብ ጽፈዋል። እንደፈረንጆች አቆጣጠር በ1980 ካይሮ ዉስጥ መክተበተ ሰዐዳህ በተባለ ድርጅት አሳታሚነት ታትሞአል።[307]

---

[304] አልሱዩጢ፣ ሁስነል መቅሰድ ፊዐመሊል መዉሊድ

[305] ሙዕጀሙል ሙአሊፊን 2/152

[306] እብንል-ዐለዊ፣አልኢዕላም...ገጽ 53

[307] እብንል-ዐለዊ፣አልኢዕላም...ገጽ 54

13) **ሰይድ ጀዕፈር እብን ሀሰን እብን ዐብዱል ከሪም አልበርዘንጂ (እስከ 1184 ሂጅሪያ)፡-** ዕዉቅ የሀዲስና የህገሸሪዐ አዋቂ ናቸዉ፡፡ በዘመናቸዉ የመዲና ሙፍቲ ነበሩ፡፡ ***‹‹አልጀዉሀር ፊመዉሊዲ ነብይል አዝሀር››*** የተባለች ኪታብ ጽፈዋል፡፡ በተለምዶ ***‹በርዘንጅ›*** በመባል ትታወቃለች፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሰፊ ተቀባይነትን አግኝታለች፡፡ በኛም ሀገር ለዘመናት በየመዉሊድ ማዕዱ ስትነበብ ኖራለች፡፡ አሁንም በመነበብ ላይ ናት፡፡

14) **ኢማም አቡል ዐባስ እብን አህመድ (እስከ 633 ሂ)፡-** ዕዉቅ የሸሪዐ ሊቅ፡፡[308]ስለመዉሊድ **‹‹አልመዉሊዱ ወጁዱሁ››** የሚል ኪታብ ጽፈዋል፡፡

15) **አቡል ቃሲም (እስከ 677 ሂጅሪ)፡-** የአቡልአባስ ልጅ እና ሊቅ ናቸዉ፡፡የአባታቸዉን የመዉሊድ ኪታብ ወደ ግጥም ቀይረዋል፡፡

16) **ሸይኹል ኢስላም ሲራጁዲን በሊቂኒ (724-805 ሂጅሪ)፡-** ለመዉሊድ ከማዕዱ ላይ በመሳተፍ ተግባራዊ ድጋፍና ይሁንታ፣ እንዲሁም ፈትዋ ሰጥተዋል፡፡[309]

17) **ኢማም አልሀፊዝ ሸሀቡዲን አልቀስጦላኒ፡-** ለኢማሙል ቡኻሪ ሸርህ ያበጁ ዕዉቅ ዐሊማ ናቸዉ፡፡ ስለመዉሊድ ጥሩነት ፈትዋ ሰጥተዋል፡፡[310]

18) **ኢማም እብን ዐቢዲን (1198-1252 ሂጅሪ)፡-** ዕዉቅ የሀነፊ መዝሀብ ሊቅ ናቸዉ፡፡በዘመናቸዉ የመዝሀቡ መሪ ነበሩ፡፡ከዚያ በኋላም በመዝሀቡ ዉስጥ ድምጻቸዉ ሲበዛ ተሰሚ ነዉ፡፡ ‹‹ረዱል ሙህታር ዐለ ዱሪል ሙኽታር›› በተሰኘዉ ባለ አምስት ጥራዝ

[308]እብን ሀጀር፣ተብሲረተል ሙሽተቢህ፣1/253
[309] አልመቅሪዚ፣አልመዋሂዙ ወልኢዕቲባር፣3/167
[310] ቀስጦላኒ፣አልመዋሂበስዱንያህ 1/148

ጥልቅ የህገ-ሸሪዐ ትንታኔ ኪታባቸዉ ይበልጡኑ ይታወቃሉ፡፡ ሌሎች ጥልቅ የሸሪዐ ትናት ኪታቦችም አሏቸዉ፡፡[311]መዉሊድን፡- ***‹‹ወደአላህ ከሚያቃርቡ ትልልቅ በጎ ተግባራት መካከል አንዱ ነዉ››*** ሲሉ ገልጸዉታል፡፡[312]

19) **አልኢማመል ባጁሪ(እስከ1276 ሂ)፡-** ***‹ቱህፈቱል በሺር ዐላ መዉሊዲ አብን ሀጀር›*** የተባለች ኪታብ በመጻፍ ለመዉሊድ ድጋፍ ችረዋል፡፡

20) በጥቅሉ የ7ኛዉና የ8ኛዉ ክ/ዘመን ሂጅሪያ የአራቱም መዝሀብ መሪ ዑለሞች ለመዉሊድ በኢጅማዕ ድጋፍ እንደቸሩ የአልመቅሪዚ የመዉሊድ ክስተቶች ዝርዝር ዘገባ ያረጋግጣል፡፡[313] ከዚያ በኋላ የተነሱ ዐሊሞችም -በጣት ከሚቆጠሩት በስተቀር- እንደዚሁ መዉሊድን መደገፋቸዉን እስከ 13ኛዉ ክ/ዘመን ድረስ ያደረግነዉ የታሪክ ዳሰሳ ያመለክታል፡፡ ተጨማሪ ዝርዝር ዉስጥ መግባት አንባቢን ማሰልቸት እንዳይሆን የጥንቶቹን እዚህ ላይ ልግታ፡፡

ከቅርብ ዘመን ዑለሞች መካከል፡-

- ኢማም ዛሂድ አልከዉሰሪ (እስከ 1371 ሂጅሪ)[314]
- ሸኽ ቡኽይተል መ.ጢዒ-የቀድሞዉ የግብጽ መ.ፍ.ቲ[315]
- ሸኽ ዶ/ር ዐብዱልሀሊም ማህመ.ድ[316]
- ዶ/ር ዩሱፍ አልቀረዳዊ[317]

---

311 አልመዉሱዐቱል ፊቅህያ፣ተራጅመል ፉቀሀአል ጁዝኢል አወል፣

312 ለአብን ሀጀር የመዉሊድ ኪታብ በሰጡት ማብራሪያ

313 ያለፈዉ ምንጭ

314 ሙሀመድ ዛሂድ አልከዉሰሪ፣መቃላቱል ከዉሰርደ፣አልመክተበተ ተዉፊቅያህ፣ካይሮ፣ ገጽ 356-370

315 አህሰኑል ከላም ፊማየተዐለቁ ቢሱነቲ ወልቢድዐ ሚነልአህካም፣ገጽ 30፣67

316 አልፈታዋ፣1/273

- ሸኽ ሁሴን መሀመድ መኽሉፍ[318]
- ሸኽ መተወሊ ሻዕራዊ[319]
- ዶ/ር ረመዳን ቡጢ[320]
- ዶ/ር ወህበተ ዙህይሊ[321]
- ዶ/ር ራቲበ ናብሊሲ[322]
- ዶ/ር ዒሳ እብን ዐብደላህ እብን መሀመድ እብን ማኒዕ አልሁመይሪ፣[323]
- ዶ/ር አህመድ ሸርባሲ[324]
- ዶ/ር ዐሊ ጁመዐህ -የቀድሞዉ የግብጽ መፍቲ[325]
- ዶ/ር መሀመድ እብን አል ዐለዊ[326]

መዉሊድን በመደገፍ ፈትዋ ካስተላለፉ የዘመኑ ዑለሞች መሀከል እነኝህ ጥቂቶቹ ናቸዉ።የሞሪታንያዉ ዐሊምና የሀዲስ ሊቅ ***ሙሀመድ ሀሰን ወለዱ ደዱ*** በባለቤትነት በሚመሩት‹‹ሀዳኢቅ››ድረገጽ ላይ ***‹‹አልኢጅማዕ ዐላጀዋዚል ኢህቲፋል ቢልመዉሊዲ ነበዊ››*** በሚል ርዕስ ባሳተሙት

---

317 በ23-2-2010 እና በሌሎች ጊዚያት በድረ ገጻቸዉ የሰጡት ፈትዋ

318 ፈታዋ ሸርዕየህ 1/131

319ማኢደቱል ፊክሪል ኢስላሚ፣ገጽ 295

320 ድረ ገጻቸዉ ላይ የሚገኝ

321አልጀዚራ ኔት፣‹አል ቢድዐ ወመጃላቱሀል ሙዐሲረህ› በሚል ርዕስ ከደ/ሩ ጋር የተደረገ ቃስ ምልልስ።

322 የድረገጻቸዉ መረጃ፣በ03-06-2009 ያደረጉት የጁመዐ ኹጥባ

323 ዶ/ር ዒሳ፣ቡሱጉል መዕሙል፣ገጽ 3-14

324 ‹የስሱነከ ፊዲኒ ወልሀያት› ከተባለዉ ባስ ብዙ ጥራዝ የፈትዋ ኪታብ ዉስጥ በርከት ያሉ መጣጥፎችን ስለመዉሲድ አስፍረዋል፤

325አልበያኑል ቀዊም፣ ገጽ25፣ አልበያን ሲማ ዩሽጊሉል አዝሀን 1/157

326 ሀዉስል ኢህቲፋል ቢዚክረል መዉሊዲ ነበዊ

ጽሁፍ ውስጥ መውሊድን በመደገፍ ፈትዋ የሰጡ 115 ያህል የጥንትና የዘመኑ ዑለሞች ተዘርዝረዋል[327]

በሀገር ደረጃ ከሳዉዲ በስተቀር የሁሉም ሙስሊም ሀገሮች ኦፊሴላዊ ፈትዋዎች ለመዉሊድ ይሁንታ የሚሰጡ ናቸዉ። የሳዉዲዎች አቋም የተለወጠዉ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንደሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ። የመዲናዉ የሀዲስአዋቂ ዶ/ር አብን አልዐለዊ ‹‹አልኢዕላም›› ከተባለ ኪታባቸዉ ውስጥ 17 የህንድ ታላለቅ ዐሊሞችና ሙፍቲዎች መዉሊድን ደግፈዉ ያስተላለፉትን ፈትዋ ያሰፈሩ ሲሆን፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ የመካ፣ የመዲና፣የሶሪያና የግብጽ የወቅቱ ዐሊሞችና ሙፍቲዎች ለዚህ ፈትዋ ድጋፍ መቸራቸዉን ሰነድ ጠቅሰዉ መዝግበዋል።[328] ይህ መረጃ የሳዉዲዎች ለዉጥ የቅርብ ጊዜመሆኑን ያሳያል።የግብጽ[329]፣የኩዌት[330]፣የተባበሩት ኤምሬትስ[331] እና የሶሪያ የፈትዋ ማዕከላት የሰጧቸዉ የቅርብ ጊዜ ፈትዋዎችም ለአብነት ይጠቀሳሉ። ሁሉም መዉሊድን ጽድቅ ችረዋል።

የሀገራችን ዑለሞች እይታ

ሀገራችን ኢትዮጵያ እስልምናን ቀድመዉ ከተቀበሉና ካስተናገዱ ሀገሮች መካከል አንዷ እንደመሆኗ ረዥም የዒልም ታሪክ ያላት ሀገር ናት። ያለጥልቅ ዕዉቀትና የዒልም ዉርስ ዲኑ 14 ክ/ዘመናትን ተሻግሮ እዚህ ሊደርስ አይችልም።

በኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ዕዉቅና ያላቸዉን ዑለሞች በዕዉቀት ብቃታቸዉ የሚወዳደሩ፣እንዲያዉም የሚያስከነዱ ዑለሞች

---

[327] www.hadaiq.com

[328] አብንል-ወሀቢ፣አልኢዕላም…ገጽ 161-162

[329] www.daralifta.org/fatawa id 140/30-07-2007/

[330] www.islam.gov.kw/fatawa id 7233/23-02-2010/

[331] www.awqaf.ae/fatawa/section id 9 and Ref id 1489/21-10- 2008/

ፈልቀዉባታል። የጥንቱን ትተን በቅርቡ በ19ኛዉና 20ኛዉ ክ/ዘመን እንኳ አስደናቂ የዒልም ሰራዊት ማፍራት ችላለች።

መዉሊድን በሀገራችን በተደራጀ ስርዓት እንዲሄድ ያስቻሉት ሸኽ ሙሀመድ ሸረፈዲን (ጀማ ንጉስ ሙጃሂዶ) ከነዚህ ብቁ ዑለሞች መካከል አንዱ ናቸዉ። በዓለም አቀፍ ደረጃም ይሁን በሀገራችን መዉሊድ በህዝባዊ መታሰቢያነት የተጀመረዉ በጃሂሎች ሳይሆን የዒልም ቁንጮ በሆኑ ዕዉቅ ዓሊሞች መሆኑን ልብ ይሏል።

ከሙጃሂዶ የመዉሊድን አደራ ዕዉቁ ዐሊም ጀማሉዲን አልዐኒ ተረክበዉ ለደረሳቸዉ ለሸኽ አህመደዳኒ አቀበሉ። የዳናዉ ኮከብ በዚክርና በዱዐ አደራጅተዉ በመላ ሀገራችን እንዲዳረስ አደረጉ።

በዚህ ሁሉ የቅብብሎሽ ሂደት ዉስጥ መዉሊድን ከማድነቅና በየዒልም ማዕዶቻቸዉ ሳምንታዊ፣ወርሀዊ ወይም ዓመታዊ ጊዜ ወስነዉለት ከማስኬድ በስተቀር የተቃዉሞ ድምጽ ያሰማ ዐሊም አልተመዘገበም።

ሂደቱ በዚሁ ቀጥሎ በደርግ ዘመነ መንግስት ዕዉቁ ዐሊም ሸኽ ሙሀመድ ሳኒ ሀቢብ እና ጓዶቻቸዉ ባደረጉት ብርቱ ጥረት በኦፊሴል ደረጃ ሀገራዊ በዐል ሆኖ እንዲከበር ታወጀ።

ስለዚህ የሀገራችን ዐሊሞች የመዉሊድን መታሰቢያ በአንድ ድምጽ (ኢጅማዕ) አጽድቀዋል ማለት ይቻላል።

ከላይ የተሰጠዉ ማብራሪያና የታሪክ መረጃዎች በሙሉ ተከታዩ የሸኽ እብን ባዝና የሌሎች የሰለፍይ/ዉሀቢ ዑለሞች ድምዳሜ ምን ያህል ስህተትና በዳይ እንደሆነ ያረጋግጥልናል። እጠቅሳለሁ፡-

وقد صرح جماعة من العلماء بإنكار الموالد والتحذير منها؛ عملاً بالأدلة المذكورة وغيرها.وخالف بعض المتأخرين فأجازها إذا لم تشتمل على شيء من المنكرات

‹‹ብዙ ዑለሞች ከላይ የተወሱና ሌሎችን መረጃዎች ተንተርሰዉ መዉሊድን አዉግዘዋል፤ከርሱም አስጠንቅቀዋል፤ጥቂት የኋለኛዉ ዘመን ዑለሞች ግን መጥፎ ነገር እስካላካተተ ድረስ ፈቅደዉታል፡፡››[332]

ሸኽ እብን ባዝ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሁፋዝ የሀዲስ ሊቃዉንት፣ ለኢጅቲሀድ ብቁ የሆኑ ዑለሞችና የሸሪዐ ፊታዉራሪዎች ያሉበትን የመዉሊድ ደጋፊዎች ጎራ ‹‹ጥቂት›› /በዕድ/ በማለት ሲያቃልሉ፤ እብን ሀጀርን፣ሱዩጢን፣አቡሻማህን ቀዘተ የሚመጥን አንድም እንኳ ዐሊም ያልተመዘገበበትንና ከአልፋኪሀኒ በስተቀር የሰለፍይ/ዉሀብይ ልሂቃን ብቻ ያሉበትን የመዉሊድ ነቃፊዎች ጎራ ‹‹ብዙ›› /ጀማዐህ/ ሲሉ አበራክተዉና አጋንነዉ አቀረቡት፡፡ ይህ ምን ማለት እንደሆነ ፍርዱን ለአንባቢ እተወዋለሁ፡፡

ይህ ሁሉ የሚልም ሠራዊት መዉሊድን ያለበቂ ሸሪዐዊ መነሻ ይደግፋል ብሎ ማሰብ ለሊቃዉንቶቻችን ትልቅ ስድብ ነዉ፡፡ ተስፋም ያስቆርጣል፡፡ ጀላሉዲን አልሱዩጢ፣ኢማም እብን ሀጀረል ዐስቀላኒ፣ጀማሉዲን አልዐኒ፣የሾንኬዉ ሸኽ ጀዉሀር አልሀይደሪ፣ የዳና ከዋክብት፣እነሸኽ ሙሀመድ ሳኒ ሀቢብ፣እነ ሸኽ ሙሀመድ ሰይድ ሳድቅ፣ጌታዉ ሸኽ ዐሊ ጎንደር፣ ሸሪፍ ዐብዱል ዐዚዝ፣ የሰሜኑ ኃያል ሸኽ ጋስ አደም… ይህችን አጀንዳ በወጉ ፈትሸዉ ከትክክለኛ ድምዳሜ ላይ መድረስ ከተሳናቸዉ እስልምና የወላድ መካን ሆኗል፡፡ ከቶም ልጅ አልወለደም፡፡

[332] ሸኽ እብን ባዝ፣ሁክሙል ኢህቲፋል ቢልመዉሊድ ነበዊ፣መክተበተ ሻሚላ፣ቂስመል ወቂዳ፣ገጽ 3

ተጨማሪ ተቃዉሞዎችና ምላሾቻቸዉ

የመዉሊድ ነቃፊዎች የነቀፊታ ስልት በሚከተሉት ነጥቦች ሊጠቃለል ይችላል፡-

1. የደጋፊ ዑለሞችን መረጃዎች ምክንያት እየፈለጉ ማጣጣል፤

2. የመዉሊድን ታሪክ ከፋጢምዮች ጋር በማያያዝ ማጣጣል፣

3. የቢድዐን ጽንሰ ሃሳብ ከመዉሊድ ላይ በማዋል መዉሊድ ቢድዐ እንደሆነ ለማሳየት መጣር፣

4. ይዘቱን ወይም ከመዉሊድ ላይ የሚፈጸሙ ነገሮችን መሀየስ፣

የመጀመሪያዉን እዚያዉ የቁርአንና የሀዲስ መረጃዎችን ሳቀርብ ያየሁት በመሆኑ አልመለስበትም። አንዲት ነጥብ ብቻ ጨምሬበት በቀሪዎቹ ላይ አተኩራለሁ።

ማዘን ሲገባ መደሰት

‹ነብዩ ﷺ የሞቱት በተወለዱበት ቀን ስለሆነ በዚያ ቀን ማዘን ሲገባችሁ መደሰት አግባብ አይደለም። በነብዩ መሞት የመደሰት ያህል ነዉ› የሚል ተቃዉሞ ይደመጣል። ከምዕተ ዓመታት በፊትም ተነስቶ ነበር። ኢማም ጀላሉዲን አልሱዩጢ በቂ ምላሽ በመስጠት ገላግለዉናል። እርሱኑ እንደወረደ ባቀርበዉ የተሸለ ነዉ፤ *‹‹ወከፈላሁል መዐሚኒል ቂታል›*፡-

إن ولادته صلى الله عليه وسلم أعظم النعم علينا، ووفاته أعظم المصائب لنا، والشريعة حثت على إظهار شكر النعم، والصبر والسلوان والكتم عند المصائب، وقد أمر الشرع بالعقيقة عند الولادة، وهي إظهار شكر وفرح بالمولود، ولم يأمر عند الموت بذبح ولا غيره، بل نهى عن النياحة وإظهار الجزع، فدلت قواعد الشريعة على أنه يحسن في هذا الشهر إظهار الفرح بولادته صلى الله عليه وسلم دون إظهار الحزن فيه بوفاته.

‹‹የነብ መወለድ ለኛ ታላቁ ጸጋችን ሲሆን፣ህልፈታቸዉ ደግሞ ታላቁ መከራችን ነዉ፡፡ ሆኖም ሸሪዐዉ ለጸጋ የሚደረግ ምስጋናን ደፋ በማድረግ፣ መከራን ደግሞ በመታገስና በመደበቅ አዟል፡፡ ልጅ ሲወለድ ዐቂቃ ይደረግ ዘንድ ያዘዘ ሲሆን፣ዓላማዉም ደስታንና ምስጋናን ደፋ ለማድረግ ነዉ፡፡ በአንጻሩ ሰዉ ሲሞት እርድ እንዲታረድ ወይም ሌላ ነገር ይደረግ ዘንድ አላዘዘም፡፡ እንዲያዉም ሙሾንና የበረታ ሀዘን ማሳየትን ከልክሏል፡፡ ስለዚህም የሸሪዐዉ መሠረታዊ መርህ ያመላከተዉ በዚህ ወር (በረቢዕ) ሀዘንን መግለጽን ሳይሆን በነብዩ ﷺ መወለድ የተሰማ ደስታን ይፋ ማድረግን ነዉ፡፡››[333]

የታሪክ ነቀፌታ

‹‹መዉሊድን የጀመሩት ፋጢምዮች ናቸዉ፤ ፋጢምዮች ሺዐዎች ናቸዉ፤ሺዐዎች ደግሞ ቢድዐ አራማጆች ናቸዉ፤ስለዚህ መዉሊድ ቢድዐ ነዉ›› ይላል ይህ ነቀፌታ፡፡ ይህች ትርክት በመዉሊድ ተችዎች ወገን በጣም ትራገባለች፡፡ መዉሊድ በመተቸት የተጻፉ መጣጥፎች በአብዛኛዉ ሌላኛዉን ትርክት ፍጹም የዘነጉ ናቸዉ፡፡

ይህን የሚያደርጉት ምን አልባትም ከፍትሀዊዉ ንጉስ ከመሊክ መዞፈር ጋር መያያዙ የትችታቸዉን ግለት ስለሚቀንሰዉ ወይም ተአማኒነቱን ክፉኛ ስለሚጎዳዉ ይመስለኛል፡፡ ለመዉሊድ ይሁንታ የሰጡ ዐሊሞች በበኩላቸዉ ለዚህ ሂስ የሚከተሉትን ምላሾች ይሰጣሉ፡-

1. የልደት ቀናቸዉን በጾም በማሰብ መዉሊድን በግለሰብ ደረጃ በሳምንታዊ ዑደት የጀመሩት ራሳቸዉ ነብዩ ﷺ እንደሆኑ በሶሂህ ሀዲስ በመዘገቡ፤እንዲሁምዐሹራን በጾም በማሳለፍ ታላላቅ ታሪካዊ ክስተቶችን በዓመታዊ ዑደት በኢባዳ አስቦ መዋልን ያስተማሩን ራሳቸዉ ነብዩ

[333] ሁስነል መቅሰድ ፊዐመሊል መዉሊድ

ስለሆኑ፤በተጨማሪም ቁርአን የአላህ ቀናትን እናስታውስ ዘንድ በማዘዙ መውሊድን ሌላ አካል እንደጀመረዉ ማስመሰል ስህተት ነዉ፤

2. እንደ እብን ከሲር፣አቡሻማህና ጀላሉዲን አልሱዩጢ ያሉ ታላላቅ የሀዲስና የታሪክ ሊቃዉንት መውሊድን በህዝባዊ በዐልነት በመንግስት ደረጃ የጀመሩት የሶለሀዲን አልአዩቢ ቤተሰቦች፣ማለትም የእህቱ ባል የሆነዉ መሊክ ሙዞፈር መሆኑን ተቀብለዉ ስላጸደቁ ትርክታችሁ ተአማኒ አይደለም።

3. ፋጢምዮች ጀመሩት የሚለዉን ትርክታችሁን ባናምነዉና ባንቀበለዉም ለዉይይት ያህል እንቀበላችሁና እንቀጥል። ከዚህ ላይ የገነባችሁት ሎጅክ ግን ዉድቅ ነዉ። ምን ማለት መሰላችሁ። ‹የቁርአንን ሀረካ ያበጀዉ፣ ሀጻጅ ስለሆነ፣ሀጻጅ ደግሞ አምባገነንና መጥፎ ስለሆነ፣ የቁርአን ሱመኖች፣ ሀረካና ቁጥሮች መጥፎዎች ናቸዉ› እንደማለት ነዉ።

ጥሩ ነገር መጥፎ ከምንላቸዉ ወገኖች ቢመጣ እንኳ መቀበልን ያስተማሩን የአላህ መልዕክተኛ ራሳቸዉ ናቸዉ። አይሁዶች የዐሹራን ቀን ሲጾሙ አገኟቸዉና ለምን እንደሚጾሙ ጠየቋቸዉ። ፊርዐዉን የሰጠመበትና ሙሳ ለድል የበቁበት ቀን መሆኑን ሲነግሯቸዉ፡ - ‹‹ለሙሳ እኛ ይበልጥ ተገቢዎች ነን›› አሉና ይጾሙት ጀመር።[334]

የትኛዉም አዲስ ነገር ከየትም ወገን ይምጣ የሸሪዐ ሚዛን ስላለን በርሱ እንመዝነዉና ጥሩ ሆኖ ካገኘነዉ ያመነጨዉ አካል መጥፎ ቢሆንም እንኳ እንቀበለዋለን። መጥፎ ሆኖ ካገኘነዉ ያመነጨዉ አካል ጥሩ ቢሆንም እንኳ ዉድቅ እናደርገዋለን። ትክክለኛዉ አቋም ይህ ነዉ። ‹‹ሀቅን በሰዎች ሳይሆን ሰዎችን በሀቅ መዝኑ›› የሚለዉ የዒማም ዐሊ እብን አቢ ጣሊብ ወርቃማ አባባል የሚያስተምረንም ይህንኑ ነዉ። ኢማም እብን ሀጀረል ዐስቀላኒ

[334] ቡኻሪና ሙስሊም

በመዉሊድ ጉዳይ የሰጡት ፈትዋ ይህን ወርቃማ መርህ መሠረት ያደረገ ነዉ። ‹‹መዉሊድ (ህዝባዊዉን ማለታቸዉ ነዉ) አዲስ ነገር ቢሆንም ከጽኑ መሠረት ላይ የታነጸ ስለሆነ መልካም ነገር ነዉ›› አሉ።[335]

[335] ሁስነል መቅሰድ

የቢድዐ ጽንሰ ሀሳብ

የመዉሊድ ተችዎች የሚያቀርቡት ሌላዉ ሂስ ‹‹መዉሊድ ነብዩﷺ ከሞቱ ከምዕተ ዓመታት በኋላ የመጣ አዲስ ነገር ነዉ፤አዲስ ነገር ሁሉ ቢድዐ ነዉ፣ ቢድዐ ሁሉ ደግሞ ጥመት ነዉ›› ይላል፡፡ መዉሊድ ከጊዜ በኋላ የመጣ ነዉ ወይስ በራሳቸዉ በነብዩﷺ የተጀመረ? በሚለዉ አጀንዳ ዙሪያ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ከአሁን ቀደም የሰጠሁ በመሆኑ አልመለስበትም፡፡ ለዉይይት ያህል ግን አዲስ ነገር ነዉ የሚለዉን የተችዎች እይታ ተቀብለን እንቀጥል፡፡

ይህ ሂስ ከቢድዐ ጽንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ጋር ስለሚገናኝ ከርሱ ላይ ጥቂት ብርሀን መርጨት ያስፈልጋል፡፡ የዚህ ጽንሰ ሀሳብ አረዳድ መፋለስ የሀይማኖቱን መስክ በትርምስ እንዲሞላ አድርጎታል፡፡ ሁሉንም ነገር ቢድዐና ሀራም በማድረግ ህዝበ ሙስሊሙን አጨናንቆ መተንፈሻ አሳጥቶታል፡፡ በተለምዶ በእንዲህ ዓይነቱ ክርክር ዉስጥ የሚከተሉት ሀዲሶች ይጠቀሳል፡-

وإياكم ومحدثات الأمور ، فإن كل محدثة بدعة، وكل بدعة ضلالة

‹‹አዲስ ነገሮችን ተጠንቀቁ፤አዲስ ነገር ሁሉ ቢድዐ ነዉ፤ ቢድዐ ሁሉ ደግሞ ጥመት ነዉ፡፡››[336]

وشر الأمور محدثاتها ، وكل بدعة ضلالة

‹‹ከነገሮች ሁሉ ክፉዎቹ አዲሶቹ ናቸዉ፤ ቢድዐ (አዲስ ነገር) ሁሉ ጥመት ነዉ፡፡››[337]

ዑለሞች እነዚህን ሀዲሶች በጥሬዉ አልተረዷቸዉም፡፡ ከሌሎች ተመሳሳይ ሀዲሶች ጋር በማዳበል ***‹‹ዐሙን መኽሱስ››***[338] ብለዋቸዋል፡፡

---

[336] አብን ማጀህ

[337] ሙስሊም፣ነሳኢ፣አብን ማጀህና አህመድ

‹‹አዲስ ነገር ሁሉ›› ወይም ‹‹ቢድዐ ሁሉ›› የሚሉት ገለጻዎች የማያካትቱት መስክ አለ ይላሉ፡፡ ሀሳባቸውን ወደፊት አፍታታዋለሁ፡፡ ከዚያ በፊት ጥቂት መንደርደሪያ ሳያስፈልገን አይቀርም፡፡

‹‹አዲስ ነገር ሁሉ የተወገዘ ቢድዐ ነዉ›› ለሚል ግለሰብ ቀጣይዋን ቀላል ጥያቄ አቅርቡለት፡፡ ‹‹ታዲያ ለምን ሞባይል ትጠቀማለህ? ለምን በበቅሎ ወይም በአህያ ሳይሆን በመኪና ትጓዛለህ...?›› የቂል ጥያቄ ትመስላለች፡፡ ግና ዉጤታ ቅጽበታዊ ነዉ፡፡ ‹‹ ቂል ነህ/ነሽ እንዴ፣እነዚህ ነገሮችማ ዱንያዊ ናቸዉ፡፡ ነብዩ ﷺ ዱንያዊ ነገሮችን ሊያስተምሩን አልመጡም፤ቢድዐ የሚመለከተዉ ዲናዊ ነገሮችን ብቻ ነዉ›› ሊል ይችላል፡፡ ወይም ከዚህ የሚቀራረብ መልስ ይሠጣችኂል፡፡ በእርግጥ መልሱ የግንዛቤ እንከን አለበት፡፡ ነብዩ ﷺ በተለምዶ ዲን ተደርጎ ከሚታሰበዉ መስክ የወጡ ነገሮችን ሁሉ አስተምረዉናል፡፡ የፊቅህ ኪታቦችን ገለጥ አድርገን ማዉጫቸዉን በወፍ በረር ብናይ ጦሀራ፣ ሶላት፣ዘካ፣ጾምና ሀጅ፣ካሉ በኂላ ጋብቻ፣ፍች፣ንግድ፣ኪራይ፣ተዉሶ፣ ስጦታ፣ወዘተ ይሉና በመጨረሻ ኑዛዜንና ዉርስን ይመለከታሉ፡፡ እነዚህ ሁሉ በተለምዶ ዱንያዊ አጀንዳዎች ተደርገዉ የሚታሰቡ ናቸዉ፡፡ ጥቂት ኪታብ የሞካከረ ከሆነ ‹‹ የሰዎች እንቅስቃሴ ‹ዐዳ› እና ‹ዒባዳ› ተብሎ ከሁለት ይከፈላል፡፡ ቢድዐ የሚመለከተዉ ዒባዳን ብቻ ነዉ›› ሊላችሁ ይችላል፡፡ መልሱን ከነእንከኑ ተቀበሉትና ቀጥሉ፡፡ ከላይ ‹‹አዲስ ነገር ሁሉ ቢድዐነዉ፤ ቢድዐ ሁሉ ጥመት ነዉ›› ሲል የነበረ ሰዉ፣ በዚህች ቀላል ጥያቄ አቋሙ ተሸርሽሮ፡- ‹‹ዱንያዊ አዲስ ነገር ሁሉ ከተወገዘዉ ቢድዐ ዉስጥ አይገባም ወይም ቢድዐ አይደለም›› ማለት ጀመረ፡፡ ምን እያለ መሰላችሁ፡፡ ‹‹ቢድዐ ሁሉ ጥመት ነዉ›› የሚለዉ ነብያዊ ቃል የማያካትተዉ መስክ አለ፣እርሱም ዱንያዊ ጉዳዮችን ነዉ፣ እያለ ነዉ፡፡ ይህ ድምዳሜ እንኳን ቀድሞ ከርሱ መጣ፡፡ እናንተ አስቀድማችሁ ብላችሁት ቢሆን ኖሮ ‹‹ነብዩ ﷺ ቢድዐ ሁሉ ጥመት ነዉ እያሉ እንዴት

[338]አልነወዊ፣ሸርህሙስሊም

አንተ ከሁለት ይከፈላል ትላለህ?›› በማለት ክፉኛ ያወግዛችሁ ነበር፡፡ ‹ነብዩን ﷺ ያልተቀበሉ ወዮላቸዉ› የሚል አንደምታ ያላቸዉን የቁርአንና የሀዲስ መልዕክቶች ያለአግባብ እየጠቀሰም ያሳቅቃችሁ ነበር፡፡

ከዉጤት ላይ ለመድረስ አሁንም ትንሽ መጫን ያስፈልጋልና ይህን ጥያቄ አቅርቡለት፡-

‹‹በቁርአን፣በሀዲስ፣በፊቅህ፣በዐረብኛ ቋንቋ ወዘተ ዙሪያ የሚደረጉ ጥናቶች እና ማደራጀቶች የዲን ወይስ የዱንያ ጉዳይ?›› በማለት ጠይቁት፡፡ ‹‹የዲን ጉዳዮች ናቸዉ›› ከማለት በስተቀር ሌላ አማራጭ የለዉም፡፡ ‹‹የቁርአን ፊደላት በነብዩና በሶሀቦች ዘመን ነጥብ አልነበራቸዉም፤ሀረካ አልነበራቸዉም፤የአንቀጾች ቁጥር አልነበራቸዉም፤ በሱመንና በጁዝእ የተከፋፈሉ አልነበሩም፤የሀዲስ መመዘኛ (ሙስጦለሀል ሀዲስ) አልነበረም ፣የፊቅህ ፍልስፍና (ኡሱለል ፊቅህ) አልነበረም፤ነህዉና ሶርፍ የተባሉ የዐረብኛ ሰዋሰዎች አልነበሩም፤ሶሀቦች ሶሂህ፣ዶዒፍ፣ሙሰልሰል፣ሙዐንዐን፣ሙአነን፣መርፉዕ፣ መዉቁፍ ወዘተ የሚባሉ የሀዲስ ጥናት ቃላትን አያዉቁም፤የዐቂዳ ጥናትም አሁን ባለዉ መልኩ ያንየ አልነበረም፤ተዉሂደሩቡብያ፣ተዉሂደል ኡሉህያ፣ተዉሂደል አስማ ወሲፋት የሚለዉ ክፍፍል ነብዩ ﷺ ካለፉ ከ700 ዓመታት በኋላ በሸኽ እብን ተይሚያህ የተደራጀ ነዉ፤ አነዚህና ሌሎች በመቶዎች የሚቆጠሩ ነገሮች ሁሉ አዲሶች ስለሆኑ ቢድዐ ወይም ጥመት ናቸዉ ማለት ነዉን?››

‹‹እነዚህማ የዲን ጉዳዮች ቢሆኑም ዒባዳ ስላልሆኑ ከተወገዘዉ ቢድዐ ጽንሰ-ሀሳብ ዉስጥ አይካተቱም›› ሊላችሁ ይችላል፡፡ ወይም ደግሞ፡- ‹‹የዲኑን ዋነኛ ክፍሎች ለመደገፍና ለማበልጸግ የተደራጁ /መሳሊሀል ሙርሰላ/ ናቸዉ›› ሊል ይችላል፡፡ ስለስያሜዉ ሳትጨነቁ መልሱን ተቀበሉትና ቀጥሉ፡፡ ከላይ ቢድዐን ‹‹ዲናዊና ዱንያዊ›› በማለት ከሁለት ከፈለላችሁ፡፡ ቀጥሎ ዲናዊ ቢድዐዎችን ‹‹ዒባዳና ዒባዳ ያልሆኑ›› ሲል ከሁለት ሰነጠቃቸዉ፡፡ ዒባዳዊ ያልሆኑ ቢድዐዎችን ‹‹መሳሊሀል

መርሰላ›› በማለት ሰየማቸዉ፡፡ አሁንም ትንሽ ተጫኑት፡፡‹‹ተራዊህ ሶላት ዲናዊ አጀንዳ ነዉ ወይስ ዱንያዊ?›› ብላችሁ ጠይቁት፡፡ ‹‹ዲናዊ ጉዳይ ነዉ እንጅ›› ይላችኋል-‹‹እንዴት ቢንቀኝ ነዉ ይህችን ቀላል ጥያቄ የሚጠይቀኝ?›› የሚል ስሜት እየተናነቀዉ፡፡ ‹‹ቢድዐ ነዉ ወይስ አይደለም?›› የሚል ጥያቄም ጨምሩለት፡፡ ‹‹አይደለም›› ካለ፣ ሰይድ ዑመር፡- ‹‹ኒዕመቲል ቢድዐቱ ሀዚሂ›› /ይህች የምታምር ቢድዐ ናት/ ማለታቸዉን ቡኻሪ እንደዘገቡ አስረዱት፡፡ ዘገባዉ ሶሂህ፣የዘገቡት ቡኻሪ ስለሆኑ የሰነድ ክርክር ሊያመጣ አይችልም፡፡ ጃሂል ከሆነ እዚህ ላይ ተደናቅፎ ይቆማል፡፡ ጥቂት ኪታብ የሞከረ ከሆነ ደግሞ፡- *‹‹ሸሪዐዊ ሳይሆን ቋንቋዊ ቢድዐ ማለታቸዉ ነዉ››* ይላችኋል፡፡ መልሱ እንከናማ ቢሆንም ተቀበሉትና ቀጥሉ፡፡ (እንከኑን የማሳየቱን ጉዳይ ለጊዜዉ አዘግዩት)፡፡

ከላይ ቢድዐን ዱንያዊና ዲናዊ ብሎ ከፈለ፡፡ ዲናዊ ቢድዐን ‹‹ዒባዳና ዒባዳ ያልሆነ›› በማለት ገመሰዉ፡፡ እዚህ ላይ ደግሞ ዒባዳዊ ቢድዐን ‹ሸሪዐዊና ቋንቋዊ› በማለት ከሁለት ሰነጠቀዉ፡፡ ‹‹ቢድዐ ሁሉ›› የምትለዉ አቋሙ በእጅጉ ተሸርሽራ ፡- *‹‹ቢድዐ ዱንያዊና ዲናዊ ተብሎ ከሁለት ይከፈላል፣ዲናዊ ቢድዐ ደግሞ ዒባዳዊና ዒባዳ ያልሆነ፣ዒባዳዊ ቢድዐም ቋንቋዊና ሸሪዐዊ ተብሎ ከሁለት ይከፈላል፣ጥመት የሚሆነዉ ከዲናዊ ቢድዐ ዉስጥ ዒባዳዊዉ፣ከርሱም ዉስጥ ሸሪዐዊ የሆነዉ ብቻ ነዉ››* ሲል ሀሳቡ ተጠናቀቀ፡፡በሌላ አባባል በግልጽ ሊናገረዉ ያመንታ እንጅ፡- ‹‹ቢድዐ ሁሉ ጥመት አይደለም ወይም ጥመት ያልሆነ ቢድዐ አለ›› እያለ ነዉ፡፡ ወይም ደግሞ እዉቅና ሊሰጠዉ ቢቀፈዉም ‹‹መልካም የሆነ ቢድዐ (ቢድዐቱል ሀሰና) የሚባል ነገር አለ›› እያለ ነዉ፡፡ **በእርግጥ ዑመር የዲን እንጅ የቋንቋ መምህር ስላልሆኑና የተናሩትም ዒባዳ ስለሆነዉ ተራዊህ ሶላት በመሆኑ ንግግራቸዉን ‹ቋንቋዊ ቢድዐ› በማለት መፈረጅ ስህተት ነዉ፡፡** ሆኖም በጎንዮሽ አጀንዳ ላለመዋጥ ለጊዜዉ ተቀበሉት፡፡

‹‹ቋንቋዊ ቢድዐ ያልከዉ እንዴት ዓይነቱን ነዉ? ወይም ምን ማለትህ ነዉ?›› በማለትም ጠይቁት፡፡ ‹‹ከቁርአን ወይም ከሀዲስ ከሀዲስ መሠረት ያለዉ ማንኛዉም የዒባዳ አፈጻጸም›› ይላችሁ ይሆናል፡፡ለምሳሌ የተራዊህ ሶላት፡፡ ነብዩ ﷺ ለአንድ ወይም ለሁለት ቀናት ከሰገዱት በኋላ ህዝብ ሊከተላቸዉ መሰባሰብ ሲጀምር ግዴታ እንዳይሆን ሰግተዉ አቆሙት፡፡ ‹‹ነብዩ ﷺ የጀመሩትና የተገበሩት ከሆነ ዑመር ቢድዐ እንዲሉት ያደረጋቸዉ ምኑ ነዉ?›› የሚል ጥያቄ አቅርቡ፡፡ ‹‹ተራዊህ ሶላት በመሰረቱ ሱና ቢሆንም በዑመር ዘመን የተፈጠረዉ አዲስ አፈጻጸም ስለሆነ ቢድዐዉ አፈጻጸሙ ነዉ›› ካላችሁ እዉነት ብሏል፡፡ ሰዎች ተበታትነዉ ሲሰግዱ ያዩት ዑመር በኡበይ እብን ከዕብ መሪነት እንዲሰግዱ አደረጉ፡፡ በቀጣዩ ቀን ወደ መስጊድ ሲገቡ ሰዎች በአንድ ኢማም ስር ሲሰግዱ ባዩአቸዉ ጊዜ፡- ‹‹ይህች የምታምር (መልካም) ቢድዐ ናት›› አሉ፡፡ ምክንያቱም የተራዊህን ሶላት ዑመር ባደራጁት መልኩ ነብዩም ﷺ ሆነ አቡበክር አያዉቁትም፡፡ ስለዚህ ተራዊህ ሁለት ገጽታዎች አሉት፡-

አንደኛዉ፡- ነብዩ ﷺ በጥቅሉ በቃላቸዉ ረመዳንን ሌሊት በዒባዳ ማሳለፍን አበረታተዋል፤ በግል ወይም ከተወሰኑ ተከታዮች ጋር ሰግደዉም አሳይተዋል፡፡ይህ አንደኛዉ ገጽታዉ ሲሆን፣

ሁለተኛ፡- ነብዩም ﷺ አቡበክርም የማያዉቁትና በዑመር የተጀመረዉ በአንድ ኢማም ስር 20 ረከዐዎችን የመስገድ ልምድ ነዉ፡፡ይህ የዑመር ‹ቢድዐ› መሆኑ ጥርጥር የለዉም፡፡ ራሳቸዉም ‹ኒዕመቲል ቢደዐቱ ሀዚሂ› በማለት እንደተናገሩት- ደግ ቢድዐ (ቢድዐቱል ሀሰና)፡፡

ከዑመር ድርጊት በሸሪዐዉ በጥቅሉ የተነገሩ ሱና ዒባዳዎችን በራሳችን መንገድ ቁጥራቸዉንና አፈጻጸማቸዉን መወሰንና መመጠን እንደምንችል እንማራለን፡፡ነብዩ ﷺ፡- ‹‹የቅን ኸሊፋዎችን

መንገድ ተከተሉ›› ስላሉን ይህ ትምህርት እጅግ አስፈላጊ ነዉ፡፡ ይህን ሀሳብ የሚያጠነክሩ መረጃዎችን ወደፊት እጨምራለሁ፡፡

‹ዐሙን መኽሱስ›

እኛ ስንት ዳክረንና ተከራክረን ጫፉን ለመያዝ የሞከርነዉን የሀዲሱን መልዕክት ዑለሞች *‹ዐሙን መኽሱስ›* በማለት ገና ጥንት ገላግለዉናል፡፡ ምን ማለት ነዉ? ‹መልዕክቱ አጠቃላይና ሁሉን አካታች (ዐም) የሚመስል፣ ግና የማያካትታቸዉ መስኮች ስላሉ የተገደበ (መኽሱስ)› *‹ቢድዐ ሁሉ ጥመት ነዉ›* የሚለዉ የሀዲሱ ቃል በጥሬዉ ሲያዩት ሁሉንም አዲስ ነገሮች ያለልዩነት የሚያካትት ይመስላል፡፡ ግና ከላይ በጥቂቱ እንዳየነዉ የማያካትታቸዉ መስኮች በእርግጠኝነት አሉ፡፡ይህን ሀዲስ ዑለሞች ብዙ ጊዜ ከሚከተለዉ የቁርአን መልዕክት ጋር አያይዘዉ ነዉ የሚያቀርቡት[339]፡-

تُدَمِّرُ كُلَّ شَيْءٍ بِأَمْرِ رَبِّهَا

‹‹በጌታዋ ትዕዛዝ ሁሉንም ነገር ታጠፋለች፤››[340]

አንቀጹዋ ስለሁድ ህዝቦች የምትተርክ ናት፡፡ ነብያቸዉን ባስተባበሉ ጊዜ የተላከችባቸዉ ቅጣት ሁሉንም ነገር የምታወድም እንደሆነች ይገልጻል፡፡ ‹ሁሉም ነገር› ከሚለዉ ገለጻ ዉስጥ ሰማይና ምድር፣ጨረቃ፣ ከዋክብትና ጸሀይ፣ጀነትና እሳት፣መላኢካ፣ጅን፣በዓለም ላይ ያሉ ሰዎች፣ እጽዋት፣እንስሳት፣ግኡዛን...ሁሉ ይጠቃለላሉ፡፡ በተግባር ግን እነዚህ ሁሉ ነገሮች አልወደሙም፡፡ አህቃፍ የተባለችዉ የከሀዲዎች መንደር ብቻ ናት የጠፋችዉ፡፡[341]የአንቀጹ ገለጻ ‹ዐሙን መኽሱስ› ይሰኛል፡፡ገለጻዉ አጠቃላይ ቢሆንም በተጨባጭ እዉነታ የተገደበ ነዉ፡፡

[339]ለምሳሌ ኢማም አልነወዊ፣ሸርህ ሙስሊም ላይ
[340] አል አህቃፍ፣25
[341] ተፍሲር ኢብን ከሲር

‹ቢድዐ ሁሉ ጥመት ነዉ› የምትለዋ ሀዲስም እንደዚሁ ገለጻዋ አጠቃላይና ሁሉንም አዲስ ነገሮች (ቢድዐዎች) የሚያካትት ቢመስልም በሌሎች ሀዲሶችና የሸሪዐዉ መርሆዎች የተገደበች ናት። የዚህችን ሀዲስ መልዕክት ከገደቡ ሀዲሶች መካከል ጥቂቶቹን ጠቅሰን ወደዑለሞች ማጠቃለያ እናምራ።

من ابتدع بدعة ضلالة، لا ترضي الله ورسوله، كان عليه مثل آثام من عمل بها، لا ينقص ذلك من أوزار الناس شيئاً

1.‹‹አላህንና መልዕክተኛዉን የማያስደስትን መጥፎ ነገር የፈበረከ በርሳ የሠሩ ሰዎችን ወንጀል ሁሉ የነርሱ ቅንጣት ሳይጎድል ይሸከማል።››[342]

من أحدث في أمرنا هذا ماليس منه فهو رد

2.‹‹ከዚህ ከጉዳያችን ዉስጥ የርሱ አካል ያልሆነን አዲስ ነገር የፈጠረ፣ፈጠራዉ ዉድቅ ነዉ።››[343]

من عمل عملاً ليس عليه أمرنا فهو رد

3. ‹‹የኛ ፈቃድ የሌለበትን አዲስ ነገር የፈበረከ ፈጠራዉ ዉድቅ ነዉ።››[344]

የመጀመሪያዉ ሀዲስ አላህንና መልዕክተኛዉንﷺ የማያስደስት ፈጠራ መወገዙን ይገልጻል። ፈጠራ ሆኖ አላህንና መልዕክተኛዉንﷺ የሚያስደስት መኖሩን ይጠቁማል።

[342] ቲርሚዚ፣ሀሰን ብለዉታል፤
[343] ቡኻሪና ሙስሊም
[344] ሙስሊም

ሁለተኛዉ ሀዲስ የዲኑ አካል ያልሆነን አዲስ ነገር መፈብረክን ይከለክላል። የዲኑ አካል የሆነ አዲስ ነገር መኖሩን ይጠቁማል። ኢማም እብን ሀጀረል ዐስቀላኒ ይህን ሀዲስ ሲያብራሩ እንዲህ ብለዋል፡-

هذا الحديث معدود من أصول الإسلام وقاعدة من قواعده فإن معناه: من اخترع في الدين ما لا يشهد له أصل من أصوله فلا يلتفت إليه.

‹‹ይህ ሀዲስ ከዲን መሠረቶች የሚቆጠር ነዉ።ትርጉሙም ከዲን መሠረታዊ ምንጮች መካከል የአንደኛዉን እማኝነት ያላገኘ አዲስ ነገር የፈበረከ ዉጣሪዉ እግምት ዉስጥ አይገባም ማለት ነዉ።››[345]

ከዲን መሠረታዊ ምንጮች መካከል አንደኛዉ በመረጃነት የቀረበበት አዲስ ነገር (ቢድዐ) ክብደትና ግምት እንደሚሰጠዉ ይህ የኢማሙ ገለጻ ያመለክታል።

ሦስተኛዉ ሀዲስ የረሱሉ ﷺ ፈቃድ የሌለበትን አዲስ ነገር መፈብረክን ይከለክላል። የረሱሉ ፈቃድ የታከለበት አዲስ ነገር መኖሩንም ይጠቁማል።

የብዙሀን ዐሊሞች የቢድዐ ትርጉም

ዑለሞች እነዚህና ሌሎችን ሀዲሶች በአንድ ከሰበሰቡ፣እንዲሁም የሶሀቦችን ግንዛቤና ተግባር በጥልቀት ከፈተሹ በኋላ ለቢድዐ የሚከተለዉን አጠቃላይ ትርጉም ሰጥተዋል፡-

1.የኢማሙ ሻፊዒ (እስከ 204 ሂጅሪያ) **ትርጉም፡-**

المحدثات من الأمور ضربان:أحدهما: ما أحدث يخالف كتاباً، أو سنة، أو أثراً، أو إجماعاً. فهذه البدعة الضلالة.والثانية: ما أحدث من الخير لا

[345] ፈትሁል ባሪ

خلاف فيه لواحد من هذا، وهذه محدثة غير مذمومة.

‹‹አዲስ ነገሮች ሁለት ዓይነት ናቸዉ፤አንደኛዉ ቁርአንን፣ ሱናን፣አሰርን ወይም ኢጅማዕን ተቃርኖ የተፈበረከ ሲሆን የጥመት ፍብረካ ይባላል፡፡ ሁለተኛዉ ከተጠቀሱት ዉስጥ አንዱንም ሳይቃረን የተፈበረከ ሲሆን፣ይህኛዉ የሚበረተታ አንጅ የሚወገዝ አይደለም፡፡››[346]

በሌላ ገለጻ እንዲህ ብለዋል፡-

البدعة بدعتان: بدعة محمودة، وبدعة مذمومة، فما وافق السنة فهو محمود، وما خالف السنة فهو مذموم.

‹‹ቢድዐ ሁለት ዓይነት ነዉ፤ የተመሰገነ ቢድዐና የተወገዘ ቢድዐ፣ከሱና ጋር የተጣጣመ ምስጉን ሲሆን ሱናን የተቃረነ ደግሞ ዉጉዝ ነዉ፡፡››[347]

2..የኢማም ዒዝ እብን ዐብዱሰላም (እስከ 660 ሂጅሪያ) **ትርጉም፡-**

البدعة فعل ما لم يعهد في عصر رسول الله صلى الله عليه وسلم وهي منقسمة إلى:بدعة واجبة، وبدعة محرمة، وبدعة مندوبة، وبدعة مكروهة، وبدعة مباحة، والطريق في معرفة ذلك أن تعرض البدعة على قواعد الشريعة: فإن دخلت في قواعد الإيجاب فهي واجبة، وإن دخلت في قواعد التحريم فهي محرمة، وإن دخلت في قواعد المندوب فهي مندوبة، وإن دخلت في قواعد المباح فهي مباحة.

‹‹በሸሪዓህ መልዕክተኛ ዘመን ያልነበረን ነገር መስራት ቢድዐ ይባላል፡፡ ዋጅብ፣ ሀራም፣የሚወደድ፣የሚጠላና የሚፈቀድ ተብሎም ከአምስት ይከፈላል፡፡ከየትኛዉ

346 አልበይሀቂ፣መናቂበሻፈዒያህ 1/468-469
347 አቡ የዕላ፣ሂልየቱል አዉሊያእ1/113

ምድብ እንደሚፈረጅ የማወቂያዉ መንገድ ቢድዐዉን በሸሪዐዉ መርሆዎች መፈተሽ ነዉ።ከዋጅብ መርሆዎች ዉስጥ ከገባ ዋጅብ፣ከሀራም መርሆዎች ዉስጥ ከገባ ሀራም፣ከመንዱብ[348] መርሆዎች ዉስጥ ከገባ መንዱብ፣ከሙባህ[349] መርሆዎች ዉስጥ ከገባ ሙባህ ይሆናል።››[350]

3.የኢማም አል ገዛሊ (እስከ 505 ሂጅሪያ) **ትርጉም፡-**

البدعة قسمان: بدعة مذمومة وهي ما تصادم السنة القديمة ويكاد يفضي إلى تغييرها . وبدعة حسنة ما أحدث على مثال سبق.

‹‹ቢድዐ ከሁለት ይከፈላል። የነበረ ሱናን ተቃርኖ የመጣና ሊቀይረዉ የተገዳደረዉ ቢድዐ ዉጉዝ ሲሆን፣ጥንት የነበረን በጎ ነገር ተመሳስሎ የተፈበረከዉ ግን መልካም ቢድዐህ (ቢድዐቱል ሀሰና) ይባላል።››[351]

وما يقال إنه أبدع بعد رسول الله صلى الله عليه وسلم، فليس كل ما أبدع منهياً عنه، بل المنهي عنه بدعة تضاد سنة ثابتة وترفع أمراً من الشرع مع بقاء علته، بل الإبداع قد يجب في بعض الأحوال إذا تغيرت الأسباب.

‹‹አንድ ነገር ከአላህ መልዕክተኛ ﷺ ዘመን በኋላ ስለተፈበረከ ብቻ የተከለከለ አይሆንም፣ከርሱ ዉስጥ ክልክሉ ጽኑ ሱናን የተቃረነዉና የሸሪዐዉ አካል የሆነን ነገር -ምክንያቱ እያለ- ያስወገደ ነዉ። ሁኔታዎች በሚቀየሩ ጊዜ ቢድዐ ግዴታ የሚሆንበት አጋጣሚ ይፈጠራል።››[352]

4.የኢማም አል ነወዊ (እስከ 676 ሂጅሪያ) **ትርጉም፡-**

---

348 የሚበረታታ

349 የተፈቀደ

350አል ነወዊ፣ተህዚቡል አስማኢ ወል ሉጋት 3/22-23

351ቀዋዒዱል አህካም፣2/172-174

352 ኢህያ ዑሉመዲን 1/277

البدعة، بكسر الباء، في الشرع هي إحداث مالم يكن في عهد رسول الله صلى الله عليه وسلم. وهي منقسمة إلى حسنة وقبيحة.

‹‹ቢድዐ በሸሪዐዉ በአላህ መልዕክተኛﷺ ዘመን ያልነበረ ማንኛዉም ነገር ሲሆን መልካምና መጥፎ ተብሎ ከሁለት ይከፈላል፡፡››[353]

5.**የኢማም እብን አሲር ትርጉም**፡-

البدعة بدعتان: بدعة هدى وبدعة ضلال .. فما كان في خلاف ما أمر الله به ورسوله صلى الله عليه وسلم، فهو في حيز الذم والإنكار، وما كان واقعاً تحت عموم ما ندب الله إليه وحض عليه أو رسوله فهو في حيز المدح.

‹‹ ቢድዐ የመቀናትና የጥመት ቢድዐ ተብሎ ከሁለት ይከፈላል፤ አላህና መልዕክተኛዉ ﷺ ያዘዙትን ተቃርኖ የመጣ ይወገዛል፡፡ በአንጻሩ አላህና መልዕክተኛዉ ﷺ በወደዱትና ባበረታቱት አጠቃላይ መርህ ሥር የተካተተዉ ይሞገሳል፡፡››[354]

6.**ኢማም እብን ሀጀረል ዐስቀላኒ (እስከ 826 ሂጅሪ)** ሁለት ዓይነት ገለጻ አላቸዉ፡፡ በአንደኛዉ ገለጻቸዉ እንዲህ ብለዋል፡

البدعة أصلها ما أحدث على غير مثال سابق، وتطلق في الشرع في مقابل السنة فتكون مذمومة. والتحقيق أنها إن كانت مما يندرج تحت

[353] አል ነወዊ፣ተህዚቡል አስማኢ ወል ጋት 3/22
[354] አል ኒሀያ ፊ ገሪቢል ሀዲስ 1/106-107

مستحسن في الشرع فهي حسنة وإن كانت مما يندرج تحت مستقبح فهي مستقبحة، وإلا فهي من قسم المباح.

‹‹ቢድዐ ማለት ድሮ ባልነበረ መልኩ የተፈጠረ አዲስ ነገር ነዉ፡፡ በሸሪዐዉ ከሱና በተቃራኒ ተደርጎ ይወሳል፡፡ ትክክለኛዉ ድምዳሜ በሸሪዐዉ በጎ ከተሰኘዉ መስክ ዉስጥ የሚካተት ሆኖ ከተገኘ መልካም ሲሆን፣በሸሪዐዉ መጥፎ ከሚባለዉ መስክ ዉስጥ የሚገባ ከሆነ መጥፎ ነዉ፡፡ ከሁለቱ ዉጭ ከሆነ ደግሞ ሙባህ (የተፈቀደ) ነዉ፡፡››[355]

ከላይ ለናሙናነት የተጠቀሱት ዐሊሞች ቃል የብዙሀን ዐሊሞች (ጁምሁር) የቢድዐ አተረጓጎም እንደሆነ አስምሬበት ማለፍ እፈልጋለሁ፡፡[356] በየትኛዉም ዘመንና ቦታ የሚመጣን አዲስ ነገር የምንመዘንበት ሚዛንም ይሰጠናል፡፡ አንድ ነገር በነብዩ ﷺ ወይም በሶሀቦች ዘመን ስላልነበረ ብቻ የተወገዘ አይሆንም፡፡ ወደ ሸሪዐዉ ምንጮችና መርሆዎች ቀርቦ መመዘንና መመርመር አለበት፡፡ ከነርሱ መነሻና መደገፊያ ካለዉ የተወደደ (ሀሰና) ይሆናል፡፡ መነሻና መደገፊያ ከሌለዉ ደግሞ የተወገዘ (ሰይአህ) ይሆናል፡፡

ይህ የቢድዐ ግንዛቤ ከዉይይታችን መጀመሪያ ላይ ያነሳነዉንና ረዥም መንገድ ያዳከረንን የተምታታ የቢድዐ ግንዛቤ ብዥታ በቀላሉ ያስወግድልናል፡፡

የአናሳዎች የቢድዐ ትርጉም

ከዚህ የተለየና የጠበበ የቢድዐ አተረጓጎም ያላቸዉ ዐሊሞች እንዳሉም ማስታወስ ያሻል፡፡ የእነዚህኞቹ የቢድዐ አተረጓጎም በተከታዩ የኢማም

[355] ፈትሁልባሪ፣13/266-267

[356] ዶ/ሚሳ አብን ዐብደላህ አልሁመይሪ፣ቢድዐቱል ሀሰና አስኑ ሚን ኡሱሊዲን፣ዳር ቁርጡባ፣ቤይሩት፣2001፣ገጽ

አልሻጢቢ (እስከ 796 ሂጅሪያ) ገለጻ ውስጥ ሊጠቃለል የሚችል በመሆኑ እርሱን እጠቅሳለሁ፡-

فالبدعة عبارة عن طريقة في الدين مخترعة تضاهي الشرعية يقصد بالسلوك عليها المبالغة في التعبد لله سبحانه

‹‹ቢድዐ ማለት ከሸሪዐዉ ጋር የሚመሳሰልና ዓላማዉም አላህን ደበልጥ ማምለክ የሆነ የሀይማኖት መንገድ ነዉ፡፡››[357]

ይህ የቢድዐ አተረጓጎም ኢማም ሻጢቢ ከሰጡት ማብራሪያ ጋር ተዳምሮ በዲን አጀንዳዎች ሸሪዐዉን በሚገዳደር መልኩ የተፈጠረን አዲስ ነገር ብቻ ይይዛል፡፡ በነዚህኞቹ እይታ ‹ቢድዐ› ሲባል ተወገዘዉን ጭማሬ ወይም አዲስ ነገር ብቻ የሚመለከት ነዉ፡፡

በእርግጥ ኢማም ሻጢቢ ገለጻ ‹ቴክኒካዊ ጣጣ› ስለሚበዛዉ ለተራዉ ህዝብ ቀርቶ ለዑለሞችም አስቸጋሪ ነዉ፡፡ ራሳቸዉ ሻጢቢ ሀሳባቸዉን ለማብራራት ረዥም መንገድ ለመጓዝ ተገደዋል፡፡ ለዚህ ይመስላል ሸኽ ሰከንደሪ አልበራድ እንዲህ በማለት መጽሀፉን የሀየሱት፡-

‹‹የሻጢቢ ኢዕቲሳም ኪታብ ከአንዳንድ ሥፍራ ሳይ አስቅጥ ደንዛዛል፤በሌላሥፍራ ደግሞ ሀሳብ ያስአግባብ ያሳጥራል፡፡ ጸሀፊዉ የምናብ ጉዞ (ኺያል) ያበዛል፡፡ አጀንዳዎችን የማበጠር (ተህቂቅ) ክህሎቱ ደካማ ነዉ፡፡ የቋንቋ ዉበት የሚያማልስዉና በምርምር መስክ ልምድ የሌለዉ ሰዉ ግን በቀላሉ ይታለልበታል፡፡››[358]

ዶ/ር ዒዘት ዐሊ ዐጥያህ በበኩላቸዉ እንዲህ መተቸታቸዉን መጥቀሴ ይታወሳል፡-

---

[357] አልሻጢቢ፣አልኢዕቲሳም፣ተህሪር አሳታሚ፣ ቅጽ 1 ገጽ 127

[358] ዶ/ር ዒዘት ዐሊ ዐጥያህ፣አልቢድዐቱ ተህዲዱሀ ወመዉቂፊል ኢስላሚ ሚንሀ፣ቤይሩተረ፣ ዳሩል ኪታብ አልዐረቢ፣1980፣ገጽ 9

‹‹መጽሀፉ ረዝምና የጸሀፊዉን ትዕግስት የሚመሰክር ቢሆንም ድግግሞሽ፣ መንዛዛት፣መጣረስና መምታታት ገልቶ ይስተዋልበታል። የጸሀፊዉ የትንተና ችሎታና መሳጭ አቀራረብ ይህን ነዉሩን ሊሸፍንስት አልቻለም።›››[359]

የእብን ረጀብ አልሀንበሊ ገለጻ የሻጢቢን ቋጠሮ ፈታ ያደርገዋል፡-

والمراد بالبدعة ما أحدث مما لا أصل له في الشريعة يدل عليه، وأما ما كان له أصل من الشرع يدل عليه فليس ببدعة شرعاً، وإن كان بدعة لغة.

‹‹ቢድዐ ማለት ከሸሪአዉ የሚደገፍበት ምንም ዓይነት መሠረት የሌለዉ አዲስ ነገር ሁሉ ነዉ። ከሸሪዐዉ የሚደገፍበት መሠረት ያለዉ ነገርማ ከቋንቋ አኳያ ቢድዐ ቢሆንም በሸሪዐዉ ቢድዐ አይባልም።››[360]

ኢማም እብን ሀጀር አልዐስቀላኒ በሌላኘዉ ገለጻቸዉ ከነዚህኞቹ ወገኖች የሚያስፈርጅ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡-

والمحدَثات . بفتح الدال . جمع محدثة، والمراد بها: ما أحدث وليس له أصل في الشرع، ويسمى في عرف الشرع بدعة، وما كان له أصل يدل عليه الشرع فليس ببدعة.

‹‹አዲስ ነገር በሸሪዐዉ መሠረት የሌለዉ ነገር ሲሆን በሸሪዐዉ አጠራር ቢድዐህ ይባላል። ከሸሪዐዉ መሠረት ያለዉ ነገር ቢድዐ አይደለም።››[361]

የሁለቱ ገለጻዎች አንድነትና ልዩነት

ሁለቱ የቢድዐ አተረጓጎሞች እርስ በርስ የሚጣረሱ ቢመስሉም ከመስመሩ መጨረሻ ላይ ይገናኛሉ። እንዲያዉም ልዩነታቸዉ የቃላት ይመስላል። ይኸዉም፡-

[359]ያስፈዉ ምንጭ
[360] ጃሚዑል ዑሱሚ ወልሂከም
[361]ፈትሁልባሪ፣13/266-267

1. ሁለቱም ወገኖች ከሸሪዐዉ መሠረት የሌለዉ የቀልብ ዒባዳ (ዐቂዳ) ወይም የአካል ዒባዳ የተወገዘ በመሆኑ ላይ ይስማማሉ።

2. ከሸሪዐዉ መነሻ መሠረትና መደገፊያ ያለዉ የቀልብም ሆነ የአካል ዒባዳ ተቀባይነት እንዳለዉ ይስማማሉ። ባይሆን እስያሜዉ ላይ ተለያይተዋል። የመጀመሪያዎቹ ከስይዲና ዑመር ‹ኒዕመቲል ቢድዐቱ ሀዚሂ› አባባልና ከሌሎች የሸሪዐዉ መርሆዎች ተነስተዉ ‹ቢድዐቱል ሀሰና› (መልካም ቢድዐ) አሉት። የኢማም ሻፊዕይን አባባል ዳግም ልጥቀስ፡-

البدعة بدعتان: بدعة محمودة، وبدعة مذمومة، فما وافق السنة فهو محمود، وما خالف السنة فهو مذموم.

‹‹ቢድዐ ሁለት ዓይነት ነዉ፤ የተመሰገነ ቢድዐና የተወገዘ ቢድዐ፣ከሱና ጋር የተጣጣመ ምስጉን ሲሆን ሱናን የተቃረነ ደግሞ ዉጉዝ ነዉ።››[362]

ሁለተኛዎቹ በበኩላቸዉ ‹‹ሱና ሀሰና›› ወይም ‹‹ቢድዐ ሑገጢያ›› አሉት። ‹ቢድዐ› የሚለዉ ቃል ምንጊዜም ከጥመት ጋር ተገኛኝቶ መቀጠሉ መልካም ሆኖ ስለታያቸዉ። ኢማም እብን ረጀብን አባባል ዳግም ልጥቀስ፡-

والمراد بالبدعة ما أحدث مما لا أصل له في الشريعة يدل عليه، وأما ما كان له أصل من الشرع يدل عليه فليس ببدعة شرعاً، وإن كان بدعة لغة.

‹‹ ቢድዐ ማለት ከሸሪአዉ የሚደገፍበት ምንም ዓይነት መሠረት የሌለዉ አዲስ ነገር ሁሉ ነዉ። ከሸሪዐዉ የሚደገፍበት መሠረት ያለዉ ነገርማ ከቋንቋ አኳያ ቢድዐ ቢሆንም በሸሪዐዉ ቢድዐ አይባልም።››[363]

---

[362] አቡ የዕላ፣ሂልየቱል አዉሊያእ1/113

[363] ጃሚዑል ዑሱሚ ወልሂከም

3. ስለዚህ የትኛውንም አዲስ አጀንዳ አዲስ ስለሆነ ብቻ ሁለቱም ወገኖች አያወግዙትም። በመጀመሪ በሸሪዐዉ መርሆዎች ይመረምሩታል። የሚጣጣም ሆኖ ካገኙት የመጀመሪያዎቹ ‹‹ቢድዐ ሀሰና›› ፣ሁለተኛዎቹ ደግሞ ‹‹ቢድዐ ሉገዉያ›› ወይም ‹‹ሱና ሀሰና›› በማለት ይጠሩታል። ከሸሪዐዉ መርሆዎች ጋር የማይጣጣም መሆኑን ካረጋገጡ ሁለቱም ዉድቅ ያደርጉታል።

4.ክርክር ሊነሳ የሚችለዉ በመርህ ሳይሆን በአፈጻጸም ላይ ነዉ።አንድን ነገር አንዱ ዐሊም ከሸሪዐዉ መርህ ጋር ይጣጣማል ሲል ፣ሌላኛዉ በዚህ በዚህ ሰበብ አይጣጣምም ሊል ይችላል። ይህ ደግሞ በማንኛዉም ጥቃቅን አጀንዳ ዙሪያ ከሚከሰት የሀሳብ ልዩነት ተለይቶ የሚታይ አይደለም።

የትኛዉ ይመረጣል?

በበኩሌ ከሁለቱ ወገኖች አተረጓጎሞች ለሚከተሉት ዋና ዋና ሰበቦች ሲባል የመጀመሪያዎቹን ትርጓሜ እመርጣለሁ፦

1. የብዙሀን ዑለሞች አቋም ስለሆነ፣

2. ሁሉንም አዲስ ነገሮች የሚያጠቃልልና በየዘርፉ ደረጃቸዉን የሚመድብ ወይም በዑለሞች አገላለጽ ‹ጃሚዕ› እና ‹ማኒዕ› ስለሆነ፣

3. በርሱ ምድብ ያሉ ዐሊሞች ከሌላኛዉ ምድብ ይበልጥ በዒልም ጉልበታቸዉ የተመሠከረላቸዉ በመሆኑ፣

4. ለመረዳትም ላተገባበርም ቀላል ስለሆነ፤

5. ያለአግባብ ጠቦ መፈናፈኛ የሚያሳጣ ስላልሆነ፤

6. ሌላኛዉ አተረጓጎም ያለአግባብ ጥቅም ላይ በመዋል ህዝበ ሙስሊሙን ለክፍፍል፣የሀይማኖት መስኩን ለትርምስ ዳርጎታል ብየ ስለማስብ፣

7. የሌላኛዉ አተረጓጎም ዋነኛ መነሻ የሆነዉ ***አልኢፊቲሳም*** የተባለዉ ኪታብ፣ የአተረጓጎሙ ፊታዉራሪ የሆኑት ***ኢማም ሻጢቢ*** (እስከ790 ሂጅሪያ) በወቅቱ በደረሰባቸዉ ጫና ምክንያት ተበሳጭተዉና ተገፋፍተዉ ያዘጋጁት ነዉ ብየ ስለማምንና ሰዉ እንደመሆናቸዉ በወቅቱ የነበሩበት ሥነ-ልቦናዊ ዉጥረት በአጠቃላይ ቅኝታቸዉ ላይ ተጽዕኖ አሳርፏል ብየ ስለምገምት። የመጽሀፉን መግቢያ ያነበበ ሰዉየዉ የነበሩበትን ዉጥረትና ጫናን የመቃወም ብርቱ ስሜት በጉልህ ያስተዉላል፤ግምቴንም ይጋራ ይሆናል፡

የተሳሳቱ የቢድዐ ትርጉሞች

በዒልሙ መስክ ምንም ዓይነት ቦታ የሌላቸዉ፣ ከኽለፍም ከሰለፍም የትኛዉም ዓሊም ያልተናገራቸዉ፣ከቁርአንም ሆነ ከሀዲስ፣ከኢጅማዕም ሆነ ከቂያስ መረጃ ሊጠቀስላቸዉ የማይችሉ፣ሆኖም ህብረተሰቡን እያደናገሩና እየመሩ የሚገኙ የቢድዐ አተረጓጎሞች በስፋት ተረጭተዉ ይገኛሉ። እነርሱም፡-

1.ቢድዐማለት ነብዩ ﷺ ያልሰሩት ነገር ነዉ፡- ለቢድዐ ይህን ትርጉም የሰጠ፣ለኢጅቲሀድ ብቁ የሆነ ሁነኛ ዐሊም በምድር ላይ አላለፈም። ሁነኛ ኪታብም ሊጠቀስለትም አይችልም። አላህ እንዲህ ይላል፡-

وَمَا آتَاكُمُ الرَّسُولُ فَخُذُوهُ وَمَا نَهَاكُمْ عَنْهُ فَانتَهُوا [٥٩:٧]

‹‹መልክተኛዉም የሰጣችሁን (ማንኛዉንም) ነገር ያዙት።ከእርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ።አላህንም ፍሩ። አላህ ቅጣተ ብርቱ ነዉና።››[364]

አላህ በዚህ የቁርአን አንቀጽ ሁለት ነገሮች አዞናል፡-

1. መልዕክተኛዉ ﷺ ያዘዙንን እንድንተገብር፣

2. እርሳቸዉ ከከለከሉን እንድንታቀብ፤

[364]አልሀሽር 7

እርሳቸዉ ያልሰሩትን ወይም የተዉትን ነገር እንድንታቀብ ግን አላዘዘም፤

የአላህ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ከከለከልኳችሁም ሙሉ በሙሉ ተከልከሉ፤ ያዘዝኳችሁን ነገር በቻላችሁት ልክ ሥረ፤፤›››[365]

በዝምታ ያለፍኩትን ወይም ያልተገበርኩትን ነገር አትስሩ ግን አላሉም፡፡ እንዲህም ብለዋል፡-

‹‹አላህ ወሰኖችን አበጅቷልና አትስፋቸዉ፤ ግዴታ ያደረጋቸዉ ነገሮች አሉና አታጥፏቸዉ (ተግብሯቸዉ)፤ የከለከላቸዉ ነገሮችም አሉና አትዳፈሯቸዉ፤ ረስቶ ሳይሆን ስናንተ በማዘን በዝምታ ያለፋቸዉ ነገሮችም አሉና ስለነርሱ አትፈላፈሉ፡፡››[366]

‹አትፈላፈሉ› የሚለዉ ትዕዛዝ ሶሀቦችን ብቻ የሚመለከት ነዉ፡፡[367] ምክንያቱም ያንጊዜ ወህይ ይወርድ ስለነበር ጸጉር ስንጠቃዉ ጠበቅ ያሉ ህግጋት እንዳያስከትል ያሰጋልና፡፡ ለዚህም ነዉ ነብዩ ﷺ ‹የተዉኳችሁን ነገር ተዉኝ›› ያሉት፡፡[368] ቁርአንም እንዲህ ሲል አዞአቸዋል፡-

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا لَا تَسْأَلُوا عَنْ أَشْيَاءَ إِن تُبْدَ لَكُمْ تَسُؤْكُمْ وَإِن تَسْأَلُوا عَنْهَا حِينَ يُنَزَّلُ الْقُرْآنُ تُبْدَ لَكُمْ عَفَا اللَّهُ عَنْهَا وَاللَّهُ غَفُورٌ حَلِيمٌ

[365] አህመድ
[366]ዳረል ቁጥኒ ዘግበዉታል፤አልነዉዊናሰምዐኒ ሀሰን ብለዉታል፤
[367]በዋሚሉ ሰዐህ ወልሙሪናህ ፈሸሪዐቲል ኢስላምየህ፣ ገጽ 15
[368]ቡኻሪ፣ሙስሊምና አህመድ

‹‹አናንተ ያመናችሁ ሆይ! ለአናንተ ቢገለጹ ከሚያስከፏችሁ ነገሮች አትጠይቁ። ቁርኣንም በሚወርድበት ጊዜ ከአርሷ ብትጠይቁ ለናንተ ትገለጻለች፤ከአርሷ አላህ ይቅርታ አደረገ።አላህም መሓሪ ታጋሽ ነው።››[369]

በሌላ ሀዲሳቸዉም እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹አላህ በመጽሀፉ ዉስጥ ሀላል ያለዉ ሁሉ ሀላል፤ሀራም ያለዉ ሁሉ ደግሞ ሀራም ሲሆን፤በዝምታ ያለፈዉ ነገር የተፈቀደ (ዐፍዉ) ነዉ። ከአላህ ፈቃዱን ተቀበሉ። ምክንያቱም ምንንም ነገር አይረሳምና።›› ይህን ካሉ በኋላ ‹‹ጌታህ የሚረሳ አይደለም››[370] የሚለዉን የቁርአን መልዕክት አነበቡ።[371]

ነብዩ ﷺ ነገሮችን ሊተዉባቸዉ የሚችሉ በርካታ ምክንያቶችን ከአሁን ቀደም መጥቀሴ ይታወቃል። በጥቅሉ ነብዩ ﷺ ያልሠሩት ነገር-ሌላ ተጨማሪ መረጃ ካልቀረበ በስተቀር-ክልክል ወይም ቢድዐ መሆኑን የሚያመለክት አንድም መረጃ የለም።

በእስልምና ነገሮችን የምንመዘንባቸዉ አምስት የአህካም ዓይነቶች አሉ። እነርሱም፡-

1.**ዋጅብ**፡- መተግበሩ ግዴታ የሆነ፤

2.**ሙስተሀብ**፡- እንዲሠራ ያበረታቱት፤

3.**ሙባህ**፡- መሠራቱም አለመሠራቱም እኩል የሆነ፤

4.**ከራሀ**፡- ባይሠራ የሚበረታታ፤

5. **ሀራም**፡- አላህና መልዕክተኛዉ በግልጽ የከለከሉት፤

---

[369]አልማኢዳህ፤101

[370]መርየም 64

[371]በዛርና ሀኪም ዘግበዉታል፤ ሰነዱ ሶሂህ መሆኑንም ተናግረዋል። አልዘሀቢም በዚህ ብይን ተስማምተዋል።

አንድ ነገር ክልክል ነዉ ለመባል በቁርአን ወይም በሀዲስ በግልጽ መከልከል አለበት። ነብዩ ﷺ የተዉት ወይም ያልሠሩት ነገር ክልክል ነዉ የሚል የኡሱል ኪታብ የለም።

በጥቅሉ ቢድዐን ‹ነብዩ ﷺ ያልሰሩት ነገር› በማለት መተርጎም ስህተት ነዉ።

2.ቢድዐ ማለት ሰለፎች ያልሰሩት ነገር ነዉ፦ ሌላዉ የተሳሳተ የቢድዐ ትርጉም‹‹**ሰለፎች ያልሠሩት**›› በማለት መተርጎም ነዉ። ሰለፎች ቀርቶ ራሳቸዉ ነብዩ ﷺ ያልሰሩት እንኳ ቢድዐ አይባልም። ነብዩ ﷺ ያልሠሯቸዉ፣ግና በሶሀቦች የተሠሩ ብዙ ነገሮች አሉ።ሶሀቦች ያልሰሯቸዉ፣ግና በታቢያች የተሠሩ፣ታቢያች ያልሠሯቸዉ፣ግና ከዚያ በኋላ ባሉ ትዉልዶች የተሠሩ ብዙ ነገሮች አሉ። በቁርአን ዙሪያ የሆነዉ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነዉ።

ሀዲስ ያለፊቅህ

ዑለሞች ‹‹ቢድዐ ሁሉ ጥመት ነዉ›› ለሚለዉ ሀዲስ የሰጡትን ትንታኔና የሀሳብ ምልልሳቸዉን ሳነብ፣እንዲሁም የመዉሊድን ጉዳይ ሳጠና የሀዲስ ዕዉቀት ብቻዉን ያለበቂ የፊቅህ ግንዛቤ ዉጤቱ አደጋ መሆኑን የገለጹ የሀዲስ አዋቂዎች መልዕክት ከልብ ገባኝ። የጥቂቶቹን አባባል ላካፍላችሁ፦

ታላቁ መሀዲስ ዐብደላህ እብን መባረክ እንዲህ ሲሉ ተደምጠዋል፦

‹‹አላህ በአቡሀኒፋና በሱፍያን ባያግዘኝ ኖሮ ተራ ሰዉ ሆኜ እቀር ነበር።››[372]

ሱፍያን እብን ዑየይነህ እንዲህ ብለዋል፦

‹‹መጀመሪያ ስሀዲስ ያስቀመጡኝና መሀዲስ ያደረጉኝ አቡ ሀኒፋ ናቸዉ።››[373]

[372]ተብይዱ ሶሂፋህ ገጽ 16፣ (መሂቀ ተቀዉል፣ገጽ 210 የተወሰደ)

ከኢማሙ ማሊክ ደረሶች መካከል አንዱ የሆኑት ዐብደላህ እብን ወህብ እንዲህ ተናግረዋል፡-

‹‹ከ360 ዐሊሞች ጋር ተገናኝቻለሁ፤ግና ማሊክ እና ለይስ ባይኖሩ ኖሮ የዕዉቀትን ጎዳና በሳትኩ ነበር፡፡››[374]

ቃዲዒያድ ባለፈሩት ዘገባ እብን ወህብ ሀሳባቸዉን ሲያፍታቱ፡- ‹‹አባህ በማሊክና በለይስ ባያግዘኝ ኖሮ ጠፍቼ ነበር›› ባሉ ጊዜ፡-‹‹ለምን?›› ተብለዉ ሲጠየቁ፡-‹‹ሀዲስ አበዛሁና ተምታታብኝ፤ ለማሊክና ለለይስ አቀረብኩሳቸዉ፡፡ ይህን ተዉ፤ይህኛዉን ደግሞ ያዝ›› በማለት መንገዱን መረኝ፡፡›› አሉ፡፡[375]

ሱፍያን እብን ዑየይናህ፡-‹‹ ሀዲስ ለፊቅህ አዋቂዎች ካልሆነ በስተቀር አሳሳች ነዉ›› ብለዋል፡፡

እብን ሩሽድ ስለዚህ የሱፍያን አባባል ተጠይቀዉ ሲመልሱ፡-

‹‹ይህ አባባል የነብዩ ﷺ አይደለም፤ የአብን ዑየይናህና የሌሎች ዐሊሞች አባባል ነዉ፡፡ ሆኖም መልዕክቱ ትክክለኛ ነዉ፡፡ ምክንያቱም ሀዲስ ቃሉ የተለየን ሁኔታ የሚመለከት፣መልዕክቱ ግን አጠቃላይ ወይም በተቃራኒዉ ሆኖ ሊመጣ ይችላል፤ ከመሀከሉ መልዕክቱ የተሸረ እና ሻሪ (ናሲክና መንሱክ) ይኖራሉ...፡፡ሀዲስ ብቻ የሰበሰበ የፊቅህ ክህሎት ከሌለዉ ነገሮችን ያደበላልቃል፡፡ ፈቂህ ስመሆን ሀዲስ ቢያስፈልግም ሀዲስ ብቻዉን ግን የፊቅህ ሊቅ አያደርግም፤ እንዲያዉም እብን ዑየይናህ እንዳሉት የፊቅህ ችሎታ የሌለዉ ሰዉ ሀዲስ ባያከማች ለርሱ የተሸለ ነዉ፡፡››[376]

ከኢማሙል ቡኻሪ ሸኾች መካከል አንዱ የሆኑት አልፈድል እብን ዱኪን እንዲህ ብለዋል፡-

---

[373] አልጀዋሂረል ሙድያህ 1/31፣ (ሙሂቀ ተቀዉል፣ገጽ 210 የተወሰደ)

[374] ከእብን ሂባን አልመጅሩሂን መጽሀፍ መግቢያ የተወሰደ

[375] አልኢንቲቃእ ፊፈዳኢሊ ሰላሳ አልፉቀሀእ፣ገጽ 27-28

[376] አቡልዐባስ ወንሸሪሲ፣አልሚዕያር አልሙዕሪብ 12/314፣ (ሙሂቀ ተቀዉል..፣ገጽ 212)

‹‹የአቡ ሀኒፋ ባልደረባ በሆኑት ዞፍር እብን ሁዘይል አጠገብ ሳልፍ በልብሳቸዉ ተሸፍነዉ አገኛቸዉና ‹ና፣ሀዲስህን ሳበጥርልህ› ይሉኛል፡፡ የሰበሰብኩትን ሀዲስ አቀርብላቸዋለሁ፡፡‹ይኛዉ ይያዛል፡፡ ይህኛዉ ዉድቅ ነዉ፡፡ይህ ናሲኽ ነዉ፡፡ ይህደግሞ መንሱኽ ነዉ› ይሉኛል፡፡››[377]

ዐብደላህ እብን መሳረክ የአቡሀኒፋን ንግግር አስመልክተዉ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹የአቡ ሀኒፋ አስተያየት አትበሉ፡፡ ይልቁንም የሀዲስ ተፍሲራቸዉ በሉ››[378]

የእነዚህ ሁሉ የሀዲስ ሊቃዉንት ምስክርነት ከተሞክሮ የመነጨ በመሆኑ እጅግ ጠቃሚ ነዉ፡፡ ይህን እዉነታ እንዲናዘዙ ያስገደዳቸዉ በሀዲስ እዉቀት ብቻ ያለፊቅህ ግንዛቤ መግፋት የሚያስከትለዉን መመሰቃቀልና ትርምስ በተግባር ማየታቸዉና አደጋዉን መረዳታቸዉ ነዉ፡፡

አንዲት ወይም የተወሰኑ ሀዲሶችን አንጠልጥለዉ፣ናሲኽና መንሱኽ፣ ዐምና ኻስ፣መፍሁምና መንጡቅ ወዘተ የሚሉ የግንዛቤ መሳሪያች ሳይኖሯቸዉ አመለካከታቸዉን የሚገነቡ ወገኖች በራሳቸዉም በሌሎችም ላይ ምን ያህል ትርምስ እንደሚያስከትሉ መረዳት አይከብድም፡፡ **የኛ ሀገር የዲን ትምህርት ሥርዓት እጅግ አስደናቂ ችሎታ የነበራቸዉን መሻኢኾች ማፍራት የቻለዉ ጅማሮዉ ከፊቅህ ስለሆነና ከታች እስከላይ በሥርዓት የተደራጀስለነበር መሆኑን መረዳት አይገድም፡፡ ወደዚያ ጎዳና ካልተመለስን የድንግዝግዝ ጉዟችን ማብቂያ አይኖረዉም፡፡**

[377] አልኽጢበል በግዳዲ፣(ሙሂቀተቀዉል፣ገጽ 213)
[378] መናቂቡል ሙወፈቅ አልመኪ፣ገጽ 234 (ሙሂቀ ተቀዉል ገጽ 213)

የትኛዉንም ሀዲስ በግል ለመረዳትና ሀሳብ ለመዉሰድ ከመሞከር ይልቅ የሀዲሱን ማብራሪያ (ሸርህ) ማየትና የፊቅህ ሊቃዉንትን እገዛ መሻት ከብዙ ምስቅልቅል ይታደጋል።

ወደ መነሻችን

በቢድዐ ጽንሰሀሳብ ዙሪያ ይህን ያህል ረዥም መንገድ የተጓዝነው መዉሊድን ‹ቢድዐ› የሚሉ ወገኖች በዚህ ረገድ የሚያነሷቸዉን መቃወሚያዎች በወጉ ለመመለስ ነበር። ከሁለቱም የዑለሞች ቡድን የቢድዐ አተረጓጎም ብንነሳ መዉሊድ የተኮነነ ተግባር ሊሆን አይችልም።

1. በብዙሀን አተረጓጎም መሠረት ቢድዐ ሁለት ዓይነት ነዉ። ከቁርአን፣ ከሀዲስ ወይም ከሌሎች የእስልምና ምንጮች መነሻ ያለዉ ‹መልካም ቢድዐ› ፣መነሻ የሌለዉ ደግሞ ‹መጥፎ ቢድዐ› ይባላሉ። መዉሊድ ከላይ የተዘረዘሩ መነሻዎች ስላሉት ‹መልካም ቢድአ› (ቢድዐቱል ሀሰና) ይሆናል።

2. በአናሳዎቹ ዑለሞች አተረጓጎም መሠረት ቢድዐ ለተወገዙ ነገሮች ብቻ የሚዉል ቃል ሲሆን፣ እርሱም ከቁርአን፣ ከሀዲስ ወይም ከሌሎች የሸሪዐ ምንጮች መነሻና መደገፊያ የሌለዉ ነዉ። መዉሊድ ደግሞ ከላይ የተዘረዘሩት የቁርአን፣የሀዲስና የቂያስ መነሻዎች ስላሉት ከነዚህኞቹ የቢድዐ ትርጉም ዉስጥ አይገባም።

በሁለቱም መንገዶች ተጉዘን የምንደርስበት መዳረሻ ተመሳሳይ ነዉ። የሰከነ ምሁራዊ ፍተሻ ከዚህ የተለየ ዉጤት ሊያስገኝ አይችልም።

ዲኑ ሞልቷል

አላህ እንዲ ብሏል፡-

الْيَوْمَ أَكْمَلْتُ لَكُمْ دِينَكُمْ وَأَتْمَمْتُ عَلَيْكُمْ نِعْمَتِي وَرَضِيتُ لَكُمُ الْإِسْلَامَ دِينًا

‹‹ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ፡፡ ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ፡፡ ለእናንተም ኢስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ፡፡››[379]

‹‹ይህ አንቀጽ የዲኑን መሙላት ይገልጻል፡፡ መዉሊድ ሸሪዐዊ ነዉ ማለት ዲኑን ጎደሎ ከማለት አይተናነስም፤ዲኑን ጎደሎ ማለት ደግሞ ኩፍር ነዉ፤ስለዚህ መዉሊድን መፍቀድ ኩፍር ነዉ›› የሚል መከራከሪያም ይቀርባል፡፡ ይህ ክስ በእስልምና ታሪክ አንቱ የተሰኙና እስካሁን የጠቃቀስናቸዉ ዐሊሞች ከሚከተሉት ሁለት ሁኔታዎች በአንዱ ዉስጥ ናቸዉ እንደማለት ነዉ፡-

1. የዚህች አንቀጽ ትርጉም አልገባቸዉም፤ወይም

2. መልዕክቷ ገብቷቸዉ ሆነ ብለዉ ጥሰዋታል፤እናም ራሳቸዉን ለኩፍር አደጋ አጋልጠዋል፡፡

ሁለቱም ትክክል እንዳልሆኑ ልቦናችን ያዉቀዋል፡፡ ስለዚህ የሚቀረዉ አማራጭ መልዕክቷን በጥልቀት ተረድረተዉ፤የመዉሊድን ጉዳይም በርሷና በሌሎች አናቅጽ ጥላ ሥር አይተዉ አቋም ይዘዋል የሚለዉ አማራጭ ነዉ፡፡እነርሱን በክፉ ከመጠርጠር አሁን በዓለም ላይ የምንገኝ ሙስሊሞችን በሙሉ እዉቀትና ኢማን ብንጠራጠር ይቀላል፡፡

የቢድዐን ጽንሰ ሀሳብ ሳብራራ ብዙ ያልኩ ቢሆንም ቅንጣት ታክል ብኸፖታ ላለማስቀረት ጥቂት ነገር እዚህ ላይም ልበል፡፡‹‹ዲኑን ሞላሁላችሁ›› ማለት ምን ማለት ነዉ? አንቀጿ የወረደችዉ በ9ኛዉ ዓመተ ሂጅራ፤እስልምና ጠላቶቹን ሁሉ አሸንፎ የበላይ በሆነበት፤ የመሰናበቻዉ ሀጅ በተጠናቀቀበት ቅጽበት ነዉና ትርጉሟን ከዚያ ክስተት ጋር ያያያዙት ዑለሞች እንዳሉ ሁሉ ዘመን ተሻጋሪ መልዕክት ያላበሷትም አሉ፡፡ እብን ከሲር፤ቁርጡቢ፤አሉሲና ሌሎችንም የተፍሲር ኪታቦች ስንገልጥ ‹‹ሞላሁላችሁ›› የሚለዉን ቃል አስመልክቶ የሚከተሉትን ማብራሪያዎች እናገኛለን፡-

[379] አልማኢዳህ 3

1. ከእንግዲህ ጣዖታውያን አብረዋችሁ ሀጅ አያደርጉም፤[380]
2. ጠላቶቻችሁን አጠፋሁላችሁ፤[381]
3. ከእንግዲህ ሌላ ሀይማኖትም፣ሌላ ነብይም አያስፈልጋችሁም፤[382]
4. የሀይማኖታችሁን ግዴታዎች፣ ወሰኖች፣ ሃላልና ሀራሞች ደመደምኩላችሁ። ክንግዲህ የሚሻርም ሆነ የሚጨመር ህግና ወሰን የለኝም፤[383]
5. የብዙሀን ዐሊሞች እይታ፡- ‹‹አብዛኛዎቹን ግዴታዎች፣ሀላልና ሀራሞች ሞላሁ›› ማለት እንደሆነ ቁርጡቢ ጽፈዋል።[384]

የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ አተረጓጎሞች ከያዝነዉ ርዕስ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ስለሌላቸዉ ስለነርሱ ብዙ አልልም። አራተኛዉና አምስተኛዉ ትርጉም የሀላልና ሀራም፣እንዲሁም የእስልምና ሀይማኖት መርሆዎችና መሠረቶች ጉዳይ የዚያን ቀን ወርደዉና ተላልፈዉ እንደንተጠናቀቁ ይገልጻሉ። ከነዚህ መርሆዎች መሀል የትኛዉንም የህይወት አጀንዳ በቁርአን፣በሀዲስ፣በኢጅማና በቂያስ መመርመር ይገኝበታል። ከነዚህ መመዘኛዎች በአንዱ ተፈትሾ ሀላል ወይም የተፈቀደ መሆኑ የተረጋገጠ ነገር አዲስ ጭማሬ ተደርጎ አይታይም። የሙሉዉ ዲን አካል ነዉ። መዉሊድም በነዚህ መስፈርቶች ተመዝኖ ካለፈ የሙሉዉ ዲን አካል እንጅ ጭማሬ አይሆንም።

ከነብዩ ﷺ ህልፈት በኋላ የተጠኑና የተጻፉ በብዙ ሺ ገጾች የሚቆጠሩ የፊቅህ፣ የተዉሂድ ወዘተ ሥራዎች የዲኑን መርህ ተንተርሰዉ እስከተሰሩ ድረስ የሙሉዉ ዲን ወገኖች ናቸዉ። የኢማሙ ሻፊኢ

[380]ተፍሲር አል በገዊ
[381] ያስፈዉ ምንጭ
[382] አብን ከሲር
[383] ጦበሪ
[384] ተፍሲር ቁርጡቢ

ኡሱሉል ፊቅህ፣የኢማሙል ቡኻሪ የሀዲስ ጥናት ሳይንስ፣የጀላሉዲን አልሱዩጢ ኡሱለተፍሲር፣የሲበወይ የነህዉ ጥናት፣የአራቱ ኢማሞች በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የእጅቲድ አጀንዳዎች የሙስዉ ዲን አካሎች ናቸዉ።

ይህ ሙስ ዲን በየትኛዉም ዘመንና ቦታ ለሚፈጠሩ ክስተቶች አጠቃላይ የሆነ ሚዛን ሰጥቶናል። በዚያ ሚዛን ለክተን ደረጃቸዉን እናዉቀዋለን። ሀላል፣ሀራም፣የሚወደዱ፣የሚጠሉ ወይም የተፈቀዱ መሆናቸዉን እንረዳለን። የሁሉም ዘመናት ሀይማኖት ያደረገዉም ይህ ነዉ።

አዲስ ዒባዳ

‹በእስልምና ያልተደነገገ አዲስ ዒባዳ ፈጥራችኋል› የሚለዉ ክስ ሌላኛዉ የተቃዉሞ መገለጫ ነዉ። የመዉሊድ ደጋፊዎች በበኩላቸዉ፡- ‹‹በመዉሊድ ከሚከናወኑ ዒባዳዎች መካከል ዲኑ እዉቅና ያልሠጠዉ የትኛዉን ነዉ?›› በማለት ይጠይቃሉ። ‹ዚክሩን? ሶለዋቱን? የነብዩ ﷺ ሲራ መነበቡን?ዱዐዉን? ድሀ መመገቡን? የትኛዉን ነዉ ሸሪዐዉ የማያዉቀዉ?› ሲሉም ይሞግታሉ። ‹የይዘት ተቃዉሞ› በሚል ርዕስሥር ይህ አጀንዳ በወጉ ተመርምሯል። ተቃዉሞዉ ራሱን መዉሊድ መታሰቡን ከሆነ ከአሁን ቀደም በቂ ማብራሪያ ተሰጥቶበታልና አልመለስበትም። ከመዉሊድ ዉሥጥ የሚሰሩ ነገሮች ሀላልና የታወቁ ዒባዳዎች ናቸዉ። ለምሳሌ፡-

- ዚክር፣
- ሶለዋት፣
- የነብዩን ﷺ ታሪክ ማንበብ፣
- ሶሀቦችንና ደጋግ ሰዎችን ማዉሳት፣
- ነብዩን ﷺ ማወደስ፣

- ድሆችን መመገብ፣

እነዚህ ሁሉ በተናጠል ደግ ስራዎች መሆናቸዉ ከተረጋገጠ በአንድ ላይ ሲደመሩ ሀራም የሚሆኑበት ሰበብ ፍጹም የሚገባ አይደለም።

በክርስቲያኖች ላይ የደረሰ ወቀሳ

አላህ ክርስቲያኖችን የወቀሰባት ተከታይዋ አንቀጽም መዉሊድ ሲነሳ አብራ ትነሳለች፡-

وَرَهْبَانِيَّةً ابْتَدَعُوهَا مَا كَتَبْنَاهَا عَلَيْهِمْ إِلَّا ابْتِغَاءَ رِضْوَانِ اللَّهِ فَمَا رَعَوْهَا حَقَّ رِعَايَتِهَا فَآتَيْنَا الَّذِينَ آمَنُوا مِنْهُمْ أَجْرَهُمْ وَكَثِيرٌ مِّنْهُمْ فَاسِقُونَ.

‹‹አዲስ የፈጠሩዋትንም ምንኩስና ፈጠሩ፡፡በእነርሱላይ (ምንኩስናዋን) አልጻፍናትም፡፡ግን የአላህን ውዴታ ለመፈለግሲሉ (ፈጠሩዋት)፡፡ተገቢ አጠባበቋንም፤አልጠበቋትም፡፡ ከእነርሱም ለእነዚያ ላመኑት ምንዳቸውን ሰጠናቸው፡፡ከእነርሱም ብዙዎቹ አመጸኞች ናቸው፡፡››[385]

እንዲህ የሚል አመክንዮ ከዚህች አንቀፅ ላይ ይታነጻል፡

‹‹እዚህ ላይ ክርስቲያኖች አላህን ለማስደሰት ሲሉ ቢድዐ ፈጠሩ፣አላህም በቢድዐቸዉ አወገዛቸዉ፡፡ስለዚህ በጥሩ ኒያም ቢሆን የሚፈጠር ቢድዐ የተወገዘ ነዉ፡፡ ስለሆነም መዉሊድ ዓላማዉና መነሻዉ ጥሩ ቢሆንም የተወገዘ ነዉ››

የሚገርመዉ አንቀጿን ካስተዋልናት ከዚህ በተቃራኒዉ የሆነ መልዕክት የምታስተላልፍ ሆና እናገኛታለን፡፡ በጣም የሚገርመዉ ደግሞ የብዙሀን የተፍሲር ሊቃዉንት ግንዛቤ ወንድሞች ካሰቡት በተቃራኒዉ መሆኑ ነዉ፡፡ በመጀመሪያ እኛዉ እንያት፡-

[385] አልሀዲድ 27

1. ክርስቲያኖች አላህን ለማስደሰት ሲሉ ምንኩስና የሚባል ቢድዐ ፈጠሩ፤

2.ይህን ቢድዐ አላህ አልጻፈባቸዉም ወይም አላዘዛቸዉም፤

3. በዚያ ቢድዐ ላይ ሳይጸኑ ቀሩ፤ጀምረዉ አቋረጡት፤

3. አላህም ፡- ‹‹በጀመራችሁት የቢድዐ ጎዳና መጽናት ሲገባችሁ ለምን አቋረጣችሁት?›› በማለት ወቀሳቸዉ፡፡

ይህ የአንቀጿ መልዕክት አላህ የፈጠሩትን ቢድዐ እንደወደደላቸዉ እንጅ እንደጠላባቸዉ አያመለክትም፡፡ ለምን? ቢጠላባቸዉ ኖሮ ‹‹ለምን አቋረጣችሁት›› ብሎ መዉቀስ አልነበረበትም፡፡ ከዚያ ይልቅ ‹‹እሰየዉ፤ ይህን ክፉ ነገር በማቆማችሁ ደግ አደረጋችሁ›› ሊላቸዉ ይገባል፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰዉ አስካሪ መጠጥ ሲጠጣ ኖሮ ቢያቆም፡ ‹‹ለምን አቆምክ?›› ብለን አንወቅሰዉም፡፡ ‹‹ደግ አደረግክ›› እንለዋለን እንጅ፡፡ በሌላ በኩል ግን የሌሊት ሶላት ጀምሮ ካቆመ ‹‹ለምን አቆምከዉ›› በማለት መዉቀሳችን አግባብ ይሆናል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ለዐብደላህ እብን ዐምር፡- ‹‹እንደ እገሌ አትሁን፤የሌሊት ሶላት ጀምሮ ነበር አቆመዉ››[386] በማለት እንደመከሩት፡፡ ‹‹መልካም ቢድዐ አለ›› የሚሉ ዑለሞች ከሚያቀርቧቸዉ መረጃዎች መካከል ይህ አንዱ ነዉ፡፡ ኢማም ቁርጡቢ እንዲህ ጽፈዋል፡-

وهذه الآية دالة على أن كل محدثة بدعة فينبغي لمن ابتدع خيرا أن يدوم عليه ولا يعدل عنه إلى ضده فيدخل في الآية

‹‹ አዲስ ነገር ሁሉ ቢድዐ እንደሚባልና መልካም ቢድዐን የፈጠረም በዚያዉ ላይ መጽናት እንደሚገባዉ ይህች አንቀጽ ታመለክታለች፡፡ በጀመረዉ ቢድዐ ላይ ያልጸና በዚህች አንቀጽ ከተገሰጸዉ ዉግዘት ዉስጥ ይገባል፡፡››[387]

386

[387]ተፍሲር አልቁርጡቢ ለአንቀጹ ከሰጡት ማብራሪያ

‹‹የተወቀሱት ቢድዐዉን የፈጠሩት ትዉልዶች አይደሉም›› የሚል ዕይታም ተንጸባርቋል። ለምን? ቢድአ የፈጠረዉ ትዉልድ አባላት በቢድዐቸዉ ላይ ስለጸኑ። እንግዲያዉስ የተወቀሱት አባቶቻቸዉ በፈጠሩት መልካም ቢድዐ ላይ ያልጸኑት ቀጣዮቹ ትዉልዶች ናቸዉ። ቁርጡቢን ልጥቀስ፦

ابتدعها هؤلاء الصالحون { فما رعوها } المتأخرون { حق رعايتها }

‹‹ደጋጎች ቢድዐዋን ፈጠሩ፤(ጸኑባትም)። የኋለኞች ግን በዚያች ቢድዐ ላይ አልጸኑም።››[388]

ቢድዐዉን የፈጠሩት ወገኖች ***ደጋጎች*** እንደሆኑና ምንዳም እንዳገኙ፣ በተፈጠረችዉ ቢድዐ ያልጸኑት ደግሞ ***‹‹አመጸኞች››*** ተሰኝተዉ መወቀሳቸዉን አንቀጹና በርሱ ዙሪያ የተሰጡ ትንታኔዎች ያመለክታሉ። ይህኛዉ አተረጓጎምም ከላይ ያሰፈርነዉን ሀሳብ ያጠናክራል። ቢድዐዉን የፈጠረዉን ትዉልድ ያመሰግናል። አባቶቹ በፈጠሩት ቢድዐ ላይ ያልጸናዉን ትዉልድ ደግሞ ይወቅሳል። በሁለቱም አተረጓጎሞች አላህ ቢድዐቸዉን መዉደዱንና በርሱ ላይ አለመጽናታቸዉን ማዉገዙን እንረዳለን። **ተፍሲር እብን ጀሪር አል ጦበሪ፣አል-ሙንተኽብ፣ሩሀል መዐኒ (አሉሲ)፣አል-በገዊ፣ፈኽሩዲነ ራዚ፣እና ሌሎች ሙፈሲሮችና የተፍሲር ኪታቦችም** የዚሁ ተመሳሳይ ማብራሪያ ይዘዋል። እብንጀሪር በተፍሲር ምሁራን መካከል ልዩነት ያለዉ ‹‹በቢድዐዉ ላይ ያልጸናዉ ቢድዐዉን የፈጠረዉ ትዉልድ ነዉ ወይስ ቀጣዮቹ ትዉልዶች?›› በሚለዉ አጀንዳ ዙሪያ መሆኑን ጠቅሰዋል።[389]የትኛዉም ይሁን ከላይ የተሰጠዉን ማብራሪያ የሚያጸና እንጅ የሚያፋልስ አይደለም። ይህን ግንዛቤ በልቦናችን ይዘን ኢማም እብን ከሲርን ማብራሪያ (አፈሳሰር) እንመልከት። ቢድዐ መፍጠራቸዉን፣በፈጠሩት ቢድዐ ላይ

[388] ያስፈዉ ምንጭ

[389]ጃሚዑል በያን ፊተአዊሲል ቁርአን (አልጦበሪ)

አለመጽናታቸውንና አላህም እንደወቀሳቸው ከገለጹ በኋላ የወቀሳቸውን ምክንያት ሲያብራሩ፡-

وهذا ذم لهم من وجهين، أحدهما: في الابتداع في دين الله ما لم يأمر به الله. والثاني: في عدم قيامهم بما التزموه مما زعموا أنه قربة يقربهم إلى الله، عز وجل.

‹‹አላህ በሁለት መልኩ ወቀሳቸዉ፤አንደኛ አላህ ያላዘዘዉን ነገር በአላህ ዲን ዉስጥ በመጨመራቸዉ፣ሁለተኛ ወደ አላህ ያቃርበናል ብለዉ በገመቱት ቢድዐ ላይ ባለመፅናታቸዉ፤››[390]

እብን ከሲር ያነሷቸው ሁለቱ ነጥቦች እርስ በርስ የሚጣረሱና አብረዉ የማይሄዱ ናቸዉ፡፡ ቢድዐ መፍጠራቸውን አላህ ከጠላባቸዉ፣እርሱ በጠላዉ ነገር ላይ ባለመጽናታቸዉ ሊመሰገኑ እንጅ ሊወቀሱ አይገባም፡፡ አላህ ‹‹በወንጀል ላይ ለምን አልጸናችሁም?›› ብሎ ባሮቹን አይወቅስም፡፡ ባለመጽናታቸዉ ስለወቀሳቸዉ፣ያልጸኑበት ነገር መልካም ነዉ ማለት ነዉ፡፡ እብን ከሲር ከሁለቱ አንዱን መምረጥ ነበረባቸዉ፡፡ ከዚህ የተነሳ ይህች ገለፃቸዉ ከብዙሀን የተፍሲር ሊቃዉንት ሀሳብ በመለየታቸዉ የተፈጠረች ግድፈት ናት፡፡ ሰዉ ከመሆናቸዉ አኳያ ይህ የሚጠበቅ ነዉ፡ ፡ አላህ ይዘንላቸዉ፡፡ አልአሉሲ እንዲህ ብለዋል፡-

وليس في الآية ما يدل على ذم البدعة مطلقاً، والذي تدل عليه ظاهراً ذم عدم رعاية ما التزموه

‹‹በአንቀጹ ዉስጥ ቢድዐን በጥቅሱ የሚነቅፍ ክፍል የለም፡፡ በጀመሩት ቢድዐ ላይ ባለመጽናታቸዉ ነዉ የተወቀሱት፡፡››[391]

390 ተፍሲር እብን ከሲር
391 ሩሀል መዐኒ

እብን ዐሹርና እብን ጀሪር በበኩላቸዉ ሰዎቹ የፈጠሩትን ቢድዐ አላህ እንደወደደላቸዉ የሚያመለክቱ ሁለት ነጥቦች ከአንቀጹ ወስጥ እንደሰፈሩ ጽፈዋል፡-

1.ቢድዐዉን የፈጠሩት የአላህን ወዴታ ሸተዉ መሆኑን መግለጹ፣

2. ‹‹ለእነዚያላመኑትምንዳቸውንሰጠናቸው›› የሚለዉ ክፍል፡፡ምክንያቱም እነዚያ ያመኑት የተሰኙት በቢድዐዉ ላይ የጸኑት እንደሆኑ የሚያመለክት የዑለሞች ቃል ስላለ፡፡ እብን ዐሹርን ልጥቀስ፡-

والمعنى:وابتدعوا لأنفسهم رهبانية ما شرعناها لهم، ولكنهم ابتغوا بها رضوان الله، فقبلها الله منهملأن سياق حكاية ذلك عنهم يقتضي الثناء عليهم

‹‹የእንቀጹ ትርጉም ስራሳቸዉ እኛ ያልደነገግንባቸዉን ምንኩስና ፈጠሩ፣ግና የአላህን ዉዴታ በዚህች ፈጠራቸዉ ከጀሱ፣አላህም ተቀበሳቸዉ፣ማለት ነዉ፡፡ የእንቀጹ ቅኝት በፈጠራቸዉ እንደተወደሱ ያሳያል፡፡››[392]

እብን ጀሪርን ደግሞ ልጥቀስ፡-

فدل بذلك على أن منهم من قد رعاها حق رعايتها، فلو لم يكن منهم من كان كذلك لم يكن مستحق الأجر الذي قال جل ثناؤه فيه: فآتينا الذين آمنوا منهم أجرهم

‹‹ከመካከላቸዉ በቢድዐዋላይ የጸና ወገን እንደነበር ያመለክታል፡፡ የጸና ወገን ባይኖር ኖሮ‹*ለነዚያ ላመኑት ወገኖች ምንዳ ሰጠናቸዉ*› በማለት ስተገለጸዉ ምንዳ ተገቢ አይሆኑም ነበር››[393]

[392]አልተህሪር ወተንዊር
[393] ተፍሲር እብን ጀሪር

ኢትዮጵያዊያኑ ዐሊሞች ሸኽ ሙሀመድ ሳኒ ሀቢብና ሸኽ ሰይድ ሳድቅ የመረጡትና ከአማርኛዉ ተፍሲር ዉስጥ ያሰፈሩት አተረጓጎምም አለ። ይኸዉም ካለፈዉ መልዕክት ጋር አያይዘዉ ተረድተዉታል፦

وَجَعَلْنَا فِي قُلُوبِ الَّذِينَ اتَّبَعُوهُ رَأْفَةً وَرَحْمَةً وَرَهْبَانِيَّةً ابْتَدَعُوهَا مَا كَتَبْنَاهَا عَلَيْهِمْ إِلَّا ابْتِغَاءَ رِضْوَانِ اللَّهِ فَمَا رَعَوْهَا حَقَّ رِعَايَتِهَا

‹‹በእነዚያም በተከተሉት (ሰዎች) ልቦች ዉስጥ መስዘብንና እዝነትን፣አዲስ የፈጠሩዋትንም ምንኩስና አደረግን።በእነርሱ ላይ (ምንኩስናን) አልጻፍናትም። ግን የአላህን ዉዴታ ለመፈለግ ሲሉ (ፈጠሩዋት)።ተገቢ አጠባበቋንም፤ አልጠበቁትም።››

ይህ አተረጓጎም አላህ ምንኩስናን ባይደነግግባቸዉም ከልቦናቸዉ ዉስጥ እንዳኖራት፣ማለትም ትዝ እንዲላቸዉ ማድረጉን ይገልጻል። ከዐረብኛ ስዋሰዉ (ነህዉ) እና ከዐቂዳ አኳያም -ዑለሞቻችን በነዚህ ሁለት መስኮች የነበራቸዉ ብቃት ፍጹም አስተማማኝ ስለነበር- እንከን የለበትም። ደግም ሆነ ክፉ ነገር አስታዉሰን የምንሰራዉ አላህ እንድናስታዉሰዉ ስላደረገን ብቻ ነዉ። ይህ አተረጓጎም ከላይ ካሰፈርነዉ ማብራሪያ ጋርም አይጋጭም። ምክንያቱም ምንኩስናን አላህ እንዳልጻፈባቸዉ እና እነርሱ ራሳቸዉ የአላህን ዉዴታ ሽተዉ እንደፈጠሯት ይገልጻልና። ሆኖም ለተራዉ አንባቢ የሚያስነሳቸዉ ብዙ ጥያቄዎች አሉ፦

- በልቦናቸዉ ላይ አደረግናት ካለ በኋላ አልጻፍናትም ማለቱ፣
- ዝቅ ብሎ ደግሞ የአላህን ዉዴታ በመሻት ፈጠሯት ማለቱ ወዘተ፣

እነዚህንና ሌሎችን የቀዳ ቀደር ጥያቄዎች ለመመለስ በዑለሞች የተኬደዉ ረዥም መንገድ ለዉይይታችን ፋይዳ ስለሌለዉ አልጠቅሰዉም። የሀገራችን ዑለሞች ከብዙሀን የተፍሲር ሊቃዉንት ሀሳብ እንዳልወጡ ከተረዳን ይበቃል።

ዉይይታችንን ስናጠቃልለዉ፡ ‹‹አላህ በዚች አንቀጽ ቢድዐን አዉግዟል›› የሚለዉ የኢማም እብን ከሲርና የኢማም ሻጢቢ ግንዛቤ ስህተት ነዉ። እንዲያዉም አላህ ያላዘዘዉን መልካም ቢድዐ መፍጠር እንደሚቻልና የሚያስወቅሰዉ በርሱ ላይ አለመጽናት መሆኑን አንቀጹ ያስረዳል። ዑለሞች ከላይ ከሰጡት ማብራሪያ አኳያ ሲታይ፡-‹‹አባቶቻችሁ የአላህን ዉዴታ በመሻት በፈጠሩት የመዉሊድ መታሰቢያ ላይ ጽኑ፤ካለበለዚያ አባቶቻቸዉ በፈጠሩት ቢድዐ ላይ እንዳልጸኑት ክርስቲያኖች ተወቃሾች ናችሁ›› የሚል መልዕክት ቢቀሰምባት ስህተት አይሆንም። ስለዚህ ለታሰበዉ ተቃዉሞ የምትዉል አንቀጽ አይደለችም። እንዲያዉም ለመዉሊድ አፍቃሪዎች ጥሩ መረጃ ትሆናለች። ‹‹ደጋጎቹ አባቶቻችን መልካም ቢድዐ ፈጠሩ። እነርሱ በቢድዐቸዉ ላይ ስለጸኑ ‹ከእነርሱምስእነዚያላመኑትምንዳቸውንሰጠናቸው› ባለዉ መሠረት ከአላህ ምንዳ ያገኛሉ። አባቶቻችን በፈጠሩት ቢድዐ ላይ እኛ ካልጸናን ግን፡- ‹ከእነርሱምብዙዎቹአመጸኞችናቸው› የሚለዉ ወቀሳ ይደርስብናል››ቢሉ ከአንቀጹ መንፈስ አልወጡም።

ከሌሎች ጋር መመሳሰል

ነብዩ ﷺ፡-‹‹ከሌሎች ጋር የተመሳሰለ የነርሱ ወገን ነዉ።››ብለዋልና የነብዩን ﷺ ልደት ማክበር የእየሱስን ልደት ከሚያከብሩት ክርስቲያኖች ጋር ስለሚያመሳስል የተወገዘ ነዉ፣ የሚል ሂስም ይነሳል። ሸኽ እብን ባዝ ይህችን ክስ እንዲ ሲሉ ጠቅሰዋታል፡-

بل هو من البدع المحدثة، ومن التشبه بأهل الكتاب من اليهود والنصارى في أعيادهم

‹‹መዉሊድ አዲስ የመጣ ቢደድዐ ሲሆን፣ከአይሁዶችና ከክርስቲያኖች ጋር በባዕላቶቻቸዉ መመሳሰል ነዉ።››[394]

[394]እብን ባዝ፣ሁክሙል ኢህቲፋል...፣ገጽ 4

‹‹ተሸቡህ›› /መመሳሰል/ የምትባለዋ ጽንሰ ሀሳብ ያለአግባብ እየተለጠጠች ብዙ ጣጣ በማምጣት ላይ ስለሆነች በሌላ መጽሀፌ ራስዋን ችላ እተነትናታለሁ፡፡ እዚህ ላይ ግን መሠረታዊ ግንዛቤዎችን በማስጨበጥ ብቻ እወሰናለሁ፡፡

1. ሀይማኖታዊ ባልሆኑ ጉዳዮች፣ለምሳሌ በአመጋገብ፣በአለባበስ፣ በአረማመድ ወዘተ ከሌሎች ወገኖች ጋርመመሳሰል በራሱ የተከለከለ አይደለም፡፡ ሙስሊሙ እንደክርስቲያኑ እንጀራና ቆጮ መመገቡ፣ሱሪና ሸሚዝ መልበሱ...በራሱ ችግር የለውም፡፡እንዲያውም በደግ ነገር ከነርሱ ትምህርት መቅሰም ይበረታታል፡፡ *‹‹ጥበብ የሙእሚን ሀብት ናት፡፡የትም ካገኛት ይወሰዳት››* የሚለዉ ነብያዊ መመሪያ ይህንኑ ያመለክታል፡፡ ጀርመኖች በሥራ ዲሲፕሊንና ጥራት የታወቁ ናቸዉ ይባላልና ከነርሱ ጋር በዲሲፕሊን ብንመሳሰል፣ቻይናዎች ሠርተዉ የማይደክማቸዉ ትጉዎች ስለሆኑ ትጋትን ከነርሱ ብንወስድ፣የአዉሮፓዉያንን ጽዳትና ሰአት የማክበር ባህል ብንቀስም፣ እንወደሳለን እንጅ አንወቀስም፡፡ በክፉ ነገር ከነርሱ ቀርቶ ከሙስሊምም ጋር መመሳሰል ደግሞ ያስወግዛል፡፡ ለምሳሌ እነርሱ ሲጠጡ አብሮ መጠጣት፣ተቀላቅለዉ ሲጨፍሩ አብሮ መጨፈር፣እርቃን የሆነ አለባበስ ወዘተ፡፡

2. ሀይማኖታዊ በሆኑ ጉዳዮችም እኛ በቁርአን ወይም በሀዲስ ታዘን የምንፈፅመዉ ነገር ከነርሱ የአምልኮ ተግባር ጋር ባጋጣሚ ተመሳስሎ ቢገኝ ችግር የለዉም፡፡ ለምሳሌ አይሁዶች የዐሹራ ቀን ሲጾሙ እኛም እንጾማለን፡፡ በተግባር ሲታይ ከነርሱ ጋር ተመሳስለናል፡፡ ሆኖም የምንጾመዉ በሀይማኖታችን ስለታዘዝን እንጅ እነርሱን ለመምሰል ብለን ባለመሆኑ የሚበረታታ እንጅ የሚነቀፍ ተግባር አይደለም፡፡ የዐረብ ጣኦታዉያን ሀጅ ያደርጉ ነበር፡፡ እኛም እናደርጋለን፡፡ ሆኖም የተግባር ምንጫችን እስልምና ስለሆነ ይህ መመሳሰል አይጎዳንም፡፡

3. መመሳሰል የሚከለከለዉ የሌሎች ሀይማኖቶች የእምነት መገለጫ በሆኑና በኛ ሀይማኖት ባልታዘዙ ጉዳዮች ሲሆን ነዉ፡፡ ለምሳሌ

ክርስቲያኖች የሚያንጠለጥሉትን ማተብ ማንጠልጠል፣የፕሮቴስታንት ቀሳዉስት ከሸሚዛቸዉ ላይ የሚያደርጓትን ነጭ ሪባን ማድረግ፣ የኦርቶዶክስ ቀሳዉስትን የቅስና ልብስ መልበስ፣መስቀል ማንጠልጠል ወይም መነቀስ፣ጥምቀትንና ፋሲካን ማክበር፣ለቅድስ ዮሀንስ ዶሮና በግ ማረድ ወዘተ፡፡

መመሳሰል/ተሸቡህ/ የሚባለዉን ጽንሰ ሀሳብ በዚህ መንገድ ካልተረዳነዉ ጣጣ ዉስጥ እንገባለን፡፡ አንዳንዶች ከፊረንጆች ጋር ላለመመሳሰል ሱሪ አዉልቀዉ ቀሚስ ወይም ሸርጥ ያደርጋሉ፣በረባሶ ጫማ ይጫመታሉ፡፡ የሚጠቀሙበት ስማርት ሞባይል፣የሚነዱት ቶዮታ ኤክሰኪዩቲቭ መኪና፣የሚያዩት ቲቪ፣ለሀጅ የሚጓዙበት አዉሮፕላን፣ቤታቸዉን ያነጹበት ቁሳቁስ፣የቤታቸዉ ዲዛየን፣መብራቱ፣የመታጠቢያ ገንዳዉ፣ የሚረገጡት ሴራሚክስ፣ጥርሳቸዉን የሚፍቁበት ሳሙናና ቡሩሽ ...ከፊረንጅ የመጣ መሆኑን፣ልክ እንዳማራ ክርስቲያን እንጀራ፣ እንደጉራጌ ክርስቲያን ቆጮና ክትፎ፣እንደፈረንጆች ፒዛና የጣልያን ፓስታ እንደሚመገቡ... ይዘነጉታል፡፡ በሌላ በኩል ጀላብያ በመልበሳቸዉ ልክ እንደነርሱ ጀላብያ ከሚለብሱ የዐረብ ክርስቲያኖች ጋር መመሳሰላቸዉን አያስተዉሉም፡፡

ሸኽ እብን ባዝ መዉሊድን፡- ***‹‹ክርስቲያኖችንና አይሁዶችን በነርሱ ባዕላት መመሳሰል ነዉ››*** ማለታቸዉ ልክ ይሆን የነበረዉ ሙስሊሞች በሀይማኖታቸዉ ያልተፈቀደን የክርስቲያን ባዕል ቢያከብሩ ኖሮ ነዉ፡፡ የዉይይታችን ጭብጥ ‹መዉሊድ በሸሪዐዉ ይበረታታል ወይስ አይበረታታም?›› የሚል ነዉ፡፡ ከተበረታታ ከየትኛዉም ሀይማኖት የባዕል አፈጻጸም ጋር ቢመሳሰል ችግር እንደሌለዉ ተመልክተናል፡፡ ያልተፈቀደ ስለመሆኑ አሳማኝ መረጃ ከቀረበ ደግሞ ረኸርም መንገድ መሄድ አያስፈልግም፡፡ መፈቀዱ ወይም አለመፈቀዱ ከተረጋገጠ በኋላ በተከታይነት ሊደረስበት የሚገባዉን ድምዳሜ ወደዚህ መጎተት ‹‹ከፈረሱ ጋሪዉ..›› የሚሉት ዓይነት ግድፈት ነዉ፡፡የመዉሊድ ነቃፊዎች ይህችን

ነጥብ ይስቷታል ብየ አልገምትም። ሆኖም ወደፊት ለምጠቅሰዉ ሰበብ እየደጋገሙ ያነሷታል።

ሀሳባችንን ወደርዕሳችን ስንመልሰዉ መዉሊድ በሀይማኖታችን መረጃዎች መሠረት የተፈቀደ በመሆኑ ላይ ከተግባባን ከክርስቲያን ወይም ከሂንዱ እምነት ጋር ባጋጣሚ ተመሳስሎ ቢገኝ ችግር የለዉም። የኛ ሱጁድ ከሌሎች ሀይማኖቶች የሱጁድ ሥርዓት፣የኛ ጾም ከሌሎች ሀይማኖቶች የጾም ሥርዓት ጋር ባጋጣሚ ተመሳስሎ ቢገኝ እንደማለት።

የይዘት ተቃዉሞ

በመዉሊድ ላይ ሌላዉ የሚነሳዉ ተቃዉሞ ይዘቱን መሠረት ያደረገ ነዉ። ‹መዉሊድ በራሱ የተፈቀደ ነዉ ብንል እንኳ ይዘቱ ሀራም ወይም ቢድዐ ያደርዋል› የሚል ነቀፌታ ይሰነዘራል። ከሸኽ እብን ባዝ፣ከሸኽ ዑሰይሚን፣ከሸኽ አልባኒ፣ከሸኽ ቱወይጅሪና ከሌሎች የመዉሊድ ነቃፊ ኪታቦች ያገኘኋቸዉን አንኳር ሂሶች ቀጥሎ እናያቸዋለን።

1. ሴቶችና ወንዶች ተቀላቅለዉ ይጨፍሩበታል፡- ሸኽ እብን ባዝና ሌሎችም የሚደጋግሚትን ክስ ልጥቀስ፡-

إن غالب هذه الاحتفالات بالموالد مع كونها بدعة لا تخلو من اشتمالها على منكرات أخرى؛ كاختلاط النساء بالرجال، واستعمال الأغاني والمعازف، وشرب المسكرات والمخدرات، وغير ذلك من الشرور

‹‹መዉሊድ በራሱ ቢድዐ ከመሆኑ በተጨማሪ አብዛኛዎቹ የመዉሊድ ባዕሎች የወንድና የሴት መቀላቀል፣ዘፈንና የሙዚቃ መሳሪያ፣ አስካሪ መጠጥ፣ እጾችና ሌሎች እኩይ ነገሮች ይስተናገዱባቸዋል።››[395]

እብንል ዐለዊ በመካና በመዲና እስካሁንም ድረስ በቀጠሉ የመዉሊድ መታሰቢያዎች ላይ ይህ ፈጽሞ ታይቶ እንደማይታወቅ በአንክሮ ይናገራሉ። መታዘብ የፈለገ ከዝግጅቶቹ ላይ ይታደም ዘንድ ደጋግመዉ ጋብዘዋል። ይህ በሆነበት ሁኔታ በዚህ ክስ ላይ ችክ ማለት የመዉሊድንና የአፍቃሪዎቹን ስም ለማጥፋት የሚደረግ ርካሽ የፕሮፓጋንዳ ጥረት መሆኑንም አስምረዉበታል።[396]

በሀገራችን የመሻኢኾች የመዉሊድ ረዥም ታሪክም ይህ ፈጽሞ አልተስተዋለም። ስለዚህ የሸኽ እብን ባዝን ‹‹*ጋሊብ›› /አብዛኛዎቹ/*

[395] ሸኽ እብን ባዝ፣ሁክሙል ኢህቲፋል...፣ገጽ 4
[396] አልኢዕላም ገጽ 37

የሚለዉን ገለጻ የመጸየፍ ስሜት በመፍጠር ለተቃዉሚቸዉ ጉልበት ለማከል የተጠቀሙት ማጋነን ነዉ ብለን ከማለፍ በስተቀር ለዉይይታችን ጭብጥ አንዳችም ፋይዳ የለዉም። የጾታዎች ቅልቅል ወይም ሌላ እንከን የታየባቸዉ አጋጣሚዎች ካሉም -ኢማም እብንል ሀጅ ወይም ኢማም ረሽድ ሪዳ እንዳደረጉት-እንዲታረሙ መጠቆም እንጅ ሂደቱን አጠቃላይ ማዉገዝ ተገቢ አይደለም። **በሰርግ ላይ የጾታዎች ቅልቅል ስለታየ ሰርግ ሀራም ነዉ፣ሀጅ ላይ ሁለቱም ጾታዎች ያለገደብ ስለሚቀላቀሉ ሀጅ ሀራም ነዉ፣መርካቶ ዉስጥ የጾታዎች ቅልቅል ስለሚበረክት ንግድ ሀራምነዉ፣ማር ጠጅ ስለሚሰራበት ንብ ማርባት ሀራም ነዉ፣ገብስ ቢራ ስለሚጠመቅበት ገብስ ማምረት ሀራምነዉ ወዘተ የሚል አመክንዮ በጣም የተሳሳተ ነዉ።**

2. በመዉሊድ ማዕዶች ላይ አስካሪ መጠጥ ይቀርባል፡- አስቀያሚ የስም ማጥፋት። ሸኽ እብን ባዝም አንስተዉታል።[397]እአላህ በሚዘከርበት፣መጭዉ ዓለም በሚታወስበት፣ነብዩ ﷺ በሚሞገሱበትና በምናብ ከአጠገብ ያሉ ያህል በሚሰማበት መድረክ አስካሪ መጠጥ ይታደላል ብሎ መናገር ርካሽ ፕሮፓጋንዳ እንጅ ሌላ ሊሰኝ አይችልም። ይህን ለማረጋገጥ ሩቅ መሄድ አያስፈልግም። በአንዋር ወይም በኑር (በኒን) መስጊዶች የሚደረጉ የመዉሊድ መታሰቢያዎችን ቀርቦ ማየት በቂ ነዉ።

3. ከመዉሊድ ላይ የሚሳተፉ ግለሰቦች በአብዛኛዉ ዲን የሌላቸዉ ፋሲቆች ናቸዉ፡- ሌላ አስቀያሚና አስነዋሪ የስም ማጥፋት ሂደት። መዉሊድን ከመነሻዉ አንስቶ በሀሳብ የደገፉትም፣በተግባር ያራመዱትም የዚህ ዲን አስኳል ስብዕናዎች፣ታላላቅ ዐሊሞችና ዳዒዎች ናቸዉ። እነርሱን በፊስቅ መጠርጠር ጋጠወጥነት ይመስለኛል። ማንነዉ ፋሲቅ? ፍትሀዊነቱ የተመሠከረለት ንጉስ መዞፈር? ኢማም አቡ ሻማህ?

[397] ከሳይ የቀረበዉን ጥቅስ ይመልከቱ፤

ኢማም እብን ሀጀረልዐስቀላኒ? ኢማም ሱዩጢ? ዶ/ር ዩሱፍ አልቀረዳዊ? ዶ/ር ረመዳን ቡጢ? ዶ/ር ናብሊሲ? ዶ/ር ወህበተ ዙሀይሊ? ወይስ የሀገራችን ታላላቅ ዑለሞች፣እነጀማ ንጉስ፣እነ ጀማሉዲን አልዐኒ፣ የዳና ከዋክብት፣እነሀጅ መ·ሀመድ ሳኒ ሀቢብ፣እነ አብራት ሸኽ፣የቃጥባሪ ሸኽ? የሰሜኑ ኃያል ሸኽ ለጋስ አደም? ከነዚህ ሁሉ ዉስጥ የትኛዉ ነዉ ፋሲቅ? የክርክር ግለት ስብዕናን ወደዚህ ደረጃ ሲያሽቆለቁለዉ ያሳዝናል።

4. የመዉሊድ ግጥሞችና መንዙማዎች ማጋነን፣ ሽርክና ተወሱል የተቀላቀለባቸዉ ናቸዉ፡-ሸህ እብን ባዝ እንዲህ ጽፈዋል፡-

وقد يقع فيها ما هو أعظم من ذلك وهو الشرك الأكبر، وذلك بالغلو في رسول الله – صلى الله عليه وسلم – ، أو غيره من الأولياء، ودعائه والاستغاثة به وطلبه المدد، واعتقاد أنه يعلم الغيب، ونحو ذلك من الأمور الكفرية التي يتعاطاها الكثير من الناس حين احتفالهم بمولد النبي – صلى الله عليه وسلم – وغيره ممن يسمونهم بالأولياء.

‹‹ከነዚህም የባሰ ነገር በመዉሊድ ማዕዶች ላይ ይከሰታል፤እርሱም ትልቁ ሽርክ ነዉ።። ማስትም ስአላህ መልዕክተኛና ወልዮች ብስዉ ስሚጠሯቸዉ ሰዎች የተጋነነ ክብር መስጠት፣ሩቅ ሚስጥር እንደሚያዉቁ መናገር እና መሰል ብዙ ሰዎች የሚተገብሯቸዉ የኩፍርና የሽርክ ድርጊቶች ይስተዋላሉ።››[398]

በመንዙማ ግጥሞች ላይ የሚሰነዘሩ ሂሶች ሁለት ዓይነት ገጽታ አላቸዉ፡

1.ፊቅሀዊ ልዩነትን መሠረት አድርገዉ የሚነሱ ክሶች አሉ።። ለምሳሌ *‹‹በነብዩ ወይም በደጋግ ሰዎች ተወሱል ማድረግ ቢድዐ ነዉ››* ብለዉ የሚያስቡ ሰዎች በተወሱል የተሞሉ የመንዙማ ግጥሞችን ይነቅፋሉ።። አንዳንዶች ተወሱል ሽርክ ይመስላቸዉና ይቸገራሉ።። መብታቸዉ ቢሆንም ተወሱልን በተመለከተ ሌላ እይታ መኖሩን ግን መዘንጋት

[398] እብን ባዝ፣ሁክሙል ኢህቲፋል...ገጽ 4

የለባቸውም።እንዲያውም የአራቱም መዝሀቦች ብዙሀን ዑለሞች (ጁምሁር) በነብዩ ﷺ ተወሱል ማድረግ የሚፈቀድ ብቻ ሳይሆን የሚወደድ ተግባር መሆኑን ያሰምሩበታል።[399] ኢማሙ ማሊክና ደረሶቻቸዉ[400]፣ኢማሙ አህመድና ተከታዮቻቸዉ[401] ኢማሙ ሻፊዒና የመዝሀባቸዉ ሊቆች ይህን ድጋፋቸዉን በግልጽ አሳይተዋል።[402] ኢማም አቡ ሀኒፋ ጽንሰ ሀሳቡን ሳይሆን የቃላት አጠቃቀምን በማረም (ለምሳሌ ነብዩ ባንተ ላይ ባላቸዉ መብት ይሁንብህ አይባልም በማለት) አጀንዳዉን አጽድቀዉታል። ይህ አባባልም ቢሆን እንደሚቻል ደረሶቻቸዉ አረጋግጠዋል።[403] ኢማም ሸዉካኒና ሌሎች ደግሞ በነብዩ ﷺ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ደጋጎችም ክብርና ልቅና ተወሱል ማድረግ እንደሚቻል ጽፈዋል።[404] በጥቅሉ የአራቱም መዝሀቦች ተከታይ ዑለሞች ለተወሱል ጽድቅ ችረዋል።[405] በመረጃ ረገድም ጠንካራዉ ይህ የብዙሀን እይታ ነዉ። በተለይም በነብዩ ﷺ ተወሱል ማድረግን ከሸኽ እብን ተይሚያህ በፊት ለ700 ዓመታት በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ የተቃወመዉ አንድም ሁነኛ ዐሊም የለም። ከሸኽ እብን ተይሚያህ አፈንጋጭ ፈትዋዎች መካከል አንዱ ይህ እንደሆነ ሀያሲዎቻቸዉ ይገልጻሉ።[406] ከሀገራችን የጥንት ዑለሞች መካከል ተወሱልን የነቀፈ እንደሌለ በግል

---

399 አል-መዉሱዐቱል ፊቅህያ፣ማዳ ‹‹ተወሱል››

400 ቀስጦላኒ፣ሸርሁል መዋሂብ፣8/304-305

401 ናስረዲን አልባኒ፣አተወሱል፣ገጽ41፣እብን ቁዳማ፣አልሙግኒ መዐ ሸርህ፣3/588

402 አልመጅሙዕ 8/274

403 ፈትሁል ቀዲር 2/337

404 ሸዉካኒ፣ቱህፈቱ ዛኪሪን፣ገጽ 37

405 ሙሂቀ ተቀዉል ፊመስአስቲ ተወሱል፣አልመዉሱዐቱል ፊቅህያ እና ሌሎችንም ይመልከቱ፤

406 ወሂቢ ሱለይማን አልጋዉንጅ ‹‹ሙሂቀ ተቀዉል..፣ሀዉስተወሱል ወል ኢስቲጋሳ..እና ከሊመቱን ሀዲአህ...›› የተሰኙ ድርሳናት በጋራ ስታተሙባቸዉ ኪታብ የጻፉት መግቢ፣ዳረ ሪሳላ አሳታሚ፣ደማስቆ፣2004

ባደረግኩት ጥናት አረጋግጫለሁ፡፡ ራሱን በቻለ መጽሀፍ ወደፊት እመለከተዋለሁ፡፡

ስለዚህ አንድን መንዙማ ተወሱል ስላለበት መንቀፍ፣ከርሱ ላይ ተነስቶም መዉሊድን መሀየስ ‹‹የኔን ሀሳብ ካልተከተላችሁ ወዮላችሁ›› የማለት ጽንፈኝነት ነዉ፡፡ ለዚያዉም በደካማና ባፈንጋጭ ሀሳብ አገር ማስቸገር ተገቢ አይደለም፡፡

2. ከክፉ ጥርጣሬ ወይም የሰዎችን ሀሳብ በክፉ ከመተርጎም የሚመነጩ ክሶችም አሉ፡፡ለምሳሌ *ቡሩዳህ* ከምትባለዉ የግብጻዊዉ ማዲህ የሸኽ ቡሰይሪ (ከ608-6997 ሂጅሪያ) *ሥራ* ዉስጥ ተከታይዋ ግጥም ክስ ሲበዛባታ አስተዉያለሁ፡-

يا أكرم الخلق مالي من ألوذ به

سواك عند حلول الحادث العمم

ነቢ የፍጡራን ሁሉ ዓይነታ

መከራዉ ሲያዳርስ ሲበረታ

እርስዎ እንጅ ማን አለልኝ

የምሸሸበት መከታ?

‹‹ብቸኛዉ መጠጊያ አላህ ሆኖ እያለ ረሱሉን ብቸኛ መጠጊያየና መሸሻየ ማለት ሸርክ ነዉ፡፡››› ነዉ የክሱ ጭብጥ፡፡ ብዙ የሰለፊ/ዉሀቢ ሸኾች በዚህችና መሰል ግጥሞቻቸዉ ሸኽ ቡሶይሪን ይነቅፋሉ፡፡ ለምሳሌ ሸኽ ዑሰይሚን በአንድ ፈትዋቸዉ ሰዉየዉን እንደጉድ ይወርዱባቸዋል፡፡ ከእስልምና ወጥተዋል ለማለትም ይዳዳቸዋል፡፡[407]ሸኽ እብን ባዝ *‹‹ታልቁ ሸርክ›› ወይም ‹‹ለነብዩ የተጋነነ ክብር መስጠት››* ያሉትን ሀሳብ በምሳሌ

[407] ፈታዋ ሙሂማህ ሲዐመቲል ኡማህ፣በኢብራሂም እብን ዑስማን አልፋሪስ የተሰበሰበ የፈትዋዎች ኪታብ፣የመጀመሪያ እትም 1413 ሂጅሪያ፣ገጽ 46 ይመልከቱ

ባያሳዩንም ይህችን የኢማም ቡሰይሪ ግጥም እዉስጡ እንደሚያካትቱ መገመት አያዳግትም።

ይህ ክስና ነቀፌታ የሰዉየዉን ሀሳብ በክፉ ከመጠርጠር የመነጨ ካልሆነ በስተቀር ሌላ ትርጉም ሊሰጠዉ እንደሚያስችግር ለግጥሟ በዐለሞች የተሰጡ ማብራሪያዎች ያመለክታሉ።[408] ለግጥሞቹ የተሰሩ ማብራሪያዎቹን (ሸርህ) አላነበቧቸዉም ለማለት እቸገራለሁ። ለቡሩዳህ በርካታ ዐለሞች ማብራሪያ አዘጋጅተዋል። ለምሳሌ ኢማም እብን ሂሻም አልሀንበሊ (እስከ 761 ሂ)፣እብን ሳጊ (እስከ 776 ሂ)፣እብን ጉማዳህ (እስከ 808 ሂ)፣ጀላሉዲን አልመሀሊ (እስከ 864 ሂ)፣ዐላኡዲን አልበስጣሚ (እስከ 875 ሂ)፣ዐሊ አልቀሳኒ (እስከ 891 ሂ)፣ኻሊደል አዝሀሪ (እስከ 905 ሂ)፣ሺሀቡዲን አህመድ እብን ሙሀመድ አልቀስጦላኒ (እስከ929 ሂ)፣ፈቂህ ኑረዲን ዐሊል ቃሪ (እስከ 1014 ሂ)፣ ሸይኽ አልባጁሪ (እስከ 1276 ሂ) ወዘተ ለቡሩዳ ግጥም ማብራሪያ አዘጋጅተዋል።[409]

የቡሩዳ ተችዎች ከነዚህ ማብራሪያዎች ዉስጥ አንዱን ገለጥ አድርገዉ ቢመለከቱ የጸሀፊዉን ሀሳብ በቀላሉ ይረዱ ነበር። ጸሀፊዉ እዚህ ላይ የተረከዉ የመጭዉን ዓለም ሁኔታና ‹መቃመን መህሙድ› የተሰኘዉን የነብያችን ታላቅ ደረጃ ነዉ። በዚያን ቀን አላህ ይቆጣል። ጸሀይ ወደ ሰዎች ጭንቅላት ትቀርባለች። የሰዉ ልጆች በጭንቅ ይዋጣሉ። መድረሻ ይጠፋቸዋል።አላህ ፍትሀዊ ፍርዱን ሰጥቶ ይገላገሉ ዘንድ እንዲለምኑላቸዉ ወደ ነቢ አደም ይሄዳሉ። የነቢ አደም ምላሽ ‹አልችልም› የሚል ይሆናል። ወደ ኑህ፣ኢብራሂም፣ሙሳ፣ዒሳ እየሄዱ ተመሳሳይ ጥያቄ ያቀርባሉ። ሁሉም ‹‹አንችልም›› የሚል መልስ

[408] ዶ/ር ዒሳ እብን ብደላህ እብን ሙሀመድ እብን ማኒዕ አልሁመይዲ፣አልቀዉሉል ሙቢን ፊቢያኒ ዒልሚ ኻተሚ ነብደን፣ ለሸኽ ዑሰይሚን ምላሽ የተሰጠበት ጥናታዊ ጽሁፍ ይመልከቱ፤

[409] ያስፈዉ ምንጭ፣ገጽ 9

ይሰጧቸዋል። ወደነብዩ ሙሀመድ ﷺ ሲሄዱ ግን የተለየ መልስ ያገኛሉ። ‹‹ይህን ሀላፊነት እኔ እወጣዋለሁ›› በሚል ቁርጥ ውሳኔ የሰውን ልጅ ከጭንቅ ሊታደጉ ከአላህ ፊት ሱጁድ ይወርዳሉ። አላህ የርሳቸውን መደፋት ሲያይ ቁጣዉ ይበርድና ‹‹ተነስ፤አማላጅነትህ ተቀባይነት አግኝቷል›› ይላቸዋል። **ይህን ክስተት የሚያብራራዉ ሀዲስ በቡኻሪ፣በሙስሊምና በቲርሚዚ ተዘግቧል።**

ሸኽ ቡሰይሪ በግጥማቸዉ የገለጹት ይህን እዉነታ ነዉ። የዚያን ቀን ሁላችንስ ብንሆን ከነብዩ ﷺ በስተቀር ምን መጠጊያ፣ማን አማላጅ አለን? አምላክማ ተቆጥቷል። ቁጣዉን ለማብረድ አማላጅ ሸቷል። ያ አማላጅ፣ ያ መጠጊያ የኛዉ ነብይ ﷺ ብቻ ናቸዉ።**ነብዩን ﷺ በዚህችም በመጭዉም ዓለም ከሌሎች ሰዎች የተለየ ተሰጥኦ የሌላቸዉ አስመስሎ የማቅረብና በዚህ አቅጣጫ የሚነገሩ ነገሮችን ሁሉ ‹‹ጉሉዉ›› እያሉ የማጣጣል አባዜ በስፋት መስተዋሉ ያሳዝናል።**

እንዲህ ዓይነት እዉነትን በዉብ ቋንቋ የገለጹ ግጥሞችን በክፉ ተረድቶ መዉሊድን ለማጣጣል መጠቀም ፍጹም አግባብ አይደለም።

የሙስሊም አደቡ የወንድምን አባባል እና ድርጊት በበጎ ጎኑ መረዳት እንጅ በጎዉን ወደ ክፉ መጠምለል ሊሆን አይገባም።

ነብዩ ﷺ፦ ‹‹ክርስቲያኖች ሚሳን እንዳሞገሱት አድርጋችሁ አታሞግሱኝ›› ባሉበት ሁኔታ የተጋነነ ሙገሳ ህጋዊነቱ ምን ያህል ነዉ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ እንደሚችል እገምታለሁ። የነብዩን አባባልና ስጋት ለመረዳት ክርስቲያኖች ለዒሳ በሙገሳቸዉ የሰጧቸዉን ደረጃ እንይ። ‹‹አምላክ ወይም የአምላክ ልጅ›› አሏቸዉ።**ስለዚህ የነብዩ አባባል ፍች ‹‹አታወድሱኝ›› ሳይሆን ‹‹በሙገሳችሁ የአምላክ አገልጋይነቴን ወሰን ጥሳችሁ በማለፍ ከአምላክ ጋር አታስተካክሉኝ›› ነዉ።**ከዚያ

ወዲህ ባለዉ፣ ዳርቻዉ የማይታወቅ፣በጉዞ የማይዘለቅ የክብራቸዉ መስክ ግን ያቅምን ያህል መሄድ ይቻላል። እርሱስ ቢሆን መች ይዘለቅና! እጠቅሳለሁ፡-

ولا محظور في التمدح بذلك نثرا و شعرا مادام ذلك في حدود المشروع الذي أمر به الشارع الكريم

‹‹ሸሪዐዉ ያኖረዉ ወሰን እስካልተጣሰ ድረስ በግጥምም በስድ ንባብም ማወደስ የተከለከለ አይደለም።››[410]

ባለቅኔዎቻችን ይህን ወሰን ጠንቅቀዉ ያዉቃሉ። ግብጻዊዉ ማዲህ ሸኽ ቡሰይሪ እንዲህ ተቀኝተዋል፡-

دع مادعته النصارى فى نبيهم

واصم بما شأت مدحا فيه واحتكم

فإن فضل رسول الله ليس له حد

فيعرب عنه ناطق بهم

فمبلغ العلم أنه بشر

وانه خير الخلق كلهم

ክርስቲያኖች ስነብያቸዉ፣የሰጡትን ደረጃ ትተህ፣

የነቢን ከበጃ ግለጽ፣ሞገስ ዉዳሴ አበጅተህ፣

ልዕልናዉ ከወሰን ሳቀ፣

[410]ሙሀመድ አብን ኸሊፋ አብን ዐሊ ተሚሚ፣ ሁቁቁ ነብይ ዐላ ኡመቲሂ ፊደዉኢል ኪታቢ ወሱና፣አድዋኡ ሰለፍ፣ሪያድ፣1997 ቅጽ 1 ገጽ 328

ክብር ስብዕናዉ መጠቀ፣

ካንደበት አቅም ዘለቀ፣

የዕዉቀታችን ዳርቻ፣

ሰዉ መሆኑን ማወቅ ብቻ፣

(የአምላክ ክህሎት ገበታ)

የፍጡራን ሁሉ ዓይነታ፤[411]

በኛ አገር የ‹መድሕ› ባላባቶች እንደ ጆማሉዲን አል ዐኒ፣ሸኽ አህመደ ዳኒ፣ሸህ ኢብራሂም ያሲን (የጫሌ ሸኽ)፣ሸኽ አህመድ ሸኽ ሲራጅ፣ሸኽ ጀዉሀር አልሀይደሪ (የሾንኬ ሸኽ)፣ ያሉ ታላላቅ ዐሊሞች፣የተዉሂድና የፊቅህ ሊቃዉንት በመሆናቸዉ በግጥሞቻቸዉ ዉስጥ የዐቂዳ ስህተት ስጋት የለም። እንደዚያ ከመሰለን ከኛ የመረዳት ድክመት የመነጨ ነዉ።

በወንድሞቻችን ላይ ያለዉ ችግር የተጋነነ ሙገሳን ሳይሆን ነብዩ ﷺ በምንም መንገድ መሞገሳቸዉን ያለመዉደድ ስሜት ነዉ። ነብዩን ﷺ ከፍ ከፍ የሚያደርጉ ገለጻዎችን እንደምንም ቀዳዳ እየፈለጉ ከሽርክ ጋር የማገናኘት አባዜ በብዛት ይስተዋላል። ይህ ስሜት በቁርአን ተፍሲር ምርጫቸዉና በሀዲስ ምዘናቸዉ ላይ ሳይቀር ተጽእኖ ሲያደርግ ይታያል። ቦታዉ ስላልሆነ ዝርዝር ዉስጥ አልገባም እንጅ በአስሮች የሚቆጠሩ መረጃዎችን ሰብስቤአለሁ።

5.**ተሰባስቦ ዚክር ማድረግ ቢድዐ ስለሆነ**፡- ‹የመዉሊድ ዋነኛ መገለጫ ተሰባስቦ ዚክርና ሶለዋት ማለት ወይም የጀመዐ ዚክር ነዉ፤የጀመዐ ዚክር ደግሞ ቢድዐ ነዉ፤ስለዚህ መዉሊድ ቢድዐ ነዉ› የሚል የይዘት ክስም ይደመጣል። ‹የጀማዐ ዚክር አይፈቀድም› የሚለዉ ሀሳብ ከቁርአንም፣

411 ቡረዳህ ከተሠኘዉ ግጥም

ከሀዲስም፣ከኢጅማዕም፣ከቂያስም ሁነኛ መረጃ ሊገኝለት የሚችል ነገር አይደለም፡-

በአንጻሩ ግን የጀማዐ ዚክር በአላህ ዘንድ ተወዳጅ መሆኑን የሚያረጋግጡ የቁርአንና የሶሂህ ሀዲስ መልዕክቶች በብዛት ይገኛሉ። ኢማም አልነወዊ <u>*‹‹ሪያዱ ሷሊሂን››* ከተባለዉ ታዋቂ የሀዲስ ስብስብ ኪታባቸዉ ዉስጥ 247ኛ ምዕራፋቸዉ</u> እንዲህ ይላል፡-

باب فضل حِلَقِ الذكر والندب إِلَى ملازمتها والنهي عن مفارقتها لغير عذر

‹‹የዚክር ስብስቦች ልቅና፣እነርሱን አዘዉትሮና አጥብቆ መያዝ የሚወደድ ስለመሆኑና ያለምክንያት ከነርሱ መነጠል ስለመከልከሉ››

ዝርዝር ዉስጥ ሳንገባ ይህ ርዕስ ብቻዉን ብዙ ይናገራል፡-

1. የዚክር ሀለቃዎች ልቅና አላቸዉ፣(ልብ በሉ፤ ልቅና እንጅ ቢድዐ አልተባለም)፣

2. ከዚክር ስብስቦች መሀከል መገኘት ይወደዳል፤

3. ያለምክንያት ማቋረጥ ክልክል ነዉ።

አልነወዊ የተጠቀሰዉን ምዕራፍ የከፈቱት በሚከተለዉ የቁርአን አንቀጽ ነዉ፡-

وَاصْبِرْ نَفْسَكَ مَعَ الَّذِينَ يَدْعُونَ رَبَّهُم بِالْغَدَاةِ وَالْعَشِيِّ يُرِيدُونَ وَجْهَهُ وَلَا تَعْدُ عَيْنَاكَ عَنْهُمْ تُرِيدُ زِينَةَ الْحَيَاةِ الدُّنْيَا

‹‹ነፍስህንም፤ ከእነዚያ ጌታቸዉን ፊቱን (ውዴታውን) የሚሹ ኾነው በጧትና በማታ ከሚግገዙት ጋር አስታግስ።የቅርቢቱንም ሕይወት ሽልማት የምትሻ ሆነህ ዓይኖችህ ከእነሱ (ወደሌላ) አይለፉ።››[412]

[412]አልከህፍ 28

በአልነወዊ ግንዛቤ መሠረት ይህ የቁርአን አንቀጽ የዚክር ስብስቦችንም የሚያካትት ሲሆን፣ከዚክር ማዕድ መሳተፍ ከአላህ ዘንድ የተወደደና የሚበረታታ እንደሆነ ይጠቁማል። ከአንቀጹ ጋር ተያይዘዉ የተነገሩ ዘገባዎች ይህንኑ ግንዛቤ ያጠናክራሉ። ዐብዱረህማን እብን ሰህል እብን ሀኒፍ እንዳስተላለፉትና ጦበራኒና እብን ጀሪር እንደዘገቡት ይህ አንቀጽ ሲወርድ ነብዩﷺ ከቤቶቻቸዉ በአንዱ ዉስጥ ነበሩ። ወዲያዉም ሊፈልጓቸዉ ወጡ-/በአንቀጹ ዉስጥየተገለጹ ባልደረቦቻቸዉን/። አላህን ተሰብስበዉ የሚያወሱ ሰዎችንም አገኙ። ከመሀከላቸዉ ጸጉሩ የተንጨባረረ፣ቆዳዉ የተጎሳቆለ፣አንዲት ልብስ ብቻ ያለዉ ይገኝ ነበር። ከመሀከላቸዉም ቁጭ አሉና፣ ‹‹ከተከታዮቼ ዉስጥ አበሪያቸዉ በመሆን ነፍሴን የማስታግስባቸዉን ሰዎች ላደረገልኝ አምላክ ምስጋና ይድረሰዉ›› አሉ።[413]

ኢማም አህመድ ‹ዙህድ› ከተባለዉ ኪታባቸዉ ዉስጥ እንደዘገቡት ሰልማን አላህን ተሰባስበዉ ከሚያወሱ ሰዎች መሀከል ነበር። ነብዩﷺ በአጠገባቸዉ ሲያልፉ ዝም አሉ።ነብዩምﷺ:- ‹‹ምን እያላችሁ ነበር?›› በማለት ጠየቋቸዉ። ‹‹አላህን እያወሳን›› በማለት መለሱ። ‹‹የአላህ ረህመት ሲወርድባችሁ ስላየሁ ከናንተ ጋር መሆንን ወደድኩ›› አሉና:- ‹‹‹‹ከተከታዮቼ ዉስጥ አብሪያቸዉ በመሆን ነፍሴን የማስታግስባቸዉን ሰዎች ላደረገልኝ አምላክ ምስጋና ይድረሰዉ›› አሉ።[414]

ስለዚህ አንቀጹ የጀማዐ ዚክርን በቀጥታ ይመለከታል። እዉቅናም ይሰጠዋል። አልነወዊ ከላይ በተወሳዉ ምዕራፉ ሥር ካሰፈሯቸዉ ሀዲሶች መካከል የተወሰኑትን ልጥቀስ።

[413] ጦበራኒና እብን ጀሪር
[414] ኢማም አህመድ

1.وعنه وعن أَبي سعيدٍ رضي الله عنهما ، قالا : قَالَ رسولُ الله – صلى الله عليه وسلم – : ((لا يَقْعُدُ قَومٌ يَذكُرُونَ اللهَ – عز وجل – إِلاَّ حَفَّتْهُمُ المَلائِكَةُ وغَشِيَتْهُمُ الرَّحْمَةُ وَنَزَلَتْ عَلَيْهِمْ السَّكِينَةُ ؛ وَذَكَرَهُمُ اللهُ فِيمَنْ عِنْدَهُ)) . رواه مسلم

1.አቡሰዒድ አልኹዱሪ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦

‹‹ሰዎች አላህን ስመዘከር አብረዉ ሲቀመጡ (ሲሰበሰቡ) ምንጊዜም መላኢኮች ይከቧቸዋል፡፡ የአላህ እዝነት (ረህማ) ትሸፍናቸዋለች፡፡ ስክነትም ትሰፍንባቸዋለች፡ ፡አላህም ከርሱ ዘንድ ካሉት መሀል ያወሳቸዋል፡፡››[415]

የሀዲሱ መልዕክት ማብራሪያ የሚሻ አይደለም፡፡ ለዚክር መሰባሰብ ያለዉን ፋይዳ አፍ አዉጥቶ ይናገራል፡፡

2. وعن أبي هريرة – رضي الله عنه - ، قالَ : قالَ رسول الله – صلى الله عليه وسلم - : ((إنَّ للهِ تَعَالَى مَلائِكَةً يَطُوفُونَ في الطُّرُقِ يَلْتَمِسُونَ أَهْلَ الذِّكْرِ ، فإذا وَجَدُوا قَوْماً يَذْكُرُونَ اللهَ– عز وجل - ، تَنَادَوْا : هَلُمُّوا إِلَى حَاجَتِكُمْ ، فَيَحُفُّونَهُمْ بِأَجْنِحَتِهِم إِلَى السَّمَاءِ الدُّنْيَا ، فَيَسْأَلُهُمْ رَبُّهُمْ – وَهُوَ أَعْلَم - : مَا يقولُ عِبَادي ؟ قالَ : يقولون : يُسَبِّحُونَكَ ، ويُكبِّرُونَكَ ، وَيَحْمَدُونَكَ ، ويُمَجِّدُونَكَ ، فيقول : هَلْ رَأَوْنِي ؟ فيقولونَ : لا واللهِ مَا رَأَوْكَ . فيقولُ : كَيْفَ لَوْ رَأَوْنِي ؟! قالَ : يقُولُونَ : لَوْ رَأَوْكَ كَانُوا أَشَدَّ لَكَ عِبَادَةً ، وَأَشَدَّ لَكَ تَمْجِيداً ، وأَكْثَرَ لَكَ تَسْبِيحاً . فَيقُولُ : فماذا يَسْأَلونَ ؟ قَالَ : يقُولُونَ : يَسْأَلُونَكَ الجَنَّةَ . قالَ : يقولُ : وَهل رَأَوْها ؟ قالَ : يقولون : لا واللهِ يَا رَبِّ مَا رَأَوْهَا . قالَ : يقول : فكيفَ لَوْ رَأَوْهَا ؟ قالَ : يقولون : لَوْ أَنَّهُمْ رَأَوْهَا كَانُوا أَشَدَّ عَلَيْهَا حِرْصاً ، وأَشدَّ لَهَا طَلَباً ، وأَعْظَمَ فِيهَا رَغْبَةً . قالَ : فَمِمَّ يَتَعَوَّذُونَ ؟ قالَ : يقولون : يَتَعَوَّذُونَ مِنَ النَّارِ ؛ قالَ : فيقولُ : وَهَلْ رَأَوْهَا ؟ قالَ : يقولون : لا واللهِ مَا رَأَوْهَا . فيقولُ : كَيْفَ لَوْ رَأَوْهَا ؟! قالَ : يقولون : لَوْ رَأَوْهَا كانوا أَشَدَّ مِنْهَا فِرَاراً ، وأَشَدَّ لَهَا مَخَافَةً . قالَ :

415 **ሙስሊም**

فيقولُ : فَأشْهِدُكُمْ أنِّي قَدْ غَفَرْتُ لَهُم ، قالَ : يقولُ مَلَكٌ مِنَ المَلَائِكَةِ : فِيهِم فُلَانٌ لَيْسَ مِنْهُمْ ، إنَّمَا جَاءَ لِحَاجَةٍ ، قالَ : هُمُ الجُلَسَاءُ لا يَشْقَى بِهِمْ جَلِيسُهُمْ)) . متفق عَلَيْهِ .

1. አቡሁረይራ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛﷺእንዲህ ብለዋል፡-

‹‹አላሕ በየመንገዱ የዚክር ሰዎችን የሚያስሱ መላኢኮች አሉት፡፡ አላህን የሚዘክሩ ሰዎችን (ስብስቦችን) ባገኙ ጊዜ፡- ‹ወደጉዳያችሁ ኑ› ተባብለዉ ደጠራራሉ፡፡ በክንፎቻቸዉም እስከመጀመሪያዉ ሰማይ ድረስ ይከቧቸዋል፡፡ ጌታቸዉም-እያወቀ፡-‹ባሮቼ ምን እያሉ ነዉ?› በማለት ይጠይቃል፡፡ ‹ያንተን ክብርና ልዕልና እየገለጹ፣እንዲሁም እያመሰገኑህ እና እያሞገሱህ ነዉ› ይሉታል፡፡ ‹አይተዉኛልን?› ሲል ይጠይቃል፡፡ ‹አላዩህም› ይሉታል፡፡ ‹ቢያዩኝ ኖሮ እንዴት ይሆኑ ነበር› ሲል ይጠይቃል፡፡ ‹ቢያዩህማ ኖሮ ከዚህ በበረታ ሁኔታ ያመልኩህ፣ ክብርህንና ልቅናህን ይገልጹ ነበር› ይሉታል፡፡ ‹የሚጠይቁት ምንድን ነዉ?›ሲልም ይጠይቃቸዋል፡፡ ‹ጀነትን› ይላሉ፡፡ ‹አይተዋታልን› ‹አምላካችን ሆይ ባንተ እንምላለን አላዩአትም› ‹ቢያዩአት ኖሮ እንዴት ይሆኑ ነበር?› ‹ይበልጥ ይንጉሳትና ይከጅሏት ነበር› ይላሉ፡፡ ‹ከምን መጠበቅ ነዉ የሚሹት?› ሲልም ይጠይቃቸዋል፡፡ ‹ከእሳት› ይላሉ፡፡ ‹አይተዋታልን?› ‹ባንተ እንምላለን አላዩአትም› ‹ቢያዩአት እንዴት ይሆኑ ነበር?› ሲልም ይጠይቃል፡፡ ‹ቢያዩአትማ ኖሮ ይበልጥ ይሸሿት፣ይበልጥም ይፈሯት ነበር› ይሉታል፡፡ ‹በእናንተ አማኝነት ምሪያቸዋለሁ› ይላል፡፡ ከመላኢኮች መሀከል አንዱ፡ ‹ከመሀከላቸዉ አገሌ የሚባል ሰዉ አለ፡፡ ለሌላ ጉዳይ ነዉ ከነርሱ መሀል የተገኘዉ› ይላል፡፡ ‹አነርሱ አብሯቸዉ የተቀመጠ ዕድለቢስ የማይሆንባቸዉ ስብስቦች ናቸዉ› ይላል፡፡››[416]

በዚህ ሀዲስ መልዕክት መሠረት በጀማዐ ተሰባስቦ ዚክር ማድረግ፣ አላህን በጋራ ማመስገን፣ ማወደስ፣ልዕልናዉን መግለጽ እና ሌሎችም ዚክሮች ከአላህ ዘንድ የተወደዱ፣ለጀነት የሚያበቁ፣ ከእሳት የሚታደጉ ናቸዉ፡፡

3.وعن أَبي سعيد الخدري – رضي الله عنه – قَالَ : خرج معاوية – رضي الله عنه – عَلَى حَلْقَةٍ في المَسْجِدِ ، فَقَالَ : مَا أجْلَسَكُمْ ؟ قالوا : جَلَسْنَا نَذْكُرُ اللهَ . قَالَ : آللهِ مَا

[416] ቡካሪና ሙስሊም

أجْلَسَكُمْ إلاَّ ذاك ؟ قالوا : مَا أجْلَسَنَا إلاَّ ذَاكَ ، قَالَ : أما إنِّي لَمْ اسْتَحْلِفْكُمْ تُهْمَةً لَكُمْ ، وَمَا كَانَ أحَدٌ بِمَنْزِلَتِي مِنْ رَسولِ الله – صلى الله عليه وسلم – أَقَلَّ عَنْهُ حَديثاً مِنِّي : إنَّ رسُولَ الله – صلى الله عليه وسلم – خَرَجَ عَلَى حَلْقَةٍ مِنْ أصْحَابِهِ فَقَالَ : ((مَا أجْلَسَكُمْ ؟)) قالوا : جَلَسْنَا نَذْكُرُ الله وَنَحْمَدُهُ عَلَى مَا هَدَانَا للإسْلاَمِ ؛ وَمَنَّ بِهِ عَلَيْنَا . قَالَ : ((آللهِ مَا أجْلَسَكُمْ إلاَّ ذَاكَ ؟)) قالوا : واللهِ مَا أجْلَسَنَا إلاَّ ذَاكَ . قَالَ : ((أمَا إنِّي لَمْ أسْتَحْلِفْكُمْ تُهْمَةً لَكُمْ ، ولكِنَّهُ أتَانِي جِبرِيلُ فَأخْبَرَنِي أنَّ الله يُبَاهِي بِكُمُ المَلاَئِكَةَ)) . رواه مسلم.

3.አቡሰዒድ አል-ኹዱሪ እንዲህ ሲሉ አዉግተዋል፡-

መዐወያህ ከመስጊድ ዉስጥ ወደነበር አንድ ስብስብ (ሀለቃ) ወጡ፡፡ ‹‹የተቀመጣችሁት ለምን ጉዳይ ነዉ?›› ሲሉም ጠየቁ፡፡ ‹‹አላህን ለማስታወስ (ለዚክር)›› አሉ፡፡ ‹‹ በአላህ ማሉልኝ፤ ከዚህ ዉጭ ሌላ ያስቀመጣችሁ ጉዳይ የለምን?›› ሲሉ ጠየቋቸዉ፡፡ ‹‹ጉዳያችን ይህ ብቻ ነዉ›› ሲሉ መለሱ፡፡ ‹‹ ያስማልኳችሁ ቃላችሁን ተጠራጥሬ አይደለም፡፡ ከአላህ መልዕክተኛﷺ ዘንድ የኔን ያህል ቅርበት ኖሮት ከኔ ያነሱ ሀዲሶችን ያወጋ የለም፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ወደባልደረቦቻቸዉ አንድ ስብስብ ወጡና፡-‹‹የተቀመጣችሁት ለምን ጉዳይ ነዉ?›› ሲሉ ጠየቁ፡፡ ‹‹አላህን ለማስታወስ (ለዚክር) እና ወደእስልምና ስለመራን፤እንዲሁም ጸጋዉን ስለሰጠን ልናመሰግነዉ›› አሉ፡፡‹‹ በአላህ ማሉልኝ፤ ከዚህ ዉጭ ሌላ ያስቀመጣችሁ ጉዳይ የለምን?›› ሲሉ ጠየቋቸዉ፡፡ ‹‹ጉዳያችን ይህ ብቻ ነዉ›› ሲሉ መለሱ፡፡ ‹‹ ያስማልኳችሁ ቃላችሁን ተጠራጥሬ አይደለም፡፡ ግና ጅብሪል ከኔ ዘንድ መጥቶ አላህ በመላኢኮች ላይ በናንተ እየተኩራራ እንደሆነ ነገረኝ›› አሉ፡፡[417]

[417] ሙስሊም

ይህ ሀዲስ በነብዩ ﷺ ዘመንም ሆነ ከርሳቸዉ በኋላ ሶሀቦች ለዚክር ይሰባሰቡ እንደነበር ያረጋግጣል፡፡ኢማም አልነወዊ ይህን ሀዲስ ሲያብራሩ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ይህ ሀዲስ የዚክርን ልቅናና ከዛኪሮች ጋር፣ዚክራቸዉን ባደጋሩ እንኳ አብሮ መቀመጥ ያስዉን ደረጃ ያሳያል፡፡›› ብለዋል፡፡[418]

ኢማም አልነወዊ በሌላ ገለጻቸዉ እንዲህ ብለዋል፡-

يُسْتَحَبُّ الْجُلُوسُ فِي حِلَقِ الذِّكْرِ

‹‹ከዚክር ስብስቦች (ሀለቃ) መሀል መቀመጥ ደወደዳል፡፡››[419]

ኢማም ጀላሉዲን አል-ሱዩጢ‹‹ነቲጀተል ፈክር ፈል ጀህሪ ቢዚክር››በተሰኘች ኪታባቸዉ ዉስጥ የጀማዐ ዚክርን ሸሪዐዊነት የሚያጸኑ 25 ያህል የሀዲስና የታሪክ መረጃዎችን አቅርበዋል፡፡

‹‹እነዚህ ግልጽ መረጃዎች እያሉ‹ለዚክር መሰባሰብ ቢድዐ ነዉ› የሚለዉ ተቃዉሞ ከየት ተገኘ?›› ብለን መጠየቅ ግድ ይለናል፡፡

ሀ.በእርግጥ የምትጠቀሰዉ ብቸኛ የታሪክ መረጃ ዐብደላህ እብን መስዑድ ‹ላኢላሀ ኢለላህ›› የሚሉ አንድ የሰዎች ስብስብ አይተዉ ‹‹መ·ብተዲኦች ናችሁ›› በማለት አባረዋቸዋል፣ የሚል ነዉ፡፡[420] ይህ ክስተት መረጃ ሆኖ ሊቀርብ እንደማይችል ከሚያመለክቱ ነጥቦች መካከል፡-

1. የዘገባዉ ሰነድ ደካማ ነዉ፤ምክንያቱም ‹አልሀከም እብን መዝክ› የተባለ አስተላላፊ አለበት፡፡ እርሱን በተመለከተ እብን አቢሀቲም ‹‹እዉነተኛ ቢሂንም ብኸርታዎች አሉበት›› ብለዋል፡፡[421] እንዲህ ዓይነቱ

[418]አልነወዊ፣ሸርህ ሙስሊም፣
[419]አል-መዉሱዐቱል ፈቅህያ ማዳ ዚክር
[420] ሱነን ዳሪሚ
[421] አልጀርህ ወተዕዲል 3/142

<u>ሙጦሀር የሰነዘሩት የተጋነነ ምላሽና ነቀፌታ የዐሲ እብን አቢ ጧሲብን ክብርና ደረጃ አስከማሳነስ ርቀት የሄደበት ሁኔታ ታይቷል››</u> ለማለት ተገደዋል፡፡[444]

እብን ተይይሚያህ በአህሉል በይት ክብር ላይ ያሳዩትን መዳፈርና ጥሰት ለመሀየስ በቅርብ ጊዜ ከተጻፉ መጽሀፍት መሀል ***ዶ/ር ማህሙድ ሰይድ ሶቢህ*** የተባሉ ግባጻዊ ምሁር ያዘጋጁት ***‹‹አሽጧኡ እብን ተይሚያህ ፊሀቂ ረሱሊሃሂ ወአህሊ በይቲሂ››***ኖተባለዉ መጽሀፍ[445] ለአብነት ተጠቃሽ ነዉ፡፡ 504 ገጾች ያሉት ደጓሳ ኪታብ ሲሆን፣የሸኹ ግድፈቶች ያላቸዉን 96 ያህል ነጥቦች አንስቶ በምሁራዊ አግባብ ይሀይሳል፡፡ በእርግጥ ከርሱም በፊት እንደ ኢማም እብን ሀጀረል ሀይተሚ[446]፣ ኢማም ታጁዲን አልሱብኪ፣ኢማም አልዘርቃኒ[447]፣ኢማም ሽሀቡዲን አልኸፋጂ[448]፣ኢማም ዐብዱረኡፍ አልመናዊ[449] ፣ኢማም ዘመልካኒ፣ ኢማም ሶፍዩዲነልሂንዲ፣ኢማም ተቅዩዲነልሁሰይኒ[450] እና ሌሎችም ብርቱ ሂስ ሰንዝረዉባቸዋል፡፡ የኢማም እብን ሀጀረል ሀይተሚ፤- *‹‹ዐብዱን አዶለሁላሁ ተዐላ ወአግዋሁ...››* /እብን ተይሚያህ አላህ ያጠመመዉና መንገድ ያሳተዉ ሰዉ ነዉ/[451] የሚለዉ ሂስ ግን ከሁሉም የጠነከረ ይመስለኛል፡፡ አልሀይተሚ በዒልሙ ዓለም ካላቸዉ ምሁራዊ ጉልበትና ተሰሚነት አኳያ ይህ ነቀፌታቸዉ እንደዋዛ የሚታይ አይደለም፡፡ እነዚህና ሌሎችን ሂሶች ዶ/ር ማህሙድ ሰይድ ሶቢህ ከላይ በጠቀስኩት መጽሀፋቸዉ መግቢያ አዉስተዋቸዋል፡፡[452]በሌላ በኩል የሸህ እብን ተይሚያህ ወዳጆች ‹‹እብን ተይሚያህ ናሲብደ አልነበረም›› በማለት

444 እብን ሀጀር፣አሲሳን፣6/319

445 ዳረ ሩክን ወልመቃም አሳታሚ፣ካይሮ፣የመጀመሪያ ፅትም 2003

446ጀዋሂሪል ሙነዞም ፌዚያሪቲ አልቀብሪ ነቦዊደ ሸሪፍ አልሙከረም፣

447 ሸርሁል መዋሂቡ ለዱንያህ ሊልቀስጦላኒ፣8/314-315

448 ሸርሁ ሸፋእ

449 ሸርሁ ሸማኢል

450 ደፍዑ ሹብሀ መን ሸበሀ ወተመረድ፣ወነሰበ ዛሊከ ኢላ ሰይድ ኢማም አህመድ

451ጀዋሂሪል ሙነዞም...

452 ገጽ 9-20

ክሶቹን ለመከላከል በብርቱዉ መፈተናቸዉ የሀያሲዎቻቸዉን የሂስ ጉልበት ያመለክታል።[453] ከክሶቹም ከፊሎቹን ወዳጆቻቸዉ በለዘብታ ተቀብለዉ ምክንያት ለመስጠት ሞክረዋል።የሸኽ አልባኒ የወዳጅ ሂሶች ለአብነት ይጠቀሳሉ። ለምሳሌ፦ *‹‹መን ኩንቱ መዉላሁ ፈዐልይ መዉላሁ›› /እኔ ወዳጅ የሆንኩለት ዐሊም ወዳጁ ነዉ/* የሚለዉ ሀዲስ ሶሂህና በሸኽ ዘሀቢ ‹‹መ-ተዋቲር›› የተባለ ከመሆኑ ጋር[454] እብን ተይሚያህ ‹‹ሀሰትና ደካማ››[455] ማለታቸዉን ሸኽ አልባኒ፦ *‹‹ በደንብ ሳያስተዉሉ ሀዲስንዶሲፍ ስማለት የእብን ተይሚያህ ችኩል ባህሪያቸዉ የመነጨ››* እንደሆነ በለዘብታ ሀይሰዋቸዋል። [456]

ከእንዲህ ዓይነቱ አወዛጋቢ ስብዕና ስለመዉሊድ አወዛጋቢ አስተያየት መነጨ። በአንድ በኩል መዉሊድን የሚሀይስ የሚመስል፣በሌላ በኩል ፈጻሚዎቹ ምንዳ ያገኛሉ የሚል እይታ ተንጸባረቀ።[457] ከአሁን ቀደም እንዳየነዉ ከሸኽ እብን ተይሚያህ የቢድዐ ጽንሰ ሀሳብ ግንዛቤ አኳያ ሲታይ መዉሊድን ያለማመንታት መፍቀድ ነበረባቸዉ። ሆኖም ሌላ መግፍኤ ያለ በሚመስል ሁኔታ አሉታዊ አስተያየት ሰነዘሩ።

ራሱን የእብን ተይሚያህ አስተሳሰብ ወራሽ አድርጎ የሚያቀርበዉ የሰለፊ/ሰለፊ ንቅናቄ ከእብን ተይሚያህ አሉታዊ አስተያየታቸዉን ወስዶ በብዙ እጥፍ እያባዛና እያራባ ረጨዉ። ምን አልባትም የነስብ ተዉሳኩንም አብሮ ወርሶ በብዙ እጥፍ አባዝቶታል የሚለዉን ጥርጣሬ በሚያጎላ ሁኔታ በመዉሊድ ላይ ጠንካራ ዘመቻ ከፈተ።

---

[453] ሸኽ ሱለይማን እብን ሳልህ አልኹራሺ፣እብን ተይሚያህ ስም የኩን ናሲብየን፣ የመጽሀፉ መግቢያ በሸኽ ሳልህ አልፈዉዛን የተዘጋጀ፣መክተበተ ሻሚላ፣ቂስመል ወቂዳ

[454] ሲየር አዕላመኑበላእ 8/335

[455] ሚንሀጀ ሱና ነበዊያ 4/87

[456] ሲልሲለቱል አሀዲሰ ሶሂሃ 5/263

[457] እብን ተይሚያህ፣እቅቲዳሹ ሲራጦል ሙስተቂም ፣መክተበተል አቅሳ፣ኢትዮጵያ፣ገጽ 400-402

ከአሁን ቀደም እንዳብራራሁትና ከታሪክ ሂደት እንደምንረዳው ሳውዲን የሚገዛው የሱዑድ ቤተሰብ ህልውናው የተመሠረተው ሂጃዝን ያስተዳድር የነበረዉንና የነብዩ ﷺ ዝርያ እንዳለው የሚታመነዉን የሀሽምዮች ቤተሰብ በማጥፋት በመሆኑ ከዚያ ቤተሰብ ጋር ግንኙነት ያላትን እያንዳንዷን ነገር ለማክሰም ካለው ብርቱ ፍላጎት አኳያ በመዉሊድ ላይ ጥርሱን መንከሱ የሚጠበቅ ነዉ። በመዉሊድ ላይ የተያዙ አቋሞች ከሀይማኖታዊ ገጽታነት ይልቅ ፖለቲካዊ ቃና ያላቸው ይመስላል ያልኩትም ለዚሁ ነዉ። በአስተሳሰብ ደረጃ ከኡመያዉያን የወገኑት ከሞላ ጎደል የመዉሊድን መታሰቢያ በክፉ ዓይን ማየታቸዉ የሚጠበቅ ሲሆን ከዚህ ጫና ነጻነት ያገኙት የአህሉል በይት ቅን ደጋፊዎች ደግሞ ጉዳዩን በአወንታዊነቱና በቅንነት ሲያስተናግዱት ኖረዋል።

ስለዚህም በአንዳንድ ወገኖች ዘንድ መዉሊድ ከዝሙት በላይ ለመወገዙ ይህ የታሪክ ዉርስ አንዱ ምክንያት ሊሆን ይችላል።

2. የመዝሀብ ወገንተኝነት

በመዉሊድ ላይ ለተነሳው ጠንካራ ተቃዉሞ ይበልጥ በጉልህ የሚታየዉ ሰበብ ***የሱፊ-ዉሀቢ*** ሽኩቻ ነዉ። የሰለፍይ/ዉሀቢ እንቅስቃሴ በተሰዉፍ ላይ ጥርሱን የነከሰ መሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ነዉ። ከአነሳሱ ጀምሮ የሱፊ መሻኢኾችን ‹ሙሽሪክ› እና መብተዲዕ፣ሥራዎቻቸዉን ‹ሽርክ› እና ‹ቢድዐ› በማለት ወስኖና ፈርጆ ሲንቀሳቀስ ኖሯል።[458] ሱፍያን ከታገሰ ለጊዜዉ እንጅ አስተሳሰቡ መወገድ ያለበት መሆኑን በጽኑ ያምናል። ‹‹ቁቡርይ፣ኹራፍይ› ወዘተ የሚሉ ለሱፍያ መስመር የሚሰጡ የማጣጣያ ስያሜዎች የጥላቻዉን መጠን ያሳያሉ። በሳዉዲም ሆነ በሌሎች ሰለፊ/ዉሀቢ ቀመስ እስላማዊ ዩኒቨርሲቲዎች እና ተቋማት ወይም በሰለፊ/ዉሀቢ ስብዕናዎች የሚሰሩ ጥናትና ምርምሮች በሙሉ ከሱፍያ መስመር ጋር የተገናኙ አጀንዳዎችን የሚያዩበት መነጽር

[458] አብደላህ አብን ሲዲቅ አልጊማሪ፣አልኢዕላም ቢአነ ተሰዉፈ ሚን ሸሪዐቲል ኢስላም፣ ጀምዕቱ አሲልበይት ሊተራሲል ኢስላምያህ፣ፈስስጢን፣ገጽ8

ምንጊዜም ጥቁር ነዉ።[459] በሌሎች አጀንዳዎች ላይ ሚዛናዊና ነጻ ለመሆን የሚሞክሩ አጥኝዎች ሳይቀር፣ምዕራቡ ዓለም ከእስልምና ጋር በተገናኘ ሚዛን እንደሚስተዉ እነርሱም በተሰዉፍና በተሰዉፍ ጉዳዮች ላይ ፍጹም ሚዛን ይጥሳሉ። ስለዚህም ተወሱልና ተበሩክ፣የጀማዐ ዚክርና ዱዐ፣የቀብር ዚያራ፣ነብዩን መዘየር፣ወልይ፣ከራማ፣ለሙታን ቁርአን መቅራት፣ከሸፍ፣ኢልሀም በሚሉና መሰል አጀንዳዎች ዙሪያ ሰለፍይ/ዉሀብይ የሚይዘዉን አቋም ለማወቅ ብዙ ምርምርና ፍተሸ አያስፈልግም። በሱፍይ ስብዕናቸዉ የሚታወቁ ዐሊሞችን እይታ ካወቅን የርሱ ተቃራኒ አቋም የሰለፍይ/ዉሀይ ነዉ።

ሱፊ ገጽታ ያላቸዉን ስብዕናዎች ማጥላላት የሰለፍይ/ዉሀቢ መስመር አብይ መገለጫ ነዉ። ለኢማም አቡሀሚድ አልዛሊና ለኪታቦቻቸዉ መስመሩ ያለዉ ጸለምተኛ እይታ ሥነ-ልቦናዊ መግፍዔዉ ይህ እንጅ ሌላ አይደለም።

ሱፍያን ለማጥላላት ሁሉንም ዓይነት መንገዶች ይጠቀማል። የሱፊ ስብዕናዎችን ልቅና፣ዒልምና ሀይማኖታዊ ይዞታ ያጣጥላል። ሱፊ ቀመስ አጀንዳዎችን እንደምንም፣የሚያምንባቸዉን መርሆዎች ጨፍልቆም ቢሆን ቢድዐ ወይም ሀራም ለማድረግይተጋል።

የኩዌት የሠለፍያ ንቅናቄ አባት ተደርገዉ የሚቆጠሩት ዶ/ር ዐብዱረህማና ዐብዱል ዃሊቅ[460] የጻፉትን ‹‹*አልፊክረሱፊ ፊደዉኢል ኪታቢ ወሱና*››[461]ወይም የህንዳዊዉን ሰለፍይ የሸኽ ሙህሲን ኢላሂ ዞሂር ‹‹*አልተሶዉፍ*›የተባሉ መጽሀፍት በወፍ በረር ማንበብ ይህን በቀላሉ ለመረዳት ያስችላል። ለሁለቱም ስብዕናዎች ሱፍያ ከህንድ፣

[459] የሸኽ አብንባዝ፣ሸኽ አብን ዑሰይሚን፣ሸኽ ፈዉዛን ፈትዋዎችን ስአብነት ማየት ይቻላል፤

[460] አህመድ ሳሊምና ዑመር በየሚ፣ማባዕደሰለፍይ፣መርከዘነማዕ ሲልቡሁሲ ወዲራሳት፣ ቤይሩት፣የመጀመሪያ ፅትም፣2015

[461] አንደ ፈረንጆች 1986 የታተመ

ከግሪክና ከሌሎች አፈር በቀል የኩፍር ፍልስፍናዎች የመነጨ የጥመት ጎዳና እንጅ የእስልምና ወገን አይደለም። የእስልምና ትልቁ ፈተና አይሁዶች ወይም ክርስቲያኖች ወይም አምላክ የለሽ አስተሳሰቦች ሳይሆኑ ተሰዉፍ ነዉ። ዐብዱረህማን በተጠቀሰዉ መጽሀፋቸዉ ሁለተኛ ፅትም መግቢያ ላይ እንዲህ ሲሉ የሱፊ መስመርን ‹‹ክፋት›› ይገልጻሉ፡-

فإن أعظم فتنة ابتلي بها المسلمون قديمًا وحديثًا هي فتنة التصوف . هذه الفتنة التي تلبست للمسلمين برداء الطهر والعفة والزهد والإخلاص، وأبطنت كل أنواع الكفر والمروق والزندقة، وحملت كل الفلسفات الباطلة ومبادئ الإلحاد والزندقة . فأدخلتها إلى عقائد الإسلام وتراث المسلمين على حين غفلة منهم، فأفسدوا العقول والعقائد . ونشروا الخرافات والدجل والشعوذة، ودمروا الأخلاق، وأتوا على بنيان دولة الإسلام من القواعد إذ حارب المتصوفة العلم والجهاد والبصيرة في الدين، بل والزواج والعمل والكسب، فنصبوا للقرآن والسنة حربًا لا هوادة فيها، وحرفوا الناس عن تعليمها بكل سبيل

‹‹ጥንትም ሆነ ዛሬ የሙስሊሞች ትልቁ ፈተና የሱፍያ ፈተና ነዉ። ይህ ፈተና የዉስጥ ንጽህና፣የቁጥብነት፣የዙህድና የሲኽላስ ስምድ ስብሶ፣ በዉስጡ ግን የክህደት፣የአፈንጋጭነትና የኒፋቅ ዓይነቶችን ሁሉ ደብቆ፣የአምላክ የለሽነት ከንቱ አስተሳሰቦችንና ፍልስፍናዎችን ተሸክሞ ለሙስሊሞች ቀረበ። ሙስሊሞች በተዘናጉበት ዘመን ሱፍዮች ክህደታቸዉን ወደ ዉስጣቸዉ በማስረግም አፅምሮዎችንና ፅምነትን ሁሉ በከሱ። ከንቱ ፅምነቶችንና አስተሳሰቦችን፣ እንዲሁም ድግምትንና ጥንቆላን ሁሉ አስፋፉ። ሥነምግባርን አወደሙ። ፅዉቀትን፣ጅሀድንና የሀይማኖት ንቃትን፣ከዚህም አልፈዉ ጋብቻንና ሥራን በመዋጋት አስላማዊ መንግስቱን ከስር ገዘገዙት።በቁርአንና በሱና ላይ ብርቱ

ጦርነት ከፈቱ፡፡ሰዎች እንዳይማሯቸዉም ሁሉንም ስልቶች በመጠቀም መልዕክታቸዉን አዛቡ፡፡››[462]

ይህ የዶ/ሩ ገለጻ በግድፈቶች የተሞላ ሲሆን፣በተለይም፡- *‹‹ዕዉቀትንና ጅሀድን በመዋጋት…››*የምትለዋ ክፍል ፍጹም ስህተት ለመሆኗ ከሀገራችን የዒልምና የጅሀድ ታሪክ በላይ ምስክር የለም፡፡ በዚህች ሀገር እስልምናን ከትዉልድ ትዉልድ ያሸጋገሩት፣በቅርብ ዘመን እንኳ ከሙፍቲ ዳዉድ እስከ ዐኖች፣እስከ ዳኖች፣እስከ ቃጥባሬ፣እስከ አብሬት፣ እስከ ሸኽ መሀመድ ሳኒ ሀቢብ ወዘተ ሱፍዮች እንጅ ሌላ ማንም አይደለም፡፡ አጼዎችን የተዋጉት እነኢማም አህመድ ኢብራሂም አልጋዚ (አህመድ ግራኝ)፣ጀማሉዲን አልዐኒ፣ሸኽ አህመድ ዳኒ፣ሸኽ ሰይድ መሀመድ ሳድቅ፣መኾሂደ ሸኽ መሀመድ ሸሪፍ፣ጦልሀ ጃዕፈር፣የሰሜኑ ኃያል ሸኽ ለጋስ አደም…ሁሉም ሱፍዮች ናቸዉ፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃም ያለዉ ዕዉነታ ተመሳሳይ ነዉ፡፡ የመስቀል ወራሪዎችን አሸንፎ ቁድስን ነጻ ያወጣዉ በኩርዳዊዉ ሱፊ በሶለሀዲን አልአዩቢ የተመራ የሱፊ ሠራዊት ነበር፡፡ የሶለሀዲን ቤተሰብ የሱፊ ቤተሰብ ነበር፡፡ ሶለሀዲን ራሱ የታላቁ ሱፊ የሸኽ ዐብዱልቃድር ጀይላኒ ተማሪ ነዉ፡፡ ሸኽ ዐብዱልቃድር ጀይላኒ በበኩላቸዉ የታላቁ ሱፊ የኢማም አቡሀሚድ አልገዛሊ ተማሪ ናቸዉ፡፡ በሊቢያ የጣሊያንን ወራሪ ሀይል የተዋጉት ዑመር ሙኽታር፣በሱዳን እንግሊዞችን የተፋለሙትና አጼ ዮሀንስን የገደሉት መህዲስቶች ሱፍዮች ነበሩ፡፡ ቦታዉ ስላልሆነ እንጅ የሰለፍዩን መሪየዶ/ር ዐብድረህማንን ታሪካዊና ሀይማኖታዊ ግድፈቶች በዝርዝር ባሳይ ደስ ባለኝ፡፡

በሸኽ እብን ባዝ የሚመራዉ የፊትዋና የሀይማኖት ጥናቶች ቋሚ ኮሚቴ (ለጅነተ ዳኢማ ሊልቡሁሲል ዒልምያህ ወል ኢፍታእ) ሱፍዮች ካሉበት መስጊድ ዉስጥ ጀማዐ ስለመስገድ ተጠይቆ የሰጠዉ ምላሽ እንዲህ ይላል፡-

[462] ከመጽሀፉ ሁለተኛ ፅትም መግቢያ የተወሰደ

لا تصل مع هؤلاء الصوفية في زاويتهم، واحذر صحبتهم والاختلاط بهم لئلا يصيبك ما أصابهم،

‹‹ከሱፍዮች ጋር ከዛዉያቸዉ ዉስጥ አብረህ አትስገድ፤ እነርሱን ካገኛቸዉ ችግር ትጠበቅ ዘንድ ከነርሱ ጋር መጎዳኘትንና መቀላቀልን ተጠንቀቅ፤››[463]

ስለሱፍያ እንዲህ ዓይነት ፍጹም ጸለምተኛ፣ፍጹም ሚዛን የሳተና ፍጹም ጽንፈኛ ዕይታ ያለዉና እስከመጨረሻዉ ሊዋጋዉ የቆረጠ ወገን የተሰዉፍ አጀንዳዎችን በቅንነት ያያል ተብሎ ፈጽሞ አይታሰብም። በየትኛዉም ቋንቋ፣እንደምንም ሆኖ ይገለጽ ለስለፊ/ዉሀቢ ንቅናቄ ሱፍያ ወገኖቹ መወገድ አለባቸዉ። ከነርሱ ለመነጨ ቅንጣት ያክል በጎ ነገር ዕዉቅና መስጠት መስመሩን ህጋዊነት ማላበስ በመሆኑ በዚህ በኩል ድርድርና መለሳለስ አያስፈልግም።የዚህ ጸለምተኛ *ዕይታ ፊት አዉራሪ የሆኑት ዶ/ር ዐብዱረህማንና ጓዶቻቸዉ መዉሊድን እንዲህ ቢገልጹት ላያስገርም* ይችላል፡-

فالمولد عندهم بدعة أنشأت بدعاً منكرة، بل شركاً وزندقة، فالاحتفال بالمولد عند أهله المبتدعين نظام وتقليد معين، واحتفال مخصوص بشعائر مخصوصة وأشعار تقرأ على نحو خاص، وهذه الأشعار تتضمن الشرك الصريح، والكذب الواضح

‹‹መዉሊድ ከባስቤቶቹ ዘንድ የተወገዘ ቢድዐ የመነጨበት ቢድዐ ነዉ። ከዚህም አልፎ የሺርክና የንፍቅና መብቀያ ነዉ። የመዉሊድ መታሰቢያ በሙብተዲዕ ወገኖቹ ዘንድ የተለየ አፈጻጸምና በተለየ ስልት የሚነበቡ ግጥሞች ያሉት ሥርዓት ነዉ። ግጥሞቹ ግልጽ ሽርክና ጉልህ ቅጥፈት ያዘሉ ናቸዉ።››[464]

---

[463] ፈታዋ ለጅነተ ዳኢማ...፣መክተበተ ሻሚላ፣ቂስመል ፈታዋ፣ቅጽ 2፣ተሰዉፍ ምዕራፍ

[464] በብዱረህማን በብዱልካሲቅ፣ሀቂቀቱል ኢህቲፋል ቢል መዉሱዲ ነበዊይ፣መክተበተ ሻሚላ፣ቂስመል በቂዳ፣ገጽ 6

መዉሊድ የዚህ መዝሀባዊ ሽኩቻና ጥላቻ አንደኛዉ ሰለባ በመሆኑ የነቀፌታ ፍላጻዎች በዝተዉበታል።

3.የፖለቲካ ሁኔታዎች

የሸኽ ሙሀመድ ዐብዱል ወሀብ ቤተሰብና የሳዉዲ መስተዳድር በመዉሊድ ላይ እንዲህ እንዲያመርሩ ያደረጋቸዉን ፖለቲካዊ መግፍኤ ማየትም ጠቃሚ ይመስለኛል።

የአሁኗ ሱዑዲ የተመሰረተችዉ ሂጃዝንና አካባቢዉን ተቆጣጥሮ ይገዛ የነበረዉንና የነብዩ ﷺ ዘር (ሀሽምይ) እንደሆነ የሚታመነዉን መስተዳድር በማስወገድ ከመሆኑ አኳያም የሳዉዲ መንግስትና የፖለቲካዉ ደጋፊ የሀይማኖት መሪዎች ያን ቤተሰብ ለሚያስታዉሰዉ መዉሊድ በታሪክ ያልታየ የመረረ ጥላቻ ማንጸባረቃቸዉ የሚጠበቅ ነዉ። ከኡመያዉያንና ከዐባሳዉያን ጋር በዘመንና በዘር ባይገናኙም ለአህሉል በይት ባላቸዉ ፖለቲካዊ እይታ ይመሳሰላሉ።የሱዑድ ቤተሰብ በሀይል ያገኘዉን ህጋዊነት (legitimacy) በአስተሳሰብ ለማጽናት ከሀይማኖት የተሻለ መንገድ የለም። የኛ አገር አጼዎች ለዘመናት መግዛት የቻሉት የቤተ ክህነትን ድጋፍ መሠረት በማድረግ ነዉ። በሳዉዲ የታየዉም ከዚህ የተለየ አይደለም።

የሱዑድ ቤተሰብ እንደ አንድ የፖለቲካ ሀይል የግድ ተቀናቃኞቹን ማሳደድና ታሪካዊ ቅሪቶቻቸዉን ማጥፋት ነበረበት። ሂጃዝ የሚለዉን የሀገሪቱን ስም ወደ ሱዑዲ በመቀየር ጀመረ። ከአህሉል በይት ጋር ትስስር ያላቸዉን ቅርሶች ቀስ በቀስ አወደመ። ያ ቤተሰብ ለቅርስ ግድ ስለሌለዉ የሶሀቦችንና የአህሉል በይትን ቀብር ሙሉ በሙሉ ከመሬት ጋር አስተካክሎታል። የትኛዉ ቀብር የማን እንደሆነ በማይለይበት ሁኔታ አከሰመዉ። ነብዩ ﷺ የተወለዱበት ቤት፣ የወህዩ የመጀመሪያ መዉረጃ የሆነዉ የዕመት ኽ ዲጃ ቤት ወዘተ ምልክታቸዉ እንዳይታይ ተደርጎ ጠፍተዋል። ገሚሶቹ መጸዳጃ ቤት ተደርገዋል ወይም ለሌላ

አገልግሎት ዉለዋል። የሚያሳዝነዉ የነብዩ ﷺ እናት የሆኑት የእመት አሚና ቢንት ወህብ ቀብር ተገርስሶ፣አጽማቸዉ ረክሶ የነዳጅ ጉድጓድ ተቆፍሮበታል።[465] በዚህ መልኩ የዚያች ቅዱስ መሬት ታሪካዊ ምልክቶች ሁሉ ጠፉ። ከሱዑድና ከቤተሰቦቹ ጋር ብቻ በሚያስተሳስራት ሁኔታ እንደ አዲስ ተጠፍጥፋ ተሰራች። ሀረም እንኳ በኢብራሂምና በእስማኤል ሳይሆን በሱዑድ ቤተሰብ የታነጸ ነዉ የሚመስለዉ። የመካና የመዲና እያንዳንዷ ስንዝር ቦታ፣የሀረሞች ግዙፍና የሚያማምሩ በሮች ወዘተ፣የነቢ ኢብራሂምን ወይም የነብዩ ሙሀመድን ቤተሰቦች ሳይሆን የሱዑድን ቤተሰቦች የሚያስታዉሱ ናቸዉ። ያን የተቀደሰ ምድር የረገጠ ሁሉ ይህን በቀላሉ ይገነዘባል።

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲደረግ በሸኹ ቤተሰቦች ቁጥጥር ስር የሆነዉ የሳዉዲ የዐሊሞች መድረክ ሙሉ ድጋፍ ከመስተዳድሩ አልተለየም። አንድ ጊዜ በተዉሂድ፣ሌላ ጊዜ ቢድዐን በመዋጋት ስም ሀይማኖታዊ ሽፋን ተሰጠዉ። ሂደቱ አሳስቧቸዉ ድምጻቸዉን ያሰሙ ሁሉ ‹‹ቁቡርይ ፣መብተዲዕ፣ጀህምይ...›› እየተሰኙ ይቀጠቀጣሉ፤ሲብስም ዘብጥያ ይወርዳሉ። መዉሊድ የሳዉዲ የጥንት መስተዳድርና ቅርስ አካል ስለሆነ እንዲከስም ቢፈረድበት አይደንቅም።

የሱዑድ ቤተሰብ ይህ ሁሉ ድርጊት የመነጨዉ ለተዉሂድና ለሽርክ፣ ለቢድዐና ለሱና ከመጨነቅ እንደሆነ አድርጎ ማሰብ የዋህነት ነዉ። ለእስልምና ቢያስቡ ኖሮ 24 ሰዓት የሆሊዉድና የቦሊዉድ ፊልሞችን የሚያሰራጩ ታላላቅ የቴሌቪዥን ጣቢያዎችን ተቆጣጥረዉ፣ የአሜሪካና የህንድ ፊልሞችን ወደዐረብኛ እያስተረጎሙ ልጆቻቸዉንና ልጆቻችንን በቁርአንና በሀዲስ፣ወይም በተዉሂድና በሱና ሳይሆን በባዕድ ባህልና

[465]ዩሱፍ አብን ሰይድ ሀሽም ሪፋዒ፣ነሲሀህ ሲኢክዋኒና ዑለማኢ ነጅድ፣ዳር ኢቅራእ፣ ደማስቆ፣1999፣ገጽ 38

ብልግና ባልጠመቁ ነበር።[466] ጸረ-ፍልስጥኤምና ጸረ ዐረብ መሆኑ የተመሠከረለትን የአሜሪካዉን ***ፎክስ ኒዉስና ሌሎች የቴሌቪዥን ጣቢያዎችን*** ተጋርተዉ በወንድሞቻቸዉ ደም ባልቀለዱ ነበር።ዐብዱል ፈታህ ሲሲን ደግፈዉ በግብጽ የራቢዐተል ዐደዊያ አደባባይ ተሀጁድ ሶላት ላይ የነበሩ ሺዎች ንጹሀንን በታንክ ባላስጨፈለቁ ነበር። የላስቬጋስን የቁማርና የወሲብ ንግድ ማዕከላት ባላጣበቡ ነበር።

አባባሌ ባዶ ክስ እንዳይመስል ሁለት ናሙናዎችን ልጥቀስ። የሳዉዲዉ ቢሊዮነር ***ልኡል ወሊድ እብን ጦላል***MBC1, MBC2, MBC3, MBC4, MBC Action, MBC Holywood፣21 century FOX, Rotana etc የቴሌቪዢን ጣቢያዎች ሙሉ ወይም ከፊል ባለቤት ሲሆኑ፣ ከ Rotana video and audio visual company የ95 በመቶ፣ ከሊባኖሱLBC sat የ91 በመቶ ፣ከNews Corporation የ7 በመቶ፣ ከCity Group የ6 በመቶ፣ከAlnehar የ17 በመቶ፣ ከAldiyar የ25 በመቶ የባለቤትነት ድርሻ አላቸዉ። ከFOXNews ሁለተኛዉ ትልቅ የአክሲዮን ድርሻ የርሳቸዉ ነዉ።[467]

አልወሊድ በኦገስት 21/2015 እስራኤልን በማስመልከት የሰጡት ተከታዩ መግለጫ የሱዑድ ገዢ ቤተሰብን የፖለቲካ ‹ዐቂዳ›በጉልህ እንደሚሳይ ተደርጎ ይጠቀስላቸዋል። እጠቅሳለሁ፡-

“Allmy Muslim brothers and sisters must understand that it became a moral imperative for all inhabitants of war-torn middle-east, namely Arabs, to desist their absurd hostility toward Jewish people” [468]

[466] የሳዉዲዉ ሀብታም ልዑል የሸኽ ወሊድ እብን ጦላል የቲቪ ጣቢያዎች ናቸዉ፣ (የዊኪፒዲያ መረጃ)
[467]የዊኪፒዲያ መረጃ፣
[468]የዊኪፒዲያ መረጃ፣

‹‹መካከለኛዉ ምስራቅ ተብሎ በሚጠራዉ የጦርነት ቀጠና ዉስጥ የሚኖሩ ሙስሊም ወንድሞቼና እህቶቼ፣ ማስትም ወረቦች፣ ለአይሁድ ህዝብ ያላቸዉን ትርጉም አልባ ጥላቻ የማቆም የሞራል ግዴታ እንዳለባቸዉ ሲገነዘቡ ይገባል፡፡››

የልዑላኑን ከስነ-ምግባር የወጡ ድርጊቶች በየጊዜዉ በዜና ማሰራጫዎች ማድመጥ የተለመደ ነዉ፡፡ ***በኦክቶበር 24/2015 ኢንዲፔንደንትና ዘጋርዲያኖች***ዜና ማሰራጫዎችየተዘገበዉን ***የልኡል መጅድ ዐብዱልዐዚዝ አልሱዑድ*** አደንዛዥ ዕጽ የመጠቀም፣ ከመጠን በላይ የመጠጣት፣የግብረ ሰዶምና አስገድዶ የመድፈር ወንጀል የሎሳንጀለስ ተደጋጋሚ ክስ ለአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ይህን ሁሉ የጠቀስኩት የግለሰቦቹን ግላዊ ነዉር የማንሳት ፍላጎት ኖሮኝ ሳይሆን የሱዑድ ቤተሰብን ድርጊቶችና እርምጃዎች ለተዉሂድና ለሸርክ፣ለቢድዐና ለሱና ከመጨነቅ የመነጨ አድርጎ ማሰብ የዋህነት መሆኑን ለማሳየት ስል ነዉ፡፡ ይህ ማለት ከቤተሰቡ አባላት መካከል ጥሩ ግለሰቦች የሉም ማለት አይደለም፡፡ ሆኖም የጥቂቶች ጥሩነት ያጠቃላይ ሥርዓቱን ቅኝት የሚቀይር አይደለም፡፡

በጥቅሉ አሁን በምድር ላይ ላሉ መንግስታት ሀይማኖት የፖለቲካ መሳሪያ ከመሆን የዘለለ ተግባርና ሚና የለዉም፡፡ የአሜሪካ ፖለቲከኞች ለፕሮቴስታንት፣የአዉሮፓ ፖለቲከኞች ለካቶሊክ፣ የኢራን ፖለቲከኞች ለሺዐ፣የሳዉዲ ፖለቲከኞች ለዉሀቢ/ሰለፊ ክንፍ ሁለንተናዊ ድጋፍ የሚያደርጉት የጀነትና የጀሀነም ጉዳይ አሳስቧቸዉ አይደለም፡፡

የሱዑዲ ገዥ ቤተሰብ ከዉሀቢ/ሰለፊ አስተሳሰብ ጋር ጥንት የመሠረተዉን የፖለቲካ ጥምረት የሳዉዲ መስራች አባት ንጉስ ዐብዱል ዐዚዝ ጠብቆ ያቆየዉ ለሁለት መሠረታዊ ዓላማዎች እንደሆነ አጥኝዎች ይናገራሉ፡-

አንደኛ፡- የሰለፊ/ዉሀቢ አይዲዮሎጂ ከጥንት ይዞ ሳዉዲ ከተቀናቃኞቿ አንጻር ያላት ማንነት መገለጫ በመሆኑ፣

ሁለተኛ፡- ከዉስጣዊ ተቀናቃኝ ሀይሎች አንጻርም ህጋዊነትን ለመላበስ የሰለፊ/ዉሀቢ ዑለሞች ስለሚያስፈልጉት፤[469]

ከላይ ከተሰጠዉ ትንተና በተጨማሪ የሙስሊሙን ዓለም ሀይማኖታዊ አመራር ለመቆጣጠር ሳዉዲ ሁለቱን ሀረሞች፣የዉሀብይ/ሰለፊ አስተሳሰብንና ዶላሯን፣ግብጽ ደግሞ አዝሀር ዩኒቨርሲቲን፣ የዘመናት እስላማዊ ታሪኳንና ቅርሷን ይዘዉ ሲፋተጉ ይስተዋላል፡፡ በሁለቱ ጎል መንግስታት መካከል የሚደረገዉ ጭስ አልባ ጦርነት በሀይማኖቱም ላይ ጥላ ማጥላቱ የሚጠበቅ ነዉ፡፡ መዉሊድ በዚህ ቁርቁስ መሀል ገብቶ ተንገላታ፡፡ በታሪክ አጋጣሚ ከግብጽ ሀይማኖታዊ ቁመና ጋር ጥብቅ ትስስር ስላለዉ ሳዉዲዎች በርሱ ላይ ጥርስ ለመንከስ ተጨማሪ ምክንያት ሆናቸዉ፡፡

ፖለቲካዉ መስመር ከመያዙ በፊት ሳዉዲዎች በመዉሊድ ላይ የያዙት አቋም ቅኝቱ የሚስተካከል አይመስልም፡፡ **የኛ ሀገር የሀይማኖት ትምህርትና የፈትዋ ሥርዓት ከመካከለኛዉ ምስራቅ ተጽዕኖ ነጻ ሆኖ መዋቀር እንዳለበት ደጋግመን የምንናገረዉም ለዚሁ ነዉ፡፡ ከዚያ አካባቢ የታሪክ ዉርስና የፖለቲካ ቁርቁስ ራሳችንንም ሆነ የሀገራችንን እስልምና ነጻ የማድረግ ሀላፊነት አለብን፡፡**

469 ማባዕደ ሰለፊያ፣ገጽ 216

ምዕራፍ አራት

ልዩ ልዩ

ስለመዉሊድ ትርጉም፣አፈጻጸምና ይዘት፣እንዲሁም ታሪኩን፣ሸሪዐዊ መነሻዎቹንና ከነቃፊዎቹ የተሰነዘሩ ሂሶችን ከነምላሾቻቸዉ ባለፉት ሦስት ምዕራፎች በዝርዝር ተመለከትን። እነሆ ወደመጠናቀቂያዉ ተቃርበናል። ከመሰነባበታችን በፊት የተወሰኑ ነጥቦችን ላንሳ።

መዉሊድ በሀገራችን የተጫወተዉ ሚና

እነሆ የነብዩ ﷺ ልደት መታሰቢያ በሀገራችን በተደራጀ መልኩ ህዝባዊ ከሆነ ከ200 ዓመታት በላይ ሆኖታል። ብሄራዊ ባዕልነቱ ከታወጀም 4 አሥርት ዓመታትን አስቆጥሯል። በነዚህ ጊዜያት ለህዝበ ሙስሊሙ ምን ፋይዳ አስገኘ? ይህችን ጥያቄ መሠረት አድርጌ በሠራኋት መጠነኛ የዳሰሳ ጥናት ለቃለ መጠይቅ ከተባበሩኝ ግለሰቦች የሚከተሉትን ምላሾች ማግኘት ችያለሁ፡-

1) **<u>የዕዉቀትና የዳዕዋ ፋይዳ</u>**፡- መዉሊድ በኛ አገር ትርጉምና ትግበራ (Semantic meaning) የግድ ዓመት ጠብቆ በረቢዑል አወል የሚደረግ ስብስብ አለመሆኑን ከአሁን ቀደም ማየታችን ይታወሳል። በየትኛዉም ወቅት አርዶና ደግሶ ድሆችን መመገብ፣መሻኢኾችን ወይም ዘመድ ወዳጅ ጠርቶ ዱዐ ማስደረግ፣ደረሶችን መጋበዝ መዉሊድ ይባላል። ይህ የመዉሊድ ወይም የሶደቃ ሥርዓት ከተለያዩ ቤቶች እየተደረገ ዓመቱን በሙሉ የሚቀጥል በመሆኑ ለሀገራችን የዕዉቀት ቅብብሎሽ የላቀ አስተዋጽኦ አበርክቷል።

በሀገራችን ለዑለሞች ደመወዝ እየከፈለ፣ለተማሪዎች ቀለብ እየሰፈረ የዕዉቀት ሂደቱን የሚመራ ተቋም ስላልነበረን የመዉሊድ ሥርዓት ለመሻኢኾች ቀለብ፣ለደረሶች ደግሞ ማህበራዊ ስኮላርሺፕ በመሆን አገልግሏል።ዓሊሞቻችን ከጠዋት እስከማታ ከዒልም ላይ ብቻ በማተኮር

እንዲሠሩና የሀገራችን የዲን ዕዉቀት አስደናቂ ስፋትና ጥልቀት እንዲኖረዉ መዉሊድ ትልቅ ድርሻ አበርክቷል።የመዉሊድ ማዕዶች ማህበረሰቡ የምክርና የዳዕዋ አገልግሎት የሚያገኝባቸዉ መድረኮችም ነበሩ።

ባጭሩ መዉሊድ ለመሻኢኾችና ለደረሶቻቸዉ የህልዉና ሰበብ (means of survival)፣ለማህበረሰቡ ደግሞ የዲን ዕዉቀትና ተግሳጽ ማግኛ በመሆን የእስልምና ዕዉቀት ቅብብሎሽ ከትዉልድ ትዉልድ እንዲቀጥል አስችሏል።

መዉሊድ ደረሶችን የመመልመያ መድረክም ነበር። ብዙ ልጆች ለዒልም ልባቸዉ የሚሸፍተዉ ከመዉሊድ መድረኮች ላይ ነበር።ቃለመጠይቅ ካደረግኩላቸዉ ዐሊሞች መካከል አንዱ የሆኑት ሸኽ ሲራጅ ማህሙድ፡- *‹‹ልቤ ለቂራአት የተነሳሳዉ ከመዉሊድ ላይ የደረሶችን ሥርዓት ሳይና የመንዙማዉ መሳጭነት ነበር››* የሚል ምስክርነት ሰጥተዋል።

<u>2) የመገናኛ መድረክ (ኮንፈረንስ)</u>፡- ከሀገራችን ህዝብ 85 በመቶ ያህሉ በገጠር ዉስጥ በተበታተነ ሁኔታ የሚኖር መሆኑ ይታወቃል። ነጋዴዎችም በሲራራ ንግድ ምክንያት ከቦታ ቦታ የሚዘዋወሩ ነበሩ። እነዚህ ሁለት ሁኔታዎች ሙስሊሙ ከመስጊድ ዉስጥ በየዕለቱ እንዳይገናኝ ተግባራዊ እንቅፋቶች ነበሩ። በየሳምንቱ የሚደረጉ የመዉሊድ ዝግጅቶች ህብረተሰቡ እርስ በርስና ከዐሊሞች ጋር እንዲገናኝ መድረክ ፈጥረዋል።

በየዓመቱ በረቢዕ የሚደረገዉ መዉሊድ ደግሞ ሰፋ ያለ ማህበረሰብ ከማገናኘቱ በተጨማሪ በዋነኛነት ዐሊሞች እርስ በርስ እንዲገናኙ፣መረጃ እንዲለዋወጡ፣አስቸጋሪ የዒልም አጀንዳዎችን ተወያይተዉ እንዲፈቱ ዕድል አመቻችቷል። የዓመታዊ ህዝባዊና ምሁራዊ ጉባኤ መድረክ ነበር ማለት እንችላለን።

ከዚህ አኳያ ሲታዩ መዉሊዶች ለማህበራዊ ትስስርና ለዕዉቀት ብልጽግና የነበራቸዉ ፋይዳ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡

3) **መንፈሳዊ ፋይዳ**፡- በመዉሊድ ስብስቦች ላይ የሚደረጉ የጋራ ዚክሮች፣ሶለዋቶች፣ዱዐዎች፣የሚነገሩ የነብዩ ﷺ፣የሶሀቦችና የደጋግ ሰዎች ገድሎች፣የሚሰጡ ምክሮች እና ተግሳጾች የተሳታፊዎችን መንፈስ ሲያድሱ፣የእስልምና ስሜታቸዉን ሲያጠነክሩ፣ስለሀጢአታቸዉ ሲያስለቅሱ ኖረዋል፡፡ በእስልምና ላይ ለመጽናት በልቦናም በአንደበትም ቃላቸዉን የሚያድሱባቸዉ መድረኮች በመሆን ለዘመናት አገልግለዋል፡፡ የኢትዮጵያ ሙስሊም ማህበረሰብ በየዘመናቱ የገጠሙትን ፈተናዎች በጽኑ መንፈስ ተቋቁሞ እዚህ እንዲደርስ የመዉሊድ ማዕዶች በዋጋ ሊተመን፣በቃላት ሊገለጽ የማይችል ዉለታ ዉለዋል፡፡

የመዉሊድ ማዕዶች ባይኖሩ ኖሮ በጎንደር፣በጎጃም፣በትግራይ፣በወሎና በሀረር፣በሰሜን፣በደቡብ፣በምስራቅ፣በምዕራብ የሀገራችን ክፍሎች እስልምና ደብዛዉ በጠፋ ነበር፡፡ እስልምና ጥልቅ ማህበራዊ መሠረት ያለዉ ሀይማኖት እንዲሆን በማድረጉ ረገድ የመዉሊድና የዱዐ መድረኮች የአንበሳዉን ድርሻ ይይዛሉ፡፡

የመዉሊድና የዱዐ ማዕዶች ሙስሊሙ ህብረተሰብ እስልምናን እንዲወድ፣ነብዩንና ሶሀቦችን በእጅጉ እንዲያፈቅርና እንዲያደንቅ፣መካንና መዲናን እየናፈቀ፣‹‹ጌታየ እንዴት ነሡ፣ምነዉ ባየነሡ››ን እያዜመ እንዲያለቅስ፣የዛሬ መከራ ሳይበግረዉ ነገን ተስፋ አድርጎ እንዲደሰት፣ የተቀናቃኞቹን ምድራዊ የበላይነት ቁልቁል በንቀት እንዲያይ፣ራሱንና ሀይማኖቱን ከፍ አድርጎ እንዲመለከት አስደናቂ ሥራ ሠርተዋል፡፡ በመዉሊድ ማዕዶች ላይ ነብዩን ﷺ በመናፈቅ ይለቀሳል፡፡ሶሀቦችን በመናፈቅ ይለቀሳል፡፡ታዳሚዉ በመንፈስ ወደ ወህዩ መዉረጃ፣ለምዕተ ዓመታት ተጉዞ በእያንዳንዷ የትግል ቅጽበት ይሳተፋል፡፡ ‹‹እርሱ

አላለቀሰም፤ላልቅሰለት እኔ›› እያዜመ የሶሀቦችን ጭንቀት ይጨነቃል፤ ስቃያቸዉን ይሰቃያል፤ሞታቸዉን ይሞታል።

የመዉሊድ ማዕዶች በተበታተነ ሁኔታ ከክርስቲያኑ ማህበረሰብ መሀል ይኖር የነበረዉ ሙስሊም ወጣት በአካባቢ፣በባህልና በጓደኛ ተጽእኖ ይፈጽማቸዉ ለነበሩ ጥፋቶች የሚጸጸትባቸዉ፣ሀጢአቱን በቁጭትና በለቅሶ የሚያጥብባቸዉ የተዉባ መድረኮችም ነበሩ።

መዉሊድ *‹‹የእርቅ ማዕድ››* በመሆንም አገልግሏል። የተኮራረፉ፣በደም የሚፈላለጉ ጠበኞች በመዉሊድ መድረኮች በነብዩ ﷺ ስም ሲለመኑ፣ ለርሳቸዉ ሲሉ ጠባቸዉን እርግፍ አድርገዉ በመተዉ እርቅ ያወርዳሉ።

መዉሊድ ለባለሀብቱም ትልቅ የመንፈስ ስንቅ ነበር። አንዳች የሚያሳስብ ነገር ሲገጥመዉ፣ጭንቀት ሲሰማዉ ደረሶችንና መሻኢኾችን ከቤቱ ጠርቶ በመጋበዝና ዱዐ በማስደረግ የተወጠረ መንፈሱን ያረግባል። ዉስጡን ያለዝባል።

መዉሊድ ለሙታን ሳይቀር የአጅር (ምንዳ) መሰብሰቢያ መድረክ ነበር። መዉሊድ የሚያወጡ ሰዎች፣ድግሳቸዉ ትነስም ትብዛ የሶደቃ ምንዳዉን *‹‹ሊጀማዒ አምዋተል ሙስሊሚን››* በማለት የመነያት አስደናቂ ልምድ ነበራቸዉ። ለራሳቸዉ ምንም ሳያስቀሩ አጅሩን ሁሉ ለሙስሊም ሙታን ይልካሉ። ተሳታፊ መሻኢኾችም እንዲህ በማለት ተመሳሳይ ተግባር ይፈጽማሉ፡-

‹‹አላሁመ አዉሲል ሰዋበ ማቀረእናሁ፣ወማ ሀስልናሁ፣ወማከበርናሁ..ሲሹዋኺና፣ ወመሻኢኺ ሺዋኺና፣ወሲጀሚዒ አምዋተል ሙስሊሚነ ወልሙስሊማት...››

‹‹አላህ ሆይ፣በዚህ መድረክ ላይ የቀራነዉን ቁርአን፣ያደረግናቸዉን ዚክሮችና ሶስዋቶች..ስሸኾቻችን፣ስነርሱ ሸኾችና ስሙስሊሞች ሙታን ሁሉ አድርስልን።››

በመዉሊድ መድረክ የአጅር ሰስት አይታወቅም። ‹‹እኔ ቀርቶብኝ ሌሎች ይጠቀሙ›› ገዢ መንፈሱ ነዉ።

4) ኪነጥበባዊ ፋይዳ፡-በሀገራችን እስላማዊ ኪነጥበብና ሥነ ጽሁፍ እንዲጎለብት መዉሊድ የማይናቅ ሚና ተጫዉቷል፡፡ ዓሊሞቻችን የዐረብኛ ቋንቋ ክህሎታቸዉን፣የዜማ ጥበብ ችሎታቸዉን የሚያሳዩት በመዉሊድ መድረኮች ላይ ነበር፡፡ ይህ ሂደት በቋንቋ ብቃታቸዉና በይዘታቸዉ ጥልቀት አቻ ሊገኝላቸዉ የማይችል የመድህና የዱዐ ግጥሞችን አበርክቶልናል፡፡ የሸኽ አህመደዳኒን ‹ራምሳ›፣የሸኽ አህመድ ሲራጅን ‹መከረሙ›፣የሸኽ ጀዉሀረል ሀይደርን ‹ዐለይከ ረበና›፣ የሸኽ ዐሊ ጎንደርን ‹ሶላቱን ዐላ፣ሰላሙን ዐላ መሀመድ...›፣የሸኽ ሰይድ ኢብራሂምን (የጫሌ ሸኽ) አስደማሚ የዐረብኛ ግጥሞችና ዱዐዎች፣ እንዲሁም ‹ነቢዘይኔ›ን እና ሌሎችንም ዘመን ተሸጋሪ ግጥሞችና መንዙማዎች ያገኘነዉ ከመዉሊድ መድረኮች ላይ ነዉ፡፡

የዐሊሞቻችን የግጥም ሥራዎች ላለፉት 700 ዓመታት ዐለምን ሲያስደምሙ ከኖሩት የሸኽ ቡሰይሪ ‹ሀምዝያ›ና ‹ቡሩዳ› ግጥሞች በየትኛዉም መመዘኛ የሚተናነሱ አይደሉም፡፡ መዉሊድ ጥልቅ መሠረት ያለዉ እስላማዊ ኪነጥበብና ሥነ-ጽሁፍ ባለቤቶች አድርጎናል፡፡ የዐሊሞቻችንን የኪነጥበብና የሥነጽሁፍ ብቃት በጣም በጥቂቱ ለማየት የከጀለ በ1430 ሂጅሪያ በነጃሽ ማተሚያ ቤት የታተመዉንና በታዋቂዉ ዐሊም ***በሀጅ ሙሀመድ ወሌ*** መግቢያ የተጻፈለትን ***የሸኽ አህመድ ደራጃ‹‹ኪታቡል መጅሙዐቲ አህዛቢ ወደዐዋት››*** የተባለ ኪታብ መመልከት ይችላል፡፡ ዶ/ር ጀይላን ኻድር ገለቱ በሸኽ አህመድ ደራ የተዘጋጀዉንና ገድላቸዉን የሚተርክ መጽሀፍ የአርትኡት ሥራ (ተህቂቅ) ሰርተዉ ለህትመት ማዘጋጀታቸዉ ሸኹ በኢልም ደረጃና ብቃታቸዉ ከዶ/ሩ ዘንድ ያላቸዉን ቦታ ያመለክታል፡፡ ዶ/ር ሀሳባቸዉን ካልለወጡ በስተቀር በቅርቡ ለህትመት ይበቃ ይሆናል፡፡

5.እስላማዊ ቁመናን የመጠበቅ ፋይዳ፡-የመዉሊድ ሌላኛዉ ሚና እስላማዊ ማንነትንና ቁመናን (identity) ሙስሊሙ ህብረተሰብ ጠብቆ እንዲቆይ ማስቻሉ ነዉ፡፡ ሙስሊሞች በየተወሰኑ ቀናት ዑደቶች

ከመዉሊድ ማዕዶች ላይ እየተገኙ የመንፈስ ስንቅ መሰነቃቸዉ ዙሪያቸዉን በከበባቸዉ የክርስቲያን ማህበረሰብ ባህል ሳይዋጡ እስላማዊ ቁመናቸዉን ጠብቀዉ፣በሀይማኖታቸዉ ተግተዉ፣የመንፈስና የዕምነት የበላይነት እየተሰማቸዉ በኩራት እንዲኖሩ አስችሏል።

6. የመዝናኛ አገልግሎት :- መዉሊድ የመዝናኛ ፋይዳም ነበረዉ። ማዕዶቹ ለሙስሊም ወጣቶች ሀላል መዝናኛዎች ሆነዉ አገልግለዋል። የመንዙማ ግጥሞች፣ዜማዎችና ዉዝዋዜዎች የሙስሊሙን ኪነጥበባዊ ፍላጎት በማሟላት በዚህ ረገድ ሊፈጠር የሚችለዉን ክፍተት ደፍነዋል። የመዉሊድ መድረኮች ባይኖሩ ኖሮ በዚያ ዘመን የነበሩ መዝናኛዎች፣ ማለትም መሸታ ቤቶች፣የአዝማሪ ዉዝዋዜዎች ወዘተ ብዙ ሙስሊሞችን ጠልፈዉ ያስቀሩ ነበር። በአንዳንድ አካባቢዎች የመዉሊድ ማዕዶች የተፈጠሩባቸዉ አጋጣሚዎችና ዓላማዎች ይህን እዉነታ ያጠናክራሉ። ለምሳሌ በጎንደር ዘወትር በፋሲካ የባዕል ቀናት ከከተማ ዉጭ የሚደረጉ የመዉሊድ ማዕዶች ነበሩ። ዓላማቸዉን ‹‹የሰሜኑ ኃያል›› በሚል ርዕስ ባሳተምኩት መጽሀፍ ላይ እንዲህ ገልጨዋለሁ፡-

‹‹በጥንት ዘመን በፋሲካ ባዕዐልና ከባዕሉ በኋላ ባሉ ሁለት ተከታታይ ቀናት የጎንደር ሙስሊም ወጣቶች ከክርስቲያን አቻወቻቸዉ ጋር በመሆን በመጠጥና በጭፈራ የማሳለፋቸዉ ሁኔታ ያሳሰባቸዉ ሸኽ ለጋስና ሌሎች የጎንደር ዑለሞች ወጣቱን ከከተማ ዉጭ ይዘዉ ለመዋል እንዲያስችላቸዉ ዘወትር በየዓመቱ ፋሲካ በሚዉልበትና በቀጣዮቹ ሁለት ቀናት ከጎንደር ወጣ ብሎ ከሚገኙ መስኮች ላይ ዓመታዊ የዱዐና የዚክር ፕሮግራም አበጁ። በዚህም መሠረት የፋሲካ ዕለት እሁድ ሸኽ አባድር፣ ሰኞ ሙቃም አህመድ፣ ማክሰኞኽብሪ ዐብዱል ባሲጥ የተባሉ የዱዐና የዚክር ፕሮገራሞችን ዘረጉ። በዚህ መንገድ ወጣቱን ከመጠጥና እርሱን ተከትሎ ከሚመጣ ጉዳት ማቀብ ቻሉ።››[470]

[470] የሰሜኑ ኃያል ገጽ 143

7.ኢስላማዊ ሜዲያ፡-የመዉሊድ ማዕዶች ተበታትኖ ይኖር የነበረዉ ሙስሊሙ ህብረተሰብ በየተወሰኑ የጊዜ ዑደቶች እየተገናኘ መረጃ እንዲለዋወጥ መድረክ በማመቻቸት ከፍተኛና አስተማማኝ የሜዲያ አገልግሎት ሲሰጡ ኖረዋል፡፡ ከዚህ የተነሳ በአንደኛዉ የሀገራችን ጥግ የሚገኝ ሙስሊም በሌላኛዉ ጥግ ስላለ ወንድሙ ተጨባጭ ሁኔታ ከታማኝ ምንጭ በተገኘ መረጃ ያዉቅ ነበር፡፡

8. የትግል ጥሪ መድረኮች፡-የኢትዮጵያ ሙስሊም ማህበረሰብ በየዘመናቱ ከነበሩ ግፈኞች ጋር ላደረጋቸዉ አስደናቂ ፍልሚያዎች ወጣቶች ለጅሀድ የሚነሳሱትና የሚመለመሉት በመዉሊድ መድረኮች ላይ ነበር፡፡ መዉሊድን በኢትዮጵያ ምድር ህዝባዊና የተደራጀ በማድረጉ ሂደት ትልቅ ሚና የተጫወቱት ሸኽ ሙመድ ሻፊ (ጀማ ንጉስ) ራሳቸዉ ታላቅ የጅሀድ ተምሳሌት ነበሩ፡፡ ‹ጀማ ንጉስ› ማለት ‹የጀመዐዉ ንጉስ› ማለት ሲሆን ይህን ቅጽል ያገኙት የራሳቸዉን ወታደራዊ ኃይል አደራጅተዉና መስተዳድር መሥርተዉ፣ለማንም ሳይገዙና ሳያጎበድዱ ልክ እንደ ንጉስ ታፍረዉና ተከብረዉ ስለኖሩ ነዉ፡፡ ህይወታቸዉን ያጡትም በዚያዉ በጅሀድ መስክ በደረሰባቸዉ ቁስለት ነበር፡፡ ‹መጃሂዶ› የሚለዉ ቅጽል ስማቸዉ ከዒልሙ በበለጠ ጅሀዳዊ ስብዕናቸዉ የጎላ እንደነበር ያመለክታል፡፡

አጼ ዩሀንስን የተፋለሙት ጀማሉዲን አልዐኒና ደረሶቻቸዉ፣እንዲሁም አብሯቸዉ የተዋጋዉ ሠራዊት የመዉሊድ የትግል ጥሪ ዉጤቶች ናቸዉ፡፡

ለዚህ የዘመናት ትግል የመዉሊድ ማዕዶች የማይነጥፍ የሰዉ ኃይል ምንጭ በመሆን አገልግለዋል፡፡ በመዉሊድ መድረኮች ላይ በመሳጭ የክየና ጥበብ ይተረኩ የነበሩ የነብዩﷺ፣ የሶሀቦችና የሌሎች ሙጃሂዶች ገድሎች ወጣቱን ለትግል ሲያነሳሱና ልቡን ሲያሸፍቱ ኖረዋል፡፡

9. የህክምና አገልግሎት፡- የመዉሊድ ማዕዶች የህክምና አገልግሎት ሚናም ነበራቸዉ።በርካታ በሽተኞች ለመዉሊድ በተሰበሰቡ መሻኢኾች አማካይነት ሥነ-ልቦናዊም፣ባህላዊም ህክምና አግኝተዉ ይመለሱ ነበር። አገልግሎቱን የሚሰጡት ለአላህ የቆሙና ከተገልጋዩ ቤሳቤስቲን የማይፈልጉ ብቁ ባለሙያዎች ነበር።

የመዉሊድ ያለፉ ሚናዎች ከሞላ ጎደል እነዚህ ናቸዉ። በአሁኑ ሰዓትስ የአገልግሎት ዘመኑ አክትሞ ይሆን ወይስ ዛሬም የሚጫወተዉ ሚና አለ? ‹ዛሬም ሚና አለዉ› የሚሉ ወንድሞች ያነሷቸዉ ነጥቦች በቀጣዩ ርዕስ ተካተዋል።

የአሁን ዘመን ሚና

ዛሬም መዉሊድ በሀገራችንና በዓለማችን ጉልህ ሚና አለዉ የሚሉ ወገኖች የሚከተሉትን ነጥቦች ያነሳሉ፡-

1.ደስታና ምስጋና ማድረስ፡-አላህ በእዝነቱና በችሮታዉ እንድንደሰት አዞናል። ታላቁ ወሮታዉ ነብዩ ሙሀመድ ﷺ ናቸዉና ይህ ደስታን የመግለጽ መንፈሳዊ ተግባር በጊዜና በቦታ የሚወሰን አይደለምና እኛንም ይመለከተናል።

አላህ ስለጸጋዉ እንድናመሰግነዉ አዞናል። ታላቁ ጸጋ ነብዩ ሙሀመድ ﷺ ናቸዉና ምስጋናችንን ለመግለጽ አስታዋሽ አጋጣሚዎች ያስፈልጉናል። የመዉሊድ መታሰቢያ አንዱ ነዉ።

የአላህን ጸጋ እንድናወጋ አዞናል። ታላቁ ጸጋ ነብዩ ﷺ ናቸዉና ስለርሳቸዉ ለማዉጋት አስታዋሽ አጋጣሚ ያስፈልገናል። ረቢዕ ጥሩ አስታዋሽ ነዉ።

2.ነብዩን ﷺ የማስታወስ ሚና፡- የዛሬ ሙስሊም ክትላንቶቹ በበለጠ ነብዩን ﷺ የሚያስታዉስበት አጋጣሚ ያስፈልገዋል። በእርግጥ

እርሳቸውን ሁልየም ማስታወስ ተገቢ ነበር። ሆኖም የህይወት ውጥረት ሰዎች ይህን እንዲዘነጉ ያደርጋቸዋል። በተጨማሪም በነብዩ ﷺ ስብዕና ላይ አጋጣሚ እየተፈለገ የሚደረገዉ ትንኮሳና ማጥላላት የልደት ወራቸውን ተጠቅመን ስለርሳቸዉ በይበልጥ እንድናወራ ግዴታ ይጥልብናል። መዉሊድ ከነብዩ ﷺ ጋር ግንኙነት ያላትን እያንዳንዷን ነገር በዝርዝር እናስታዉስ ዘንድ ሰፊ ዕድል ይፈጥራል።

3.<u>ነብዩን ﷺ የማስተዋወቅ ሚና</u>:- ነብዩን ﷺ በተለይ ደግሞ ሙስሊም ላልሆኑ ወገኖች ለማስተዋወቅ የሚደረግ ሙከራ አናሳ ነዉ። ለመፍጠር ቢሞከርም ከባድ ነዉ። **በብሄራዊ ደረጃ ክብረ በዐል የሆነዉ የነብዩ ﷺ ልደት መታሰቢያ ስለዓለማት ዕዝነት ﷺ በመንግስትና በግል ሚዲያዎች ወጭ ሳናወጣ በስፋት የምናስተዋዉቅበትን ዕድል ይፈጥርልናል።**

ይህን ዕድል ማባከን ቂልነት ነዉ። አስቡት። በአስሮች የሚቆጠሩ የሬድዮ ጣቢያዎች፣የቲቪ ማሰራጫዎች ለ24 ሰዓታት ፕሮገራማቸዉ ነብዩን ﷺ ማወደስ እና ማስተዋወቅ ሲሆን። ይህ የማስታወቂያ ሥራ በገንዘብ ቢተመን እጅግ ብዙ ነዉ። ሸኽ መሀመድ ሳኒና ሌሎች የሀገራችን አንጋፋ ዐሊሞች መዉሊድ ብሄራዊ በዓል ሆኖ ይታወጅ ዘንድ የታገሉት እንዲህ ዓይነቱን አጋጣሚ መፍጠር በመሻት ሳይሆን አይቀርም። አጋጣሚዉ ተፈጥሯል። የኤሌክትሮኒክስና ፕሪንቲንግ ሜዲያዎች፣የማህበራዊ ድረገጾች እነሆ ከዓመቱ ቀናት ዉስጥ በአንዱ ስለዓለማት ዕዝነት ሊተርኩ ፈቅደዋል። ህዝባችን ይህን ትረካ በጥሞና ያደምጥ ዘንድም መንግስት ቀኑን የዕረፍት ቀን አድርጎታል። ነብያችንን ﷺ ለማንገስ ከዚህ በላይ ምን ዕድል አለ?

4.**<u>የነብዩን ﷺ ፍቅር የማስረጽ ሚና</u>**:- አሁን አሁን በየመድረኩ የሚሰሙ ሰበካዎች በአብዛኛዉ ደረቅና ‹ወታደራዊ› ስለሆኑ ፍቅርን

የማስረጽ ጉልበት የላቸውም፡፡ እንዲያውም አንዳንዶቹ ከመመሰጥ ይልቅ ያናድዳሉ፡፡ ከፍቅር ይልቅ ጥላቻን ይዘራሉ፡፡

ነብዩን ﷺ ማፍቀር ግድ መሆኑን መግለጽ አስፈላጊ አይደለም፡፡ መዉሊድ በዚህ ረገድ የተጫወተዉንና የሚጫወተዉን ሚናም ከአሁን ቀደም ስላብራራሁ አልደግመዉም፡፡ ይህ ትዉልድ ልክ እንደ ትላንቱ ሁሉ የነብዩን ﷺ ፍቅር የሚያሰርጽለት አጋጣሚና ጥበብ ይፈልጋል፡፡ መዉሊድ ከዚህ አቅጣጫም ሚናዉ ምንጊዜም ህያዉ ነዉ፡፡

5.<u>**መንፈስን የማደስ ሚና**</u>፡- ቁሳዊነት ገነነና የቀልብ ድርቀት ጸነሰ፡፡ ብዙዎች በዚህ በሽታ ይማቅቃሉ፡፡ ሶላቱ እና ሌሎች የዒባዳ እንቅስቃሴዎች ‹መካኒካል› ከመሆናቸዉ የተነሳ ቀልብ ሊለዝብ አልቻለም፡፡ የዒባዳ ለዛ ጠፋ፡፡ እዉነተኛ ትስስር እና ወንድማማችነት ከሰመ፡፡አላህን በማዉሳት፣ነብዩን ﷺ በመናፈቅ ማልቀስ ሩቅና ተረት መሰለ፡፡ ከዚህ የመንፈስ ድርቀት መሸሻ መድረክ ሙስሊሙ ይፈልጋል፡፡ ከዚክርና ከዱዐ፣ከሶለዋትና የደጋጎችን ገድል ከማድመጥ የተሻለ መሄጃ የለም፡፡ የመዉሊድ ማዕዶች አብይ ሚና ይህ ነዉ፡፡

በተጨማሪም አሁንም አብዛኛዉ ህዝባችን የሚኖረዉ በገጠር ዉስጥ ነዉ፡፡ የገጠሩ ህዝብ አሁንም የሚሰበስበዉ፣በቀላል ቋንቋ ስለነብዩና ሶሀቦች የሚነግረዉ፣እያስመሰጠ የሚያስተምረዉ፣መንፈሱን የሚያድስለት፣ቀልቡን በፍቅር የሚያበራለት መንፈሳዊ ስብስብ ይፈልጋል፡፡ መዉሊድ ይህን ክፍተት ለመሙላት ከሚያስችሉ መንገዶች አንደኛዉ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

6. <u>**የዳዕዋና የፈትዋ መድረክ**</u>፡-በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የዜጎች አኗኗር ከቀድሞዉ ብዙ የተለየ አይደለም፡፡ አሁንም የተበታተነ ነዉ፡፡ መዉሊድ በዚህ ረገድ ጥንት የተጫወተዉን ሚና አሁንም ይጫወታል፡፡

7.<u>የመዝናኛ አገልግሎት</u> ፡- ሙስሊሙ ከህይወት ዉጣ ዉረዶች ለከን የሚልበት ሀላል እና ጠቃሚ ሥፍራ ይፈልጋል፡፡ ዓመቱን ሙሉ ሳይቋረጡ የሚደረጉት የሀገራችን የመዉሊድ ማዕዶች ይህን ክፍተት ያለጥርጥር ይሞላሉ፡፡ እያዝናኑ ያስተምሩታል፡፡ እያስለቀሱ ያስደስቱታል፡፡ እየመሰጡ ይመክሩታል፡፡ስሜቱን ማርከዉ ይገዙታል፡፡

8. **<u>የትዉልድ ድልድይ</u>**፡- መዉሊድ ያለፈዉን ትዉልድ ዉርሶችና ቅርሶች ለአዲሱ ትዉልድ የማስተላለፍ ሚናዉ የላቀ ነዉ፡፡ እሰላማዊ ታሪክና ባህል በመዉሊድ ይተላለፋል፡፡ በመንዙማዎች ይተላለፋል፡፡

መዉሊድን መንቀፍ ያለፉ ሙስሊም ትዉልዶች ሁሉ በተሳሳተ ጎዳና ዉስጥ ነበሩ ማለት ነዉ፡፡ ጅማሉዲን አልዐኒ፣የዳና ከዋክብት፣ከምስራቅ እስከ ምዕራብ፣ከሰሜን እስከ ደቡብ የነበሩ፣እስልምናን ከዘመን ዘመን ያሸጋገሩ ዑለሞች በሙሉ ራሳቸዉ መንገድ ስተዉ ህዝቡንም አስተዋል ማለት ነዉ፡፡ ትክክለኛዉ እስልምና ወደዚች አገር የገባዉ ከሁለት አሥርት ዓመታት (ከሸኽ ሙሀመድ ዐብዱልወሀብ ኡሱሉ ሰላሳ) ወዲህ ነዉ ማለት ነዉ፡፡ ከዚያ በፊት ሽርክ ነበር፤ ጃሂልያ ነበር፤ቢድዐ ነበር፡፡ የሀገራችን እስልምና ያለፈበት ቱቦ ቢድዐ በተሰኘ ቆሻሻ የተበከለ፣በሽርክ የገማ ነበር ማለት ነዉ፡፡ ዓለም አቀፍም ሆነ አገር አቀፍ ዑለሞች አንዲት ቀላል አጀንዳ በወጉ ፈትሸዉ ትክክለኛ አቋም መያዝ የተሳናቸዉ ድኩማን ናቸዉ ማለት ነዉ፡፡ ከሸኽ እብን ተይሚያህ በፊት የመዉሊድ ጉዳይ በዑለሞች ስምምነት የጸደቀ ስለነበር ህዝበሙስሊሙ በጥመት ላይ ተስማምቶ ኖሯል ማለት ነዉ፡፡ ከዚያ ወዲህም ቢሆን ከአልፋኪሀኒና ከሠለፊ/ዉሀቢ መስመር በስተቀር ሌሎች ዐሊሞች ሁሉ መዉሊድን ስለደገፉ ጥመቱ ከትዉልድ ትዉልድ ቀጥሏል ማለት ነዉ፡፡ እናም ታላቁ ነብይ ﷺ ‹‹ኡመቴ በጥመት ላይ አይስማማም›› ማለታቸዉ ግድፈት ኖሯል፡፡

ይህ ጸለምተኛ አስተሳሰብ በራሱ እጅግ ሲበዛ ስህተት ከመሆኑ በተጨማሪ ታሪክ አልባ፣ታሪካዊ ስብዕና አልባ ያደርጋል፡፡ ሀይማኖታችን

በዚህች ሀገር ውስጥ ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ በኖረባቸዉ 14 ክ/ዘመናት የረባ ግለሰብ ማፍራት የተሳነዉ ስንኩል አድርገን እንድናየዉ ያደርገናል፡ ፡ ይህ ዓይነቱ እይታ ተስፋ አስቆራጭ በመሆኑ የትኛዉንም የተሀድሶ እንቅስቃሴ ገዳይ ነዉ፡፡ ምክንያቱም ትላንት ሰዎችን ማፍራት ያልቻለ ሀይማኖት ዛሬ ወይም ነገ ስለማፍራቱ ምንም ዓይነት መተማመኛ የለም፡፡ *‹‹ትላንት በታላቅነት ዘመኑ ያልተሳካለት ዛሬ ወድቆና ደቆ እንዴት ሊሳካለት ይችላል?›*ያሚል፣ መልስ የሌለዉ ጥያቄ ከአዕምሮ ዉስጥ ይፈጥራል፡፡

ያለፈዉን ታሪካችንን በሙሉ የሽርክ፣የቢድዐና የጃሂልያ አድርገዉ የሚያቀርቡ አተያዮች ትልቁ ጥፋት ባለፈ ታሪኩ የሚያፍር፣ በሀይማኖቱ ሰዉ የማፍራት ጉልበት የማይተማመን፣ወደኋላ ሲያይ ጨለማ እንጅ የማይከሰትለት፣ታሪኩ ባዶ ነዉና ሁሉንም ነገር እንደ አዲስ የሚሞክር፣የራሱ ማንነት የለዉምና ከየዓለማቱ ለሚመጡ አስተሳሰቦች የተጋለጠ ወፍ ዘራሽ ስብዕና እንዲፈለፈል መደላድል መፍጠራቸዉ ነዉ፡፡

9. <u>**የታሪካችን አካል**</u>**፡-** መዉሊድ የኢትዮጵያ እስልምና ታሪክ አካል ሆኗል፡፡ ጥልቅ ማህበራዊ መሠረት ያለዉ ባህልም ፈጥሯል፡፡ የኢትዮጵያን እስልምና ከመሻኢኾች የዒልም ማዕዶች፣እነርሱንም ከመዉሊድ መድረኮቻቸዉ ነጥሎ ማየት የማይቻል ነዉ፡፡ የኢትዮጵያ እስልምና ታሪክ ዋነኛ ክፍል የዒልምና የፍቅር እንጅ እንደሌሎች ሀገሮች የመሳሪያ ግብግብ አይደለም፡፡ መዉሊድን ከታሪካችን ነጥለን ማዉጣት የሚቻል አይሆንም፡፡ እርሱን ስንጥል የሚተርፈን ነገር የለምና ሙሉ ታሪካችንን አብረን እንወረዉራለን፡፡

‹‹ይህን ማንነታችንን የዘነጋ ወይም ያጣጣለ እስላማዊ የተሀድሶ ንቅናቄ አረም እንጅ ሰብል አይሆንም፡፡ እንክርዳድ እንጅ ስንዴ አይሆንም፡፡ ለጊዜዉ የሚበጅ ቢመስለንም ዉሎ አድሮ ጥፋትማስከተሉ የሚቀር

አይደለም፡፡ የሀገራዊዉን እስልምና በጋራ ያስተሳሰረዉን ገመድ የበጠሰ ማንኛዉም ንቅናቄ የበለጠ መበታተንን፣መዳከምን፣ግራ መጋባትንና መቃወስን እንጅ አንድነትን፣ጥንካሬንና ፍቅርን ሊያፈራ አይችልም፡፡›› ይሉናል ስለመዉሊድ ህያዉ ተልዕኮ የሚሞግቱ ልሂቃን፡፡

ስለመዉሊድ የአሁን ዘመን ሚና ያዋየኋቸዉ ወንድሞች የሰጡኝ ምላሽ በኔ ቋንቋ ሲገለጽ ይህን ይመስላል፡፡

ማጠቃለያ

በማህበረሰባችን ዉስጥ ያለአግባብ ተበትነዉ ያለአግባብ እያመሱን ከሚገኙ 20 ያህል አጀንዳዎች መካከል በዚህች አነስተኛ ጥናት አንዱን ብቻ በመጠኑ መመልከት ችለናል። የጥናቱ ዓላማ ላለፉት 20 ዓመታት ደጋግመን ከሰማነዉ የአናሳ ዑለሞች እይታ አንጻር የሚገኘዉን የብዙሀን ድምጽ በማሰማት በአጀንዳዉ ዙሪያ ሚዛናዊ ግንዛቤ መፍጠርና ከተዛቡ ግንዛቤዎች በመነሳት ለዑለሞቻችንና ለታሪካችን የተሰጡ የተሳሳቱ ግምቶችን ማስተካከል፤ብሎም መ-ስሊ-ሙ ህብረተሰብ በዚህ አጀንዳ ሰበብ በየዓመቱ ረቢዕ በተቃረበ ቁጥር መጨቃጨቁን ትቶ ሁሉም ያመነበትን መስመር እየተከተለ ከጋራ ጉዳዮቹ ላይ እንዲያተኩር ማድረግ እንጅ ሁሉም መ-ስሊ-ሞች በዚህች መጽሀፍ ዉስጥ ጎልቶ የወጣዉን ሀሳብ ይከተሉ ዘንድ መጫን አይደለም። በመሆኑም የጥናቱ ሂደት፣የብዙሀን ሊቃዉንት ፈትዋ ያላሳመናቸዉንና ‹መዉሊድ ቢድዐ ነዉ› በሚል ዕምነት በመዉሊድ መታሰቢያዎች ላይ ላለመሳተፍ የወሰኑ ወገኖችን የፊቅህ ምርጫ ማክበር ተገቢ መሆኑን ማሳሰብ ግድ ይላል። የነብዩንﷺ ፍቅር መግለጫና ማስረጫ፣ ገድላቸዉን ማስታወሻና ማንገሻ መድረክ መዉሊድ ብቻ አለመሆኑን መገንዘብም ያሻል። መዉሊድን ላለማሰብ የወሰኑ ወንድሞችን እና እህቶችን ነብዩንﷺ የማይወዱ፣ከሸሪዐዉ ያፈነገጡ አድርጎ በክፉ መጠርጠርም ፈጽሞ ተገቢ አይደለም። ትክክለኛዉ አቅጣጫ ሁላችንም ያሳመነንን የፊቅህና የፈትዋ መስመር እየተከተልን በወንድማማችነት መንፈስ መቀጠል መሆኑን በአንክሮ አሳዉቃለሁ። በዚህና በመሰል ቅርንጫፍ አጀንዳዎች ቡድን ለይቶ መጨቃጨቅ እንደሚያጠፋን ቁርአን እንዲህ በማለት አስጠንቅቋል፦

وَأَطِيعُوا اللَّهَ وَرَسُولَهُ وَلَا تَنَازَعُوا فَتَفْشَلُوا وَتَذْهَبَ رِيحُكُمْ , وَاصْبِرُوا , إِنَّ اللَّهَ مَعَ الصَّابِرِينَ [٨:٤٦]

‹‹አላህንና መልክተኛውንም ታዘዙ፡፡ አትጨቃጨቁም፡፡ ትፈራላችሁና ኃይላችሁም ትኼዳለችና፡፡ ታገሱም፤ አላህ ከትዕግስተኞች ጋር ነውና፡፡››[471]

በዚህች ጥናት ቢያንስ የሚከተሉትን ግንዛቤዎች እንደጨበጥን ተስፋ አለኝ፡-

1) የነብዩ ﷺ ልደት መታሰቢያ (መውሊድ) ከቁርአን፣ከሀዲስ፣ከኢጅማዕና ከቂያስ በቂ መነሻዎች እንዳሉት፣

2) የነብዩን ﷺ ልደት በግለሰብ ደረጃ በዒባዳ አስቦ መዋልን የጀመሩት ራሳቸዉ ነብዩ ﷺ መሆናቸዉን፣

3) የሶለሀዲን አልአዩቢ የእህት ባል የሆነዉ የኤርቢሉ ፍትሀዊ፣ዐሊምና ሱኒ ንጉስ አልሙዞፈር መውሊድን ይፋና ህዝባዊ ካደረገበት ዕለት አንስቶ የፊቅህ፣የሀዲስና የሌሎችም የሸሪዐ መስኮች ታላላቅ ዑለሞች መውሊድን ኢጅማዕ ሊባል በሚችል ሁኔታ እንደተቀበሉትና እንዳጸደቁት፣ከዚህም አልፈዉ ብዙዎቹ ስለመውሊድ ኪታብ እንደከተቡ፣

4) በሀገራችን መውሊድ በዑለሞች ኢጅማዕ እንደጸደቀ፣

5) ከሸኽ እብን ተይሚያህ በፊት መውሊድን ተቃዉሞ ድምጽ ያሰማ ሁነኛ ዐሊም እንዳልነበርና የሸኽ እብን ተይሚያህም አቋም ወደ ድጋፍ እንደሚያደላ፣

6) የሸኽ እብን ተይሚያህ የተቃዉሞ ዝንባሌም በነእብን ሀጀረል ዐስቀላኒ ወዲዉኑ እንደታረመ፣

7) ከእብን ተይሚያህ በኋላ መውሊድን የሀየሱ ሁነኛ ዐሊም አልፋኪሂኒ ሲሆኑ፣ የእርሳቸዉም ተቃዉሞ በነጀላሉዲን አልሱዩጢ እርማት

[471] አል አንፋል 46

እንደተደረገለትና ባጠቃላይ መዉሊድ በብዙሀን ዑለሞች ኢጅማዕ ሊባል በሚችል ሁኔታ እንደጸደቀ፣

8) በሳዉዲም ከሰለፊ/ዉሀቢ መከሰት በፊት መዉሊድ በብሄራዊ ደረጃ ይከበር እንደነበር፣

9) በአሁኑ ዘመን የመዉሊድን መታሰቢያ በመደገፍ ከሳዉዲ በስተቀር የሁሉም ሙስሊም ሀገሮች ዐሊሞች ፈትዋ እንዳስተላለፉ፣

10) በዘመነዘችን የመዉሊድ ብቸኛ ተቃዋሚዎች የሠለፊ/ዉሀቢ አቅጣጫ የሚከተሉ ዐሊሞች እንደሆኑና የነብዩ ﷺ ልደት የማይታሰብባት ብቸኛዋ ሀገር ሳዉዲ መሆኗ፣

ይህ ግንዛቤ በሂደት መከባበርንና መቻቻልን ይፈጥራል ብየ አምናለሁ። በእርግጥም መቻቻል ሊመጣ የሚችለዉ ወደ ህዝብ የተበተኑ አጀንዳዎችን አለባብሶና ሸፋፍኖ በማለፍና እዉነትን በመድፈቅ ሳይሆን፣ የሁሉም ወገኖች እይታዎች በወጉ እንዲቀርቡ አስተዋጽኦ በማድረግና ሰዎች የትኛዉንም ዕይታ ቢከተሉም ይነስም ይብዛ ሸሪዐዊ መነሻ እንዳላቸዉ አዉቆ ምርጫቸዉን የማክበርን ድባብ በመፍጠር ነዉ።

በኺላፍ አጀንዳዎች ዙሪያ የአንደኛዉን ወገን እይታ ብቻ አጉኖና አጋንኖ፣ቁርአንንና ሀዲስን፣እንዲሁም ዑለሞችን የሚከተለዉ እርሱ ብቻ እንደሆነ አስመስሎ፣ሌላኛዉ ወገን መጽሀፍ ቅዱስንና ቀሳዉስትን ይከተል ይመስል አሳንሶና አንቋሾ፣መረጃዎቹንና መነሻዎቹን ደብቆ የማቅረቡ ልምድ በአንድ በኩል ከሀይማኖት አኳያ ያልተገባ ተግባር ሲሆን፣በሌላ በኩል ላለፉ ዐሊሞች ከፍተኛ ክብር ያለዉን ሙስሊም ማህበረሰብ ግራ የሚያጋባ፣ በታሪኩን እንዲያፍር፣የጥንት አባቶቹን እንዲጠራጠር፣ማንነት እንዲያጣ የሚያደርግ እና የልዩነትን እሳት እያቀጣጠለ የህዝበ ሙስሊሙን አብሮነትና ሰላም የሚበላ አቅጣጫ እንደሆነ በተግባር ታይቷል።

መዉሊድን እንደናሙና ብንወስድ ስንሰማዉና ሲነገረን የኖረዉ፣አሁንም ለወጣቱ እየተነገረ ያለዉ ምንም ዓይነት ሸሪዐዊ መነሻ የሌለዉ፣ በዑለሞች ያልተደገፈ፣በዒልሙ መድረክ የማይታወቅ፣ ኹራፋትን መከተል የሚቀናቸዉ፣የቁርአንና የሀዲስ ዕዉቀት የሌላቸዉ ወገኖች የሙጥኝ ያሉት እንደሆነ ተደርጎ ነዉ። ያ ሁሉ ዓለማቀፍ የሀዲስና የፊቅህ ሊቅ፣እንዲሁም ሁሉም ሙስሊም ሀገሮች ኢጅማዕ ሊባል በሚችል ሁኔታ መዉሊድን መፍቀዳቸዉና ማወደሳቸዉ ላለፉት 25 ዓመታት ተደብቆን ኖሯል።ይህ ሚዛን የሳተ አቀራረብ የመታለል ስሜትን በዉስጣችን መፍጠሩ አልቀረም። ***‹‹የቁርአንና የሀዲስ››*** ወይም ***‹‹የሰለፍ››*** እየተባለ የተነገረንን እያንዳንዱን ዐቂዳዊና ፊቅሀዊ አጀንዳ-ልክ እንደ መዉሊድ ሁሉ ሸፍጥ ተፈጽሞብን እንዳይሆን በመስጋት-በጥርጣሬ እንድንመለከተዉ አስገድዶናል። እነሆ ቁርአኑ፣እነሆ ሀዲሱ፣ እነሆ የዓለማችን ያለፉና በህይወት ያሉ ክንደ-ብርቱ ዑለሞች።

በሌሎችም አጀንዳዎች ላይ እንደዚሁ ጠንካራና ጽኑ የጉሉሀን አቋሞችን ይፋ በማድረግ የሚቻቻል ማህበረሰብ የመፍጠሩን ሂደት የሚያሳልጥ ግላዊ አስተዋጽኦ ለማድረግ እተጋለሁ። ይህን ሥራ የሀገራችን ታላላቅ ዐሊሞች ተገናኝተዉና ተወያይተዉ ቢሠሩት እወድ ነበር። በሚሊኒየሙ ዘመን 30 ያህል ዑለሞችን በማስተባበር ለመሥራት የተሞከረዉ ይህ ነበር። ሆኖም ያ ሊሳካ ስላልቻለና የግድ አንድ ሰዉ ኃላፊነት መዉሰድ ስላለበት ራሴን ለዚህ ኃላፊነት አጭቻለሁ። ሥራዉንም አሀዱ ብየ ጀምሬዋለሁ።

ከዚህች ጥናት በዓይነታቸዉ አራት የሆኑ ምላሾችን እጠብቃለሁ፡-

1. ብዙሀን አንባቢዎች፡- ‹‹አ፣ለካ ይህም ዕዉነት አለ›› በማለት ለግንዛቢያቸዉ መስፋት በተደረገዉ አስተዋጽኦ ይደሰታሉ።

2. ከፊሎቹ አንባብያን የማይስማሙባቸዉን ነጥቦች ነቅሰዉ በማዉጣት ጽሁፉን በምሁራዊ አግባብ በአደብ ይተቻሉ።

3. የጽሁፉን ሀሳብ በመረጃ የሚያዳብሩ፣ጭብጡን የሚያጠነክሩም ይኖራሉ።

4. ከጽሁፉ ጭብጥ ርቀዉ፣ *‹‹ሀሰን ምንትስ ነዉ፣ይህን ያለዉ እንዲህ ለማለት አስቦ ነዉ››* እያሉ በለመዱት የሀሜትና የአሉባልታ መንገድ የሚገፉም ይኖራሉ።

ከመግቢያየ ላይ እንደገለጽኩት ሀሳቤን በሀሳባቸዉ ለማበልጸግ ወይም ለማረቅ የሚተጉ ደጋፊ ወይም በአደብ ነቃፊ ወንድሞችን ከወዲሁ ከልብ እያመሰገንኩ ያልተገባ መንገድ የሚከተሉትን ደግሞ አላህ ሂዳያ እንዲሰጣቸዉና የስልጣኔን እስላማዊ የዉይይት አደብ እንዲያገራላቸዉ በድጋሜ ከልቤ ዱዐ አደርጋለሁ።

የመረጃ ምንጮች
المراجع

1. القرآن الكريم
2. جامع البيان في تأويل القرآن: محمد بن جرير بن يزيد بن كثير بن غالب الآملي، أبو جعفر الطبري
3. الجامع لأحكام القرآن: محمد بن أحمد بن أبي بكر بن فرح القرطبي أبو عبد الله
4. روح المعاني في تفسير القرآن العظيم والسبع المثاني: شهاب الدين محمود ابن عبدالله الحسيني الألوسي.
5. معالم التنزيل: محيي السنة :أبو محمد الحسين بن مسعود البغوي
6. تفسير القرآن العظيم: أبو الفداء إسماعيل بن عمر بن كثير القرشي الدمشقي.
7. تنوير المقباس من تفسير ابن عباس: ينسب لابن عباس رضي الله عنهما
8. مفاتيح الغيب: الإمام العالم العلامة والحبر البحر الفهامة فخر الدين محمد بن عمر التميمي الرازي الشافعي
9. فتح القدير الجامع بين فني الرواية والدراية من علم التفسير: محمد بن علي الشوكاني
10. تفسير المنتخب: لجنة من علماء الأزهر
11. التحرير والتنوير: الشيخ محمد الطاهر بن عاشور
12. الدر المنثور:عبد الرحمن بن الكمال جلال الدين السيوطي
13. المعجم المفهرس لألفاظ القرآن الكريم: محمد فؤاد عبد الباقي
14. مقدمة في أصول التفسير:حمد بن عبد الحليم بن تيمية الحراني
15. تاريخ القرآن الكريم : محمد طاهر الكردي

16. صحيح البخاري: محمد بن إسماعيل أبو عبدالله البخاري الجعفي

17. صحيح مسلم: مسلم بن الحجاج أبو الحسن القشيري النيسابوري

18. سنن أبي داود: سليمان بن الأشعث أبو داود السجستاني الأزدي

19. سنن النسائي: أحمد بن شعيب أبو عبد الرحمن النسائي

20. سنن الدارمي: عبدالله بن عبدالرحمن أبو محمد الدارمي

21. سنن ابن ماجه: محمد بن يزيد أبو عبدالله القزويني

22. سنن البيهقي: أحمد بن الحسين بن علي بن موسى أبو بكر البيهقي

23. سنن الدارقطني: علي بن عمر أبو الحسن الدارقطني البغدادي

24. مسند الإمام أحمد بن حنبل: أحمد بن حنبل

25. الزهد: أحمد بن حنبل

26. المصنف في الأحاديث والآثار: أبو بكر عبد الله بن محمد بن أبي شيبة الكوفي

27. صحيح ابن خزيمة: أبو بكر محمد بن إسحاق بن خزيمة السلمي

28. المعجم:سليمان بن أحمد بن أيوب أبو القاسم الطبراني

29. البحر الزخار:أبو بكر أحمد بن عمرو بن عبد الخالق البزار

30. حديث أبي نعيم عن أبي علي الصواف: لأبي نعيم الأصبهاني

31. رياض الصالحين: للامام أبي زكريا يحيى بن شرف بن مرّي النووي

32. الأَذْكَارُ النَّوَوِيَّة: للامام أبي زكريا يحيى بن شرف بن مرّي النووي

33. مجمع الزوائد ومنبع الفوائد:للحافظ نور الدين علي بن أبي بكر الهيثمي

34. مصنف عبد الرزاق : أبو بكر عبد الرزاق بن همام الصنعاني

35. دلائل النبوة للبيهقي

36. السلسلة الصحيحة: محمد ناصر الدين الألباني

37. فتح الباري شرح صحيح البخاري: أحمد بن علي بن حجر أبو الفضل العسقلاني الشافعي

38. عمدة القاري شرح صحيح البخاري: بدر الدين العيني الحنفي

39. : المنهاج شرح صحيح مسلم بن الحجاج: للامام أبو زكريا يحيى بن شرف بن مري النووي

40. تهذيب الأسماء واللغات: للامام أبي زكريا يحيى بن شرف بن مرّي النووي

41. المجموع شرح المهذب:للامام ابي زكريا محي الدين بن شرف النووي

42. جامع العلوم والحكم: أبو الفرج عبد الرحمن بن أحمد بن رجب الحنبلي

43. . تبصير المنتبه بتحرير المشتبه: ابن حَجَر العسقلاني

44. المواهب ادنية:احافظ قسطلاني

45. شرح السنة: الحسين بن مسعود البغوي

46. لسان الميزان: أحمد بن علي بن حجر العسقلاني

47. النهاية في غريب الحديث والأثر: أبو السعادات المبارك بن محمد الجزري

48. شرح المنظومة البيقونية في مصطلح الحديث:محمد بن صالح بن محمد العثيمين

49. المستصفى في علم الأصول:حجت الإسلامإمام أبو حامد الغزالي

50. أصول الفقه الإسلامي: د.ر وهبة الزحيلي

51. عوامل السعة والمرونة في الشريعة الإسلامية:الإمام يوسف القرضاوي

52. الجامع للمسائل الأصول الفقية وتطبيقاتها على مذهب الراجه:د.ر عبد اكريم ابن محمد النمل

53. الموافقات:إبراهيم بن موسى بن محمد اللخمي الغرناطي الشهير بالشاطبي

54. الاعتصام: الشاطبي

55. قواعد الأحكام في مصالح الأنام: أبو محمد عز الدين عبد العزيز بن عبد السلام بن أبي القاسم بن الحسن السلمي الدمشقي، الملقب بسلطان العلماء

56. إحياء علوم الدين: محمد بن محمد الغزالي أبو حامد

57. حول الإحتفال بذكرى المولد النبوي الشريف: د.ر السيدمحمد ابن العلوي المالكي الحسني

58. الإعلام بفتاوى أئمة الإسلام حول مولده عليه الصلاة والسلام: د.ر السيدمحمد ابن العلوي المالكي الحسني

59. مفاهيم يجب ان تصحح:د.رالسيدمحمد ابن العلوي المالكي الحسني

60. محق التقول فى مسألة التوسل:الإمام محمد زاهد الكوثري

61. مقالات الكوثرية:الإمام محمد زاهد الكوثري

62. كلمة علمية هادية فى البدعة وأحكامها:وهبى سليمان غاوجى

63. اقتضاء الصراط المستقيم مخالفة أصحاب الجحيم: أحمد بن عبد الحليم بن تيمية الحراني

64. منهاج السنة النبوية: شيخ الإسلام بن تيمية

65. الأعلام العلية في مناقب ابن تيمية : عمر بن علي بن موسى البزار أبو حفص

66. الحاوي للفتاوي في الفقه وعلوم التفسير والحديث والأصول والنحو والإعراب وسائر الفنون : جلال الدين عبد الرحمن بن أبي بكر السيوطي

67. حسن المقصدفيعمل المولدل: جلال الدين عبد الرحمن بن أبي بكر السيوطي

68. تبين الحقائق شرح كنز الدقائق:فخر الدين عثمان بن علي الزيلعي الحنفي

69. المغني في فقه الإمام أحمد بن حنبل الشيباني: عبد الله بن أحمد بن قدامة المقدسي أبو محمد

70. الفروق أو أنوار البروق في أنواء الفروق:أبو العباس أحمد بن إدريس الصنهاجي القرافي

71. الموسوعة الفقهية الكويتية

72. نصيحة للإخوانن علماء نجد:الشيخ يوسف ابن السيد ابن هاشم الرفاعي

73. البدعة الحسنة أصل من أصول الدين:د.ر عيسى ابن عبد الله ابنمحمد ابن مانع الحميري

74. فتاوى مهمة لعمت الأمة:الشيخ ابن عثيمينالقول المبين فى بيان علم خاتم النبيين:د.ر عيسى ابن عبد الله ابنمحمد ابن مانع الحميري

75. سبحت الفكر في الجهر بالذكر:تحقيق أبو غدة

76. جواهر المنظمة فى زيارت قبر النبي المكرمة

77. دفع شبهة من شبها وتمرد ونسب ذالك إلى إمام أحمد

78. جلاء الأفهام في فضل الصلاة على محمد خير الأنام:ابن قيم الجوزية (محمد بن أبي بكر أيوب الزرعي أبو عبد الله)

79. حكم الاحتفال بالمولد النبوي .الشيخ. ابن باز

80. مجموع الأحزاب والدعوات:الشيخ أحمد درى

81. حكم الاحتفال بذكرى المولد النبوي .. للشيخ صالح بن فوزان الفوزان

82. أم القرى فى مدح خيرالورى القصيدة الهمزية:الإمام ابى عبد الله محمد ابن سعيد ابن حماد البصيري,تحقيق وتعليق الشيخ محمد الشاذلي النفير

83. البدعة تحديدها وموقف الإسلام منها:د.ر عزت على عطية

84. الباعث على إنكار البدع والحوادث: عبد الرحمن بن إسماعيل أبو شامة

85. أحسن الكلام فى تعلق السنة والبدعة من الحكام: الشيخ بخيت مطيع

86. مائدة الفكر الإسلامي:محمد متولي الشعراوي

87. يسألونك في الدين والحياة:د.ر أحمد الشرباصى

88. البيان لما يشغل الأذهان:د.ر على جمعة

89. بدعة الاحتفال بالمولد النبوي:عبد الله بن عبد العزيز بن أحمد التويجري

90. بدعة المولد:محمد ناصر الدين الألباني

91. حقيقة الاحتفال بالمولد النبوي: عبدالرحمن عبدالخالق

92. حقوق النبي صلى الله عليه وسلم على أمته في ضوء الكتاب والسنة. محمد بن خليفة بن علي التميمي. أضواء السلف، الرياض، المملكة العربية السعودية. الطبعة : الأولى، 1418هـ|1997م

93. الفكر الصوفي (في ضوء الكتاب والسنة) : عبد الرحمن بن عبد الخالق اليوسف

94. ما بعد السلفية (قراءة نقدية فى الخطاب السلفي المعاصر):أحمد سالم و عمرو بيوني

95. تاريخ الخلفاء:جلال الدين عبد الرحمن بن أبي بكر السيوطي

96. سير أعلام النبلاء: شمس الدين أبو عبد الله محمد بن أحمد بن عثمان بن قَايْماز الذهبي

97. الكامل في التاريخ: ابن الأثير

98. تاريخ الأمم والملوك: محمد بن جرير الطبري أبو جعفر

99. البداية والنهاية:إسماعيل بن عمر بن كثير القرشي أبو الفداء

100. تاريخ الإسلام ووفيات المشاهير والأعلام : شمس الدين محمد بن أحمد بن عثمان الذهبي

101. وفيات الأعيان وأنباء أبناء الزمان: أبو العباس شمس الدين أحمد بن محمد بن أبي بكر بن خلكان

102. مناقب الشافعي:البيهقي

103. أبو حنيفة:الإمام محمد أبو زهرة

104. الشافعي:الإمام محمد أبو زهرة

105. شذرات الذهب في أخبار من ذهب:عبد الحي بن أحمد بن محمد العكري الحنبلي

106. المواعظ والاعتبار: المقريزي

107. إيقاظ همم الأغبياء:الشيخ محمد ولي

108. الموسوعة الميسرة فى التاريخ الإسلامي:

109. ابن تيمية لم يكن ناصبياً: الشيخ سليمان بن صالح الخراشي

110. معجم البلدان:ياقوت بن عبد الله الحموي أبو عبد الله

111. ديوان البوصيري

112. معجم المؤلفين:عمر كحالة

113. المعجم الوسيط:إبراهيم مصطفى ـ أحمد الزيات ـ حامد عبد القادر ـ محمد النجار

114. Husen Ahmde (professor), From local to national prominence:The life and achivment of shaykh Mohamed Thanu b.Habib b.Beshir (1914-1989):Ethiopian Muslim scholar, teacher and spiritual leader,A papere orepared in advance for presentation to the 16the international conference of Ethuopian studies to be held in Trondhem-norway 2-6 Julay 2007.

115. የሸኽ ሰይድ ኢብራሂም (የጫሌ ሸኽ) የግጥም ስብስቦች

116. በሸኽ አህመድ ዳኒ የተደራጀ የዱዐ መድብል (ራምሳ)

117. የጌታዉ ሸኽ ዐሊ ጎንደር የዱዐ መድብል

118. የሸኽ አህመድ ሸኽ ሲራጅ እና የሌሎች የመድህ ግጥሞች

119. ሸኽ ሰይድ ሙመድ ሳዲቅና ሸኽ ሙሀመድ ሳኒ ሀቢብ፣የቅዱስ ቁርአን የአማርኛ ትርጉም፣አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ፣
120. ሀሰንታጁ፣የሰሜኑሀያል፣አዲስአበባኢትዮጵያ፣ሶፋ መርዋ አታሚዎች፣ 2007 ዓ.ል፣
121. ..... ፣ የስዉፕ ቡቃያ፣ያልታተመ የግል ማስታወሻ፣
122. http/www.daralifta.org/fatawa id 140/30-07-2007/
123. http/www.islam.gov.kw/fatawa id 7233/23-02-2010/
124. http/www.awqaf.ae /fatawa/section id 9 and Ref id 1489/21-10- 2008/
125. http/www.hadaiq.com

ሀገራዊ ፈትዋዎችና ዋቢ ስብዕናዎች

126. ሸኽ ሲራጅ ማህሙድ፣ የፌደራል ሸሪዐ ፍስቤት የቀድሞ ፕሬዝዳንትና በሀገራችን የእስልምና ሥርዓተ ትምህርት ተምረዉ ለከፍተኛ ዐሊምነት ደረጃ የበቁ፣

127. ሸኽ ዐብደላ አድሪስ፣በሀገራችን የሀይማኖት ትምህርት አግባብየተማሩና በአዝዘር ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዲግሪያቸዉን የሠሩ፣ ለ40 ዓመታት በአወልያ ት/ቤት ያስረተማሩና ለተመሳሳይ ዓመታት የማቅራት ልምድ ያካበቱ፤

128. የቀዳሚ ሙፍቲ ሀጅ ዑመር አድሪስ፣የቀድሞዉ የአዲስ አበባ እ/ጉ/ከ/ም/ቤት ፕሬዝዳንትና ዕዉቅ ዐሊም ፈትዋ፣

قُلْ بِفَضْلِ ٱللَّهِ وَبِرَحْمَتِهِۦ فَبِذَٰلِكَ

فَلْيَفْرَحُواْ هُوَ خَيْرٌ مِّمَّا يَجْمَعُونَ

وَمَآ أَرْسَلْنَٰكَ إِلَّا رَحْمَةً لِّلْعَٰلَمِينَ

ይህች መጽሀፍ እንደሚገባዉ
ሳሳከበርናቸዉና ሀቃቸዉን
ሳልተወጣነዉ ለዉዱ ነብያችን ﷺ
እና
ለተከበሩ ዉድ ቤተሰቦቻቸዉ
መታሰቢያ ትሁንልኝ::